ጅማ ዩኒቨርስቲ

የሒዩማኒቲስ እና የማኅበራዊ ሳይንስ ኮሌጅ፤

በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ የአማርኛ ትምህርት ክፍል፤

የሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት

የድኅረ ምረቃ መርኃ ግብር፤


# የመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ አቀባበል ሥርዓት ክወና (ድግትስ ጋሕጃ) ትንተና፤ በጉሙዝ ብሔረሰብ ተተኳሪነት፤

በ


አበበ ጥላሁን ወንድማገኝ


ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ለሁለተኛ ድግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ፡፡

ነሐሴ፤ ፳፻፲፫ ዓ.ም

ጅማ

# የመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ አቀባበል ሥርዓት ክወና (ድግትስ ጋሕጃ) ትንተና፤ በጉሙዝ ብሔረሰብ ተተኳሪነት፤

በ


አበበ ጥላሁን ወንድማገኝ



ጅማ ዩኒቨርስቲ

የሒዩማኒቲስ እና የማኅበራዊ ሳይንስ ኮሌጅ፤

በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ የአማርኛ ትምሕርት ክፍል፤

የሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምሕርት

የድኅረ ምረቃ መርኃ ግብር፤


ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምሕርት ለሁለተኛ ድግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ፡፡

አማካሪ፡- ማንያለው አባተ (ዶ.ር)

ነሐሴ፤ ፳፻፲፫ ዓ.ም

ጅማ

**ጅማ ዩኒቨርስቲ**

**የሒዩማኒቲስ እና የማኅበራዊ ሳይንስ ኮሌጅ፤**

**በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ የአማርኛ ትምሕርት ክፍል፤**

**የሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምሕርት**

**የድኅረ ምረቃ መርኃ ግብር፤**

**የመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ አቀባበል ሥርዓተ ክወና (ድግትስ ጋሕጃ) ትንተና፤ በጉሙዝ ብሔረሰብ ተተኳሪነት፤ በሚል ርዕስ በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ለማስትሬት ዲግሪ ማሟያ በአበበ ጥላሁን ወንድማገኝ በነሐሴ 2013 ዓ.ም. የቀረበው ይህ ጥናት የዩኒቨርሲቲውን የጥራትና የወጥነት መስፈርት ስለሚሟላቱ በፈታኞች ተረጋግጦ ተፈርሟል፡፡**

**የፈታኝ ቦርድ አባላት**

**አማካሪ፡- ማንያለው አባተ (ዶ/ር) ፊርማ ---------------**

**የውጪ ፈታኝ፡- ዋልተንጉስ መኮነን (ዶ/ር) ፊርማ ----------------**

**የውስጥ ፈታኝ፡- ለማ ንጋቱ (ዶ/ር) ፊርማ ---------------**

# ማረጋገጫ

የመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ አቀባበል ሥርዓት ክወና (ድግትስ ጋሀጃ) ትንተና፤ በጉሙዝ ብሔረሰብ ተተኳሪነት፤ በሚል ርዕስ በጅማ ዩኒቨርሲቲ ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ትምሕርት ክፍል በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ጥናት ዘርፍ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ያቀረብኩት ይህ ጥናት ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራ የእኔ ስራ መሆኑንና የተጠቀምኩባቸው ዋቢ መረጃዎችም በትክክል ዋቢ የሆኑ ናቸው፡፡ የጅማ ዩኒቨርሲቲም የጥናቱ ሕጋዊ ባለቤትነት መብት ያለው መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም………………………ፊርማ ……………………..ቀን………/………/2014 ዓ.ም

ማስረከቢያ ቀን………/……..2014 ዓ.ም

# ምስጋና

ይህ ጥናት እዚህ ደረጃ እንዲደርስ ድጋፍና እገዛ ላደረገልኝ፤ እንዲሁም ከተለመደው የሥነ ጽሑፍ ዕይታ ወጣ ብዬ አዳዲስ አተያዮችን እንዳጤን በታላቅ ትህትና በር የከፈተልኝን መምሕሬና አማካሪዬን ማንያለው አባተን (ዶር) እንዲሁም የፎክሎር ጥናትን በር የከፈቱልኝና ተጨባጭ ግንዛቤ የፈጠሩልኝ ውድ መምሕሬ ለማ ንጋቱን (ዶ.ር.) ከልብ አመሰግናለሁ!

ይህን የማሟያ ጥናት ከግብ እንዳደርስ መረጃ በመስጠት በቅንነት እና በፅኑ ፍላጎት የተባበራችሁኝ የጉሙዝ ብሔረሰብ ምክር ቤት ባለሙያዎች፣ የማንዱራ ወረዳ የባሕልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት ባለሙያዎች፣ የማንዱራ ወረዳ ዱዋዝ ባጉና ቀበሌ የጉሙዝ ብሔረሰብ አባላት እና የጉሙዝ ብሔረሰብ የሀገር ሽማግሌዎች ሁላችሁንም ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

መረጃ በምሰበስብበት ወቅት ጉሙዝኛውን ወደ አማርኛ በመተርጎም ለረዳችሁኝ ለአቶ ዳኜ እና መምህር ወርቁ፤ እንዲሁም ተፈጥሯዊ መቼቱን በማመቻቸት በመንገዴ ሁሉ ላገዥኸኝ አቶ ጉደታ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

## አበርክቶ

ይህ ጥናት ሌሎች ተደጋጋሚ ጥናቶችን እንዳደርግ ለኔ በር ከፋች ነው፡፡ ወደ ምድር እንድመጣ ፈቃዱ የእግዚአብሔር ቢሆንም የሕይወቴ በር ከፋች እና በጎ ምክንያቴ ግን እናቴ ናት፡፡ በሕይወት ተስፋ እንዳልቆርጥ፤ በመከራም እንዳልናወጥ በዓለት ላይ የተከለችኝ እናቴ ናት፡፡ ከፈጣሪ በታች ለነፍሴም ለስጋዬም በብዙ ብርና ወርቅ የማይተመን ዋጋ የከፈለችልኝ እናቴ ናት፡፡ እናቴ ሁሉ ነገሬ .... የበኩር ልጄ መጽሐፌ፣ የበኩር ጥናቴ፣ ወደፊትም በኩር የሚሆነው ሥራዬ ሁሉ የእናቴ መታሰቢያ ነውና፤ ይህም የበኩር ጥናቴ ለእናቴ ለወ/ሮ ብርሃኔ መኩሪያው መታሰቢያ ይሁንልኝ፡፡

# አጠቃሎ

*ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ የመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ አቀባበል ሥርዓት ክወና (ድግትስ ጋህጃ) ትንተና፤ በጉሙዝ ብሔረሰብ ተተኳሪነት፤ በሚል ርዕስ የቀረበ ነው፡፡ የጥናቱ ዓላማ የጉሙዝ ብሔረሰብ የመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ አቀባበል ሥርዓተ ክዋኔን መተንተን ነው፡፡ ይህንና ሌሎች ዝርዝር ዓላማዎችን ለማሳካት ክዋኔ ተኮር ንድፈ ሀሳብን ተከትሎ በመከወን፣ ቁልፍ መረጃ አቀባዮችን ዕድል የማይሰጥ የንሞና ዘዴ አካል በሆነው በታላሚ ናሙና ስልት ተመርጠዋል፡፡ የድርሳናት መረጃዎችን ከቤተ መጻሕፍት፣ የክወና መረጃዎች በምልከታ፣ በቃለ-መጠይቅ እና በተተኳሪ የቡድን ውይይት ተሰብስቧል፡፡ ጥናቱ ከማኅበረሰቡ ማኅበራዊ፣ ሥነ ልቡናዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ሥርዓተ ጾታዊ እና እንስታዊ ምልከታ ጋር በማገናኘት የተተነተነ በመሆኑ ዓይነታዊ የምርምር መተንተኛ ላይ አተኩሮ ገላጭ የምርምር ስልትን መጠቀም ተችሏል፡፡ ጥቅል የዲስኩር እና የትዕምርት ትንተና ሂደት ተተግብሯል፡፡ በተገኘው ውጤት መሠረት የጉሙዝ ብሔረሰብ የመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ አቀባበል ሥርዓተ ክወና የመከሰቻ አጋጣሚው፣ የሥነ ልቡና፣ የመከወኛ ቦታ፣ ቁሳቁስ፣ አልባሳት፣ ጌጣጌጥ እና የምግብና የመጠጥ ዝግጅቶችን ያደርጋሉ፡፡ በማኅበራዊ ደረጃና በፆታ የአከዋወን ልዩነቶች መኖራቸውን ለማየት ተችሏል፡፡ ብሔረሰቡ ለመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ አቀባበል ሥርዓት (ድግትስ ጋህጃ) ያለው ምልከታና የሚሰጠው ቦታ ከፍ ያለ መሆኑን፤ ይህ አጋጣሚ ማኅበራዊ ትስስሩን እና ሥነ ልቡናዊ ከፍታውን የሚያጠናክርበት፣ የሥነ ተፈጥሮን ነጻነት የሚያውጅበት፣ ለሴት ልጅ ያለውን ክብር የሚገልጽበት፣ ልዩ ልዩ ዕሴቶቹን እና እምነቱን የሚያፀናበት መንፈሳዊ የመሸጋገሪያ ከበራ መሆኑን አሳይቷል፡፡*

## ማውጫ


ማረጋገጫ ..... iv
ምስጋና ..... v
አበርክቶ ..... vi
አጠቃሎ ..... vii
ማውጫ ..... viii
የአህፅሮተ ቃላት መፍቻ ..... xi
የጉሙዝኛ ቃላት አማርኛ ትርጉም ..... xii
ምዕራፍ አንድ ..... 1
1. መግቢያ ..... 1
1.1 የጥናቱ ዳራ ..... 2
1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ..... 5
1.3. የጥናቱ ዓላማ ..... 6
1.4. የምርምሩ ጥያቄዎች ..... 6
1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ ..... 7
1.6. የጥናቱ ወሰን ..... 7
1.7. የጥናቱ ውስንነት ..... 8
ምዕራፍ ሁለት ..... 9
2. ክለሳ ድርሳናት ..... 9
2.1. የጽንሰ ሀሳቦች እና የንድፈ ሀሳቦች ቅኝት ..... 9
2.1.1. የጽንሰ ሀሳቦች ቅኝት ..... 9
2.1.1.1. ሥርዓተ ጾታ ..... 9
2.1.1.2. ሥነ ልቡናዊ ጫና ..... 11
2.1.1.3. ማኅበራዊ ዕሳቤ ..... 11
2.1.1.4. የእንስታዊነት (ሴትነት) ፅንሰ ሀሳብ (Feminism) ..... 12
2.1.1.5. ሃይማኖታዊ ዕሳቤ ..... 13
2.1.1.6. የከበራ (Ritual) ምንነት ..... 14
2.1.1.6.1 የከበራ መገለጫዎች ..... 16
2.1.1.6.2. የከበራ ዓይነቶች ..... 18
2.1.2. የንድፈ-ሀሳቦች ቅኝት ..... 20
2.1.2.1. ክዋኔ ተኮር ንድፈ ሀሳብ ..... 21

2.2. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ........ 23
2.2.1. ትኩረታቸውን በጉሙዝ ብሔረሰብ ላይ ያደረጉ ጥናቶች ........ 23
2.1.2 ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር የሚዛመዱ ጥናቶች እና ጽሑፎች ዳሰሳ ........ 24
2.2.2.1. የወር አበባ አቀባበል ስርዓት ላይ ያተኮሩ የኤም.ኤ. ጥናቶች ........ 25
2.1.2.2 የወር አበባ ላይ ያተኮሩ ሌሎች ጽሑፎች ........ 27
ምዕራፍ ሶስት ........ 29
3. የጥናቱ አካባቢያዊና ማኅበረ ባሕላዊ ዳራ ........ 29
3.1. የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ወሰን ገፅታ ........ 29
3.2. አስተዳደራዊ ገፅታ ........ 30
3.3. የማንዱራ ወረዳ መልክዓ ምድራዊ ዳራ ........ 30
3.4. የጉሙዝ ብሔረሰብ ታሪካዊ አመጣጥና አሰፋፈር ........ 31
3.4.1. የጉሙዝ ብሔረሰብ ታሪካዊ አመጣጥ ........ 31
3.4.2. የጉሙዝ ብሔረሰብ አሰፋፈር ........ 32
3.5. የጉሙዝ ብሔረሰብ ኢኮኖሚያዊ ገፅታ ........ 32
3.6. የጉሙዝ ብሔረሰብ ባሕላዊ ምግብና አመጋገብ ........ 33
3.7. የጉሙዝ ብሔረሰብ የሕይወት ዘመን ዑደት ........ 34
ምዕራፍ አራት ........ 36
4.የጥናቱ ዘዴ ........ 36
4.1. ጥናቱ የተካሄደበት ቦታ እና የመረጃ አቀባዮች ናሙና አመራረጥ ........ 36
4.1.1. የጥናት ቦታ አመራረጥ ........ 36
4.1.2. የመረጃ አቀባዮች ናሙና አመራረጥ ........ 36
4.2. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ........ 37
4.2.1 ምልከታ ........ 38
4.2.2 ቃለ- መጠይቅ ........ 39
4.2.3 ተተኳሪ የቡድን ወይይት ........ 40
4.3. የመረጃ አደረጃጀትና አተናተን ዘዴ ........ 41
4.3.1. የጥናቱ መረጃ አደረጃጀት ........ 41
4.3.2. የጥናቱ መረጃ አተናተን ዘዴ ........ 41
ምዕራፍ አምስት ........ 42
5. የመረጃ ትንተና ........ 42
5.1. የክወናው መከሰቻ አጋጣሚ ........ 42

5.2. ለድግትስ ጋህጃ ክወና የሚያስፈልግ ዝግጅት ...... 42
5.2.1. የሥነ ልቡና ዝግጅት ...... 42
5.2.2. የሥርዓቱ መከወኛ ቦታ ዝግጅት ...... 44
5.2.3. ሀገረሰባዊ የመከወኛ ቁሶች ዝግጅት ...... 45
5.2.4. ሀገረሰባዊ የምግብና የመጠጥ ዝግጅት ...... 47
5.2.5. ሀገረሰባዊ የአልባሳትና የጌጣጌጥ ዝግጅት ...... 48
5.3. የድግትስ ጋህጃ ክዋኔ ትንተና ...... 51
5.4. የድግትስ ጋህጃ ሥነ ልቡናዊ ፋይዳ ...... 74
5.5. የድግትስ ጋህጃ ማኅበራዊ ፋይዳ ...... 78
5.6. የድግትስ ጋህጃ ሃይማኖታዊ ዕሳቤ ...... 80
5.7. የድግትስ ጋህጃ ሥርዓተ ጾታዊ ምልከታ ...... 84
5.8. የድግትስ ጋህጃ እንስታዊነት (ሴትነት) ምልከታ ...... 86
ምዕራፍ ስድስት ...... 88
6.ማጠቃለያ ...... 88
6.1 አስተያዬት ...... 90
ዋቢ ጽሑፎች...... 93
አባሪዎች ...... 97

## የአህፅሮተ ቃላት መፍቻ

| ተ.ቁ | አህፅሮተ ቃላት | የአህፅሮተ ቃላት ፍች |
|---|---|---|
| 1. | የቤ.ጉ.ክ.መ.ብ.ድ. | የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት መገናኛ ብዙኃን ድርጅት፤ |
| 2. | የማ.ወ.ባ.ቱ.ጽ.ቤት | የማንዱራ ወረዳ ባሕልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት፤ |
| 3. | የቤ.ጉ.ክ.መ.ባ.ቱ.ቢ.ሮ | የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ባሕልና ቱሪዝም ቢሮ፤ |
| 4. | የቤ.ጉ.ክ.መ. | የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት |
| 5. | ቃ.መ 1 | ቃለ - መጠይቅ አንድ |
| 6. | ቡ.ተ.ው 1 | ቡድን ተኮር ውይይት አንድ |
| 7. | CSA | Central Statistics Agency |

በመሆኑም አንባቢ እነዚህን ጉዳዮች ከግምት ውስጥ አስገብቶ ጥናቴን ያነብልኝ ዘንድ አስቀድሜ እጠይቃለሁ፡፡

# የጉሙዝኛ ቃላት አማርኛ ትርጉም

**ጉሙዝኛ ቃላት** **አማርኛ አቻ ፍቺ**

ሆሴኛ ---- በወገብ ላይ የሚደረግ የዛጎል ጌጥ

ልባ ---- በወገብ ላይ የሚደረግ የጨሌ ጌጥ

ልባንዳ ---- ጠመንጃ

መጻ ሚያ ---- ትልቁ መኖሪያ ቤት

መጻ ኮዋ --- ትንሿ ጎጆ ቤት

መነንድቋ አወ --- ልብስ መሸፋፈን

መክሻ ከበበጻ ብጋ አፕንጽጎ --- ትልቅ ሰው አለማናገር

መፋጽ ኔል ጋች ---- ወንዝ መታጠብ

መንዛ ፂንጃ --- እርጥብ ቅጠል

ሙሳ --- አምላክ

ሙዋ/ጊፃ --- ከእንስሳት ቆዳ የሚሰራ የእጅ ጌጥ

ሚንዛ --- ጨሌ

ሚንዘ ጺያ ---- የአንገት ጨሌ

ሚንዝ ቸጓ --- በእግር ላይ የሚደረግ የጨሌ ጌጥ

ማሀሻ --- ወፍጮ

ማንድጉ ሸቤቋ --- ፀጉር መከርከም

ማንጉዛ --- የጠለፋ ጋብቻ

ማንጅልማ --- የለውጥ ጋብቻ

ምዳንጓ --- የማደጎ ጋብቻ

ምቅኘኮታ ---- ለጋብቻ የነጻነት ስርዓት

ምኸሮማ --- ጓደኛ

ምፕንቋ --- የውልደት ሥርዓት

ምጫ --- ከሾላ ዛፍ ልጥ የሚሰራ የወር አበባ ንጽህና መጠበቂያ

ምሻ --- ሞት

ምታ --- ደሮ

ምኋ --- አንካሴ

ምስ ኤል ምኸሮማ ---- በጓደኛ እጅ መብላት

| | | |
|---|---|---|
| ምውድ አለዳጨ | --- | ምዕራብ አቅጣጫ |
| ሰሀዳ | ---- | ባህላዊ ምላጭ |
| ሰሆ ኤያ | --- | አምባር |
| ሰርማ | --- | ከበሮ |
| ሽፓ | --- | የወንድ ልጅ ግርዛት |
| ቆሻ | --- | ቃጭማ |
| ቢዣ | --- | የጥሎሽ ጋብቻ |
| ባክላ ጀባ | --- | ባሕላዊ ሽበጥ ጫማ |
| ቤጀ | --- | ጨረቃ |
| ተጉ ጋሀጀ | --- | የወር አበባ ያየችው ሴት መቀመጫ ወንበር |
| ትባን ጼያ | --- | የጀሮ ጌጥ |
| ትባን ኢታ | --- | የአፍንጫ ጌጥ |
| ቻብ ድዋ | --- | የውርስ ጋብቻ |
| ችቻ | --- | የሾላ ልጥ |
| ቻጋ | --- | የክንድ ቢላዋ |
| አሂጻ | --- | የወር አበባ ያየችው ልጅ |
| አምፕላ | --- | የወንዶች ባሕላዊ ቁምጣና ቲሸርት |
| ኡፋ | --- | አመድ |
| ኦካ ጎኩሆ ኦካ ጎፕያ | --- | ፀሐይ ስትገባ፤ ፀሐይ ሳትወጣ |
| ደጓ | --- | ቀስት |
| ዳጉና | --- | ልጃገረድ |
| ድግትስ ጋሀጀ | --- | የወር አበባ አቀባበል ሥርዓት |
| ጋሀጀ | --- | የወር አበባ |
| ጋንዘኛ | --- | ቁጥር |
| ጋፊቃ | --- | መዋቢያ ቀይ አፈር |
| ጋፋ ግፅኃ | --- | ሴት ደሮ |
| ግላባ | --- | ባሕላዊ ጉርድ ቀሚስ |
| ጌይ ጋሀጀ | ---- | የመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ ጭፈራ |
| ጎምቦ | --- | ዱላ (ዘንግ) |
| ጣቂያ | ---- | ባርኔጣ |

| | | |
|---|---|---|
| ከኤላ ያያ ማንጎሽ ምዳዳ | --- | በእናት እጅ ስራ መጀመር |
| ከይምሻ | --- | ተስካር |
| ኪያ | --- | ቦርዲ |
| ኮታ | --- | ቁራጭ እርጥብ እንጨት |
| ክይ ጋህጃ | --- | የመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ ጠላ |
| ዘራነ | --- | ዝናር |
| ኙርማ | --- | ቅመማ ቅመም |
| ጸልኛ | --- | አረቄ |
| ፍቋ | ---- | የሾላ ዛፍ |
| ፐሀቅ | ---- | በግንባር ላይ የሚደረግ የዛጎል ጌጥ |
| ፐሀቅ ልቋ | ---- | በራስ ላይ የሚደረግ የዛጎል ጌጥ |
| ፖንጻ | ---- | ገንፎ |

❖ ማሳሰቢያ በጥናቱ ውስጥ ያሉ ፎቶዎች በሙሉ በአጥኝው የተነሱ ናቸው፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## 1. መግቢያ

‹‹ባሕል የሰውን ልጅ ከየት መጣነት ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ መስታዋት ነው፡፡›› (አባ ጎርጎሪዮስ ካልዕ፤ 2) እንደሚባለው እያንዳንዱ ማኅበረሰብ ስለዓለም ያለውን እሳቤና እውቀት የሚያንጸባርቀው በባሕሉ ውስጥ ነው፡፡ ለጥቂት ማኅበረሰብ የችግር መፍቻ የሆነ ባሕል ሲጠና በሀገር ለሚንጸባረቅ ችግር፤ የቁልፍ መፍቻ ሆኖ ሊገኝ ይችላል፡፡ በሀገራችን ካሉ ብሔረሰቦች መካከል በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የሚገኘው የጉሙዝ ብሔረሰብ አንዱ ሲሆን፤ የብሔረሰቡ ሴት ልጆች ለመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ ሲያዩ የሚከወነውን ክዋኔ ለማየት ተሞክሯል፡፡

የወር አበባ ሴት ልጅ በየወሩ የምታየው፣ የሴትነቷ መገለጫ እና ተፈጥሮ ያደላት ፀጋ ነው፡፡ ይህን ተፈጥሯዊ ፀጋ የሚቀበሉበት መንገድ፣ ስለወር አበባ ያላቸው አመለካከትና ፍልስፍና ግን ከብሔር ብሔር ይለያያል፡፡ የዚህ ጥናት ዋና ትኩረቱ የመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ አቀባበል ሥርዓተ ክወና (ድግትስ ጋህጃ) ትንተና በጉሙዝ ብሔረሰብ ተተኳሪነት ነው፡፡ ጥናቱ የተነሳበትን ጉዳይ በአግባቡ ለመመርመር ያመች ዘንድ የጥናት ወረቀቱ በስድስት ዋና ዋና እና በሌሎች በርካታ ንዑሳን ክፍሎች ተከፋፍሎ ቀርቧል፡፡

በምዕራፍ አንድ የጥናቱ መግቢያና ዳራ፣ እንዲሁም ጥናቱን ለማጥናት ያነሳሱ ምክንያቶች፣ የጥናቱ ዋናና ዝርዝር ዓላማዎች፣ የምርምር ጥያቄዎች፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የጥናቱ ወሰንና ውስንነት ተካተውበታል፡፡ ምዕራፍ ሁለት ክለሳ ድርሳናት የሚቀርቡበት ሲሆን ሁለት ንዑሳን ክፍሎች ይኖሩታል፡፡ የመጀመሪያው ክፍል የፅንሰ ሀሳብ ቅኝቶች ተቃኝተውበታል፤ በሁለተኛው ክፍል ከዚህ ጥናት ጋር የሚዛመዱ ንድፈ ሀሳቦች ቀደምት ጥናቶችና ጽሑፎች ተካተውበታል፡፡ ምዕራፍ ሶስት ጥናቱ የተካሄደበት ብሔረሰብ አካባቢያዊና ማኅበረ ባሕላዊ ዳራዎች የተዳሰሱበት ነው፡፡ ምዕራፍ አራት ስለ ጥናቱ ዘዴ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች እና የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ቀርበዋል፡፡ ምዕራፍ አምስት ከመስክ የተገኙ መረጃዎች በዓይነት በዓይነታቸው የተተነተኑበት ሲሆን፤ ምዕራፍ ስድስት የጥናቱ ማጠቃለያ እና አስተያዬት የተካተቱበት ነው፡፡

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

የወር አበባ በሴት ተፈጥሮ ወስጥ አብሮ የሚኖር ፀጋ ቢሆንም ለመጀመሪያ ጊዜና እስኪለምዱት ድረስ በተከሰተ ጊዜ በሴቶች ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ አለ፡፡ የወር አበባን የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል የአማርኛ መዝገበ ቃላት፡- ‹‹በየወሩ እስከ ሰባት ቀናት ከሴቶች ማኅፀን የሚፈስ ደም፣ አደፍ ሲል ይበይነዋል፡፡›› (1993፡405)

የወር አበባ በሴት ተፈጥሮ ወስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የመጣው ሔዋን ዕፀ በለስን በልታ ከገነት በተባረሩ ጊዜ በሔዋን የጥፋት እርግማን ምክንያት እንደሆነ የሃይማኖት መጻሕፍት ይጠቁማሉ፡፡ ‹‹ወበከመ አድመውኪያ ለእንትኩ ዕፅ ከማሁ ድምዊ ለለወርኁ፤ ደመ ዕፀ በለስን አፍስሰሻልና ደምሽ በየወሩ ይፍሰስ!›› ሲል እግዚአብሔር ፈረደባት ይላል፡፡ (አዕማደ ምሥጢራት ትርጓሜ 26፤ ኩፋ 4፥17 አስከ ፍጻሜ እና ዘፍ. 3፥1-19 ትርጓሜ) የወር አበባን በሴት ልጅ ተፈጥሮ ወስጥ ያመጣብን ኃጢአት ወይም/እና ሕግን መተላልፍ ነው፡፡ ይህ ተፈጥሯዊ ክስተት **በዘመነ ብሉይ (ኦሪት)**[1] **የእርኩሰት**[2] እና **የመርገም**[3] ምልክት ነበር፡፡ የወር አበባ ላይ ያለችን ሴት ‹‹በመርገሟ ርኩሰት ሳለች›› እና ‹‹ባለ መርገም ሴት›› በማለት ሲገልፅ፤ ባንጻሩ ደግሞ ከወር አበባዋ ነጻ የሆነችን ሴት ‹‹ከርኩሰቷ ነጽታ›› በማለት የወር አበባ የእርኩሰትና የመርገም ምልክት መሆኑን ይገልጻል፡፡ (ኦ.ዘሌ. 15፥ 19)

በሌላ በኩል በእስልምናው አስተምህሮ በአደም ሴት ልጆች ላይ አላህ እንደፈጠረውና በእርግዝና ጊዜ ፅንስን እንዲመግብ፣ በወሊድ ጊዜ ወተት እንዲሆን እና ከእርግዝናም ከወሊድም ነጻ በሆኑ ጊዜ፤ ወቅት ጠብቆ እንዲፈስ የተፈጠረ ነው ይላሉ፡፡

---

[1] ዘመነ ብሉይ ወይም ኦሪት የሚባለው ከክርስቶስ ልደት በፊት (ቅድመ ክርስቶስ ልደት ‹ቅልክ›) የነበረውን ዘመን፣ በክርስትና አማኞች ዘንድ ዓመተ ፍዳ ወይም ዓመተ ኩነኔ እየተባለ የሚጠራውን ዘመን ለመጠቆም የገባ ነው፡፡

[2] እርኩሰት ማለት በኦሪታዊ እሳቤ መርገም የሆነውን የወር አበባ ሴቷ በማየቷ፤ በደሙ የተነኩና የተነካኩ ቁሶች በመንካታቸው ቀድሞ የነበራቸው ቅድስና ተሸሮ እርኩስ (ያልተቀደሰ) ሆነዋል ማለት ነው፡፡ ከእርኩሰታቸው ለመንጻትም የእንስሳት መስዋዕት ይሰው ነበር፡፡ ከክርስቶስ ትንሳኤ በኋላ የወር አበባ በማየቷ እርኩስ የሆነች ሴት እርግማኑ በክርስቶስ ደም ተሸሮ ፀጋ ሆኖላታል፡፡ ከሰውነቷ የሚወጣውም የወር አበባ ቆሻሻ እንጅ ነፍስን የሚነካ እርኩስ አይደለም፡፡ ስለዚህ ቆሻሻ ደግሞ በውኃ እጥበት ብቻ ይጠራል እንጅ መስዋዕት አይጠይቅም፡፡ (አዕማደ ምስጢራት ትርጓሜ)

[3] መርገም ማለት በኦሪታዊ እሳቤ ‹‹የዕፀ በለስን ደም አፍስሰሽ እንደበላሽ፤ ያንቺም ደም በየወሩ ይፍሰስ›› ተብሎ በሔዋን ላይ ያደረው እርግማን ነው፡፡ የወር አበባ ያየች ሴት መርገም ላይ ናት ይባላል፡፡ ከክርስቶስ ትንሳኤ በኋላ መርገም ላይ የሆነች ሴት እርግማኑ በክርስቶስ ደም ተሸሮላትና ፀጋ ሆኖላት የወር አበባ ላይ ናት ይባላል፡፡ (አዕማደ ምስጢራት ትርጓሜ)

‹‹ሐይድ[4] ደም አላህ (ሱ.ወ) የፈጠረው ሲሆን፣ ሴቷ በእርግዝና ወይም በማጥባት ላይ ካልሆነች ይህ ደም የሚሄድበት ስለማይኖረው በየተወሰነ ጊዜው ከማኅፀን ይወጣል፤ ይህም የወር አበባ ተብሎ ይታወቃል፡፡ የወር አበባ የሚከሰተው ከዘጠኝ ዓመት ጀምሮ እስከ ሃምሳ ዓመት ባሉ ሴቶች ነው፡፡›› (ሷላህ 23) የወር አበባ የምታይ ሴት በእስልምና ሃይማኖታዊ ትዕዛዝ መሰረት አትጾምም፣ መስጅድ አትገባም፣ ቅዱስ ቁርሃኑን መንካት አትችልም፣ ሶላት መስገድ አትችልም፣ እንዲሁም ከግብረ ስጋ ግንኙነት ትከለከላለች፡፡ ይህ ሃይማኖታዊ ትዕዛዝ በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ እስከአሁን የሚተገበር ፅኑ ትዕዛዝ ነው፡፡

አዳምና ሔዋን በበደሉት በደል ምክንያት የደረሰባቸው እርግማን በልጆቻቸው ላይ ሁሉ መርገም ሆኖ ይኖር ነበር፡፡ የእግዚአብሔር ልጅ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት በዘር ሲተላለፍ የነበረው ኃጢአትና መርገም ሁሉ ተሻረ፡፡ አዳምና ሔዋን ከኃጢአታቸውና ከመርገማቸው ነፃ ወጡ፣ በሰው ልጆች ላይም ተጭኖ የነበረ የሞት ቀንበርና መርገም ተሰበረ፣ ተሻረ፡፡ ‹‹ብሉይ ኪዳን ሲነበብ ያ መጋረጃ ሳይወሰድ እስከዛሬ ድረስ ይኖራልና፤ በክርስቶስ ብቻ የተሻረ ነውና፡፡›› (2ኛ ቆሮ 3፤ 14) እንዲል የነፍስ ሞት ወደ ስጋ ሞት፤ መርገምት ወደ ፀጋ ተቀየረ፡፡ በሐዲስ ኪዳን ቀድሞ መርገምት የነበረው ፀጋ ሆኖ የወር አበባ ተባለ፤ እርኩሰት የነበረው አደፍ (ቆሻሻ) ተባለ፡፡ እርኩሰት ነፍስን የሚነካ ውስጣዊ ሲሆን ካለ ንስሃ አይጠራም፡፡ አደፍ ወይም ቆሻሻ ግን ከማኅጸን ውስጥ ሲወጣ ውጫዊ ገላን (ስጋን) ብቻ የሚያቆሽሽ ሆኗል፡፡ ግዝፈ አካል ላይ ያለ የሚታይና ውኃ የሚያጠራው ነው፡፡ በሴቶች ባህርይ ውስጥ መኖሩ ቆሻሻ አያሰኘውም ነገር ግን እንደ ዛህል (ንፍጥ)፣ ሽንት፣ ምራቅ፣ ዓይነ ምድርና ሌሎችም ከውስጥ ሲወጣ ቆሻሻ ይሆናል፡፡ (ትርጓሜ አዕማደ ምስጢር)

‹‹የወር አበባ ከአስር እስከ 14 ዓመት አንስቶ ከ45 እስከ 50 ዓመት የሚዘልቅ ዑደት ነው። የወር አበባ ወርኃዊ ዑደት የሚፈጠረው በየ28 ቀን ልዩነት ሲሆን፣ ወደ ጽንስነት ያልተለወጠ እንቁላል ፈርሶ በደም መልክ የሚወጣበት ሂደት ነው። የ28 ቀን ዑደቱ ኹለት ደረጃዎች አሉት። የመጀመሪያው የወር አበባ ከጀመረበት ቀን አንስቶ ያሉትን ኹለት ሳምንታት ያካትታል። በዚህ ወቅት ከሴቶች መራቢያ ህዋስ በአንዱ እንቁላል ማደግ ይጀምራል።

የእንቁላሉን እድገት የሚያፋጥን ሆርሞንም ይመረታል። ወደ አስራ አራተኛው ቀን አካባቢ እንቁላሉ ሲያድግ በማኅጸን ቧምቧ አድርጎ ወደ ማኅጸን ይወርዳል። እንቁላሉ ከወንድ ዘር ጋር ከተዋሐደ የእርግዝና ሂደት ይጀመራል። ውሕደቱ ካልተፈጠረ እንቁላሉ ከሁለት ወይም

---

[4] ‹‹ሐይድ ማለት የወር አበባ ማለት ሲሆን፤ በቋንቋ ትርጉሙ መፍሰስ ማለት ነው፡፡ በሸሪዓዊ ትርጉሙ ደግሞ ከማኅፀን ግድግዳ በታወቀ ጊዜ ያለ በሽታና ያለ ችግር ወደ ውጭ የሚፈስ ደም ማለት ነው፡፡›› (መሐመድ ዓሊ 8)

ከሦስት ቀናት በኋላ ሞቶ ይወገዳል። የዑደቱ ሁለተኛ ደረጃ በአስራ አራተኛው ቀን ጀምሮ በኻያ ስምንኛው ቀን ይጠናቀቃል። በኻያ አምስተኛው ቀን በማኅጸን ውስጥ የሚመረተው የሆርሞን መጠን ቀንሶ ከሦስት እስከ ሰባት ቀን ደም ይፈሳል። በዚህ መንገድ የሚፈጠረው የወር አበባ ወርኃዊ ሂደትን ይከተላል።›› (ዶ/ር ሙስጠፋ፤ 3)

በሀገራችን ኢትዮጵያ ሁሉም ብሔር ብሔረሰቦች በወር አበባ ላይ የራሳቸው የሆነ ባሕላዊ አመለካከት አሏቸው፡፡ ይህ ጥናት በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ከሚገኙ አምስት በተለምዶ ነባር ከሚባሉ ብሔረሰቦች መካከል የጉሙዝ ብሔረሰብ ባሕል ላይ የሚያተኩር ሲሆን፤ ጥናቱ በጉሙዝ ብሔረሰብ ተተኳሪነት **ድግትስ ጋሀጃን**[5] መተንተን ላይ አተኩራል፡፡ በብሔረሰቡ ዘንድ የወር አበባ ማለት ለአቅመ ሔዋን የመድረስ ምልክት ነው የሚል እምነት አላቸው፡፡ ብሔረሰቡ ለመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ አቀባባል ሥርዓት ጋር አያይዘው የሚከውኗቸው ክዋኔዎች በርካታ ናቸው፡፡ በመሆኑም በመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ አቀባባል ሥርዓት ላይ በቅድመ ዝግጅት፣ በጊዜ የወር አበባ እና በድኅረ የወር አበባ ወቅት የሚከወኑ ባሕላዊ ተግባራትና ሥርዓቶች ሲፈጽሙ ከሥርዓቱ ባሻገር ስለወር አበባ ያላቸውን ፍልስፍና የሚገልፁበትን ክዋኔ በማጤን ትንተና ተደርጎበታል፡፡

በማንኛውም ብሔረሰብ የወር አበባ አቀባባል ሥርዓት ላይ የተደረገ ጥናት ባላገኝም በጉሙዝ ብሔረሰብ ሌሎች ባሕሎች ላይ የተጠኑ ጥናቶችን ስመለከት ድርብወርቅ ብፁዕ፤ ‹‹የጉሙዝ ብሔረሰብ ዋና ዋና የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ሥርዓት በማንዱራ ወረዳ፤›› (ኤምኤ ድማፅ)፣ አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ (ሰኔ፤2007)፡፡ ሽፈራው ቁሜና ሌሎችም፤ ‹‹የጉሙዝ ብሔረሰብ አኗኗር፣ ወግና ባሕሎች፣›› ሰኔ 1993 ድባጤ፤ ያልታተመ፡፡ ገረመው ፈይሳ፣ ‹‹ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና የሴቶች ተፅዕኖ በጉሙዝ ብሔረሰብ፣›› መጋቢት 1995 አሶሳ፤ ያልታተመ፡፡ ሳሙኤል አክሊሉ “የጉሙዝ ብሔረሰብ ሀገረሰባዊ ልማድ በተለይ የጋብቻ ሥርዓትና ክዋኔ”፣ ቢኤ ዲማፅ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ (2000 ዓ.ም)፡፡ ከላይ የቀረቡት ጥናቶች በሙሉ በአንድ ብሔረሰብ የተለያዩ ባሕል ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ የጉሙዝ ብሔረሰብ በተለያዩ ማኅበራዊ አጋጣሚዎች የሚከውኗቸው በርካታ ሥርዓቶች እና ፎክሎራዊ ጉዳዮች አሏቸው፡፡ ይህ ጥናትም ቀዳሚዎቹ ጥናቶች ባተኮሩበት ብሔረሰብ ላይ አትኩሮ ነገር ግን በተለዬ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የተሰራ ጥናት ነው፡፡

---

[5] ድግትስ ጋህጃ (Deagats gahaja) ማለት በጉሙዝ ብሔረሰብ ሴት ልጅ ለመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ ስታይ የሚከበረው ሥርዓት ስያሜ ነው፡፡ በዚህ ጥናትም የመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ አቀባባል ስርዓት በሚል ተተክቷል፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የዚህ ጥናት አጥኚ የቤ.ጉ.ክ.መ. ባሕልና ቱሪዝም ቢሮ የሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክተር በነበረበት ጊዜ የጉሙዝ ብሔረሰቦችን የተዝካር አወጣጥ ሥነ ሥርዓት ቀረጻ በማድረግ በቴሌቪዥን ፕሮግራም ለማሰራጨት ዳንጉር ወረዳ አንጃኳያ ቀበሌ ላይ ከጋዜጠኞች ጋር ይገኛል፡፡ ለሥራ የመጣበትን ክዋኔ እያስቀረጸ በዚያው ቀበሌ አንድ ጎጥ ውስጥ ሌላ ዐይቶትና ሰምቶት የማያውቀው አዲስ የሆነበት ነገር ግን በባሕሉ ዘንድ የታወቀ ስነ ስርዓት ሲከወን ይመለከታል፡፡ ይኸውም ለመጀመሪያ ጊዜ የብሔረሰቡ ሴት ልጅ የወር አበባ ስታይ የሚከበር የአቀባበል ሥነ ሥርዓት (ድግትስ ጋህጃ) ነበር፡፡

ይህን ክዋኔ ካዬና አንዳንድ የማኅበረሰቡ አዛውንቶችን ጠጋ ብሎ ስለክወናው ከጠዬቀ በኋላ፡- ‹‹ይኼ ማኅበረሰብ የወር አበባን እንዴት ነው የሚመለከተው? እንደ መርገም ነው ወይስ እንደ ፀጋ? ሴት ልጅ የወር አበባ ስታይ ለብቻዋ ሌላ ቤት ውስጥ የምትቀመጠው ለምንድነው? እርጥብ ቅጠል የሚቆረጠው፣ ሴቶች ተሰብስበው የሚዘፍኑት፣ ሴት ደሮ የሚታረደው፣ በእናቷ እጅ ወፍጮ መፍጨት የምትጀምረው ለምንድነው? የወር አበባ ማዬት ለዚህ ማኅበረሰብ የሚሰጠው አንድምታ ምንድነው? ›› የሚሉ ጥያቄዎች በሕሊናው ሲመላለሱ ብዙ ማወቅ የሚጠበቅበት ማኅበረሰባዊ እውቀት እንዳለ ተገነዘበ፡፡ በዚህም መሠረት አጥኚው የድኅረ ምረቃ ትምሕርቱን ሲማር ጥናታዊ ጽሑፉን በዚህ ሥርዓተ ክወና (ድግትስ ጋህጃ) ትንተና ላይ ለማካሄድ በመወሰን የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምሕርት ከሚሰጥበት ጅማ ዩኒቨርስቲ ለመግባት ችሏል፡፡

ሌላው የጉሙዝ ብሔረሰብ በተለያዩ ማኅበራዊ አጋጣሚዎች የሚከውኗቸው በርካታ ሥርዓቶች እና ፎክሎራዊ ጉዳዮች ቢኖሯቸውም በፎክሎር ጥናት ዘርፍ የተጠኑ ጥናቶች ብዙም ባለመኖራቸው እና ይህ ጥናት አካባቢውን፣ ብሔረሰቡን እንዲሁም ባሕሉን ከማስተዋወቅ አንፃር የራሱ የሆነ የጎላ ድርሻ አለው ብሎ በማሰቡ፤ ሌሎች አጥኚዎች ባጠኗቸው ጽሑፎች ላይ ያልተዳሰሰና ያልታዬ ክወና ከመሆኑ ባሻገር ሥርዓቱ ሲከወን የሚጠቀሟቸው ሀገረሰባዊ ቁሶችና የሚናገሯቸው ሥነ ቃሎች አንድምታ ምን እንደሚመስል የሚያስረዳ የተሰነደ ነገር ያልገጠመው በመሆኑ፤ እንዲሁም ባሕል ሁሌም በለውጥ ሂደት ውስጥ መሆኑ ስለሚታወቅ የጉሙዝ ብሔረሰብ የመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ አቀባበል ሥነ ሥርዓት (ድግትስ ጋህጃ) ለወደፊት በተለያዩ ምክንያቶች ቅርፅና ይዘቱን እየለቀቀ ከሄደ ከጅማሬው እስከ ፍፃሜው በተለያዩ መንገዶች ቀርሶ ለትውልድ ለማቆየት መጣር ለነገ የማይባል ተግባር መሆኑን ማመኑ ሌላኛው ምክንያት ነው፡፡

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ፡- ‹‹ የጉሙዝ ብሔረሰብ የመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ አቀባበል ሥርዓት ክዋኔን (ድግትስ ጋህጃ) መተንተን ነው፡፡ ›› በንዑስነት ደግሞ፡-

- የመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ አቀባበል ስርዓተ ክወና (ድግትስ ጋህጃ) የሚፈፀሙ ባሕላዊ ድርጊቶችን፣ የዘፈንና የምርቃት ግጥሞችንና ትዕምርቶችን በማኅበራዊ ደረጃ መተንተን፤
- የጉሙዝ ብሔረሰብ ለወር አበባ ያለውን ማኅበራዊ፣ ስነ ልቡናዊ፣ ሃይማኖታዊ እና ሥርዓተ ጾታዊ ምልከታ መፈከር፤
- የመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ አቀባበል ስርዓተ ክወናን (ድግትስ ጋህጃ) ባይፈጽሙት ምን ሊፈጠር እንደሚችል ያለውን እምነት ማብራራት፤

## 1.4. የምርምሩ ጥያቄዎች

- ❖ በመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ አቀባበል ስርዓተ ክወና (ድግትስ ጋህጃ) የሚፈፀሙ ባሕላዊ ድርጊቶች፣ የዘፈንና የምርቃት ግጥሞችና ትዕምርቶች በማኅበራዊ ደረጃ ሲታዩ ምን ይመስላሉ?
- ❖ የጉሙዝ ብሔረሰብ ለወር አበባ ያለው ማኅበራዊ፣ ስነ ልቡናዊ፣ ሃይማኖታዊ እና ሥርዓተ ጾታዊ ምልከታ ምንድነው?
- ❖ ክዋኔውን ባይፈፅሙትስ ምን ይፈጠራል ተብሎ ይታመናል?

## 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት የጉሙዝን ማኅበረሰብ ማንነት በከፊልም ቢሆን ለሌሎች ብሔረሰቦች ለማስተዋወቅ፣ የመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ አቀባበል ሥርዓት (ድግትስ ጋህጃ) ውስጥ በተለያዬ ማኅበራዊ ደረጃ፤ በባሕላዊ፣ በተፈጥሯዊ ገፅታ በአጠቃላይ ስለወር አበባ ያላቸውን ፍልስፍና የሚገልፁበት እና ይህንን ውጣ ውረድ ከነጓዙ ለማሳየት የሚጠቀሙበት ሥነ ወግና ክወና ምን እንደሚመስል ከማሳዬቱም ባለፈ የብሔረሰቡ ወግ፣ ቱባ ባሕሉንና ቅርሱን በተወሰነ መልኩ ለመጪው ትውልድ ቀርሶ ለማስቀመጥ ይረዳል፡፡

ጥናቱ ተጠንቶ ካለቀ በኋላ በዚሁ ርዕስና በሌሎች የጉሙዝ ብሔረሰብ ባሕል ላይ ጥልቅ ጥናት ማካሄድ ለሚፈልጉ አጥኝ ምሑራን ፍንጭ ይሰጣል፡፡ በሀገራችን የፎክሎር ጥናት የወር አበባ ላይ የተካሄደ ጥናት በመሆኑ በዘርፉ አዲስ ዕይታን ይጨምራል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ የጉሙዝ ማኅበረሰብ የሚኖርበት አካባቢ ብዙም የቱሪስት ፍሰት ጎልቶ የማይስተዋልበት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ይህ ጥናት በተለያዩ የመገናኛ አውታሮች የመሰራጨት ዕድሉን ካገኘ፤ ጎብኝዎች ፊታቸውን ወደ ባሕሉ ባለቤቶች እንዲያዞሩ ያነሳሳል፡፡ እንዲሁም የመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ አቀባበል ሥርዓቱ ለሌሎች የሀገሪቱ ብሔረሰቦች በበጎ ጎኑ መልካም ተሞክሮ ይሆናል ተብሎ ይገመታል፡፡

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

የዚህ ጥናት ዐብይ ትኩረት የጉሙዝ ብሔረሰብ የመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ አቀባበል ሥርዓተ ክዋኔን መመርመር ነው፡፡ ስለዚህ ጥናቱ የተወሰነው በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የጉሙዝ ብሔረሰብ በብዛት ከሚኖሩባቸው ዐስር ወረዳዎች ውስጥ በማንዱራ ወረዳ ላይ ብቻ ተወስኗል፡፡ ምክንያቱም ከማንዱራ ወረዳ ውጭ ያሉ የብሔረሰብ አባላት በብዛት ከሌሎች ብሔረሰቦች ጋር ተሰባጥረው በመኖራቸው እንዲሁም ከሌላው ብሔረሰብ ተነጥለው ለደኅንነት ስጋት ባለበት አካባቢ ስለሚኖሩ ትክክለኛ ባሕሉ ለማግኘትና ከስጋት በነጻ መንገድ ለመስራት ነው፡፡ የጉሙዝ ብሔረሰብ የበርካታ ባሕሎች ባለቤት ቢሆንም ይህ ጥናት የጉሙዝ ብሔረሰብ የመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ አቀባበል ሥርዓተ ክዋኔን (ድግትስ ጋህጃ) በመመርመር ላይ ብቻ ያተኩራል፡፡ በተለያዩ ማኅበራዊ ደረጃዎች የሚከወኑ ሥርዓቶችን መነሻ በማድረግ የተለያዩ ሥነ-ቃሎችን እና ክዋኔዎችን በመጠቀም የሚገልፁበትን መንገድ በመፈተሽ እምነታቸው፤ አመለካከታቸውንና በአጠቃላይ ፍልስፍናቸው ምን እንደሚመስል ተንትኖ ማሳየት ላይ አተኩራል፡፡

## 1.7. የጥናቱ ውስንነት

በዚህ የጥናት ርዕስ ውስጥ ከዚህ ቀደም በቀጥታ የሚገናኝ ምንም ዓይነት ጥናት ባለመካሄዱ በክለሳ ድርሳናት ውስጥ ከሌሎች ጥናቶች ጋር ያለውን ልዩነት ለማሳዬት አልተቻለም፡፡ የጉሙዝ ብሔረሰቦች በክልሉ ዐስር ወረዳዎች ላይ ቢገኙም የዚህን ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ የተጠቀምኹት የማንዱራ ወረዳን ብቻ መሆኑ በፀጥታ ስጋት ከቦታ ቦታ ያለውን የክወና ለውጥ በማዬት ለመተንተን አልተቻለም፡፡ ሌላው በዚህ ጥናት ውስጥ የሚተነተነው የመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ አቀባበል ሥርዓት ብቻ ስለሆነ ከዓላማ አንጻር ወርኃዊው የወር አበባ ሲመጣ ያለውን ማኅበረ ባሕላዊ ምላሽ ምን እንደሚመስል እና ምን እንደሚደረግ አያይም፡፡ ጥናቱን የሚያካሂደው ወንድ በመሆኑ የማይረዳው ወይም የሚጎለው መረጃ ይኖራል ተብሎ ይገመታል፡፡ እንዲሁም በክወና ወቅት በዘፈንና በምረቃ የሚባሉ ሥነ ቃሎችን ከመተንተን ውጭ አይመድብም፡፡ ይህ በአጠቃላይ የጥናቱ ውስንነት ሆኖ ይታያል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# 2. ክለሳ ድርሳናት

## 2.1. የጽንሰ ሀሳቦች እና የንድፈ ሀሳቦች ቅኝት

በዚህ ክፍል ጥናቱ የሚያተኩርበትን ርዕሰ ጉዳይ የተመለከቱ ‹‹ጽንሰ ሀሳቦች›› እና ጥናቱ የሚመሰረትባቸው ‹‹ንድፈ ሀሳባዊ ዳራዎች›› ተቃኝተዋል፡፡

### 2.1.1. የጽንሰ ሀሳቦች ቅኝት

በዚህ ንዑስ ክፍል ስለወር አበባ አቀባበል ሥርዓት የተፃፉ እሳቤዎች የሚዳሰሱበት ሲሆን የሥርዓተ ጾታዊ እና እንስታዊነት (ሴትነት)፣ ሥነ ልቡናዊ ጫና፣ ማኅበራዊ ዕሳቤ እና ሃይማኖታዊ ዕሳቤ የሚሉት ነጥቦች ተተንትነውበታል፡፡

#### 2.1.1.1. ሥርዓተ ጾታ

ሥርዓተ ፆታ የወንዶችና የሴቶች ኅብረተሰባዊ ሚና፣ ግንኙነት፣ ጥቅምና ደረጃ የሚወሰንበት ሥርዓት ነው፡፡ በኅብረተሰብ ባሕል፣ አስተሳሰብ፣ እምነት፣ የአኗኗር ስልትና የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ የሚገለጥና የሚገነባም ሲሆን የርዕዮተ ዓለም አካልም ሆኖ አመለካከታቸውንና ዕሴቶቻቸውን ይወስናል፡፡ ሥርዓተ ፆታ በተረት፣ በሐቲቶች፣ በክወና፣ በቃልና በጽሑፍ መልክ እንደየዘመኑ ደረጃ እየታደሰ እየተጣጣመ ወደ ትውልድ ይሻገራል፡፡ (ተስፋዬ መለሰ Sheehan 2004፤11) ጠቅሶ እንደገለፀው

‹‹ተረኮች፣ ክወናዎችና ምስሎች ስብዕናን ለመቅረጽ፤ ዳግም ለማደስ፣ የተለዬ ቅርፅ ለማስያዝ እንዲሁም ስብዕናን ማኅበረሰቡ በሚያስቀምጠው መልክና መስመር ለማስያዝ ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ፡፡ ተረኮች ተቀባይነት ያላቸውን አስተሳሰቦች ወይም እምነቶች ለመገንባት፣ ክወናዎች ሐሳቦችንና ልምዶችን ለማንሸራሸርና ተቀባይነት የሌላቸውን አስተሳሰቦች ለማንጓለል እንዲሁም እንክርዳዱን ከምርቱ አበጥሮ ለመለየት ያገለግላሉ፡፡ በሌላ አባባል፣ ስብዕና ማኅበራዊ ሥርዓትና እምነት በተረኮች ነገራና በክወናው በውስጣችን በሚፈጠሩ የሁነቶች ወይም የድርጊቶች ምስል ላይ ተፅዕኖ ይፈጥራሉ፡፡››

የሰዎችን ግላዊና ማኅበራዊ መስተጋብር ለመግለጽና ለመወሰን፣ በጾታ ረገድ የተሰራ መዋቅራችንን ለማሳዬት ክወናዎችና ተረኮች ትልቅ ድርሻ አላቸው፡፡ ሰዎች ራሳቸውን የሚገልጹትና ዓለምን የሚረዱት በተረኮችና በክወና ነው፡፡ በዛው ልክ ተረኮች ግላዊ ስብዕናችንን፣ ማኅበራዊ መስተጋብራችንን እንድናስተካክል ሚናቸው የጎላ ነው፡፡ ሥርዓተ ፆታ የሁለቱን ሥርዓተ ፆታ አባላት የተዛባ ግንኙነት ማመጣጠን ዓላማው ሲሆን፤ ለእኩልነት፣ ለነፃነት፣ ለፍትሐዊነትና ለሌሎችም. ተገቢውን ትኩረት ይሰጣል። በሁለቱ ሥርዓተ ፆታ (በሥነ ተፈጥሯዊው "ፆታ" እና ማኅበረሰብ ሠራሹ "ሥርዓተ ፆታ") አባላት መካከል ያለን ተፈጥሯዊ ልዩነት በውል ይገነዘባል፤ ሴቶች ልዩ እንክብካቤ ያስፈልጋቸዋል ብሎም ያምናል።

የሥርዓተ ፆታ እኩልነት በኢትዮጵያ፤ ፍልስፍናው ከፈላስፋው **ዘርዐ ያዕቆብ**[6] ጀምሮ የነበረ መሆኑ ሳይዘነጋ፤ የሕግ ጥበቃና ከለላ የተደረገለት ዐቢይ ሀገራዊ ጉዳይ ነው፡፡ የሀገራችን ሕገ መንግስትም በተለያዩ አንቀፆቹ (በተለይም በአንቀፅ 35፤ "የሴቶች መብቶች") ሴቶች በኢኮኖሚያዊ፣ በፖለቲካዊና በማኅበረ-ባሕላዊ ዘርፎች ከወንዶች እኩል መሆናቸውን በማረጋገጥ ሁለንተናዊ መብቶቻቸውን በጽሑፍ አቀዳጅቷቸዋል።

---

[6] ዘርዓ ያዕቆብ ስለ ስርዓተ ጾታ እና እንስታዊነት በተናገረው የፍልስፍና ድርሳኑ፤ ስለሴቶች በእስልምና እና በክርስትና መጻሕፍት የተባሉትን ከተፈጥሮ አንጻር መርምሮ ትክክል አይደሉም ብሎ ተሟግቷል፡፡ በሥራ እና በአስተሳሰብ ሴትም ሆነ ወንድ እኩል እንደሆኑ ይሞግታል፡፡ ዳንኤል ወርቁ (አሰናጅ)፡፡ (2007)፡፡ ሐተታ ዘርዓ ያዕቆብ እና ሐተታ ወልደ ሕይወት፡፡ አ/አበባ፤ (ዓመተ ምሕረት የሌለው)፡፡ ላይ እንደተጻፈው፡፡

‹‹የሚወለዱ ሰዎች ወንድና ሴት ቁጥራቸው ትክክል ነው። በአንድ ሰፌ ቦታ የሚኖሩ ወንድ እና ሴት ብንቆጥር ለእያንዳንዱ ወንድ አንዲት ሴት ትገኛለች እንጂ ለአንድ ወንድ ስምንት ወይም አስር ሴቶች አይገኙም። የተፈጥሮ ሕግም አንዱ ከአንዲት ጋር እንዲጋቡ አዟል። አንድ ወንድ አስር ሴት ቢያገባ ግን ዘጠኝ ወንዶች ሴት የሌላቸው ይቀራሉ። ይኸም የፈጣሪን ሥርዓትና ሕገ ተፈጥሮን የጋብቻንም ጥቅም ያጠፋል። አንድ ወንድ ብዙ ሴቶች ሊያገባ ይገባዋል ብሎ በእግዚአብሔር ስም ያስተማረ መሐመድ ግን ትክክል ነው አልልም:: ...... ፈጣሪ በመልካም ጥበቡ ከሴት ልጅ ማኅፀን በየወሩ ደም እንዲፈስ አድርጓል። ይህ የደም መውረድ ለሴት ሕይወት እና ልጆች ለመውለድ ያስፈልጋል። ይህ ደም የማይወርዳት ሴት መካን ነች። መውለድ አትችልም። ምክንያቱም ፍጥረቷ ተበላሽቷልና ነው። ሙሴና ክርስቲያኖች ግን ይህን የፈጣሪ ጥበብ እርኩስ አደረጉ። እንደገና ሙሴ እንዲህ ያለችውን ሴት የተገናኛትን ያረክሳል። ይህም የሙሴ ሕግ የሴትን ኑሮ በሙሉ እና ጋብቻዋን ከባድ አድርጎታል። የመራባትንም ሕግ አጥፍቷል። ልጆችን ከማሳደግ ከልክሎ ፍቅርንም ያፈርሳል። ስለዚህም ይህ የሙሴ ሕግ ሴትን ከፈጠረ ሊሆን አይችልም።››

‹‹ይህችም ሒሩት ሚስቴ ሆነችና በጣም ወደደችኝ። በጌታዬ ሃብቱ ቤት የተናቀች ነበረችና፤ ቤተሰቦቿም ዘወትር ያሳዝኗት ስለነበሩ ዛሬ በጣም ተደሰተች፡፡ እኔም፣ ስለወደደችኝ በተቻለኝ ሁሉ እንዳስደስታት በልቤ ወሰንኩ፡፡.... ከሚስቴ ጋር በፍቅር ነበርኩ፡፡ እኔ እየጻፍኩ የጌታዬን ሃብቱን ልጆች ሳስተምር እርሷም ቀንና ሌሊት ትፈትል ነበር።›› እዚህ ላይ ሴቷን ከእርሱ ጋር እኩል እያደረገ የሚገልጽበት መንገድ አስደናቂ ነው። ስለወደደችው እንዲሁ ተቀብሎ አልተዋትም፤ ይልቁንም እሱ መልሶ አብልጦ እንዴት እንደሚወዳት ይጨነቅ ነበር። መዋደድ ከሁለቱም ወገን መምጣት እንዳለበት ያምናል። በንብረት ክፍፍልም እኩል ነበሩ። የሚያገኙትን ሁሉ እኩል እንዳገኙና እኩል የንብረት ተካፋይነት መብት እንዳላቸው ይናገራል፤ በስራ ክፍፍልም እንደዚሁ፤ እርሱ በመጻፍና በማስተማር ገቢ ያገኛል፤ እሷ በበኩሏ ተግታ በመፍተል ገቢ ታስገኛለች ። ‹‹ዳዊት ግርማ፤ እንስታዊነት በኢትዮጵያ ፍልስፍና፣ ሐተታ ዘርዓ ያዕቆብ እና ሐተታ ወልደ ሕይወት፤ ደብረ ብርሃን፤ ነሐሴ/2011 ዓ.ም፡፡ በጥናቱ እንደተብራራው፡፡

የሴቶች፣ የሕፃናት እና የወጣቶች ሚኒስቴር በእስከ ዛሬው የታሪክ ሂደት የኀበጠውንና የተዛባውን የሥርዓተ ፆታ ግንኙነት ለማቃናት የሚያስችሉ ልዩ ልዩ **ደንቦችን**[7] በመደንገግ ሴቶችን በማብቃትና ተሳትፎና ተጠቃሚነታቸውን በማረጋገጥ ላይ መሆኑንም የመንግስት እና የሥርዓተ ፆታ አባላት ሪፖርት ይገልጻል። ስለሆነም በጉሙዝ ብሔረሰብ የወር አበባ አቀባበል ስርዓተ ክወና ላይ ስርዓተ ጾታዊ ምልከታው እንዴት ይታያል በሚል ጾታን መሰረት ያደረጉ ክወናዎች ተፈክረውበታል፡፡

### 2.1.1.2. ሥነ ልቡናዊ ጫና

‹‹ሴቶች የወር አበባ የሚያዩበት የመጀመሪያ ወቅት አካላዊና ሥነ ልቦናዊ ለውጦችን ተከትለው የሚመጡ አለመረጋጋቶች የሚስተዋሉበት፣ የወሲብ ፍላጎትና ማንነትን የመፈለግ ጥያቄዎች የሚከሰቱበት የእድሜ ክልል መሆኑን የስነ-ልቦና ባለሙያዎች ያስረዳሉ፡፡›› (Bandura,2001 ጠቅሰው ኃይሉና ተዋበች 2004 እንደገለፁት)፡ ከዚህም ባሻገር በማኀበራዊ፣ በሥነልቦናዊ፣ በሞራላዊና በአካላዊ አቋም ረገድ ራስን ማዕከልና የበላይ አድርጎ የማሳየት፣ በማንኛውም የግንኙነት ዘርፎች በሙሉ ነፃነት የመንቀሳቀስ፣ በአጠቃላይ ራስን በራስ ለማስተዳደርና ለመምራት ጽኑ ፍላጎት መያዝና ማንኛውንም አዲስና አደገኛ ነገሮችን የመሞከር ከፍተኛ ፍላጎት የሚያንፀባርቁበት ወቅት ነው፡፡ ስለዚህ ይህን ወቅት በማፈን ሳይሆን በማኀበረሰቡ ዘንድ ዕውቅና በመስጠት አካሄዱን በአካባቢያዊ ስርዓት መምራት ያስፈልጋል፡፡ በጉሙዝ ብሔረሰብ የመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ አቀባበል ስርዓት ላይ ማኀበረሰቡ ለሴቷ ልጅ የሚያደርገው ስነ ልቡናዊ ማረጋጊያ በጥናቱ ውስጥ ተተንትኗል፡፡

### 2.1.1.3. ማኀበራዊ ዕሳቤ

ማኀበራዊ ዕሳቤ የሚጀምረው ከቤተሰብ ነው፡፡ በአንድ ቤተሰብ ውስጥ በማኀበራዊ ደረጃ ሴት ልጅ የወር አበባ ስታይ የራሱ የሆነ ሚና ይኖረዋል፡፡ በማኀበራዊ ደረጃ እንደየባሕሉ እና ሃይማኖቱ ሁኔታ የተለያዩ ቢሆንም አባላቱ የየራሳቸው ተግባራት ይኖሯቸዋል፡፡ በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ለአንድ ሰው የሚሰጠው ቤተሰባዊ ደረጃ ማኀበራዊ ደረጃውን ይወስንለታል፡፡ ክወናዎች አንድ ማኀበረሰብ ተለይቶ የሚታወቅባቸው ገፅታዎች ቢሆኑም፣ በክወና ወቅት

---

[7] በሥርዓተ ጾታ ላይ የወጡ ዓለማቀፍ፣ አህጉራዊና ቀጠናዊ ስምምነቶች፣ ደንቦች፣ አዋጆች፣ የመንግስትና የሥርዓተ ጾታ አባላት ሪፖርት የሚገለፅባቸው ደንቦች የሚከተሉት ናቸው፡፡ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የፀደቀው ‹‹Convention on the Elimination of All Forms of Discrimination Against Women (CEDAW) (1979)››፣ በአፍሪካ ደረጃም በአባል መንግስታት የተፈረመው የሰብዓዊና የሕዝቦች መብት ቻርተር ‹‹African Charter on Human Rights & Peoples right.››፣ በቢጂንግ ቻይና ላይ የተደረሰዉ የተግባር መድረክ የተሰኘው ስምምነት ‹‹Beijing Plat form for Action1995››፣ የምዕተ ዓመቱ የልማት ግብ ‹‹Millennium Development Goals፣ 2015›› ፣ የኢፌዲሪ ሕገ መንግስት ከአንቀጽ 35 ጀምሮ እስከ 41 ድረስ 1983 ዓ.ም፣ የሴቶች ጉዳይ ፖሊሲ1986 ዓ.ም፣ በአዲስ ተሻሽሎ የወጣዉ የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ 1999 ዓ.ም፡፡

በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ ያለን ማኅበራዊ ደረጃ በዕድሜ፣ በጾታና በሥራ ደረጃ ተለይቶ እንዲታወቅ ያደርጋሉ፡፡ (Yoder 1972; 304)

በጉሙዝ ማኅበረሰብ ውስጥ ለአንድ ሰው የሚሰጠው ቦታ ወይም ማኅበራዊ ደረጃ ከሚገለጽባቸው መንገዶች አንዱ ለመጀመሪያ ጊዜ ሴት ልጅ የወር አበባ ስታይ የሚደረገው የአቀባበል ሥርዓት ነው፡፡ ይህ ሥርዓት ልጃገረዷ ከልጅነት ሕይወት አልፋ የራሷን ቤተሰብ ለመመስረት አቅም (ለአቅመ ሔዋን) **በመብቃቷ**[8] ሰፊውን የማኅበራዊ ሕይወት በይፋ በመቀላቀሏ፣ የሚጠበቅባትን ሰፊ ኃላፊነት በብቃት እንድትወጣ የሚሰጣት የመጀመሪያ ክብር ነው፡፡ የወር አበባ ስታይ እንዳታፍር በቤተሰብና በማኅበራዊ ደረጃ የሚደረግላት እንክብካቤ ልጅቱ ሴትነቷን በማኅበረሰቡ እሳቤ ውስጥ ከታ ኃላፊነቷን እንድትወጣ ከማድረጉም በላይ በሥነ ልቡና እንድትጠነክር ያደርጋታል፡፡ ይህንንም አጥኚው በምልከታ በማረጋገጥ በጥናቱ ላይ ፈክሮታል፡፡

### 2.1.1.4. የእንስታዊነት (ሴትነት) ፅንሰ ሀሳብ (Feminism)

እንስታዊነት (ሴትነት) በጽሑፍ ውስጥ ወይም በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ ሴትና የሴት መገለጫ እንዴት እንደተገለፀ የምናይበት መንገድ ነው፡፡ የእንግሊዝኛው መዝገበ ቃላት ሴትነትን እንዲህ ይፈታዋል፡፡ Feminism is:- The advocacy of women's rights on the basis of the equality of the sexes. The theory of the political, economic, and social equality of the sexes. The belief that men and women should have equal rights and opportunities. The doctrine advocating social, political, and all other rights of women equal to those of men. ይህም ‹‹ እንስታዊነት (ሴትነት) ማለት በጾታ እኩልነት ላይ የሴቶች መብት ተሟጋችነት፣ የጾታ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እኩልነት ፅንሰ ሀሳብ ማራመድ፣ ወንዶችና ሴቶች እኩል መብትና ዕድሎች ሊኖሯቸው ይገባል የሚል ዕኑ እምነት ያለው እና ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ሌሎች የወንዶች መብቶች ሁሉ እኩል ለሴቶችም መብቶች እንዲሆኑ በአስተምህሮው ይደግፋል፡፡››

[8] በጉሙዝ ብሔረሰብ ዘንድ አንዲት ሴት ልጅ የወር አበባ ካየች በእነሱ አባባል አሂጻ ከሆነች 18 ዓመት ባይሞላትም ልጅ ለመውለድና እናት ለመሆን፣ ቤተሰብን ለመምራት በፈጣሪ ሙሳ ተመርጣለች፣ ለአቅመ ሔዋንም ደርሳለች ተብሎ ይታመናል፡፡

በእንስታዊነት (ሴትነት) ጽንሰ ሀሳብ ውስጥ የሴቶችን እኩልነት፣ በማኅበራዊ እኩል ተጠቃሚነት፣ እኩል መብትና እድል ማግኘትን ከወንዶች ጋር መጋራትን እንዲሁም የሴቶች ተሳትፎ በማኅበረሰቡ ዘንድ የሚሰጠውን አንድምታ ሁሉ የሚያጠቃልል ነው፡፡ ስለዚህ በዚህ ጥናት ውስጥ የጉዳዩ ባለቤት ሴቷ ብትሆንም በማኅበረሰቡ ዘንድ እንዴት እንደምትታይበት ክወናውን እና የክወናውን መገለጫ ቃል ግጥም ወይም ተረክ በመመርመር ስለሴት የሚነሳው ሀሳብ ተፈክሮበታል፡፡

## 2.1.1.5. *ሃይማኖታዊ ዕሳቤ*

የአንድ ሃይማኖት ተከታይ የሆነ ሰው የእሱ እምነት ከተቀሩት እምነቶች ሁሉ ትክክለኛውና ዓይነተኛው እምነት ስለመሆኑ ሁሌም ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ ሆኖ እናገኘዋለን። የእያንዳንዱ ግለሰብም ሆነ ማኅበረሰብ ሃይማኖት ተከታይ ሃይማኖቱን የሚተነትንበት የራሱ የተለዬ መንገድ አለው። በዓለማችን ላይ ብዙ ሃይማኖቶች ቢኖሩም የክርስትና፣ የእስልምና እና የባሕል ሃይማኖቶች ሰፊውን ቦታ ይይዛሉ፡፡

{(ነገሩ) እንደዚሁም ነው፤ ከበፊትህ በማንኛይቱም ከተማ ውስጥ አስፈራሪን አልላክንም፣ ቅምጥሎችዋ፣ እኛ አባቶቻችንን በሃይማኖት ላይ አገኘን፤ እኛም በፈለጎቻቸው ላይ ተከታዮች ነን ያሉ ቢኾኑ እንጅ። (አስፈራሪው) አባቶቻችሁን በርሱ ላይ ከአገኛችሁበት ይበልጥ ቀጥተኛን (ሃይማኖት) ባመጣላችሁም አላቸው፤ እኛ በርሱ በተላካችሁበት ነገር ከሓዲዎች ነን አሉ።} [አል ዙኽሩፍ:23-24] ስለሆነም ሃይማኖት ከአላህ ለሰው ልጆች የተሰጠ ስጦታ ነው፡፡ ሰው በራሱ የሚያበጅለት አሰራር የለውም፡፡ ሰው በተሰራውና በተሰጠው ሃይማኖት ውስጥ ገብቶ መኖር ነው ደርሻው፡፡

ሃይማኖት የሚለው ቃል ‹‹አመነ›› ከሚለው የግእዝ ግስ የተገኘ ሲሆን ከእርሱም እምነት /ሃይማኖት/ የሚል ስም ይወጣል፡፡ ትርጓሜውም ማመን፣ መታመን፣ በፅኑ ተስፋ መፅናት ማለት ነው፡፡ ማመን፡- ማለት በስጋ ዓይን አይቶ በስጋ ጆሮ ሰምቶ፣ በስሜት ሕዋሳት መርምሮ ሊደረሰበት የማይቻለውን በረቂቅነትና በርቀትነት ያለውን ፈጣሪ ‹‹አለ›› ብሎ መቀበል ነው፡፡ መታመን፡- ደግሞ ይደረጋል ብለው ለተቀበሉት ነገር ለመሆኑና ለመደረጉ ተግባራዊ ምላሽ መስጠት ነው፡፡ አጠቃላይ ትርጉሙም ማመን፣ መታመን፣ አማኝነት፣ አመኔታ ማለት ሲሆን መቀበል ተስፋ ማድረግ፣ አለመጠራጠር፣ ያዩትን እና የሰሙትን እንዲሁም ያመኑትን እውነት በማያምኑት ፊት መመስከር ማለት ነው። /ሮሜ 10÷9፤ ቆላ 2÷6-7፤ ዮሐ 14÷1/

ክወናዎች ማኅበረሰቡ እምነቱን፣ አመለካከቱን፣ ብልሃቱን፣ እውቀቱን.... የሚቀርፅባቸው እና የሚያስተላልፍባቸው መንገዶች ናቸው፡፡ ከተግባራቸው በተጨማሪ ሃይማኖታዊ መልዕክት ማስተላለፊያም ናቸው፡፡ በማለት (Bronner) ያስረዳሉ፡፡ ሃይማኖት ምንጩና ባለቤቱ ፈጣሪ ነው። ሃይማኖት የሰው ልጆች ከእውቀት ማነስ ወይም ከፍርኃትና ከድንጋጤ ያመጡት አይደለም። ከፍልስፍና እንዲሁም ከመራቀቅም የተገኘ ሳይሆን ፈጣሪ ለሰው ልጆች የሰጣቸው ውድ ስጦታ ነው የሚሉ አሉ። በዚህ ጥናት ውስጥ የመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ አቀባበል ሥርዓት ክወና (ድግትስ ኃሀጀ) ትንተና፤ ከሃይማኖት አንጻር ያለው ቁርኝት፤ ክወናው በመከወኑ የሚያስገኘው ሃይማኖታዊ ጥቅም እና ክወናው ባይካሄድ ሊያስከትል የሚችለው ጉዳት በጉሙዝ ብሔረሰብ ሃይማኖታዊ ዕሳቤ ከሌሎች ሃይማኖቶች ጋር ተዛምዶ ተፈክሯል፡፡

### 2.1.1.6. የከበራ (Ritual) ምንነት

ማኅበራዊ ዝግጅቶች የአንድን ማኅበረሰብ ውስጣዊ ስሜት ከፍ ባለ ድምጽ መግለጫ ዕሴቶች ናቸው፡፡ በጉሙዝ ብሔረሰብ ከሚገኙ ማኅበራዊ ዝግጅቶች ውስጥ አንዱ የመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ አቀባበል ስርዓት ከበራ ነው፡፡ በከበራው ላይ የሚነገሩ ንግሮች፣ የሚቀነቀኑ ዜማዎች፣ የሚለበሱ አልባሳት፣ የሚጠለቁና የሚነገቱ ጌጣጌጦች፣ የሚከወንባቸው ቁሳቁሶች፣ የሚታዩ ትዕምርቶች ወዘተ ክወናዎች በመነሳት የጉሙዝን ማኅበረሰብ ውስጣዊ ፍላጎት፣ አመለካከት፣ ፍልስፍና፣ እምነት፣ የምንረዳበት አጋጣሚ ይፈጥርልናል፡፡ ይህን ጉዳይ አስመልክቶ እነSims ‹‹Groups frequently devise ceremonies or performances that enact deeply held beliefs or values. These are ritual, and they make our inner experience of traditions visible and observable to members of the group and often to out siders.›› (2005;94) ብለዋል፡፡

ከበራን በተመለከተ በርካታ ፎክሎረኞች ሀሳባቸውን ሰንዝረዋል፡፡ ከበራ ምንድነው? ፣ ምን ላይ ያተኩራል? ፣ እንዴት ይጠናል? ፣ ዓይነቶቹ ምን ምን ናቸው? እና ከመሳሰሉት ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ሀሳባቸውን በጽሑፉ ካሰፈሩት በርካታ ፎክሎረኞች መካከል የተወሰኑት ከሰነዘሩት ሀሳብ ውስጥ ለዚህ ጥናት አስፈላጊ የሆኑ ነጥቦች እንደሚከተለው ተቃኝተዋል፡፡ ጽንሰ ሀሳቡን በተመለከተ ሀሳብ ካሰፈሩ ጽሑፎች መክከል አንዱ የሆነው Encyclopidia of Social and Cultural Anthropology ከተለያዩ ትወራዎች በመነሳት ከበራ በድርጊትም ሆነ በፋይዳ ከሰዎች የዕለት ተዕለት ሕይወት የተለዩና በውስጡ የሚደረጉት ድርጊቶች የተለዩ ፋይዳና ትርጉም ኖሯቸው የሚከወኑ መሆናቸውን ይጠቁማል (2002፡ 738) ፡፡

ክበራዎች በሰዎች ሕይወት ከውልደት ጀምሮ እስከ ሞት ከዚያም አስከ ተዝካር የሚኖር የማኅበረሰብ የሕይወት ገጽታ ናቸው፡፡ ክበራ በሃይማኖት፣ በብሔር፣ በጎሳ፣ በመልክዐ ምድር የየራሳቸው የተለዬ ቀለም፣ የአከዋወን ስልትና መታወቂያ አላቸው፡፡ አንድን ክበራ ለመከወን የሚያነሳሳ፣ የሚገፋፋ በማኅበረሰብ ውስጥ የጋራ የሆነ እምነትና ዕሴት ይኖራል፡፡

Dorson (1972;160) :- ‹‹ክበራዎች በስርዓት የተቀናጁ እና የተሳታፊ አካላቱን አስተሳሰብ ትዕምርታዊ በሆነ መልኩ የሚገልጡ ናቸው፡፡›› በማለት ክወናዎች በዘፈቀደ የሚከወኑ ሳይሆኑ ማኅበረሰቡ ይሁነኝ ብሎ የሚፈፅማቸው በመሆኑንና የማኅበረሰቡን አመለካከትና ፍልስፍና እንደሚያሳዩ ይገልጻሉ፡፡ እነSims (2005፤ 95) ፡- ‹‹Most rituals bring together many types of folklore; verbal, such as chants, recitations, poems or material, such as food, books, awards, clothing and costumes.›› በማለት በሆነ ምክንያት በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ ክበራ ካለ በልዩ ልዩ የፎክሎር ዘውጎች አምሮና ደምቆ እንደሚቀርብ ያስረዳሉ፡፡

መመገብ፣ መልበስ፣ ንግግር፣ እንቅስቃሴ፣ ወዘተ. የመሳሰሉት ጉዳዮች የሰው ልጅ የዕለት ተዕለትና የማይቋረጡ ተግባራት ቢሆኑም በክበራ ውስጥ ግን የተለዬ ትርጓሜ ይኖራቸዋል፡፡ ፀዳለ ታደሰ፤ (2007፤ 16) Milton Cohen ጠቅሳ የሚከተለውን ብያኔ አስቀምጣለች፡- “Ritual is behavior; it is “religion in action”. It is personal and private behavior, as it is social.” “ክበራ ባሕርይ ነው፤ ሃይማኖት የሚተገበርበት፡፡ በኅብረተሰቡ ውስጥ ያለ የግለሰብና የግል ባሕርይ ነው፡፡”

ክበራን ክበራ ከሚያሰኙት ጉዳዮች አንዱ ድግግሞሽ ነው፡፡ ድግግሙም ወቅትን ጠብቆ ተደግሞ በመከወን እና በአንድ የክበራ አውድ ላይ አንድን ድርጊት ወይም ንግግር ደጋግሞ ማቅረብን የሚገልፅ ነው፡፡ ተመሳሳይ አከዋወን በተደጋጋሚ ሲከወን የግለሰብ ብሎም የማኅበረሰብ መለያ ይሆናል፡፡ ምንም እንኳ ከዋኝ በተለያዩ ምክንያቶች ሊቀያየር ቢችልም የክዋኔ ስርዓቱ ግን እንዴ በተፈጠረው እና በማኅበረሰቡ ዘንድ በተለመደው መልኩ የሚቀጥል ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ሲደጋገም ባህሪ ይሆናል፡፡

በሌላ በኩል Sims እና Stephens ባዘጋጁት መጻሕፋቸው ውስጥም ይህን ከላይ የተጠቀሰውን ሀሳብ በሚያጠናክር መልኩ “… rituals are performances that are repeated and patterned and frequently include ceremonial symbols and actions’’ (2011፡ 98). በማለት ሀሳባቸውን አስፍረዋል፡፡ “ክበራዎች የሚደጋገሙ፣ ቅደም ተከተል ያላቸውና

ተከታታይ የክብረ በዓል ትዕምርቶችን እና ድርጊቶችን ያካተቱ ክዋኔዎች ናቸው፡፡" የሚል ይሆናል፡፡ ይህም ብያኔ የከበራን ተደጋጋሚነት፣ በድርጊት የሚገለፁ ክንውኖች ያሉበት እንዲሁም ድርጊቶቹ ትዕምርታዊ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ከላይ ከተሰነዘሩት ብያኔዎች በመነሳት ከበራ ታስቦባቸው ተደጋግመው የሚከወኑና የግለሰብ ብሎም የማኅበረሰብ ባሕርይን የሚያመላክቱ የክንውኖች ስብስብ ነው ብሎ ማጠቃለል ይቻላል፡፡

ከበራዎች ማኅበራዊ ትስስርን በማጠናከር፣ ግለሰባዊ ማንነትን ከማኅበረሰቡ አመለካከት አኳያ የመቅረጽና የማፅናት፣ ሥነ ልቡናን የመገንባት፣ በሽታን የመፈወስ፣ ዘርን የማብዛት፣ ኃጢአትን የማንጻት፣ ማኅበራዊ ደረጃን የመለወጥ፣ ረጅም ዕድሜን የማጎናጸፍ ፋይዳ እንዳላቸው፤ Dorson (1972; 167) ይገልጻሉ፡፡ ከበራን በምናጠናበት ወቅት አውድና ክዋኔ ተሳስረው መገኘታቸው የግድ ስለሆነ ከበራው የትና እንዴት ተከወነ? ከበራውን የሚሰሩት እነማን ናቸው? ተሳታፊዎች እነማን ናቸው? የተሳታፊዎቹ ምላሽ ምን ይመስላል? ከበራውን ለማድመቅ አገልግሎት ላይ የዋሉት የፎክሎር ገፅታዎች እንደምን ያሉ ናቸው? የታሪኩ መዋቅር ምን ይመስላል? በከበራው ወቅት የሚከውኑት ነገር፤ በሰርካዊው ሕይወታቸው ከሚከውኑት በምን ይለያል? እንዴት ጀምረው እንዴትስ ነው የሚቋጩት? ወዘተ የሚሉ መሠረታዊ ነገሮች ላይ ማተኮር እንዳለብን Bauman (1975; 312) ይገልጻሉ፡፡

ውልደት እንደሚመጣ በእርግዝና ይታወቃል፣ ሞት እንደሚመጣ ሰው በመሆን የተገለጠ ነው፤ የወር አበባ እንደምታይ ደግሞ ሴት ሆና በመወለድ እና በተፈጥሮ አካላዊ ምልክቶች ይታወቃል፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚከወን የወር አበባ አቀባበል ሥርዓት ጊዜ ተቆርጦ በቀጠሮ ባይከወንም፤ ከተከሰተ በኋላ ግን የወዲያው ጊዜና ቦታ ስላለው እና ሴት በመሆንና በተፈጥሯዊ ምልክት ስለሚታወቅ ከበራ ነው፡፡ ባጋጣሚ ሲመጣ ቢቀበሉትም ከበራውን የሚከወኑት ግን ይሁነኝ ብለው አስበውበት ነው፡፡

### 2.1.1.6.1 የከበራ መገለጫዎች

Pascal Boyer እና Pierre Liénard የከበራን የሰው ልጅ ባሕርይነት በጥልቀት ያሳዩ ሲሆን የከበራ አጠቃላይ መገለጫዎች ናቸው ያሏቸውን አምስት ነጥቦች እንደሚከተለው ዘርዝረዋል፡፡

**ሀ. አስገዳጅነት** /Compulsion/፡- ከበራ በተለመደበት ማኅበረሰብ ውስጥ የሚኖር አንድ ሰው እንደሌሎቹ የማኅበረሰቡ አባላት እርሱም እንዲያከብር ይገደዳል፡፡ የሚያስገድደው ከበራውን ባለመከወኑ ሊደርሱብኝ ይችላሉ ብሎ የሚያስባቸው ነገሮች በሚፈጥሩበት ስጋት ነው፡፡

ከስጋት ነፃ የሆነ ኑሮ ለመምራት ሌሎቹ የማኅበረሰቡ አባላት የሚከውኗቸውን ከበራዎች መከወን እና ከማኅበረሰቡ ጋር መመሳሰል ይኖርበታል፡፡

**ለ. ጥብቅነት /ኢ-ተለዋዋጭነት** /Rigidity, adherence to script/፡- ይኸኛው መገለጫ የሚያመለክተው ከበራ መከወን ያለበት ከዚህ በፊት ይከወን በነበረበት መንገድ ነው የሚለውን የሰዎች እሳቤ ነው፡፡ ቀድሞ ከነበረው የከበራ ስርዓት ማፈንገጥ አደገኛና ለመቅሰፍት ያጋልጣል የሚል እምነት በልቦናቸው ያሳድራሉ፡፡ ስለዚህ በፊት የነበረውን ሥርዓተ ክዋኔ ሳይለቁ አጥብቀው በመያዝ ከበራውን ያከናውናሉ፡፡ እነርሱም ለቀጣይ ከዋኞች ያንኑ የማይለዋወጥ ሥርዓተ ክዋኔን ያስተላልፋሉ፡፡

**ሐ. ግብ ቅነሳ** /Goal-demotion/፡- በከበራ ክዋኔ ውስጥ የሚታዩት ድርጊቶች ከተለመደው የሰው ልጆች እንቅስቃሴ የተቀዱ ድርጊቶች ናቸው፡፡ የእነዚህ ተለምዷዊ ድርጊቶች በክዋኔው ውስጥ ተደጋግሞ መታዬት የከበራውን ግብ ዝቅ ያደርጉታል፡፡ ምክንያቱ ደግሞ በትክክል ግባቸው ያልተለዩ ስለሆኑ ወይም ግባቸው ስውር (ሰዎች በቀላሉ ሊረዱት የማይችሉት) በመሆኑ ነው፡፡

**መ. ውስጣዊ ድግግሞሽና አላስፈላጊ ድግግም** /internal repetition and redundancy/፡- ቀደም ባሉት ትርጓሜዎች ውስጥ ድግግሞሽ አንዱ የከበራ መለያው እንደሆነ ለመጥቀስ ተሞክሯል፡፡ ከበራ አንድ ወቅት ላይ ወይም አንድ ጊዜ ብቻ ተከውኖ የሚያቆም አይደለም፡፡ የሰው ልጆች ባሕርይ እንደመሆኑ መጠን እየተደጋገመ የሚከወንና ከአንዱ ትውልድ ወደሌላኛው የሚተላለፍ ነው፡፡ ይህ አንዱ የድግግም መልኩ ሲሆን በተጨማሪም በአብዛኛው በአንድ የከበራ ክዋኔ ውስጥ አንድ ድርጊት፣ የሰውነት እንቅስቃሴ ወይም አባባል ተደጋግሞ ይቀርባል፡፡

**ሠ. የመልዕክት /የጭብጥ መገደብ**/A restricted range of themes/፡- በዚህ የከበራ መገለጫዎች በሰፈሩበት መጣጥፍ ውስጥ Dulaney & Fiske (1994)ን በመጥቀስ እንደተገለፀው አብዛኞቹ ከበራዎች ትኩረታቸው ከእርኩሰት መንፃት፣ አደጋ መከለልና የመሳሰሉት ጉዳዮች ነው፡፡ የሚከወኑትም ከእነዚህ ነጥቦች ጋር በተያያዘ ልቦናንና አካልን ወይም ቁስን ከእርኩሰት ማንፃት ወይም ሊከሰት ከሚችል አደጋ መጠበቅ ነው (Boyer & Liénard፣ 2006፣4)፡፡ የከበራ ዓይነቶችና ዘውጎች እንዲሁም የአከባበር ሂደቶቻቸው በርካታ ቢሆኑም እነዚህ አምስት ነጥቦች በአብዛኛዎቹ ከበራዎች ላይ የሚታዩና የጋራ መገለጫዎች

ናቸው፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት በሚዳስሳቸው የከበራ ዓይነቶች ውስጥ እነዚህ መገለጫዎች የሚታዩ መሆን አለመሆናቸው በትንታኔው ውስጥ ተዳሷል፡፡

### 2.1.1.6.2. የከበራ ዓይነቶች

ከበራዎች ከሚከወኑባቸው አውዶች አንጻር የከፍተኛ አውድ ከበራ (high context) እና የዝቅተኛ አውድ ከበራ (low context) በማለት በሁለት ይከፍሏቸዋል፡፡ የከፍተኛ አውድ ከበራ በተደራጀና በታቀደ መልኩ የሚከወን ከበራ ሲሆን፤ የዝቅተኛ አውድ ከበራ በተቃራኒው ድንገቴ በሆነ ባልተደራጀና ባልታቀደ መልኩ የሚከወን ከበራ ነው፡፡ (Sims and Stephens (2005; 98-99) በሌላ በኩል ደግሞ ከበራዎችን ከይዘታቸው አንጻር ‹‹መንፈሳዊ›› (Sacred) እና ‹‹ዓለማዊ›› (Secular) ብለውም በሁለት ይከፍሏቸዋል፡፡ መንፈሳዊ ከበራዎች ሃይማኖታዊ ጉዳዮች፣ መንፈሳዊ ነገሮች በትዕምርታዊነትና በዜማ የሚጠናባቸው ናቸው፡፡ በዋናነት የከዋኞችን እምነት የሚያሳይ፣ ስለዓለም ያላቸውን አመለካከት፣ ስለሰዎች፣ ስለሕይወት፣ ስለወር አበባ ያላቸውን አተያይ የሚያሳይ የከበራ ዓይነት ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ዓለማዊ ከበራዎች ከሃይማኖት ሥርዓት የወጡ ናቸው፡፡

ደሞ በሌላ በአንዳንድ ድርሳናት ውስጥ የከበራ ዓይነቶች በአራት ተከፍለው ይቀርባሉ፡፡ ከእነዚህም ድርሳናት መካከል ለአብነት ያህል Living Folklore የተሰኘውን የSims እና Stephens መጽሐፍ መመልከት ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል Catherine Bell መሰረታዊ የከበራ ዓይነቶች ናቸው በማለት የሚከተሉትን ስድስት ነጥቦች ከበርካታ ምሳሌዎች ጋር በጽሑፋቸው ውስጥ አብራርተዋል፡፡ አያይዘውም የከበራ ዓይነቶችን እነዚህ ብቻ ናቸው ማለት እንዳልሆነና በርካታ ዓይነቶች እንዲሁም መገለጫዎች እንዳሏቸውም ጠቅሰዋል፡፡

1. **የመሸጋገሪያ ከበራ** (Rites of Passage) ፡- ይህ የከበራ ዓይነት ሰዎች ከአንድ የማኅበራዊ ሕይወት ወይም ከአንድ የሕይወት ደረጃ ወደ ሌላ ሲሸጋገሩ የሚያከብሩት የከበራ ዓይነት ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ግርዛት፣ የወር አበባ፣ ሰርግ ወዘተ… የመሳሰሉትን ያካትታል፡፡ የሕይወት ደረጃዎች መሸጋገሪያ በመሆኑም የሕይወት ዑደት በመባል ይታወቃል፡፡

2. **ቀነ ቀመራዊ ከበራ** (Calendrical Rites) ፡- የእነዚህ ሽግግሮች መገለጫ ከብርሃን፣ ከአየር ንብረት፣ ከግብርና ሥራ እና ከሌሎች ወቅት ላይ የተመሰረቱ ማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች ለውጥ ጋር የተቆራኘ ነው፡፡ ቀነ ቀመራዊ ከበራዎች ፀሐይን ወይም ጨረቃን የተከተሉ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የፀሐይ ቀመርን የሚከተሉ ከበራዎች በየዓመቱ

በተመሳሳይ ቀን የሚከሰቱና የሚከወኑ ናቸው፡፡ የጨረቃ ቀመርን የሚከተሉት ደግሞ ቋሚ የሆነ ቀን የሌላቸውና የጨረቃ መውጣትን (የጨረቃ ብርሃንን) ተከትለው የሚከበሩ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡- ዘመን መለወጫ፣ መስቀል፣ ጥምቀት፣ ልደት ወይም መውሊድ፣ ረመዳን ወዘተ… የመሳሰሉትን ያካትታል፡፡

3. **የመስዋዕት ማቅረቢያ ከበራ** (Rites of Exchange and Communion) ፡- በሰዎችና በመለኮታዊ ኃይል መካከል ያለ ግንኙነት የሚገለፅበትና የሚጠናከርበት የከበራ ዓይነቶች በዚህ ውስጥ ይመደባሉ፡፡ በሃይማኖታዊ በዓላት ላይ ሰዎች ለአምላካቸው ስለት፣ መባ የሚያቀርቡበት ከበራ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- የምስጋና ጊዜ፣ ዝክር፣ ወዘተ … የመሳሰሉትን ያካትታል፡፡ ለአምላካቸው ያላቸውን ፍቅር ለመግለፅ ብቻ የተለያዩ ስጦታዎችን የሚሰጡ አምልኮ የሚፈፅሙ አሉ፡፡

4. **የመከራ ጊዜ ከበራ** (Rites of Affliction) ፡- ሰዎች በሕይወት ዘመናቸው በሽታ፣ ጎርፍ፣ ድርቅ፣ ረሀብ እና ሌሎችም ተፈጥሯዊ ወይም ሰው ሠራሽ የሆኑ በርካታ አስከፊ ነገሮች እንደ ግለሰብም እንደ ማኅበረሰብም ይገጥሟቸዋል፡፡ እነዚህን መከራዎች በሚያመልኩት አምላክ ኃይል ከክፉ ደዌ፣ ከህመም ለመፈወስ ምሕረት ለማግኘት የሚደረግ ከበራ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- የጻጉሜ ፀበል፣ የአድባር ልመና፣ የወንዝ ዳር መስዋዕት፣ ሰደቃ ወዘተ … የመሳሰሉትን ያካትታል፡፡ እንደየባሕሉ የመከራ ወይም የመቅሰፍት ትርጓሜና አረዳድ ቢለያይም በባሕሉ ውስጥ ከዚህ ወገን ለሚመደቡ ክስተቶች ማኅበረሰቡ ቀድሞ ለመከላከል ወይም ምሕረት ለማግኘት የተለያዩ ከበራዎችን ይከውናል፡፡

5. **ግብዣ፣ ፆምና ክብረ በዓል** (Feasting, Fasting, and Festivals) ፡- ፆምና ግብዣ ሰዎች በሃይማኖታቸው ያላቸውን ቁርጠኝነትና ፅኑ እምነት የሚገልፁበት ከመሆኑም ባለፈ እርስ በርስ ያላቸውን ፍቅርና አንድነት የሚያንፀባርቁበትም ጭምር ነው፡፡ በጾም ወቅት ከሰርካዊ ክዋኔዎች በተለዩ መልኩ የሚከውኑት ክወና ነው፡፡ ለምሳሌ ፡- ከምግብ ዝግጅት አንጻር የጥሉላት ወይም የጾም ምግብ ማዘጋጀት፣ ከአለባበስ አንጻር ሙሉ ሰውነት የሚሸፍን ልብስ መልበስ፣ ባዶ እግር መሄድ፣ ከጸሎትና ከመዝሙራት አንጻር ወቅታዊ ፀሎት ማድረግና የንስሃ መዝሙራት መዘመር፣ ከአነጋገር አንጻር ቁጥብ መሆን ወዘተ .. የመሳሰሉትን ያካትታል፡፡

6. **ፖለቲካዊ ክበራ** (Poletical Rites) :- በፖለቲካ መሪዎች ዕሳቤ በደስታ ይሁን በሀዘን፤ በስራ ይሁን በዕረፍት የሚከበሩ ናቸው፡፡ ለምሳሌ በኛ ሀገር፡- ግንቦት 20፣ የብሔር ብሔረሰቦች ቀን፣ የሰማዕታት ቀን ወዘተ .... የመሳሰሉትን ያካትታል፡፡ የዚህ ዓይነቶቹ ከበራዎች በተለያዩ ተቋማት የሚገኙ የስልጣን ዓይነቶችንና እርከኖችን ለመገንባት፣ ለማሳዬትና ለማስተዋወቅ የሚደረጉ ናቸው፡፡ ከተራ የዕሴትና መልዕክት መተላለፊያነትም ባለፈ በአስተዳዳሪውና በሕዝቡ መካከል ያለውን መስተጋብር ተጨባጭ በሆነ መንገድ የሚያቀርቡበት የከበራ ዓነቶችን የያዘ ክፍል ነው፡፡ Catherine Bell (1997፣ 93-137)

ቀደም ባሉት ብያኔዎች ውስጥ ከበራ የሰዎች ብሎም የማኅበረሰብ ባህርይ እንደሆነ ለማሳዬት ተሞክሯል፡፡ ባህርይ ደግሞ መገለጫው ብዙ እንደመሆኑ መጠን የከበራ መገለጫዎች በርካታ ናቸው፡፡ የመገለጫዎቹ መለያየትም ከበራ የተለያዩ ዘውጎች እንዲኖሩት ያደርጋል፡፡ የእነዚህ ስድስት ነጥቦች መዘርዘርም የዚህ ውጤት ሲሆን በየባሕሉ ከዚህ የተለዬ መገለጫ ያላቸውም የከበራ ዓይነቶችም ይኖራሉ፡፡ ይህ ጥናት ከስድስቱ የከበራ ዓይነቶች ውስጥ ተፈጥሯዊ ዑደትን ተከትሎ የሚከወን፤ የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግርን የሚያሳይ እና ትዕምርታዊ እና ምስል ከሳች በሆኑ ስርዓቶች የሚከወን በመሆኑ የመሸጋገሪያ ከበራ ላይ የሚያተኩር ይሆናል፡፡

ድርብ ወርቅ (2007፤ 20) ‹‹ የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ከበራዎች ተፈጥሯዊ ዑደትን ተከትለው በየጊዜው የሚመጡ ለውጦች ናቸው፡፡ ለውጦቹ የአካል፣ የሥነ ልቡና፣ የአስተሳሰብ፣ የማኅበራዊ ደረጃ እና የባሕርይ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ለውጦችንም ሰዎች ትዕምርታዊ እና ምስል ከሳች በሆኑ ሥርዓቶች ይከውኗቸዋል፡፡›› በማለት ትገልጻለች፡፡

## 2.1.2. የንድፈ-ሀሳቦች ቅኝት

በንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት ውስጥ ክዋኔ ተኮር ንድፈ ሀሳብን (performance centered approach) እና የከበራን ምንነት የምንዳስስ ይሆናል፡፡ ክዋኔ ተኮር ንድፈ ሀሳብ በከበራ ወቅት የሚታዩ መሠረታዊ ጉዳዩችን ነቅሶ በማውጣት በአግባቡ ለመተንተን የሚያስችሉ ልዩ ልዩ ገፅታዎች ያሉት በመሆኑ እንዲሁም ከበራዎች በሰዎች ሕይወት ከውልደት ጀምሮ እስከ ሞት ከዚያም እስከ ተዝካር የሚኖር የማኅበረሰብ የሕይወት ገጽታ በመሆናቸው እያንዳንዳቸውን በዝርዝር ተመልክቷል፡፡

### 2.1.2.1. ክዋኔ ተኮር ንድፈ ሀሳብ

በአንድ ባሕላዊ ጥናት የማኅበረሰቡን ቃላዊ ጥበባትን (verbal arts) ብቻ ሰብስቦ የተወሰኑ ንድፈ ሀሳቦችን በመጠቀም እየተነተኑ ስለ ማኅበረሰቡ ባሕል የተወሰነ ማጠቃለያ ላይ መድረስ ይቻላል፡፡ ግን እነዚህን የባሕል ዘውጎች ማኅበረሰቡ ሲተርታቸው፣ ሲዘፍናቸው፣ ሲያንጎራጉራቸው፣ ሲያከብራቸው በአጠቃላይ የራሱን ስርዓት ተከትሎ ሲከውናቸው ስናይ የሚሰጡት ፍቺ የተለያዩና ሚዛን የሚደፋ ይሆናል፡፡

ክዋኔ ውበት ያለው፣ የተቀናጀ፣ በጊዜ እና በቦታ ተወስኖ በድምፅ ቅላፄ እና በአካል እንቅስቃሴ ታጅቦ ተደጋግሞ በመቅረብ የቡድንን ማንነት መገንባት የሚችል ነው፡፡ ክዋኔ ተግባቦታዊ ድርጊት ነው፡፡ ብዙውን ጊዜ ከተውኔት ጋር የሚቀራኝ ጥበባዊ ድርጊት ነው፡፡ እያንዳንዱ ክዋኔ በአጋጣሚ ውስጥ በቃልም ሆነ በተግባር እየተከወነ ይኖራል፡፡ በዚህም ህልውናውን ያስጠብቃል፡፡ ክዋኔ ከትንሽ አጋጣሚ እስከ ከፍተኛ ዝግጅት የሚያስፈልገው አጋጣሚ ድረስ ማኅበረሰቡ የሚገለገልበትን እና ራሱን የሚገልፅበት መንገድ ነው፡፡ Finnegan (1992:95) performance takes place kinds of situation from highly organized and to quite informal and impromptu. በማለት የክዋኔ መከሰቻ አጋጣሚዎችን ይገልጻሉ፡፡

ለባሕል ጥናት ክዋኔ ብቻ ሳይሆን የክዋኔው አውድ፣ (context) ከዋኝ፤ (performer) ተሳታፊዎች፣ (audiences) አውዱ፣ (context) እና የክዋኔ ጠቋሚዎች (markers) የሚጠቀሱ መሆናቸውን ነው፡፡ ክዋኔው ብቻም ሳይሆን ማኅበረሰቡ ስለክዋኔው ምንነትና ፋይዳ የሚሰጠው ፍቺ ምን እንደሆነ መገንዘብ አስፈላጊ እንደሆነ አጠንክረው ያስረዳሉ፡፡

**ሀ. ከዋኝ** የክዋኔ አለባውያን ከሚባሉት ውስጥ መሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ ከዋኙ ክዋኔውን በሚገባ አቀናጅቶ ለማቅረብም ሆነ የክዋኔውን ዓላማ ለማሳካት ማንነቱ፣ ማኅበራዊ ደረጃው፣ እድሜው፣ የአከዋወን ብቃቱ፣ የታዳሚን አያያዝ ችሎታው እና የፈጠራ ችሎታው ጉልህ ሚና አላቸው፡፡ Finnegan (1992;90) performers are also of certain ages, gender, social position, training, reputation and competence all needing investigation. በማለት ይገልጻሉ፡፡ ከዋኝ በክዋኔ ወቅት የሚያሳያቸው አካላዊ እንቅስቃሴዎች እና ድምፀቶች ለክዋኔው ወሳኝ ናቸው፡፡ እነዚህን በድል የተወጣ ከዋኝ በማኅበረሰቡ ተመራጭና ተደናቂ ይሆናል፡፡በአንድ ክዋኔ ውስጥ አንድ ሰው ብቻውን የክዋኝነት ሚና ሊጫወት ይችላል፡፡ በሌሎች ክዋኔዎች ደግሞ ታዳሚዎች ባሉበት ሊከውን ይችላል፡፡ ይህንን ሀሳብ (Finnegan (1992;89) They may be acting singly; in pairs; in asmallor large group; interacting or exchanging with other single or collective performers as leader, follower, or equal; overlapping

or interchanging with more audience- like roles. በማለት ይገልፁታል፡፡ በጉሙዝ ብሔረሰብ የመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ አቀባበል ሥርዓት ላይ ከዋኞች ሁሉ በሴቷ ስም መጪው ጊዜ መልካም እንደሚሆን በዜማ እና በንግግር ምኞታቸውን እንዲወጡ ያደርጋል፡፡

**ለ. ታዳሚ** (audiences) ለክዋኔው ህልውና ከፍተኛ አስተዋፆ አለው፡፡ የከዋኙም የከዋኝነት ሚና የሚረጋገጠው በታዳሚው በኩል የሚሰጡ አስተያየቶችና መስተጋብሮች ሲኖሩ ነው፡፡ የክዋኔው ውጤታማነት እና ግብ መቺነት የሚወሰነው በከዋኞችና በታዳሚዎች ብቃት፣ እድሜ፣ ጾታ፣ ባሕርይና ሚና ነው፡፡

**ሐ. አውድ (context)** (sims and stephens 2005;137) ‹‹… context refers to anything and everthing that surrounds a text and performance. ›› አውድ አንድ ክዋኔ በሚከወንበት ወቅት ያለው አጠቃላይ ሁኔታ እንደሆነ ነው፡፡ ይህም ክዋኔው የሚከወንበትን ጊዜና ቦታ፣ በከዋኝ እና በታዳሚ መካከል ያለ መስተጋብር፣ የመከወኛ ቁሳቁሶችን ጭምር የሚያጠቃልል ነው፡፡

1.**ተጨባጭ አውድ** (physical context)፡- የምንለው በክዋኔው ወቅት የሚታየው የመልክዓ ምድር ሁኔታ፣ የአየር ንብረቱ ሁኔታ፣ የአካላዊ እንቅስቃሴ፣ ክዋኔው የሚካሄድበትን ጊዜ፤ ከዋኙንና ታዳሚውንም በመመልከት ብቻ ተጨባጭ ሁኔታውን ለመግለፅ የሚሞከርበት የአውድ ዓይነት ነው፡፡ (ሰሎሞን፤2007 ዓ.ም.)

2. **ማኅበራዊ አውድ** (social context)፡- የምንለው ደግሞ በክዋኔ ወቅት የሚታየውን ጠቅላላ የክዋኔ መዋቅር ማለት ነው፡፡ የከዋኙን እና የታዳሚን ማንነት፣ ማኅበራዊ ደረጃ፤ (በእድሜ፣ በጎሳ፣ በመደብ፣ በፆታ፣ በሃይማኖት፤ በሙያ፣ በባህልና በሌሎች ጉዳዩች) ምክንያት የሚፈጠረው ጠቅላላ አውድ የሚመለከት ነው፡፡ በአንድ ክዋኔ ላይ የሚታዩ የከዋኝን እና የታዳሚን ስብጥር፣ በክዋኔው ላይ ያሳደረውን ተፅዕኖ፣ ከሌሎች ማኅበረሰቦች ጋር ያላቸውን ግንኙነት የምናይበት ይሆናል፡፡ (ሰሎሞን፤ 2007 ዓ.ም.)

**መ. የክዋኔ ጠቋሚዎች** (markers)፡- በአንድ ክዋኔ ውስጥ የክዋኔውን መጀመርና መጠናቀቅ እንዲሁም እየተከወነ መሆኑን የሚያሳውቁ ጠቋሚዎች መኖራቸው ይታወቃሉ፡፡ እነዚህ ጠቋሚዎች በከዋኝና በታዳሚ መካከል ያለ ግንኙነት እንዲሰምር የሚያደርጉ፣ የክዋኔውን ስርዓት መልክ የሚያስይዙ፣ የከዋኝንና የታዳሚን የክዋኔ ቅደም ተከተል የሚያሳውቁ እና ማኅበረሰቡ ይሁነኝ ብሎ ተስማምቶ የፈጠራቸው ናቸው፡፡ እነዚህ ስምምነቶች በክዋኔው ወቅት ምን መደረግ እንዳለበት ወይም የእያንዳንዱን የስራ ድርሻ ምን ሊሆን እንደሚችል

የሚጠቁሙ ናቸው፡፡ አንድ ሎር ሲከወን ከተለመደው የማኅበረሰቡ የአከዋወን ስልት እንዳይወጣ የክዋኔ ጠቋሚዎች ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ የታዳሚና የከዋኝ እንቅስቃሴ፣ መከወኛ ቁሳቁሶች ክዋኔ ጠቋሚዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ጠቋሚዎች ታዳሚዎች በክዋኔው በንቃት እንዲሳተፉ፣ እረፍት እንዲወስዱ እንዲሁም ከአንድ ድርጊት ወደ ሌላ ድርጊት እንዲሸጋገሩ ፍንጭ ይሰጣሉ፡፡ (ሰሎሞን፤ 2007 ዓ.ም.)

## 2.2. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር ጥናቱ ከሚያተኩርበት የወር አበባ አቀባበል ስርዓት (ድግትስ ጋህጃ) ጋር የተዛመዱና ጥናቱ ከሚያተኩርበት የጉሙዝ ብሔረሰብ ላይ አተኩረው የተሰሩ በተለያዩ ደረጃ የሚገኙ ጥናታዊ ጽሑፎች እና ልዩ ልዩ ጽሑፎች ተዳሰዋል፡፡ ከዚህ ጥናት ጋር በርዕሰ ጉዳዩ የሚመሳሰሉ የቢ.ኤ እና የኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሑፎች እንዲሁም በEthnological Society Bulletin ላይ የወጡ የተለያዩ ብሔረሰብ የወር አበባ አቀባበል ሥርዓትን የተመለከቱ ጽሑፎች የዳሰሳው አካል ሆነዋል፡፡ እነዚህ ልዩ ልዩ ጽሑፎች የሚዳሰሱበት መንገድም ጥናቶቹ የተሰሩበትን ደረጃ እና ዘመን መሠረት በማድረግ ነው፡፡ ይህም ማለት ከዚህ ጥናት ጋር በርዕሰ ጉዳዩ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ግንኙነት አላቸው ተብሎ የታመነባቸውን ጥናቶች ለቢ.ኤና ለኤም.ኤ እንዲሁም ሌሎች በሚሉ ርዕሰ ጉዳዮች ስር በየፈርጁ ዳሰሳ ተደርጓል፡፡ በቅድሚያ ይህ ጥናት የሚያተኩረው በጉሙዝ ብሔረሰብ ላይ አትኩረው የተሰሩ ጥናቶችን ዳሷል፡፡ ይህም እንዲሆን የተፈለገበት ምክንያት ብሔረሰቡን የተመለከቱ መረጃዎችን አስቀድሞ መገንዘብ ተገቢ ነው በሚል እምነት ነው፡፡

### 2.2.1. ትኩረታቸውን በጉሙዝ ብሔረሰብ ላይ ያደረጉ ጥናቶች

ሽፈራው ቁሜና ሌሎችም፤ ‹‹የጉሙዝ ብሔረሰብ አኗኗር፣ ወግና ባሕሎች፣ ሰኔ 1993 ድባጤ፤ ያልታተመ፡፡›› ይህ ጥናት በድባጢ ወረዳ መምህራን የተጠና ሲሆን የጉሙዝ ብሔረሰብ አኗኗር፣ ወግና ባሕላቸውን ማሳዬት ዓላማው ያደረገ ነው፡፡ አጥኝዎቹ ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስም ጥናቱን ያካሄዱበት ሂደት የጉሙዝ ብሔረሰብ በብዛት ከሚኖርባቸዉ የድባጢ ወረዳ ቀበሌዎች ውስጥ ሁለቱን ብቻ በመምረጥ እና ከ13 በላይ የሀገሩ ሽማግሌዎችን ቃል-መጠይቅ በማድረግ ነው፡፡

ጥናቱ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ባይተነተንም የጉሙዝ ብሔረሰብ ዕለታዊ አኗኗር ማለትም ሀዘንና ደስታቸውን፣ የዘወትር ሥራቸውን፣ ማኅበራዊ ግንኙነታቸውን፣ ምግብና መጠጣቸውን፣ ወዘተ... በመግለጽ ምን እንደሚመስል በትርክት ያሳያል፡፡ የመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ አቀባበል ሥርዓትም አንዱ ባሕላዊ ዕሴታቸው መሆኑን ጠቁሟል፡፡ በክለሳ ድርሳናት በኩል ምንም አለመጠቀማቸውና መረጃውን በትረካ ከማስቀመጥ ውጪ አለመተንተናቸው የጥናቱን ድክመት ያሳያል፡፡

ገረመው ፈይሳ፣ ‹‹ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና የሴቶች ተፅዕኖ በጉሙዝ ብሔረሰብ፣ መጋቢት 1995 አሶሳ፤ ያልታተመ፡፡›› ይህ ጥናት በካማሽ ዞን ካሉ ወረዳዎች ውስጥ በያሶ ወረዳ የተሰራ የኤም ኤ ማሟያ ጥናት ሲሆን በጉሙዝ ብሔረሰብ ውስጥ የሚታዩ ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶች፣ በሴቶች ላይ የሚያደርሱትን ተጽዕኖ መተንተን ዓላማው ያደረገ ነው፡፡ አጥኚው ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስም ጥናቱን ያካሄዱበት ሂደት የጉሙዝ ብሔረሰብ በብዛት ከሚኖርባቸዉ ወረዳዎች ውስጥ ያሶ ወረዳን በመምረጥ እና ከስድስት በላይ የሀገሩ ሽማግሌዎችን፣ የተማሩ የብሔረሰቡ ተወላጆችን ቃል-መጠይቅ በማድረግ፤ ቦታው ድረስ ሄዶ ምልከታ በማድረግ፣ የቡድን ውይይት በማድረግ መረጃዎችን ሰብስቦ ለመተንተን ችሏል፡፡

በጥናቱም በብሔረሰብ ውስጥ ያሉ ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶች የሚባሉትን ሳይንሳዊ በሆነ የጎጅነት መለኪያ የተለዩትን ብቻ ወስዶ በሴቶች ላይ የሚያደርሱትን ተፅዕኖ ከሥነ ልቡናዊ ጉዳት፣ ከማኅበራዊ ተፅዕኖ፣ ከጉልበት ብዝበዛ፣ ከቤተሰብ ኃላፊነት ወዘተ.. አንጻር እየተነተነ ለማሳየት ችሏል፡፡ ተዛማጅ ጽሑፎችን በመጠቀሙና ከሌሎች ብሔረሰቦች ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶች ጋር ለማስተሳሰር እና የተፅዕኖውን መጠን ከፍ አድርጎ ለማሳዬት መሞከሩ ጉዳዩ ትኩረት እንዲሰጠው ያደርገዋል፡፡

### 2.1.2 ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር የሚዛመዱ ጥናቶች እና ጽሑፎች ዳሰሳ

በዚህ ርዕስ ስር በቢ.ኤ. እና በኤም.ኤ. ደረጃ የመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ አቀባበል ስርዓት ላይ አትኩረው የተሰሩ ጥናቶችን እንዲሁም በ Ethnological Society Bulletin ላይ የወጡ የተለያዩ ብሔረሰብ የመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ አቀባበል ስርዓት የተመለከቱ ፅሁፎችን እንዲሁም ለኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ የቀረቡና ሌሎች በሚሉ ምድቦች ስር አካትቼ ተመልክቷል፡፡

### 2.2.2.1. የወር አበባ አቀባበል ስርዓት ላይ ያተኮሩ የኤም.ኤ. ጥናቶች

በቀጥታ የወር አበባ እና የወር አበባ አቀባበል ሥርዓት (ድግትስ ጋሀኛ) ላይ ብቻ ያተኮሩ የኤም.ኤ. ጥናቶችን፣ በየትኛውም ብሔር ላይ ማግኘት አልቻልኩም፡፡ ነገር ግን በጉሙዝ ብሔረሰብ የተለዩ ፎክሎራዊ ጉዳይ ላይ ጥናት ሲያደርጉ በተያያዥነት የመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ አቀባበል ሥርዓት ላይ ጥቂት ማብራሪያ የተሰጠባቸው ሁለት ጥናቶችን ለማዬት ችያለሁ፡፡

የመጀመሪያው የሳሙኤል አክሊሉ ‹‹የጉሙዝ ብሔረሰብ ሀገረሰባዊ ልማድ በተለይ የጋብቻ ሥርዓተ ክዋኔ፣ (ቢ.ኤ ዲግሪ) ፣ አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ፣ (2000 ዓ.ም) ፡፡ ›› የቀረበ ጥናት ነው፡፡ ይህ ጥናት የቢ.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ ሲሆን በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በመተከል ዞን ዳንጉር ወረዳ መረጃ ተሰብስቦ የተጠና ነው፡፡ በጉሙዝ ብሔረሰብ ዘንድ በተለይ ከጋብቻ ጋር ተያይዞ ያሉ ልማዳዊ ድርጊቶችን በገላጭ ትንተና አስፍሯል፡፡

የጉሙዝ ሴት ልጅ በብሔረሰቡ ከሚታወቁ አምስት ዓይነት የጋብቻ ስርዓቶች ማለትም የለውጥ ጋብቻ፣ የማደጎ ጋብቻ፣ የጥሎሽ ጋብቻ፣ የጠለፋ ጋብቻ እና የውርስ ጋብቻ በአንዱ ከመዳሯ በፊት ዳሪውም ሆነ አግቢው አካል ልጅቱ የወር አበባ ማዬቷና ማኅበራዊ የጋብቻ ነጻነትና ዕውቅና መሰጠቷን ያረጋግጣሉ፡፡ የሚል ሀሳብ በማንሳት የወር አበባ ለመጀመሪያ ጊዜ ስታይ የሚደረገው ክዋኔ ለጋብቻ መድረሷን የማወጃ ሥርዓት እንደሆነ በጥናቱ ውስጥ ጠቁሞ አልፏል፡፡ በአጠቃላይ በጥናቱ ውስጥ የጉሙዝ ብሔረሰብን የጋብቻ ሂደት እና ልማዳዊ ክንውኖችን ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በገላጭ ትረካ ከመግለፅ ውጭ በወር አበባ ላይ የሰጠው ጠለቅ ያለ ትንታኔ የለም፡፡

ሁለተኛው ጥናት የድርብወርቅ ብፁዕ ‹‹ የጉሙዝ ብሔረሰብ ዋና ዋና የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ሥርዓት በማንዱራ ወረዳ፣ (ኤም ኤ ዲግሪ)፣ አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ፣ (ሰኔ/2007 ዓ.ም) ፡፡›› የቀረበ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ ነው፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ አጥኝዋ የጉሙዝ ብሔረሰብ ዋና ዋና የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች በማለት የውልደት ስርዓት፣ የመጀመሪያ የወር አበባና የወንድ ግርዛት ስርዓት፣ የጋብቻና የሰርግ ስርዓት እንዲሁም የሀዘንና የተስካር ሥርዓት በማለት በአራት ከፍላ እንዴት የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃ እንደሆነ ተንትናለች፡፡

በዚህ ጥናት ከኔ ጥናት ጋር የተገናኘው የመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ አቀባበል ሥርዓት ሲሆን አጥኚዋ ክዋኔውን በአጭሩ በመግለፅ የወር አበባ ያየችው ልጅ ከቤተሰቦቿ ተለይታ ጎጆ ቤት የቆየችበትን ጊዜ መለየት (ለ ይጠብቃል) የሽግግር ደረጃ፣ ከወር አበባ መሄድ በኋላ የምትቆይበትን ጊዜ የመሸጋገር ደረጃ እና ከክዋኔው ፍጻሜ በኋላ ያለውን የቤተሰብ መቀላቀል ደግሞ የመዋሐድ ደረጃ በማለት መድባዋለች፡፡ ነገር ግን በመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ አቀባበል ሥርዓት (ድግትስ ጋህጃ) ላይ ያሉና የሚባሉ ተረኮችን፣ ትዕምርቶችን፣ ክዋኔዎችን፣ ሙሉ በሙሉ ከመግለጽ ጀምሮ ማኅበረሰቡ ለወር አበባ ያለውን አመለካከትና ፍልስፍና አልተነተነችም፡፡ የኔ ጥናት ይህን ክፍተት በመሙላት የተሠራ ነው፡፡

ሶስተኛው ጥናት ደግሞ ‹‹የኦሮሚያና የሶማሌ ክልሎች የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች የወር አበባ ንጽህና አጠባበቅ›› በሚል ዩኒሴፍ በቅርቡ በኦሮሚያና በሶማሌ ክልሎች የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ላይ ያስጠናው ነው፡፡ (©UNICEF Ethiopia /2017/Tadesse KAP) የወር አበባ ተፈጥሯዊ የሴቶች ጉዳይ ቢሆንም፣ ‹‹በተማሪዎቹ ላይ የዕውቀት፣ የአመለካከት እና የልምድ ችግር ጎልቶ ይታያል፡፡ ወንዶች ስለሚያሾፉባቸው ሴቶች ብዙውን ጊዜ የወር አበባ ሲያዩ እያለቀሱ ትምሕርታቸውን አቋርጠው መሄዳቸው በምክንያትነት ይነሳል፡፡ አንዳንድ ጊዜ በአጠቃላይ ትምሕርት ቤቱን ለቀው እንዲወጡ ወይም ትምሕርታቸውን እንዲያቋርጡ ምክንያት ይሆናል፡፡››

እንደ ዩኒሴፍ እውቀት፣ አመለካከትና ተግባር (KAP) ጥናት ‹‹በኢትዮጵያ ከሚገኙ ልጃገረዶች ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ለመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ ከማየታቸው በፊት ስለወር አበባ ምንም ነገር ስለማያውቁ ይደናገጣሉ፡፡ ብዙ የጉርምስና ዕድሜ ያላቸው ልጃገረዶች ስለወር አበባ ከሌላ ሰው ጋር በጭራሽ አይወያዩም፡፡ በወር አበባ ወቅትም ትምሕርት ቤት የሚቀሩባቸው ዋና ዋና ምክንያቶች የህመም ስሜት፣ ምቾት ማጣት እና መሳለቂያ መሆን የሚሉ ተጠቅሰዋል፡፡ የወር አበባ ለመጀመሪያ ጊዜ ማዬት ሲጀምሩ ‹ልጃገረዶች ከእንግዲህ ድንግል አይደላችሁም› የሚለው የተለመደና የተሳሳተ አመለካከት አለ፡፡ እነዚህ አለመግባባቶች ከማሾፍ በተጨማሪ ልጃገረዶች እፍረት እንዲሰማቸው እና እራሳቸውን እንዲያገሉ ያደርጋቸዋል፡፡ በኢትዮጵያ 11% ሴት ተማሪዎች ከወር አበባ ጋር በተያያዘ ምክንያት ትምህርታቸውን ያቋርጣሉ፡፡ ››

ስለሆነም የወር አበባ ንጽህና አጠባበቅ በተመለከተ በትምሕርት ቤት ላይ በመስራት ልጆችን በመረዳት ግንዛቤያቸውን ማስፋትና የወንዶችን ማሾፍ በመቀነስ ሴቶች ልጆች ትምሕርት ቤት እንዲቆዩ ለማድረግ ቁልፍ ሚና አለው፡፡ በወር አበባ ዙሪያ ያለውን ዝምታ መስበር እና

ወንዶችን ስለዚህ ተፈጥሯዊ ፀጋ ማስተማር፣ ጎጂ የሆነን ኩርፊያ መቀነስ እንደ ቁልፍ መፍትሄ ይታያል፡፡ ልጃገረዶች በትምሕርት ቤት ውስጥ የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍ ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ የግንዛቤ ስሜትን ይጨምራል በሚል ሀሳብ ይቋጫል፡፡

### 2.1.2.2 የወር አበባ ላይ ያተኮሩ ሌሎች ጽሑፎች

በዚህ ርዕስ ጉዳይ ስር ቅኝት የሚደረግባቸው የተለያዩ ብሔረሰቦችን የወር አበባ አቀባበል ስርዓት አስመልክቶ የታተሙና በተለያዩ ሴሚናሮች ላይ የቀረቡ ጽሑፎች ናቸው፡፡ በቅድሚያ ለማዬት የተፈለገው አንድ ሴት የወር አበባ ስታይ እንዲህ ታድርግ፣ እንዲህ አታድርግ ተብሎ የታዘዘውን መጽሐፍ ቅዱሳዊና ቅዱስ ቁርሃናዊ መመሪያ ነው፡፡

ይኸውም የመጀመሪያዉ በኦ ዘሌ 15 ፤19 - 30 ድረስ ያለው እና በቅዱስ ቁርሃን አል በቀራ፤ 222 ያለው ፍካሬያዊ ፍች እና ሃይማኖታዊ ትርጓሜ ይዳሰሳል፡፡ ትዕዛዛቱ በቅደም ተከተል እንዲህ ይላሉ፡- ‹‹ሴት ፈሳሽ ነገር ቢኖርባት በስጋዋም ያለው ፈሳሽ ነገር ደም ቢሆን፤ በመርገምዋም ሰባት ቀን ትቀመጣለች፤ የሚነካትም ሁሉ እስከ ማታ ድረስ ርኩስ ነው፡፡ መርገምም ስትሆን የምትተኛበት ነገር ሁሉ ርኩስ ነው፤ የምትቀመጥበትም ነገር ሁሉ ርኩስ ነው፡፡ መኝታዋንም የሚነካ ሁሉ ልብሱን ያጥባል፤ በውኃም ይታጠባል፤ አስከ ማታም ድረስ ርኩስ ነው፡፡ የምትቀመጥበትንም ነገር ሁሉ የሚነካ ሁሉ ልብሱን ያጥባል፤ በውኃም ይታጠባል፤ አስከ ማታም ድረስ ርኩስ ነው፡፡ በመኝታዋም ላይ ወይም በምትቀመጥበት ነገር ላይ ቢሆን ሲነካው አስከ ማታም ድረስ ርኩስ ነው፡፡ ማንም ከእርሷ ጋር ቢተኛ መርገምዋም ቢነካው፤ ሰባት ቀን እርኩስ ነው፤ የሚተኛበትም መኝታ ሁሉ ርኩስ ነው፡፡ ሴትም ከመርገም ቀን ሌላ ደምዋ ብዙ ቀን ቢፈስ፤ ወይም ደምዋ ከመርገምዋ ወራት የሚበልጥ ቢፈስ፤ በመርገምዋ ወራት እንደሆነች እንዲሁ በፈሳሽዋ ርኩስነት ወራት ትሆናለች፤ ርኩስ ናት፡፡ ደምዋም በሚፈስበት ወራት ሁሉ የምትተኛበት መኝታ ሁሉ በመርገምዋ ጊዜ እንደነበረው መኝታ ያለ ይሆንባታል፤ የምትቀመጥበት ነገር ሁሉ እንደ መርገምዋ ርኩስነት ርኩስ ነው፡፡ እነዚህንም ነገሮች የሚነካ ሁሉ ርኩስ ነው፤ ልብሱንም ያጥባል፤ በውኃም ይታጠባል፤ እስከ ማታም ድረስ ርኩስ ነው፡፡ ከፈሳሽዋም ብትነጻ ሰባት ቀን ትቆጠራለች ከዚያም በኋላ ንፁሕ ትሆናለች፡፡ በስምንተኛውም ቀን ሁለት ዋኖሶች ወይም የርግብ ግልገሎች ይዛ ወደ ካህኑ ወደ መገናኛው ድንኳን ደጃፍ ታመጣቸዋለች፡፡ ካህኑም አንደኛውን ለኃጢአት መስዋዕት፤ ሌላውንም ለሚቃጠል መስዋዕት ያቀርባል፤ ካህኑም ስለ ፈሳሽዋ ርኩስነት በእግዚአብሔር ፊት ያስተሰርይላታል፡፡›› ይህ ሃይማኖታዊ አንድምታው ተቃኝቷል፡፡

ሁለተኛው በቅዱስ ቁርሃን እንዲህ ይላል፡- ‹‹ ከወር አበባም ይጠይቁሃል፣ እርሱ አስጠያፊ ነው፡፡ ሴቶችንም በወር አበባ ጊዜ ራቋቸው፡፡ ንፁህ እስከሚሆኑም ድረስ አትቅረቧቸው፡፡ ንፁህ በሆኑም ጊዜ አላህ ካዘዛችሁ ስፍራ ተገናኙዋቸው፡፡ አላህ (ከኃጢአት) ተመላሾችን ይወዳል፤ ተጥራሪዎችንም ይወዳል በላቸው፡፡›› (አል በቀራ፤ 222) የወር አበባ የምታይ ሴት በእስልምና ሃይማኖታዊ ትዕዛዝ መሰረት አትጾምም፣ መስጅድ አትገባም፣ ቅዱስ ቁርሃኑን መንካት አትችልም፣ ሶላት መስገድ አትችልም፣ እንዲሁም ከግብረ ስጋ ግንኙነት ትከለከላለች፡፡ ይህ ሃይማኖታዊ ትዕዛዝ በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ እስከአሁን የሚተገበር ፅኑ ትዕዛዝ ነው፡፡ ስለዚህ ሃይማኖታዊ ትርጓሜው ከባህሉ ጋር ተሰናስሎ ተቃኝቷል፡፡

ሶስተኛው ሳይንሳዊ እይታው ነው፤ (ዶ/ር ሙስጠፋ፤ 4) ላይ ‹‹የወር አበባ ከአስር እስከ 14 ዓመት አንስቶ ከ45 እስከ 50 ዓመት የሚዘልቅ ዑደት ነው። የወር አበባ ወርኃዊ ዑደት የሚፈጠረው በየ28 ቀን ልዩነት ሲሆን፣ ወደ ጽንስነት ያልተለወጠ እንቁላል ፈርሶ በደም መልክ የሚወጣበት ሂደት ነው። የ28 ቀን ዑደቱ ሁለት ደረጃዎች አሉት። የመጀመሪያው የወር አበባ ከጀመረበት ቀን አንስቶ ያሉትን ሁለት ሳምንታት ያካትታል። በዚህ ወቅት ከሴቶች መራቢያ ሕዋስ በአንዱ እንቁላል ማደግ ይጀምራል። የእንቁላሉን እድገት የሚያፋጥን ሆርሞንም ይመረታል። ወደ አስራ አራተኛው ቀን አካባቢ እንቁላሉ ሲያድግ በማኅጸን ቧምቧ አድርጎ ወደ ማኅጸን ይወርዳል። እንቁላሉ ከወንድ ዘር ጋር ከተዋሐደ የእርግዝና ሂደት ይጀመራል። ውሕደቱ ካልተፈጠረ እንቁላሉ ከሁለት ወይም ከሦስት ቀናት በኋላ ሞቶ ይወገዳል። የዑደቱ ሁለተኛ ደረጃ በአስራ አራተኛው ቀን ጀምሮ በኻያ ስምንኛው ቀን ይጠናቀቃል። በኻያ አምስተኛው ቀን በማኅጸን ውስጥ የሚመረተው የሆርሞን መጠን ቀንሶ ከሦስት እስከ ሰባት ቀን ደም ይፈሳል። በዚህ መንገድ የሚፈጠረው የወር አበባ ወርኃዊ ሂደትን ይከተላል።›› ይላል፡፡ ስለሆነም በጉሙዝ ማኅበረሰብ ዘንድ ያለው ባሕላዊ ፍልስፍና እና ምልከታ በዚህ ጥናት ተፈክሯል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

## 3. የጥናቱ አካባቢያዊና ማኀበረ ባሕላዊ ዳራ

### 3.1. የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ወሰን ገፅታ

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ከኢትዮጵያ አስር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት አንዱ ሆኖ በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍል የሚገኝ ክልል ነው። 50 ሺህ 380 ስኩዌሩ ኪሎ ሜትር ስፋት ይዞ የሚገኘው ይኸው ክልል ሶስት ዞኖችና 21 ወረዳዎች፣ ሶስት ከተማ አስተዳደሮች እና አንድ ልዩ ወረዳ ያለው ሲሆን በሰሜን ከአማራ፣ በምስራቅ ከኦሮምያ፣ በደቡብ ከጋምቤላ እና በምዕራብ ከሱዳን ይዋሰናል፡፡ (ቤጉክመ ዓመታዊ መጽሔት መግቢያ)

በአሁኑ ሰዓት የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ግንባታም የሚካሄደው በዚሁ ክልል ነው። የኢፌዴሪ ማዕከላዊ ስታስቲክስ ኤጀንሲ እ.ኤ.አ. በ2007 ባደረገው የሕዝብና ቤት ቆጠራ ውጤት እንደሚያመለክተው በክልሉ 784 ሺህ 345 ሕዝብ የሚኖር ሲሆን በርታ፣ ጉሙዝ ሽናሻ፣ ማኦ እና ኮሞ የተሰኙ አምስቱ ነባር[9] የሚባሉ ብሔረሰቦችን ጨምሮ አማራ፣ ኦሮሞ፣ አገው፣ ትግሬ፣ ሀድያና ሌሎችም የኅብረተሰብ ክፍሎች በክልሉ ይኖራሉ። በክልሉ በሕዝብ ብዛት በቁጥር የበርታ ብሔረሰብ አንደኛ ደረጃ ሲይዝ ሁለተኛውን ደረጃ የሚይዘው የአማራ ብሔር ሲሆን ቀሪዎቹ በቅደም ተከተል ተዘርዝረዋል፡፡ ጉሙዝ፣ ኦሮሞ፣ ሺናሻ፣ አገው፣ ማኦ፣ ኮሞ፣ ትግሬ፣ ሃዲያ በቅደም ተከተል እንደሚገኙ የማዕከላዊ ስታትስቲክስ መረጃ ያስረዳል (CSA, 2007)።

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የተለያዩ የተፈጥሮ ሐብቶች እና ሰፋፊ የልማት አማራጮች ያሉበት ክልል ነው። በክልሉ ከሚገኙ ተፈጥሯዊ ሀብቶች መካከል ወርቅ፣ እብነበረድ፣ የእጣንና የሽቶ ዛፎች የሚጠቀሱ ናቸው። ምንጭ (የኢፌዲሪ ሕገ-መንግስትና የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ሕዝቦች ታሪክና ተጠቃሚነት ፡፡ ለ9ኛው የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን በዓል ለውይይት የቀረበ ሰነድ፣ ህዳር 2007 ዓ.ም)

---

[9] በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ሕገ መንግስት አንቀፅ ሁለት መሠረት ነባር የሚባሉ ብሔረሰቦች በርታ፣ ጉሙዝ፣ ሽናሻ፣ ማኦና ኮሞ ሲሆኑ ክልሉን የመሰረቱና የክልሉ ባለቤት ናቸው ይላል፡፡

## 3.2. አስተዳደራዊ ገፅታ

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ከ1983 ዓ.ም ወዲህ በአዲስ መልክ የተቋቋመ ክልል ሲሆን፤ የክልሉ ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት መሥርተው ራሳቸውን በራሳቸው እንዲያስተዳድሩ ባገኙት መብት መሠረት፤ ከክልል ጀምሮ እስከ ቀበሌ መስተዳድር ድረስ የራሳቸውን አስተዳደር መሥርተዋል፡፡ በአሁኑ ሰዓትም ክልሉ በሦስት ዞኖች፣ በ21 ወረዳዎች፣ በሶስት ከተማ አስተዳደሮች፣ በአንድ ልዩ ወረዳ እና በ475 የገጠርና የከተማ ቀበሌ አስተዳደሮች የተዋቀረ ነው፡፡

የክልሉ ዋና ከተማም አሶሳ ስትሆን ከአዲስ አበባበ 678 ኪ.ሜ. እርቀት ላይ ትገኛለች፡፡ በክልሉ ነባር የሚባሉ ብሔረሰቦች በርታ 25.41%፣ ጉሙዝ 20.88 %፣ ሽናሻ 7.72%፣ ማኦ 1.96 % እና ኮሞ 0.99 % ሲሆኑ አማራ 21.69%፣ ኦሮሞ 13.55% እና ሌሎች 7.80% ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በክልሉ ይኖራሉ፡፡ ምንጭ (የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ሕዝቦች ታሪክና ተጠቃሚነት፡፡ ለ9ኛው የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን በዓል ለውይይት የቀረበ ሰነድ፣ ህዳር 2007 ዓ.ም)

## 3.3. የማንዱራ ወረዳ መልክዓ ምድራዊ ዳራ

የማንዱራ ወረዳ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በመተከል ዞን ካሉ ሰባት ወረዳዎች ውስጥ አንዷ ናት፡፡ የማንዱራ ወረዳ በ17 የገጠር እና በሁለት የከተማ ቀበሌዎች የተዋቀረች ስትሆን፤ የወረዳዋ ዋና ከተማ የግልገል በለስን ወንዝ ተንተርሳ በ1991 ዓ.ም የተመሰረተችው ግልገል በለስ ከተማ ናት፡፡ ከተማዋ የመተከል ዞንም ዋና ከተማ ናት፡፡ ወረዳዋ ከአዲስ አበባ በደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ 550 ኪ.ሜ. ላይ ስትገኝ፤ ከክልሉ ዋና ከተማ አሶሳ 340 ኪ.ሜ. ትርቃለች፡፡ ወረዳዋ ሙሉ በሙሉ (100%) ቆላማ ስትሆን፤ የሙቀት መጠኗም ከ25°c-39°c ይደርሳል፡፡ የወረዳዋ የሕዝብ ቁጥር 36,568 እንደሚደርስ ይገመታል፡፡ የወረዳዋ ነዋሪ 80% የጉሙዝ ብሔረሰብ ሲሆን ቀሪው 20% አማራ፣ አገው፣ ኦሮሞ እና ሽናሻ ናቸው፡፡ ከወረዳዋ ሕዝብ 75% የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ፣ 15% የሀገረሰባዊ እምነት፣ 5% የፕሮቴስታንት እና 5% የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ናቸው፡፡ የወረዳዋ ሕዝብ በዋናነት የሚተዳደረው በእርሻ፣ በእንስሳት እርባታ፣ በንብ ማነብ እና በአሳ ማጥመድ ስራ ነው፡፡ የብሔረሰቡ ቋንቋ **ጉሙዝኛ**[10]

---

[10] ጉሙዝኛ (ሲ ጉሙዛ) አንዳንድ ጎሳዎች ‹‹እንግሽ ብጋ›› በማለት የሚጠሩት ሲሆን ቋንቋውም በኮሞዋን ቋንቋ ተናጋሪዎች ምድብ ውስጥ የተመደበ ቋንቋ ነው፡፡

ሲሆን ቋንቋውም "እንግሽ ብጋ" ይባላል፡፡ "ብጋ" ማለት ጉሙዞች እራሳቸውን የሚጠሩበት ቃል ሲሆን፤ ጉሙዝ ያልሆኑትን "ሸዋ" በማለት ይጠራሉ፡፡ በማንዱራ ወረዳ የሚገኙ ጉሙዞች ከጉሙዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ አገውኛ እና አማርኛ ይናገራሉ፡፡ ምንጭ (ማንዱራ ወረዳ መ/ኮ/ባ/ቱ/ ጽ/ቤት) ፡፡

## 3.4. የጉሙዝ ብሔረሰብ ታሪካዊ አመጣጥና አሰፋፈር

‹‹የጉሙዝ ብሔረሰብ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በመተከል ዞን፣ በካማሽ ዞን፣ በአማራ ክልል፣ በኦሮሚያ ክልል፣ በደቡብ ክልል እና በሱዳን በሚገኙ ወረዳዎች ተሰራጭተው ይኖራሉ፡፡›› (ልሳነ ቤጉ 8ኛ ዓመት ልዩ ዕትም)

### 3.4.1. የጉሙዝ ብሔረሰብ ታሪካዊ አመጣጥ

የጉሙዝ ብሔረሰብ ጥንታዊ መኖሪያቸው በጐንደርና ጐጃም ጣና ሐይቅ አካባቢ ለብዙ ዘመናት ይኖሩ እንደነበር የብሔረሰቡ አባቶች በአፈ-ታሪክ ይናገራሉ፡፡ መተዳደሪያቸውም የእርሻ ሥራ /ግብርና/፣ እንስሳት እርባታ፣ አደንና ዓሣ ማሥገር እንደሆነ ጨምረው ይገልፃሉ፡፡ የጉሙዝ ብሔረሰብ አሠፋፈር በጐሣና በንዑስ ጐሣ ሆኖ እንደ ንጉስ በሚያምኑት "ሙሳ" በሚባል የብሔረሰቡ መሪ ይተዳደራሉ፡፡ የብሔረሰቡ መጠሪያም "ጉሙዝ" ይባል የነበረ ሲሆን፤ በተለያዩ የገዥ መደቦች እንደሰው ባለመቆጠር ባሪያና ሻንቅላ፣ የሚል ስያሜ ተሰጥቷቸው ይኖሩ ነበር፡፡ አሁን ግን ትክክለኛ ማንነታችንን የሚገልጽ ስያሜ ይዘን ጉሙዝ ተብለን እየተጠራን ነው ይላሉ፡፡

የጉሙዝ ብሔረሰብ በተለያዩ ዘመናት በደረሰባቸው ጭቆናና ጥቃት በጐሣዎች መካከል በሚፈጠር ግጭት ምክንያት ከቦታ ቦታ ሲንቀሣቀስ ቆይቷል፡፡ አሁን ግን በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በመተከል ዞንና በካማሽ ዞን ፣ በአማራ ክልል በአዊ ዞን ጓንጓ ወረዳና በደቡብ ጐንደር ዞን እስከ መተማ አካባቢ፣ በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በጉራጌ ዞን በወልቂጤ አካባቢ እንዲሁም በሱዳን ደማዚን፣ አርስርስ፣ ሸረሻ፣ ዶማ፣ ያብጭር፣ ዳሮሬ መጋንዛ፣ ሰርማ፣ ባምቡዲ፣ ለህዳ፣ ድልጐበር፤ ድርዋ በተሠኙ አካባቢዎች በብዛት ይገኛሉ፡፡

ጉሙዝ የሚለው መጠሪያ ጉንዛ ከሚለው የብሔረሰቡ ቃል የመጣ ሲሆን ትርጉሙም ጀግና፣ ጐበዝ፣ ታታሪ ሰርቶ የማይደክም ማለት ነው፡፡ የሚናገሩት ቋንቋ ጉሙዝኛ (ሲ ጉሙዛ) አንዳንድ ጎሳዎች ‹‹እንግሽ ብጋ›› በማለት የሚጠሩት ሲሆን ቋንቋውም በኮሞዋን ቋንቋ ተናጋሪዎች ምድብ ውስጥ ይመደባል፡፡ የብሔረሰቡ አመጣጥ ከከነአን /ሃሞ/ የኖህ ልጅ ሲሆን ከቀደምት ነዋሪ ጥቁር አፍሪካ የሚመደብና ለብዙ ዘመናት በኢትዮጵያ የኖረ ብሔረሰብ

እንደሆነ የታሪክ ድርሳናት ያስረዳሉ፡፡ ይህ ብሔረሰብ በ "ኩሳ" የአስተዳደር ዘመን ሶስት ጐሣዎች ማለትም ጉሙዝ፣ ቅማንትና ወይጦ በተለያዩ ጊዜያት ወደ ኢትዮጵያ እንደገቡ እና የዘር ምንጫቸውም ሶኒ፣ አረዋድና ሳምሪ እንደሚባል ተገልጿል፡፡

አንዳንድ ፀሐፊያን ደግሞ የጉሙዝ ብሔረሰብ የጥቁር አፍሪካ ሕዝብ ዘር የሆነ እንጅ ባንድ ወቅት ወደ ኢትዮጵያ የገባ እንዳልሆነ አስረግጠው ይመሰክራሉ፡፡ (የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ሕዝቦች ታሪክና ተጠቃሚነት፡፡ ለ9ኛው የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን በዓል ለውይይት የቀረበ ሰነድ፣ ህዳር 2007 ዓ.ም) ፡፡

### 3.4.2. የጉሙዝ ብሔረሰብ አሰፋፈር

የጉሙዝ ብሔረሰብ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በመተከል ዞን በሚገኙ ወረዳዎች ማለትም በወንበራ፣ በቡለን፣ ድባጢ፣ በዳንጉር፣ በማንዱራ እና ጉባ እንዲሁም በከማሺ ዞን በከማሺ፣ በያሶ፣ በሰዳል፣ በበሎ ጅጋንፎይ እና በአጋሎ ሚጢ በብዛት ሰፍረው የሚገኙ ሲሆን በተጨማሪም የክልሉ ርዕሰ ከተማ በሆነችው አሶሳ ከተማ ላይ በስራ ምክንያት ይገኛሉ፡፡ ከክልሉ ውጪ በአጎራባች ክልሎች በአማራ ክልል እስከ መተማ ድረስ በኦሮሚያ ክልል በወለጋና አካባቢዎች እንዲሁም በሱዳን ብሉ ናይል ግዛት ተሰራጭተው ይኖራሉ፡፡ (ልሳነ ቤጉ 8ኛ ዓመት ልዩ ዕትም)

## 3.5. የጉሙዝ ብሔረሰብ ኢኮኖሚያዊ ገፅታ

በአብዛኛው የጉሙዝ ብሔረሰብ የኢኮኖሚ ምንጫቸውና መተዳደሪያቸው እርሻ ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ ዕደ-ጥበብ የቀርቀሃ ውጤቶች፣ ሕገ ወጥ አደን፣ ማገዶ ሽያጭና ሌሎችም ይገኙበታል፡፡ በጉሙዝ ብሔረሰብ ዘንድ በዋናነት የሚታወቁ የሰብል ዓይነቶች በቆሎ፣ ዳጉሳና ማሽላ ሲሆኑ እኒህም ለቦርዴ (ባሕላዊ መጠጥ) እና ለገንፎ የሚውሉ ናቸው፡፡ ከጥራጥሬ ዓይነቶች ውስጥ ቦለቄ (አሾቴሬ) እና ኤጶ በብዛት የሚታወቁ ሲሆኑ ክማም (ሀረግ መሰል ዕፅ) በማምረት ለምግብነት ይጠቀማሉ፡፡

## 3.6. የጉሙዝ ብሔረሰብ ባሕላዊ ምግብና አመጋገብ

አብዛኛው ብሔር ብሔረሰብ የራሱ የሆነ ባሕላዊ የምግብ ዓይነቶችና አመጋገብ ሥርዓት እንዳለው ሁሉ የጉሙዝ ብሔረሰብም የራሱ የሆነ ባሕላዊ የምግብና የመጠጥ ዓይነቶች ከመኖሩም ባሻገር የአመጋገብ ሥርዓትም አለው፡፡ ከእነዚህም መካከል ከእህል ፖኝጋ ‹‹ገንፎ››፣ ከወጥ ‹‹ክማ››፣ ታዋቂ ምግቦች ናቸው፡፡

**ገንፎ** (ፖኝጋ)፡- ከዳጉሳ፣ ከሜራ፣ ከበቆሎ፣ ከማሽላና ከመሳሰሉት እህሎች በእጅ ተፈጭቶ አቡክቶ በማሳደር እና ለምግብነት ሲፈለግ በእሳት በማገንፋት የሚመገቡት የምግብ ዓይነት ነው፡፡ ለማባያነት እንደ ወጥ ክማ ይጠቀማሉ፡፡

**ክማ፡-** በብሔረሰቡ ታዋቂ የሆነ የወጥ ዓይነት ሲሆን ተክሉ ሀረግ መሰልና ሲደቆስ የመዝለግለግ ባህሪ ያለው ነው፡፡ ክማ በሽናሽኛ ሴዶ ይሉታል፤ የሚዘጋጀው ተክሉን ከሚጥሚጣ በርበሬ፣ ከአሻቦና ከሌላ ቅመማ ቅመም ጋር በመደቆስ ነው፡፡ በዚህ መልክ የተዘጋጀው የክማ ወጥ ከገንፎ ጋር ይቀርብና ይበላል፡፡

**ቦርዴ፡-** ከዳጉሳ፣ ከሜራ፣ ከበቆሎ፣ ከማሽላና ከመሳሰሉት እህሎች በእጅ ተፈጭቶ ብቅል እና እንኩሮ ተደርጎ የሚሠራ ባሕላዊ መጠጥ ነው፡፡በብሔረሰቡ ዘንድ በሁሉም ሥርዓት አፈፃፀም ላይ ከስጋ ጋር የሚቀርብ ሲሆን ክማው ለሆድ ድርቀትና ለጨጓራ ህመም ፍቱን ምግብ በመሆኑ በብሔረሰቡ የተለመደና የሚዘወተር ምግብ ነው፡፡ አመጋገባቸውም የተሰራው ወይም የተዘጋጀው ምግብ አብሮ ላለው ሰው ሁሉ የዕድሜ፣ የጾታ ልዩነት ሳይኖር እኩል ተከፍሎ ነው፡፡ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት የምግብ ዓይነቶች በጉሙዝ ብሔረሰብ የመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ አቀባበል ሥርዓት በሚፈጸምበት ወቅት ከሚቀርቡ የምግብ ዓይነቶች ውስጥ ዋቂቶቹ ናቸው፡፡ ምንጭ (6ኛው ሀገር አቀፍ የባሕል ሳምንት ላይ ከቀረበ ማብራሪያ የተወሰደ፡፡ 2009 ዓ.ም)፡፡

## 3.7. የጉሙዝ ብሔረሰብ የሕይወት ዘመን ዑደት

በጉሙዝ ብሔረሰብ መወለድን፣ ለአቅመ ሔዋን/አዳም መድረስን፣ ጋብቻን፣ ሞትን እና ተስካርን ምክንያት በማድረግ የሚፈፀሙ ሥርዓቶች መለየት (ለ ይጠብቃል)፣ ሽግግር እና አዲስ ማንነት ማግኘት በመባል የሚታወቁትን ደረጃዎች ያልፋል፡፡ ‹‹በማንኛውም የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች የሚኖሩ ሦስት ምዕራፎች አሉ እነሱም መለየት (separation)፣ መሸጋገር (transition) እና መዋሐድ (incorporation) ናቸው፡፡ እነዚህ ምዕራፎች በሁሉም ሽግግሮች እኩል ሚና የላቸውም፡፡ መሸጋገር (transition) በመጀመሪያ ልጅን ማርገዝ ላይ እና መዋሐድ (incorporation) በመጀመሪያ ጋብቻ ላይ ይጎላል፡፡›› በማለት ድርብ ወርቅ ብፁዕ 2007/21 ላይ Gennep,1960:11ን ጠቅሳ ትገልጻለች፡፡

**ሀ. የውልደት ሥርዓት (ምፐቋ) ፡-** የጉሙዝ ብሔረሰብ የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ስንመለከት የመጀመሪያው የውልደት ሥርዓት ነው፡፡ በዚህ በውልደት ሥርዓቱ ውስጥ ሦስት ዋና ዋና ክፍሎችን እናያለን፡፡ ቅድመ ውልደት፣ የውልደት ወቅት እና ድኅረ ውልደት፡፡ ቅድመ ውልደት የጉሙዝ ሕፃን በእናቱ ማኅፀን ተረግዞ ከመወለዱ በፊት እናት እና አባቱ ትዳር ከመሰረቱበት ጊዜ ጀምሮ ለደኅንነቱ ጥንቃቄ ይደረግለታል፡፡ የወሊድ ወቅት ሥርዓት በወሊዱ ጊዜ የምትጠቀምባቸውን ምላጭ፣ ክር እና በጉሙዝኛ "ምጫ" የሚባለውን የወር አበባ ንፅህና መጠበቂያ ከሾላ ዛፍ ልጥ የሚሰራ ነገር ታዘጋጃለች፡፡ በድኅረ ወሊድ ጊዜ እናቲቱ በረንዳ ላይ ተቀምጣ ጫጩት ደሮ በእናትና ልጅ ራስ ላይ አዙረው አንገቱን ይቆርጣሉ፡፡ ጫጩቱ ከተቆረጠ በኋላ ቆዳው ተገፎ በልጁ የቀኝ እጅ ይታሰራል፡፡

**ለ. የመጀመሪያ የወር አበባ (ድግትስ ጋሀጃ) እና የወንድ ልጅ ግርዛት (ሽፓ)፡-** በጉሙዝ ብሔረሰብ ሕፃናት ከተወለዱ በኋላ ወደ ማኅበረሰቡ በተለያዩ ሥርዓቶች በመቀላቀል ማኅበራዊ ሰውነትን ያገኛሉ፡፡ ይህ ሽግግር ተፈጥሯዊ ቢሆንም በማኅበረሰቡ ባሕላዊ ስርዓት እየተመራ ማኅበረሰቡ የሚያከናውነው እና የልጅነት ጊዜያቸውን ያጠናቀቁ ሕጻናትን ወደ ወጣትነት የሚቀላቅሉባቸውም የተለያዩ ሥርዓቶች ውስጥ ዋነኞቹ የመጀመሪያ የወር አበባ አቀባበል ስርዓት (ድግትስ ጋሀጃ) እና የወንድ ልጅ ግርዛት (ሽፓ) ናቸው፡፡

**ሐ. የጋብቻ እና የሰርግ ሥርዓት፡-** በጉሙዝ ብሔረሰብ የጋብቻ ሥርዓት ቤተሰብ ከመመስረት በላይ ትርጉም ያለው ጉዳይ ነው፡፡ በብሔረሰቡ ጋብቻ የሚፈፀመው በሁለት የተለያዩ ጎሳዎች መካከል ነው፡፡ በአንድ ጎሳ ውስጥ ብቻ የሚፈፀም ጋብቻ ፈፅሞ የተከለከለ ነው፡፡ ጋብቻው የሚካሄደውም በአምስት ዓይነት መንገድ ነው፡፡ እነሱም፡- የለውጥ ጋብቻ (ማንጅልማ)፣

የጠለፋ ጋብቻ (ማንጉሣ)፣ የጥሎሽ ጋብቻ (ቢጓሣ)፣ የውርስ ጋብቻ (ቻምብ ድዋ) እና የማደጎ ጋብቻ (ምዳንቋ)::

***መ. የሀዘንና የተስካር ሥርዓት፡-*** ሀዘን አንድ ሰው በአካል ከኖረበት ማኅበረሰብ በሞት ሲለይ የሚከሰት ጉዳይ ነው፡፡ የሀዘን ሥርዓት የሚፈፀመው እንደየማኅበረሰቡ እምነት፣ ባሕል፣ ዕሴት እና የሕይወት ፍልስፍና ነው፡፡ በጉሙዝ ብሔረሰብ የሚፈፀመው የሀዘን ሥርዓት እንደ ሟቹ ዕድሜ የተለያዩ ሲሆን ከዕድሜ በተጨማሪም ሟቹ የሞተበት ምክንያትም ለሀዘን ሥርዓቱ ወሳኝነት አለው፡፡ በለጋ ዕድሜ ያለ ወጣት ሲሞት ሀዘኑ መሪር ለቅሶው የደመቀ ይሆናል፡፡ በዕድሜው የገፋ፣ ያረጀ እና በምድር ላይ ወልዶ ከብዶ ብዙ ዓመት የኖረ ሰው ሲሞት ከለቅሶ ይልቅ በጭፈራ እና በዘፈን ይሸኛል፡፡

የተስካር ሥርዓቱም ሰው በአካል ከማኅበረሰቡ ተለይቶ ከሞተ በኋላ በመንፈስ ከማኅበረሰቡ ጋር መሆኑን የሚያመለክት ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ በሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ውስጥም የመጨረሻው የሽግግር ሥርዓት ነው፡፡ ተስካር በጉሙዝ ብሔረሰብ በድምቀት ከሚከበሩ ሥርዓቶች ውስጥ ቀዳሚው ሲሆን "ክይ ምሽ" ተብሎ ይጠራል፡፡ በባሕላቸው መሠረት ከአንድ ጊዜ እስከ ሦስት ጊዜ ተስካር ሊወጣለት ይችላል፡፡ የመጀመሪያው ተስካር ሰውዬው በሞተበት ቀን አቅራቢያ ሊሆን ይችላል፡፡ ሁለተኛው ቤተ-ዘመድ ወስኖ ሁሉም ተረዳድቶ በዓመቱ ወይም በሁለት ዓመቱ በሰፊው የሚፈፀም ይሆናል፡፡ ድርብ ወርቅ (2007፣ 20-23)

# ምዕራፍ አራት

## 4.የጥናቱ ዘዴ

በዚህ ምዕራፍ የጥናቱ ዘዴ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች፣ የመረጃ አቀባዩች አመራረጥ፣ የመረጃው አደረጃጀትና የትንተናው ዘዴ ተካቷል፡፡ ይህ ጥናት በጉሙዝ ብሔረሰብ የመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ አቀባበል ሥርዓት ክወናን በመተንተን ያቀርባል፡፡ ጥናቱን ለማካሄድ ገላጭ የምርምር ዓይነትን በመጠቀም መረጃዎች ተተንትነዋል፡፡ ይህ የምርምር ዓይነት መረጃዎችን ለመግለፅ ለመተንተን፣ ለመተርጎም እንዲሁም ለማነፃፀር አመቺ በመሆኑ ምርጫ ተደርጓል፡፡

### 4.1. ጥናቱ የተካሄደበት ቦታ  እና የመረጃ አቀባዮች ናሙና አመራረጥ

ይህ ጥናት የተካሄድበትና መረጃ የተሰበሰብበት ቦታ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል፤ መተከል ዞን ማንዱራ ወረዳ ሲሆን የመረጃ አቀባዮች ናሙና የተመረጠውም እድል በማይሰጥ የንሞና ዘዴ (non probability sampling) አካል በሆነው በታላሚ ናሙና (purposive sampling) አመራረጥ ነው፡፡

#### 4.1.1.የጥናት ቦታ አመራረጥ

አጥኝው የመረጃ መሰብሰቢያ ቦታዎችን በዓላማ ተኮር የንሞና ዘዴ መርጧል፡፡ በመሆኑም የጉሙዝ ማኅበረሰብ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ከሚገኙ ኻያ ወረዳዎች ውስጥ በስፋት በዐስሩ ወረዳዎች ውስጥ ይገኛል፡፡ አጥኝው የጉሙዝ ማኅበረስብ ባሕልን በትክክል ሊገልጹ ይችላሉ ወይም ቱባ ባሕሉ ሊገኝ ይችላል ብሎ ያሰበው ከዐስሩ ወረዳዎች ውስጥ በማንዱራ ወረዳ እንደሆነ በማመን ወረዳውን መርጦታል፡፡ በማንዱራ ወረዳም 19 ቀበሌዎች የሚገኙ ሲሆን የጉሙዝ ብሔረሰብ ብቻ የሚኖሩበት ቀበሌ ተመራጭ ሆኗል፡፡ ይህ ወረዳ  የተመረጠው በዓላማ ተኮር የንሞና ዘዴ ነው፡፡ ጥናቱ የመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ አቀባበል ሥርዓት በማኅበረሰብ ደረጃ መከወኑ ምን እንደሚመስል ፍንትው አድርጎ ማሳየትን ስለሚሻ አጥኝው አካባቢውን ከሌሎች  የዞን ወረዳዎች  በተሻለ ሁኔታ ስለሚያውቀው ሊመርጠው ችሏል፡፡

#### 4.1.2. የመረጃ አቀባዮች ናሙና አመራረጥ

የባሕል መረጃ አቀባዩችን ለመምረጥ፣ እድል የማይሰጥ የንሞና ዘዴ (non probability sampling) አካል የሆነው ታላሚ ናሙና (purposive sampling) ስልት ተጠቅሟል፡፡ ቁልፍ መረጃ አቀባዩችም በዚሁ በታላሚ ናሙና ዘዴ ተመርጠዋል፡፡ ስለሆነም የመረጃ አቀባዮች

ናሙና፣ በቡድኑ ውስጥ የማኅበረሰቡን ባሕልና አጠቃላይ ሁኔታዎችን ያውቃሉ ተብለው የሚጠቆሙ ሰዎችን ከወጣት እስከ ሀገር ሽማግሌ ድረስ በመምረጥ ተካሂዷል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የፆታና የእድሜ ልዩነት የሚያመጡትን የመረጃ ልዩነት ለማግኘት ሲባል ከሁለቱም ፆታዎች በተለያየ የእድሜና የዕውቀት ክልል ያሉ መረጃ አቀባዮችን በዓላማ ተኮር የአመራረጥ ዘዴ የማካተት ሥራ ተሠርቷል፡፡ ‹‹ጥናቱ ሲካሄድ ዓላማውን ለማሳካት ዓላማ ተኮር ናሙና ይመረጣል፡፡›› ያለው (1998)

## 4.2. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

አጥኝው ለዚህ ጥናት የሚበጁ መረጃዎችን በሁለት መንገድ ሰብስቧል፡፡ ቀዳሚው ወደ መስክ ከመውጣቱ በፊት በቤተ መጻሕፍት ውስጥ በመገኘት በመስኩ እንዴት የተሳካ ጥናት ማድረግ እንደሚቻል የሚያስረዱ ልዩ ልዩ ጽሑፎችን አንብቧል፡፡ ከዚያም በሚያካሂደው ምርምር ርዕሰ ጉዳይም ሆነ በጥናቱ አካባቢ ዝምድና ያላቸውን ጥናቶች፣ የዚህን ጥናት ፅንሰ ሀሳባዊ እና ንድፈ ሀሳባዊ ማህቀፍ በተገቢው መንገድ ለመስራት የሚያስችሉ መረጃዎችን ከልዩ ልዩ መጻሕፍት፣ የመረጃ መረቦች እና ከተለያዩ ጽሑፎች በማሰባሰብ አደራጅቶ ተመልክቷል፡፡ እነ Sims(2004:205) ሌላው Goldstein (1964:65) ‹‹የተለያዩ መረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች መኖራቸውን ገልጸው የተሟላ መረጃ ለመሰብሰብ ጥልቀት ያለው መረጃ አሰባሰብ ዘዴ ተመራጭ መሆኑን ይመክራሉ፡፡››

ከመስክ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ደግሞ ጥናቱ መስክ ወጥቶ መረጃ መስብሰብን ስለሚጠይቅ በምልከታ፣ በቃለ መጠይቆች እና በተተኳሪ የቡድን ውይይት በመታገዝ መረጃዎች ሰብስቧል፡፡ ይህንን አስመልክቶ ፈቃደ አዘዘ (1991፣90) “የመስክ ምርምር ዋና የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ሲሆን በሶስት ልዩ ልዩ መንገዶች ሊካሄድ ይችላል፡፡ እነሱም ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅ እና መጠይቅ ናቸው፡፡ የመስክ ምርምር በብዙ ሙያተኞች ዘንድ አስፈላጊና ዋና የመረጃ መሰብሰቢያ ዜዴ ነው፡፡.›› በማለት ይገልጻሉ፡፡ እነዚህ የመስክ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች እርሰ በርስ ተደጋጋፊና የመረጃ ክፍተት እንዳይኖር የሚረዱ ናቸው፡፡ ይህም በአንድ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ ያልተገኘን ወይም አጠራጣሪ መረጃ በሌላ መንገድ በመፈተሽ ማረጋገጥ ስለሚቻል ነው፡፡ እነዚህን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች አጥኝው ለምን እንደሚጠቀም እንደሚከተለው ለመግለፅ ሞክሯል፡፡

### 4.2.1 ምልከታ

በዚህ ጥናት ምልከታ አስፈላጊ እና አይቀሬ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት አጥኝው በቦታው በመገኘት እና የወር አበባ አቀባበል ሥርዓት ክወናን በመመልከት በገላጭ የምርምር ዘዴ ለመተንተን ስለሚረዳው በዋነኝነት ተጠቅሞበታል፡፡ ክወናዊ ሂደቱን በቅደም ተከተል በመመልከት መረጃ ለመሰብሰብ፣ አውዱን ለመረዳት ይረዳል፡፡ ይኸውም ሥርዓቱ በሚከወንበት ወቅት ክወናዊ ሁኔታውን እንዲሁም የአውዱን አጠቃላይ እንቅስቃሴ ለመመልከት ረድቷል፡፡ Goldstin(1964:77) እንደገለፁት “ the term “observation” as used in this context is not limited only to visual aspect of the situation,but also involves afull range of sesual experience including hearing,feeling,smeling and testing whenever thes may be appropriate”.

እንዲሁም Gray (2004፣138) ምልከታ አንድን ጉዳይ የመመልከት እና ማስታወሻ የመውሰድ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የአጥኝውን አምስቱንም የስሜት ሕዋሳት ቅንጅትን የሚጠይቅ ሥራ ነው ይላሉ፡፡ ከዚሁ ጋር አያይዞም ምልከታ የሰዎችን ድርጊት በተነቃቃ መንፈስ የመከታተልን፣ ትዕይንቱን በአግባቡ ቀርጾ የማስቀመጥን እና የተጠኝዎችን ባሕርይ የመተንተን (የመፈከር) እውቀት የሚጠይቅ መሆኑን አስፍሯል፡፡

በተጨማሪም Goldstein (1964፣92) ምልከታ ስናካሂድ በዋናነት ትኩረት ልንሰጥባቸው የሚገቡን ጉዳዮች የክዋኔው ባሕላዊ እና ማኅበራዊ አውድ፣ ከዋኝ፣ ተደራሲ፣ በሁለቱ መካከል ያለው መስተጋብር፣ ቅርጽ፣ መቼት እና የሚከወንበት አጋጣሚ መሆናቸውን ገልጿል፡፡ ምልከታ በሁለት ዓይነት መንገድ ሊከናወን እንደሚችል ይጠቅሳሉ Kothari (2004፣ 96) ፡፡ ይኸውም ተሳትፎአዊ እና ኢ-ተሳትፎአዊ በሆነ መልኩ ሊከወን የሚችል ሲሆን ተሳትፏዊ የሚባለው አጥኝው የተጠኝው ማኅበረሰብ አካል ሲሆን እና የሚጠናውን ባሕል እና ቋንቋ የሚያውቅ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡

ኢ-ተሳትፏዊ ምልከታ የሚባለው ደግሞ ተመራማሪው ስለሚያጠናው ማኅበረሰብ ባሕል የማያውቅ በመሆኑ ምክንያት ዳር ቆሞ የሚያየውን በሙሉ የሚመዘግብበትን ሂደት የሚመለከት ነው፡፡ አጥኝው የዚህን ጥናት ምልከታ ያካሄደው ኢ-ተሳትፏዊ በሆነ የምልከታ ዘዴ ነው፡፡ ምክንያቱም አጥኝው የጉሙዝ ብሔረሰብ አባል ባለመሆኑ እና ቋንቋውን ባለመቻሉ ነው፡፡ ይኼውም ባሕሉን በጥንቃቄ እንዲከታተል፣ ይሄ አይጠቅምም ብሎ እንዳያስብ፣ ይሄ በይፋ መውጣት የለበትም ብሎ እንዳይወግን ስለሚረዳው ኢ- ተሳትፏዊ ምልከታን መርጦ ተጠቅሟል፡፡

### 4.2.2 ቃለ- መጠይቅ

ቃለ-መጠይቅ በአጥኝው እና በመረጃ አቀባዩ መካከል በቃል የሚካሄድ መረጃ የመሰብሰቢያ ዘዴ ነው፡፡ ይህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ በምልከታ ወቅት አጥኝው ያያቸው እና ማኅበረሰቡ እንዲመልስለት የሚፈልጋቸውን ጥያቄዎች እንዲጠይቅ ስለሚያግዘው ሊጠቀመው ችሏል፡፡ በቃለ መጠይቁ የሥርዓቱ ተሳታፊዎች፣ የክወናው ተሳታፊዎች እና የወር አበባ ያየችው ልጃገረድ ተካተዋል፡፡ ይህም ውስጣዊ ስሜቶችን እና የክወና አንድምታዎችን ለመረዳት ፍላጎትን መሠረት ባደረገ መልኩ ፊት ለፊት የተከወነ ነው፡፡ ቃለ መጠይቅ ጠያቂና ተጠያቂ ፊት ለፊት ተቀምጠው የሚያደርጉት ሀሳብ ልውውጥ በመሆኑ ጠያቂው የመላሹን አጠቃላይ እንቅስቃሴ ማለትም አካላዊ ገለፃን፣ ስሜትን ድምፀትን፣ በመከታተል መረጃ የሚያገኝበት መንገድ ነው፡፡ Goldstine (1964:77-78) ቃለ-መጠይቅ "the method used by the field workers to obtain data aabout ideas or events outside the context of the interview itself through questioning persons believe or known to have that informatant" በማለት ይገልፃሉ ፡፡

የቃለ-መጠይቅ ዓይነቶች የተለያዩ እና አጠቃቀማቸውም አንድ ዓይነት አለመሆኑን Gray እና Zoltan ይጠቅሳሉ፡፡ ይህም የተገደበ ቃለ-መጠይቅ (structured interview)፣ ከፊል የተገደበ ቃለ-መጠይቅ (semi-structured interview)፣ ቀጥተኛ ያልሆነ ቃለ-መጠይቅ (non-directive interview)፣ ተተኳሪ ቃለ-መጠይቅ (focus interview) እና መደበኛ ያልሆነ ቃለ-መጠይቅ (informal conversational interview) ናቸው ፡፡ ከእነዚህ የቃለ-መጠይቅ ቴክኒኮች መካከል አጥኝው ለዚህ ጥናት ይስማማሉ ብሎ የመረጠው ከፊል የተገደበ እና ቀጥተኛ ያልሆነ የቃለ-መጠይቅ ዓይነቶችን ነው፡፡ የGrayን እና Zoltan ሀሳብ በመመርኮዝ፡-

**ከፊል የተገደበ ቃለ-መጠይቅ** (semi-structured interview)፡- ይህ ዘዴ አጥኝው የሚጠይቃቸውን ጥያቄዎች በከፊል ተዘጋጅቶባቸው የሚያቀርብበት ነው፡፡ በምልከታ የተመለከታቸውን ትዕምርቶች አንድምታ ለመረዳት ያስችለዋል፡፡ ጥያቄዎቹ በሚቀርቡበት ወቅት ከመረጃ አቀባዩ የሚመጡ አዳዲስ ሀሳቦች ካሉ ለመቀበል በከፊል ዝግጁ የሚሆንበት እና ተጨማሪ ጥያቄዎችንም ለመጠዬቅ የሚችልበት ነው፡፡ በተጨማሪም አጥኝው በቅደም ተከተል ያዘጋጃቸውን ጥያቄዎች አፋልሶ በሚመቸው መንገድ ማቅረብ ይችላል፡፡ ይህንን ሀሳብ Zoltan,(2007፣123) ሲያጠናክር አብዛኛዎቹ ቃለ መጠይቆች የሚካሄዱት በከፊል በተዋቀረ ቃለ መጠይቅ ላይ ተመርኩዘው ነው፡፡ ይህም በተዋቀረና ባልተዋቀረ ቃለ መጠይቅ የሚቀርቡ መረጃዎችን በአስታራቂ መንገድ ለመቃኘት ይረዳል፡፡

**ያልተገደበ ቃለ-መጠይቅ** ፡- ይህ የቃለ-መጠይቅ ቴክኒክ ለጠያቂውም ለመላሹም ነጻነት የሚሰጥ ዘዴ ነው፡፡ አጥኚው ጠቃሚ መረጃ ያስገኝልኛል ብሎ የሚያስባቸውን ጥያቄዎች ለተጠያቂው ይመቻል ብሎ ባሰበው መንገድ እያነሳ ተጠያቂው ደግሞ ነጻና መልስ ይሆናል ብሎ የሚገምተውን መረጃ የሚሰጥበት ነው፡፡ ማብራሪያ የሚጠይቃቸውን ሰዎች ከማግኘቱ በፊት ጥቂት ጥያቄዎችን ወይም ሀሳብ ብቻ በመያዝ ከምልልሱ በርካታ ጥያቄዎችን የሚያመነጭበት እና የሚጠይቅበት ነው፡፡ ይህ ዘዴ ለአጥኚው እና ለመረጃ ሰጪው ሰፊ ነጻነት በመስጠት ጥሩ የሆነ መግባባት የሚፈጠርበት ነው፡፡ መረጃ ሰጪው የሚፈልገውን መረጃ ሰጠም አልሰጠም ሳያቋረጥ ሀሳቡን እንዲጨርስ ማድረግ ግድ የሚሆንበት ነው፡፡ ያለው (1998፣ 185)፤ Gray (2004፣ 215-217)፡፡ በዚህ ጥናት ተጠያቂዎች ስለወር አበባ ሥርዓት ክወና ለምን እንደሚከውኑት የሚያስገኝላቸውን ፋይዳ በነጻነት እንዲመልሱ ተጠይቋል፡፡

## 4.2.3 ተተኳሪ የቡድን ወይይት

ተተኳሪ የቡድን ውይይት በተሳታፊዎቹ መካከል በሚነሱ የሀሳብ ልውውጦች መረጃ ለማግኘት የሚረዳ ዘዴ ነው፡፡ ተተኳሪ የቡድን ውይይት በቃለ መጠይቅም ሆነ በምልከታ ያልተሟሉ፣ ግልጽ ያልሆኑ፣ ማብራሪያ የሚፈልጉ፣ ወዘተ መረጃዎችን ስለወር አበባ ሥርዓቱና ስለኅብረተሰቡ ባሕል ጠንቅቀው ያውቃሉ ከሚባሉ የማኅበረሰቡ አባላት ጋር የተደረገ ውይይት ነው፡፡ ይህንንም መረጃዎችን አሟልቶ በመገኘት እርግጠኛ እና ሁሉ አቀፍ መረጃ ለማግኘት አጥኚው ተገልግሎበታል፡፡ አጥኚው እነዚህን የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን በመጠቀም መረጃዎችን ሲሰበስብ ተወያዮቹ ፈቅደውለት እንደ መቅረፀ ድምፅ፣ ቪዲዮ ካሜራና የፎቶ ግራፍ ካሜራ ተጠቅሟል፡፡ Zoltan, (2007፣130)

ተተኳሪ የቡድን ውይይቱ በምልከታ እና በቃለ መጠይቅ ምላሽ ያላገኙ ማኅበረሰባዊ ጉዳዮች ምላሽ እንዲያገኙ ለአጥኚው ያግዘዋል፡፡ ለምሳሌ የትዕምርቶች አንድምታ፣ የዘፈንና የምርቃት ትርጓሜ በውይይት ሲሆን አንዱ የሳተውን ሌላው እየሞላው ምላሽ ያገኛል፡፡ በዚህ ጥናት አጥኚው እያንዳንዱ ስድስት፣ ስድስት የቡድን አባላት ያሉት ሁለት (የእናቶች እና የአባቶች) ተተኳሪ ቡድን፤ በክዋኔ ጊዜ ስላላቸው ሚና፣ የክዋኔው አንድምታ፣ ማኅበራዊ ትስስሩ፣ ሥርዓተ ጾታዊ ዕሳቤውንና ሥነ ልቡናዊ ፋይዳውን ወዘተ በተመለከተ ውይይት አካሂዷል፡፡

## 4.3. የመረጃ አደረጃጀትና አተናተን ዘዴ

### 4.3.1. የጥናቱ መረጃ አደረጃጀት

አጥኚው ከላይ በቀረቡ የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች መረጃዎችን እያደጋገፈና እያስማማ በማደራጀት ለመጠቀም ሞክሯል፡፡ የአንደኛውን የመረጃ መሰብሰቢያ ክፍተት በሌላኛው በሚሟላት የተሟላ መረጃ ለማግኘት ጥረት አድርጓል፡፡ የሁለቱን ተተኳሪ የቡድን ውይይቶች በየቡድናቸው፣ እንዲሁም የስድስቱን ቃለ መጠይቅ ምላሾች በየስማቸው የድምፅ ቅጅውን በተለያዩ ማስቀመጫዎች ይዟል፡፡ ሁሉንም የድምፅ ቅጅ በጀሮ ማዳመጫ በመከታተል ወደ ጽሑፍ መቀየር ችሏል፡፡ በምልከታ የተገኙ መረጃዎችን የግል ማስታወሻን በማመሳከር አጠቃላይ የክዋኔውን ሂደት በገለጻ በመጻፍ መረጃውን ማደራጀት ችሏል፡፡ በክወና ወቅት የተነሱ ፎቶዎች እና ምስልና ድምፆች በተናጠል በየስማቸው ተመዝግበው ተይዘዋል፡፡ በፎቶ ላይ የሚታዮ መረጃዎች እና በምስልና ድምጽ የሚታዩና የሚሰሙ መረጃዎች በምልከታ መረጃው ላይ መያዛቸውን ለማረጋገጥ ሞክሯል፡፡

### 4.3.2. የጥናቱ መረጃ አተናተን ዘዴ

በዚህ ጥናት ጥሬ መረጃዎችን ከላይ በቀረበው መንገድ ከተመደቡ በኋላ ከቤተ-መፃህፍትና ከመረጃ መረብ ከተገኙ ንድፈ- ሀሳብና ፅንሰ-ሀሳቦች ጋር እያገናዘበ ተንትኖ ጥናቱን ውጤት ላይ ለማድረስ ጥረት ተደርጓል፡፡ መረጃዎች በሚሰበሰቡበት ወቅትም ሆነ ከተሰበሰቡ በኋላ የእያንዳንዱ ክወና ትዕምርትም ሆነ ትርጉም ከባሕል ጋር ለማገናኘት ጥረት ተደርጓል፡፡ የጥናቱ ዘዴ ዓይነታዊ የምርምር መተንተኛ ላይ በማተኮር ገላጭ የምርምር መተንተኛ ስልትን በመጠቀም መረጃዎችን በዓይነታቸው እና በቅደም ተከተል ተንትኗል፡፡ ምሁራን፣ መረጃን መተንተን ማለት ከመስክ የተሰበሰበው ጥሬ መረጃ በንድፈ ሀሳቦችና ቀድሞ በተገኙ ውጤቶች እየተገናዘበ ትርጉም እንዲያገኝ ማድረግ ወይም ጥናቱ ውጤት ላይ እንዲደርስ ማድረግ ማለት ነው ሲሉ ይገልፃሉ Maykut and Morehouse (1994, 110)፡፡

አጥኚው በምልከታ የተገኘውን መረጃ ክዋኔዎችን በጥንቃቄ በመመልከት፤ ትዕምርቶችን በማጤን፣ የሚባሉ ተረኮችን በመገኛ ቋንቋቸውና በትርጉማቸው በመፃፍ፣ በመመርመር ከንድፈ ሀሳቦችና ፅንሰ ሀሳቦች ጋር በማገናዘብ ተንትኗል፡፡ በቃለ መጠይቅ የተገኘውን መረጃም በጥንቃቄ በመጻፍ በምልከታ ለተገኙ መረጃዎች ማጠናከሪያነት በሚገባው ቦታ በማስገባት ተንትኗል፡፡ እንዲሁም በተተኳሪ ቡድን ውይይት የተገኙ መረጃዎችን እንደክወናው ቅደም ተከተል ወደ ጽሑፍ በመገልበጥ ለእያንዳንዱ ክወናና ትዕምርት ማብራሪያ በማድረግ እና ፋይዳውን በመጠቆም መረጃውን ተንትኗል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# 5. የመረጃ ትንተና

## 5.1. የክወናው መከሰቻ አጋጣሚ

በጉሙዝ ማኅበረሰብ ውስጥ የድግትስ ጋህጃን ሥርዓት ክወና ለመከወን በቤተሰቡ ውስጥ ለአቅመ ሔዋን የደረሰች እና ለመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ ያየች ሴት ልጅ መገኘት ብቻ ለሥርዓት ክወናው መከሰቻነት አጋጣሚ ይሆናል፡፡

የዓመቱ፣ የወሩ፣ የሳምንቱ እና የቀኑ ጉዳይ በእርግጠኝነት ባይታወቅም፤ በቤተሰቡ ውስጥ ሴት ልጅ እስካለች ድረስ የሆነ ዓመት፣ የሆነ ወር፣ የሆነ ሳምንትና ቀን ላይ ሴት ልጃቸው ለመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ እንደምታይ ተፈጥሯዊ ግምትና ተስፋ አላቸው፡፡ በዚህም የድግትስ ጋህጃ ሥርዓተ ክወና እንደሚፈፅሙ ሥነ ልቦናዊ ዝግጅት አድርገው ይጠብቃሉ፡፡

በቤተሰቡ የሴት ልጅ መወለድና ማደግ ለሽግግር ወቅት እንደሚያደርሳት ተስፋ በማድረግ የደስታ ቀናቸውን በጉጉት እንዲጠባበቁ ያደርጋቸዋል፡፡ በጥቅሉ በቤተሰቡ ውስጥ ያለች ሴት ልጅ ለአቅመ ሔዋን ደርሳ ለመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ ማየቷ ክወናውን ለመፈፀም የሚያበቃ የክወና መከሰቻ አጋጣሚ ይሆናል፡፡

## 5.2. ለድግትስ ጋህጃ ክወና የሚያስፈልግ ዝግጅት

በአንድ የጉሙዝ ቤተሰብ ውስጥ ያለች ሴት ልጅ ዐስር ዓመትና ከዚያ በላይ ሲሆናት ጀምሮ ቤተሰቦቿ ስለ ሥርዓተ ክወናው አፈጻፀም፣ ስለልጃቸው ለአቅመ ሔዋን መድረስ የሥነ ልቡና ዝግጅት ያደርጋሉ፡፡ የወር አበባ እንዳዩች ከተነገረበት ቀን ጀምሮ ለማጠቃለያ ክወናው የሚሆን የመከወኛ ቦታ ዝግጅት፣ የመከወኛ ቁሳቁስ ዝግጅት እና የምግብና የመጠጥ ዝግጅቶች ያደርጋሉ፡፡

### 5.2.1. የሥነ ልቡና ዝግጅት

በአንድ የጉሙዝ ቤተሰብ ውስጥ ያለች ሴት ልጅ ዕድገት እየጨመረ ሲመጣ፤ ቤተሰቦቿ ልጃቸው ለመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ ባየች ጊዜ የድግትስ ጋህጃን ሥርዓት ክወና ባሕሉንና የልጃቸውን ክብር በጠበቀ መልኩ እንዴት መፈፀም እንዳለባቸው አዕምሯዊ ዝግጅት ያደርጋሉ፡፡

የልጃቸውን ጓደኞች፤ በዝግጅቱ ላይ የሚገኙትን ሽማግሌዎች፣ የጎረቤቶችን፣ የዘመድ አዝማዱንና የሕጻናቱን ቁጥር ይገምታሉ፡፡ ለዚህም የሚበቃ ድግስ ለመደገስ የሚበቃቸውን የምግብ፣ የመጠጥና የወጥ ዝግጅታቸውን ያሰላስላሉ፡፡ ስለመከወኛ ቦታው፣ ስለመከወኛ ቁሳቁሱ፣ ስለዘፈኑ፣ ስለሽማግሌዎቹ ምርቃት፣ ወዘተ... አንዱን እያነሱ አንዱን እየጣሉ ያሰላስላሉ፡፡ የስነ ልቡና ዝግጅት ያደርጋሉ፡፡

ከዚህ ቀደም ልጃቸው ለመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ ዐይታ ሥርዓቱን የፈፀሙላት እናት ‹‹... ጓደኞቿ ባለፉበት ዕድሜ ላይ ስትደርስ ወሩን፣ ሳምንቱንና ቀኑን በእርግጠኝነት ባናውቀውም፤ ያ ዓመት ካለፈ በቀጣዩ አሂጻ እንደምትሆንና ስርዓቱን እንደምንፈፅም እናስባለን፡፡ እንኳን እኛ ጎረቤቱና ዘመድ አዝማዱ ሁሉ ይቺ ልጅ አደገችልን እኮ፤ ዐይናችን እያየ ደረሰችልን ቀኑ መቼ ይሆን በስሟ ተሰብስበን የምንዘፍነው? እያሉ ይጓጓሉ፡፡ እኛም ቤተሰቡ በተለይ አባት፣ እናት እና ታላላቆች ስለሚጠራው ሰው፣ ስለዘፈኑ፣ .... እያሰብን እናወራለን፡፡›› (ወ/ሮ ሞጋካ ንጉሴ ቃ.መ. 2፤ 2)

ልጅቱም ቢሆን ለመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ ያዩ ጓደኞቿ የደረሱበት ዕድሜ ላይ ስትደርስ፤ አንድ ቀን እሷም እንደምታይ ተስፋ በማድረግ ማንን ቅርብ ጓደኛ (ምኸማ) ማድረግ እንዳለባት፣ እነማን ለጭፈራው እንደሚጠሩ፣ ስለሚዘፈንላት ዘፈን፣ ስለሚፈፀምላት ሥርዓተ ክወና፣ ስለሚደርሳት ምርቃት ወዘተ. እያሰላሰለች ኩራት ይሰማታል፡፡

ከዚህ በፊት የወር አበባ ዐይታ ሥርዓቱ የተፈፀመላትን ወጣት፡- ‹‹ የወር አበባ ይታዬኛል ብዬ ማሰብ የጀመርሁት ሁለት ዓመት አልፏል፡፡ የኔ ታላቅ የአክስቴ ልጅ ባየችበት ዕድሜ በ11 ዓመቴ ጠብቄ ነበር፤ ግን አልፎ 13 ዓመት ሊሞላኝ ሲል መጣ፡፡ ገና ሳይመጣኝ እንደሚመጣኝ እያሰብሁ በሚደረግልኝ ስርዓት አስቀድሞ ደስ ይለኝ ነበር፡፡ ስለጓደኞቹ ዘፈን፣ ስለጠባቂ ጓደኛዬ አስብ ነበር፡፡›› (ወ/ሪት ማሙሽ አቫቢ ቃ.መ. 1፡2)

ከላይ ለመረዳት እንደተሞከረው፤ የአካባቢው ማኅበረሰብ፣ ዘመድ አዝማዱ፣ ጎረቤቶቹ ሁሉ በየአጋጣሚው የልጅቱን ዕድገት እያዩ ‹‹ይቺ ልጅ እኮ አደገች፤ የወር አበባ ማያ ጊዜዋ ደረሰ፤›› እያሉ ያወራሉ፡፡ ልጃችን ደረሰች ልታኮራንና ደስ ልታሰኘን ነው ይላሉ፡፡ ይህ ሁሉ በቤተሰቦቿ፣ በአካባቢው ማኅበረሰብና በልጅቱ ዘንድ የሚደረግ የሥነ ልቡና ዝግጅት አካል ነው፡፡

### 5.2.2. የሥርዓቱ መከወኛ ቦታ ዝግጅት

በጉሙዝ ማኅበረሰብ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ ላየች ልጃገረድ (አሂጻ) የአቀባበል ሥርዓት (ድግትስ ጋህጃ) የሚከወንበት የራሱ የሆነ ቦታ አለው፡፡ ለሰባት ቀናት የምትቀመጥበት መጻ ኮዋ (ትንሿ ጎጆ ቤት) አርጅታ ከሆነ ትታደሳለች፤ ወይም ፈርሳ ከሆነ በአዲስ መልክ ትሠራለች፡፡

በተለይ ወላጆች ልጃቸው የወር አበባ እንዳየች ከተሰማበት ጊዜ ጀምሮ፤ ልጆች የሚዘፍኑበት፣ አመድ የሚራጩበት ቦታ በመጻ ኮዋ (ትንሿ ጎጆ ቤት) እና በመጻ ሚያ (ትልቁ ቤት) መካከል ያለው ሜዳው ሁሉ ይፀዳል፡፡ ወንዝ የሚሄዱበት መንገድ ድንገት ክረምት ሆኖ ዳዋ ከዋጠው መንገዱ ተጠርጎ ይከፈትላቸዋል፡፡ ለመጨረሻው ቀን ዝግጅትም መጻ ሚያ (ትልቁ ቤት) ጎረቤቶችን፣ ሽማግሎችንና ዘመድ አዝማዱን ለመቀበል ይሰናዳል፡፡

ከዚህ በፊት ልጃቸው ለመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ ዐይታ ሥርዓቱን የፈፀሙላት እናት ‹‹… ቤተሰቡ በተለይ አባት፣ እናት እና ታላላቆች፤ ስለአጠቃላይ ዝግጅቱ፣ ስለትንሿ ጎጆ ቤት፣ ስርዓቱ ስለሚፈፀምበት ቦታ፣ የሚቀረን የለም እያሰብን እናወራለን፡፡›› (ወ/ሮ ሞጋካ ንጉሴ ቃ.መ. 2፤2) እንዳሉት የመከወኛ ቦታ ዝግጅት ያደርጋሉ፡፡



**ፎቶ1፡-** የሥርዓቱ መከወኛ ትልቁ ቤትና ትንሿ ጎጆ ቤት ከኋላ

### 5.2.3. ሀገረሰባዊ የመከወኛ ቁሶች ዝግጅት

አንዲት ለአቅመ ሔዋን የደረሰች የጉሙዝ ብሔረሰብ ሴት ልጅ የወር አበባ የምታየው ለመጀመሪያ ጊዜ እና አመጣጡም ድንገቴ ስለሚሆን ለመቀበያነት የሚያገለግል ከሾላ ዛፍ የሚሰራ ምጫ የሚባል ባሕላዊ የሴቶች ንፅህና መጠበቂያ ያዘጋጃሉ፡፡ የወር አበባ ያየችው ልጅ የምትቀመጥበት ተጉ ጋሀጃ (ወንበር) ታጥቦና ንፁህ ሆኖ ይዘጋጅላታል፡፡ መሸፋፈኛ ጨርቅ፣ ለእጆቿ መታሻ የቆሻ (ቃጭማ) ፍሬ፣ ጓደኞቿ ሲዘፍኑ በቀኝ እጃቸው የሚይዟት ኮታ (ትንሽ እርጥብ እንጨት)፣ መሬት እየደበደቡ ዘፈን የሚያደምቁበት ረዥም ዱላ በቁጥራቸው ልክ ይዘጋጅላቸዋል፡፡

ፀጉራቸውን የሚስተካከሉበት ምላጭ፣ ለመመገቢያ የሚሆኑ ጥራሮች፣ ለመጠጫ የሚሆኑ ዋንጫዎችና ቅሎች፣ ለገንፎ ማገንፊያ ቶፋ፣ ለቦርዲ መጥመቂያ እንስራ፣ ለቡና ማፍያ ጀበና፣ ለወጥ መስሪያ ድስት፣ ለስጋ መጥበሻ ብረት ምጣድ፣ ለእህል መፍጫ ወፍጮ፣ ለሰሊጥና ለቡና መውቀጫ ሙቀጫ፣ ቻጋ (ቢላዋ)፣ የቡና መጠጫ ስኒ፣ የውኃ መቅጃ እንስራ እና የመሳሰሉት ሀገረሰባዊ የእጅ ሥራ የሆኑ የመከወኛ ቁሳቁሶች ሁሉ ይዘጋጃሉ፡፡ ሁሉም ሥርዓቱ በተሳለጠ መንገድ እንዲፈፀም የራሳቸው አገልግሎታዊ ፋይዳ አላቸው፡፡



**ፎቶ2፡-** ከቅል የተሠራ የሥርዓቱ መከወኛ ማቡኪያ፣



**ፎቶ3፡-** ለሥርዓቱ መከወኛነት የሚያገለግሉ የሸክላ እቃዎች፤

ሴቶችና ወንዶች የሚራጩበት ንፁህ ዑፋ (አመድ)፣ የወር አበባ ያየችው ልጅ ስራ የምትጀምርበት እህል የምትፈጭበት ማህሻ (ወፍጮ)፣ እህል የምትወቅጥበት ሙቀጫ፣ ዱቄት የምታቦካበት ማቡኪያ፣ ወኃ የምትቀዳበት ትንሽ እንስራ እና ቡና የምታፈላበት ጀበና የመከወኛ ቁሳቁሶች ሁሉ ይዘጋጃሉ፡፡ የሚዘጋጁትም ይሁነኝ ተብሎ ለስርዓቱ መፈፀሚያነት እንዲያገለግሉ ታስቦ ቤት ውስጥ የለለው ቶሎ እንዲሟላ ይደረጋል፡፡ (ወ/ሮ ሞጋካ ንጉሴ ቃ.መ. 2፤2)



**ፎቶ4፡-** ከሸክላ የተሠራ የሥርዓቱ መከወኛ የቦርዲ መጥመቂያ፤

በሥርዓቱ ፍጻሜ በሚካሄደው ክዋኔ አሂጻዋ ‹‹ሁሉም ነገር ስላለቀ ደስ ይለኛል፡፡ እናቴ ከቤታችን አምላክ ሙሳ ጋር እያስተዋወቀችኝ ነዉ፡፡ የቤተሰቡ አባል ነኝ፤ በቀጣይ ደግሞ እኔ እናት እሆናለሁ፤ የቤቱን ኃላፊነት በራሴ እወጣለሁ፤ በዚህም በጣም ደስ ይለኛል፡፡›› (ወ/ሪት ማሙሻ አቫቢ፤ ቃ.መ. 1፤6) ይህ የሚያሳየው ሀገረሰባዊ ቁሳቁሱ በሥርዓቱ ክወና ላይ የራሳቸው ፋይዳ እንዳላቸውና ከዋኝዋ ደስታ እንደምታገኝበት ነው፡፡

### 5.2.4. ሀገረሰባዊ የምግብና የመጠጥ ዝግጅት

ይህ ዝግጅት በተለዬ የሚከወነው ሴት ልጃቸው የወር አበባ ማዬቷ ከተበሰረበት ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡ አስቀድመው በሥነ ልቡና ዝግጅት ወቅት ባሰላሰሉት መሠረት የእንግዶችን፣ የሽማግሌዎችን፣ የጎረቤቶችን፣ የዘመድ አዝማዱን፣ የጓደኞቿን፣ የሕጻናትን ቁጥር ታሳቢ በማድረግ፤ ለፖኝጋ (ገንፎ)፣ ለኪያ (ቦርዴ)፣ ለቡና፣ ለጸልኛ (አረቄ) የሚሆን የበቆሎ፣ የቦቤ፣ የዳጉሳ እህል እና ቡና ተፈጭቶ፣ ተጠምቆ ይዘጋጃል፡፡ ለወጥ የሚሆን ፍየልና ለሥርዓቱ መከወኛ ተራምዳ የምትገባው ሁለት ጋፋ ግፅጎ (ሴት ደሮዎች) ይዘጋጃሉ፡፡ በዕለቱም ለሥርዓቱ መከወኛነት፤ ለምግብነትና ለመጠጥነት እንደሚያሰናዱ ከላይ በተሰጠው የቃለ መጠይቅ ምላሽ መረዳት ተችሏል፡፡

ምግብና መጠጡ የሚዘጋጀው በአቅም ልክ እንጅ ከማን አንሼ በሚል እልህ ዕዳ ውስጥ እየተገባ አይደለም፡፡ ትንሽም ቢሆን ለሥርዓቱ መፈፀሚያ፣ ለሽማግሌዎች፣ ለዘመድ አዝማዱና ለወጣት ጓደኞቿ መሰባሰቢያ በሚሆን መጠን ይዘጋጃል፡፡ ድግስ የምትደግሱ ብዙ ነው ትንሽ? ‹‹ቤት ባለው ነው እንጅ ከለለ የት መጦ ይደገሳል፡፡ እኛኮ እንደከተማ ሰው ብድር አናውቅም፡፡ ለድግትስ ጋሀጃ የሚሆን የቦርዴና የገንፎ፤ የደሮና የፍየል መቼም አይጠፋም፡፡›› (አቶ ጊሳ ዝማቻ ቃ.መ. 2፤5)



ፎቶ5፡- ለምግብነት የሚያገለግሉ ዕፅዋቶች

## 5.2.5. ሀገረሰባዊ የአልባሳትና የጌጣጌጥ ዝግጅት

በጉሙዝ ብሔረሰብ በተለያዩ በዓላትና ከበራዎች እንዲሁም በተለያዩ የሽግግር ወቅቶች ወንዶችም ሆኑ ሴቶች የተለያዩ ዓይነት አለባበስ ይለብሳሉ፤ በልዩ ልዩ ጌጣጌጦችም ያጌጣሉ፡፡ ለወር አበባው መቀበያ ከሾላ ዛፍ ልጥ የሚሰራ ምጫ ትጠቀማለች፡፡ ምጫው በእናቷ እንደሚሰራም ይገልጻሉ ‹‹አዲስ ተሠርቶ የተቀመጠ ከቤት ውስጥ ስለሚኖር ይሰጣታል፡፡ ድንገት እንኳ ባይኖር እናቷ ወይም ሌላ ሴት ጓደኞቿ ሰርተው ያመጡላታል፡፡›› (ተ.ቡ.ው. 1፤5)

በምልከታዬ እንዳረጋገጥሁት አብዛኛው ወጣት ወንዶችና ጎልማሶችም ‹‹አምፕላ›› የሚባል ከነጭ ሸማ የሚሠራ ቁምጣና የላይ አላባሽ ይለብሳሉ፡፡ ሚንዘ ጺያ የሚባል አንገት ላይ የሚታሰር ጨሌ፣ ባክላ ጃባ የሚሉት ሸበጥ ዓይነት ባሕላዊ ጫማ፣ ልቢንዳ ከዘራነ - ጠበንጃና ዝናር፣ ደጓ ወይም ቀስት፣ ቻጋ በቆዳ ተሰርቶ ክንድ ላይ የሚንጠለጠል ቢላዋ፣ ጣቂያ ወይም ባርኔጣ ይለብሳሉ፡፡ ሽማግሌዎች ጋቢና ጣቂያ ይለብሳሉ፤ ምጓ ወይም ጫፉ ላይ ጦር ያለው ዘንግ ወይም ጠመንጃ ይይዛሉ፡፡



**ፎቶ6፡-** ለሥርዓቱ መከወኛነት የሚያገለግሉ ወጣቶች ሴቶች የሚታጠቁት ልባ ፤

ወጣት ሴቶች ለከበራው ማድመቂያ ከነጭ ሸማ የሚሰራ ወገብ ላይ የሚጠመጠም ግላባ (ጉርድ) እና ከላይ በተለያዩ ክር ያጌጠ ቲሸርት ይለብሳሉ፡፡ ቺቻ የሚባል ከዛፍ ስር የሚወጣ ልጥ ቀጥቅጠው በማለሰለስ ወገባቸው ላይ እንዲሁም አኚ የሚባል ለአገልድም የሚሆን ልብስ እንደ መቀነት በወገባቸው ላይ ይታጠቃሉ፡፡ ሴቶቹ ሚንዛ የሚባል ጨሌ በአንገታቸው ላይ ያደርጋሉ፡፡ ጋፌቃ በሚባል (የተለየ ከቀይ ድንጋይ ተፈጭቶ በዘይት የሚቦካ አፈር) ይዋባሉ፡፡

በእጃቸው የሚያስሩት ከዱር እንስሳት ቆዳ የሚሰራ የእጅ ጌጥ (ኬቢ.ያ)፣ ፀጉራቸውን ይከረከማሉ፣ እሽክርክሪቷ ላይ አሂጻዋ ትላጫለች፡፡



**ፎቶ7፡-** ወጣት ሴቶች የሚያጌጡበት የጆሮ ጌጥ፤

ለሴት ተተኳሪ የቡድን ተወያዮች የወር አበባ ያየችው ልጅ ፀጉሯን ትስተካከለች፤ መሐል ላይም ትላጫለች ፣ ጋፈቃ ትቀባለች ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ፡- ‹‹አዎ ትላጫለች፤ በኛ በጉሙዞች ብዙ ዓይነት የፀጉር አለጫጨት አለ፡፡ የወር አበባ ያየችው ልጃገረድ የምትላጨው የብስራት ማሳያ ምልክት ነው፡፡ ዙሪያውን ክብ ቅርጽ እና መሐል እሽክርክሪቷ ላይ ትላጫለች፡፡ ይህም ጋህጃ ዐይቻለሁ፤ ለአቅመ ሔዋን ደርሻለሁ፤ ማግባትም፣ መውለድም፣ እችላለሁ ማለት ነው፡፡ ጋፈቃ የምትቀባው ደግሞ የአዲስነት ምሳሌ ነው፡፡ ›› (ተ.ቡ.ው. 1፤13)



**ፎቶ8፡-** ባሕላዊ የራስ፣ ያንገት፣ የእጅ ጌጣጌጦችና አልባሳት



ፎቶ9፡- የወጣት ሴቶች አለባበስ

ክንዳቸው ላይ የሚታሰር ትንሽ ጨቤ (ቻጋ) ይዘጋጃል፡፡ ትባን ዬያ የሚባል የጆሮ ጌጥ፣ ትባን ኢታ የሚባል የአፍንጫ ማስጌጫ አፍንጫ ተበስቶ የሚንጠለጠል ያደርጋሉ፡፡ ጋህጃ (የወር አበባ) ያዩች ወጣትም መጀመሪያ ቃጭማ (ቆሻ) በሚባል ፍሬ አስሩን ጣቶቿን ትታሻለች፡፡ ‹‹የቃጭማ ፍሬ ፀጉርን ለማሳመር፣ ለውበት፣ ቆንጆ እንድትሆን ይደርጋል፡፡ በጋህጃ (የወር አበባ) ጊዜ እጇ የሚታሸውም በቀለሙ ጣቷን ለማሳመር ነው፡፡›› (ተ.ቡ.ው.2፤ 3)

ፔህቅ የሚባል ዛጎል በክር ተደርድሮ በግምባራቸው ላይ፣ ፔህቅ ልቋ የሚባል በለሰላሰ ቆዳ የተደረደረ ዛጎል በራሳቸው ላይ፣ ሚንዞ ጺያ የሚባል የተለያዩ የጨሌ ዓይነቶችን በክር ላይ ደርድረው በአንገታቸው ላይ፣ ከቤያ የሚባል የተተለተለ ቆዳ እንዲለሰለስ ተደርጎ በክንዳቸው ላይ፣ ሆሴኛ የሚባል በለስላሳ ቆዳ ላይ ተደረደሮ የሚሰፋ ዛጎል በወገባቸው ላይ፣ ልባ የሚባል በክር ላይ የተደረደረ ጨሌ ወገባቸው ላይ፣ ሚንዞቾን የሚባል በክር ላይ የተደረደረ ጨሌ በእግራቸው ላይ ፣ ሰሆኤያ የሚባል ከመዳብ ተቅጥቅጦ የተሰራ አምባር እጅ ላይ አስረው ወደ ማጠቃለያ ዝግጅቱ ይመጣሉ፡፡(ተ.ቡ.ው.2፤ 4)



ፎቶ10፡- የጉሙዝ እናቶች ባሕላዊ አለባበስ፤

## 5.3. የድግትስ ጋሀጇ ክዋኔ ትንተና

በጉሙዝ ብሔረሰብ አንዲት ልጃገረድ (ዳጉና) ለመጀመሪያ ጊዜ ጋሀጇ (የወር አበባ) ስታይ አሂጻ የሚል ስያሜ የሚሰጣት ሲሆን፣ ጋሀጇ ካየችበት ቀን ጀምሮ ከትልቁ መኖሪያ ቤት በመዉጣት ከትንሿ ጎጆ ቤት ከምዃማ ወይም ከአንዲት ጓደኛዋ ጋር ትገባለች፡፡ በድግትስ ጋሀጇ ክወና የወር አበባ የክዋኔው ሰበብ ነው፡፡ በጉሙዝ ብሔረሰብ ውስጥ የወር አበባ የራሱ ትርጉም እና አንድምታ አለው፡፡ የወር አበባ ፈጣሪያቸውም፣ እነሱም የሚጸየፉት ቆሻሻ ነው፡፡ አንድም ትልቁ መኖሪያ ቤት የሙሳ[11] (ፈጣሪ) ቤት ስለሆነ ቆሻሻውም፣ ቆሻሻው የነካውም አይገባም፡፡ አንድም ጋሀጇ የጤነኛ እና መውለድ የምትችል ሴት ምልክት ነውና ደስ ይላቸዋል፡፡

ይህንንም ‹‹ጋሀጇ በኛ መጥፎ አይደለም፤ እርግማንም እርኩሰትም አለው ብለን አናምንም፡፡ ነገር ግን ከሽንት፣ ከንፍጥ ከሰገራ በላይ የምንፀየፈው መጥፎ ቆሻሻ ነው፡፡ ቆሻሻ ያየች ሴት የነካቸው እቃ ሁሉ ቆሻሻ  ይሆናል፤ በዚህም አምላክ ይቆጣል ብለን እናምናለን፡፡ አምላክ (ሙሳ) ንፁህ ነው፤ ቆሻሻም አይወድም፤ እኛም ቆሻሻ አንወደም፡፡ በተለይ ጋሀጇ ሲሆን ደግሞ ሴት ንፁህ እስክትሆን ስራ እንዳተሰራ ይደረጋል፡፡ ደሞ ብዙ ጊዜ ጋሀጇ ሲመጣ ያማልና ቁጭ ማለት አለባቸው ብለን እናምናለን፡፡ ጋሀጇ ከሰውነት ሲወጣም መጥፎ ሽታ አለው፤ ሲታይም ደስ አይልም፤ ስለዚህ ለሌሎች አእምሮ ጤንነት፤ ለኛም ደህንነት በዕረፍት ተቀብለን እናፀዳዋለን፡፡ ጋሀጇ ለኛ ኩራት ነው፤ መውለድ እንደምንችል የሚያሳውቀን የደስታ ምልክት ነውና ደስ ይለናል፡፡ እናፍርበትም ደሞ እንኮራበታለን፡፡ ፈጣሪ ለኛ ለሴቶች የሰጠን የፀጋ ምልክት ነው ፡፡›› (ተ.ቡ.ው. 1፤6) በማለት ይገልጻሉ፡፡

መጳ ሚያ (ትልቁ መኖሪያ ቤት)፡- በጉሙዝ ብሔረሰብ እምነት የአምላክ ሙሳ ቤት ተደርጎ ይታመናል፡፡ ከቤቱ ምሰሶ ጋር ቤቱን እየጠበቀ ይኖራል፤ ስለዚህም ወደ ትልቁ መኖሪያ ቤት አምላክ ሙሳ የማይወደው ነገር ሁሉ አይገባም፡፡ በተለይ ቆሻሻና ነውር የሆነ ነገር ፈፅሞ አይታሰብም፡፡ ሴት ልጅ ስትወልድ ብዙ ቆሻሻ ስለሚፈሳት አትገባም፡፡ የወር አበባ ያየች

---

[11] ሙሳ የሚለው ስያሜ በጉሙዝ ማኅበረሰብ ዘንድ ፈጣሪ፣ አምላክ፣ ቆሻሻ የሚፀየፍ ንፁህ አምላክ፣ በትልቁ ቤት ምሰሶ ላይ የሚኖር፣ እነሱ የሚበሉትንና የሚጠጡትን ሁሉ የሚቋደስ ተደርጎ የሚመለክ ነው፡፡ በመጻሕፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ብሏል፡- ‹‹ከግብፅ ምድር ከባርነት ያወጣሁህ እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ፡፡›› (ኦ.ዘጻ 5፤1-6) ፡፡ በቅዱስ ቁርኃን አላህ (ሱ.ወ.) ሙሳን እንዲህ ብሏል፦ ‹‹.... ባንተ ላይም ያልተረክናቸውን መልዕክተኞች እንደላክን ላክንህ። አላህም ስለሃይማኖቱ ሙሳን ማነጋገርን አነጋገረው።›› [አል ኒሳእ፡163-165]፡፡ ምናልባት ጉሙዞች ፈጣሪያችን ሙሳ የሚሉት የቅዱስ ቁርኃኑን የአላህ መልዕክተኛ ሙሳ ወይም/እና የመፅሐፍ ቅዱሱን ሊቀ ነብያት ሙሴን ይሆን እንዴ? ምናልባትስ ሕገ ልቡና የኅበኛቸው፣ ኦሪትም የተሰበከችላቸው ማኅበረሰቦች ይሆኑ እንዴ? በማን? መቼ? ልቡ የተነሳሳ ይሂድበት፡፡

ሴትም አትገባም፡፡ ትልቁ ቤት ውስጥ መናፈጥ፣ መትፋት፣ መሽናትና ማራትም አይቻልም፡፡ እጅን ለመታጠብ እንኳ ማስታጠቢያ ፋጋ ከሌለ ወጥቶ ይታጠባል እንጅ መሬቱ ላይ መታጠብ አይቻልም፡፡ ከውጭ የሚመጣ እንግዳ እንኳ ቢኖር ድንገት አልቦት ከሆነ ከውጭ ዛፍ ስር ቁጭ ብሎ ቆይቶ ታጥቦ ነው የሚገባው፡፡ ትልቁ መኖሪያ ቤት በታሰበ ቁጥር ፈጣሪ ሙሳን በማያሳዝን መልኩ መግባት፣ መውጣትና መስራት ይታሰባል፡፡ ‹‹ትልቁ ቤት ንፁህ ነው፡፡ አምላካችን ሙሳም በትልቁ ቤት ከኛ ጋር ይኖራል ብለን እናምናለም፡፡ እሱ እንደ ሰው አይደለም፤ ለሰው የማይታይ ሁሉ ይታየዋል፡፡ ስለዚህ ቆሻሻ የወር አበባ ዐይቶ እንዳይቆጣት ንፁህ እስክትሆን በጎጆ ቤት ትቆያለች፤ ይህም የኛ እምነት ሥርዓት ነው፡፡ አምላክ ንፁህ ነገር ይወዳል ቆሻሻም ይፀየፋል፡፡›› (ተ.ቡ.ው.2፤4)

መጻ ኮዋ (ትንሿ ጎጆ ቤት)፡- ይህች ጎጆ ቤት ምሰሶ የላትም፡፡ ምሰሶ አለመኖሩ ሙሳ አምላክ ወደዚች ጎጆ እንደማይገባና ቆሻሻና ነውር የሆኑ ነገሮችን ዐይቶ እንደማያዝን ይታመናል፡፡ ጫካ ወልዳ የመጣች እናት፣ የወር አበባ ያዩ ሴቶች፣ እንቅፋት የመታቸው፣ ሰውነታቸው የቆሸሸ፣ ላበት የሆኑ፣ ቶሎ ቶሎ ወደታች ወደላይ የሚል በሽታ የያዛቸው፣ ሳልና አክታ የሚያበዙ ወዘተ ሰዎች የሚበሉት የሚጠጡት እየቀረበላቸው ከዚች ጎጆ ቤት ይቆያሉ፡፡ ‹‹መጀመሪያ ጋህጃ እንዳየች ከዋናው መኖሪያ ቤት ወጥታ ለብቻ በተሰራች አነስተኛ ጎጆ ቤት ትገባለች፡፡ ይሄን ቀድሞ ቤት ውስጥ ሲወራ፣ መንደሩ ላይ ከሷ የቀደመች ልጃገረድ ስታደርገው ታውቃለች፡፡ ትንሿ ጎጆ ቤት ምሰሶ ስለሌላት ፈጣሪ ሙሳ ገብቶ ቆሻሻና ነውር የሆኑ ነገሮችን ዐይቶ አያዝንብንም፡፡ ስለዚህ ሁሉም የጉሙዝ ማኅበረሰብ ቤት ሰርቶ ጎጆ ሲወጣ ትንሿን ጎጆ ቤት መስራት ግዴታው ነው፡፡›› (ተ.ቡ.ው.1፤27)



**ፎቶ11፡-** ጓደኞቿ እንኳን ደስ አለሽ ሊሏት ከትንሿ ጎጆ ቤት ሲገቡ

ምኸርማም በቃጭማ ፍሬ ከጎጆው በር ላይ የአሄጻዋን ዐስሩን የእጅ ጣቶቿን አሻታ ታጥባቸዋለች፡፡ እጇን እፍፍ.. እፍፍ.. ብላ ስማ ወደ ጎጆው ታስገባታለች፡፡ ለእናትና ለአባቷም ልጃቸው ጋህጃ እንዳየች ታበስራለች፡፡ በጎጆዉ ዉሰጥ ስትኖር ትልልቅ ሰዎች እንዳያዩዋት መላ ሰዉነቷን በልብስ ትሸፋፈናለች፡፡ መነንድቋ አወ (ልብስ መሸፋፈን)፡- በጉሙዝ ብሔረሰብ ልብስ የሚሸፋፈኑ የተገረዙ ወንድ ልጆች፣ ባሕላዊ መድኃኒት የተደረገላቸው ሰዎች፤ በተለይ በሽታው የፈጣሪ ቁጣ ነው ተብሎ ከተወራ እና ለመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ ያዩ ሴት ልጆች ናቸው፡፡ የሚሸፋፈኑበት ምክንያት የሚያውቋቸውን ሰዎች በማዬት እንዳያፍሩ እና በንፋስና በፀሐይ የሚመጣ በሽታ እንዳያገኛቸው እንደሆነ የብሔረሰቡ አባላት ይናገራሉ፡፡ ‹‹የምሸፈነዉ የማውቃቸው ሰዎች እንዳያሳፍሩኝ፤ የፀሐይና የነፋስ በሽታም እንዳያገኘኝ ነዉ፡፡ ሥርዓቱ ሁሉ መፈጸሙ ከሰዉም ከፈጣሪም ክብርና ፍቅር እንድናገኝ ያደርገናል፡፡ ለኔም በራስ መተማመን አገኛለሁ፤ ለቤተሰቤም ኩራት ነዉ፡፡ ሥርዓቱ ካልተፈጸመ መጤ በሽታ (ወረርሽኝ) ይቀጣናል፤ እኔም ኃፍረት ይሰማኛል፣ የበታችነት ይሰማኛል፡፡›› (ወ/ሪት ማሙሽ አቫቢ፤ ቃ.መ. 1፤ 4)

አሄጻ ትልቅ ሰዎችን ማናገር አትችልም፡፡ መክሻ ከበበጻ ብጋ አፐንጽጎ (ትልቅ ሰው አለማናገር) ጓደኛዋ (ምኸርማ) አጋኸር ካልሆነቻት ከጎጆዋ አትወጣም፡፡ ይህን የማኅበረሰብ ሕግ አፈንግጣ ወጥታ ትልቅ ሰው ብታናግር ለወዲያው በፍጥነት የሚፈፀም መቅሰፍት ባይኖርም እርጉም ትሆናለች፣ ዕድሜዋ ያጥራል፣ ዘረ ጎደሎ ትሆናለች ተብሎ ይታመናል፡፡ ‹‹በኛ እምነት እና ከዚህ ቀደም ሆኖ ያየነው እንዲሁም የምናውቀው መሐን ትሆናለች፡፡ ካለ እድሜዋም ትሞታለች፡፡ ወጣቶችም ይህን ስለሚያውቁ በድፍረትም ቢሆን አያደርጉትም፡፡›› (ተ.ቡ.ው. 1፤4)

አሄጻዋ አብራት የምትኖር እና የሚያስፈልጋትን ነገር ሁሉ የምታቀርብላት እንዲሁም መልዕክት ሲኖራት ለቤተሰቦቿ የምትነግርላት ወይም መልዕክት አስተላላፊ እና አጋኸር ምኸርማ አብራት እንድትቀመጥ ይደረጋል፡፡ አሄጻ በእጇ ምግብ ስለማትበላ ምኸርማ ምግቡን እያጎረሰች ታበላታለች፡፡ ምስ ኤል ምኸርማ (በጓደኛ እጅ መብላት)፡- ምኸርማ ጋህጃ ያየችው ልጅ የመረጠቻት አጋኸር ጓደኛዋ ናት፡፡ ይችን ጓደኛዋን ለመምረጥ ሁለት መስፈርት ማሟላት አለባት፡፡ ይኼውም አንደኛ ምኸርማዋ ከዚህ በፊት ጋህጃ ዐይታ ሥርዓቱ የተፈፀመላት፤ ልምዱን የምታካፍላት፣ ፍርኃቷን የምታጠፋላት እና ሁለተኛ ለልጅቱ የቅርብ ጓደኛና ምስጢረኛ የሆነች መሆን አለባት፡፡ (ወ/ሪት ሙሉ ዋድም ቃ.መ. 1፤7) ፡፡ ጋህጃ ላየችው ልጃገረድ የሚደረገው ሁሉ ለጓደኛዋም ይደረጋል፡፡ ምክንያቱም ጓደኛዋ እንደ ሚዜ ነች፤ ከሷ በፊት ሁሉም ሥርዓት የተፈፀመላት፤ ልምድ ያላት ስለሆነች በራሷ እያሳየች ነው

እንዲደረግላት የምታደርጋት፡፡ አዲስ ነገርን ለብቻ መቀበል ፍርኃት ስላለው፤ ጓደኛዋ ፍርኃቷንና ኃፍረቷን እያስወገደች እና እያሳዬች ለሥርዓቱ ፍፃሜ ታደርሳታለች፡፡ (ተ.ቡ.ው.1፤14)፡፡ ጋህጇ ያየችው ልጅም በመጀመሪያዎቹ ሶስት ቀናት አካባቢ ምግብ የምትበላው በምኸርማ እጅ ነው፡፡ ይሄም የራሱ ትዕምርታዊ ፋይዳ እንዳለው ሴት ሽማግሌዎች ይናገራሉ፡፡ አዎ አሂጻ በጓደኛዋ እጅ ትመገባለች፡፡ የኛ እምነት ምን መሰለህ፤ ልጅቱ ጋህጇ እየፈሰሰ የፈለገ ጠንቃቃ ብትሆን፤ እጇ ጋህጇ አካባቢ መነካካት ዐይተውም፡፡ በቆሻሻ መመገብ ፈጣሪን ያስቆጣል ብለን እናምናለን እና ጓደኛዋ ታጎርሳታለች፡፡ ይህ የኛ ትልቅ እምነት ነው፡፡ (ተ.ቡ.ው.1፤22)

አሂጻ በምትኖርበት ጎጆ ውስጥ የምትቀመጥበት ወንበር (ተጉ ጋህጇ) ይሰጣታል፡፡ በዚህ ወንበር ወንዶች ወይም ሌሎች ሴት ጓደኞቿ መቀመጥ አይችሉም፡፡ ተጉ ጋህጇው (የልጅቱ መቀመጫ ወንበር) የወር አበባ ላየችው ልጅ የመጀመሪያ ስጦታ ነው፡፡ ራስሽን ችለሽ ተቀመጭ፣ የተከበርሽ ሴት ነሽ፤ የሚወዱሽና የሚፈልጉሽ ሁሉ ወዳንቺ ይመጣሉ፣ ከእንግዲህ ማንም አይዳፈርሽም፣ እንደ ትልቅ ሴት እንጅ እንደ ልጅ (ህጻን) አናይሽም፣ አንቺ መሬት ነሽ ዘራችን ሁሉ ባንቺ ላይ ፍሬውን ያፈራል እንደማለት ነው፡፡ በልጅቱ ወንበር ላይ በድፍረት ማንም አይቀመጥም፡፡ የክብሯ መገለጫ ነው፡፡ ‹‹ልጅቷ እኮ ንግስት ናት፤ ተጉ ጋህጇ የሷ ብቻ ነው፤ በኛ ልቡና የከበረና የተከበረ ስለሆነ ማንም አይቀመጥበትም፡፡ ባሌ በእኔ ተጉጋህጇ ላይ ተቀምጦ አያውቅም፤ ለምን ይመስልሃል? ባሌ ስለሚያከብረኝ ነው፤ መገለጫውም ይሄ ነው፡፡ በኔ ተጉ ጋህጇ ላይ ከተቀመጠ ንቀቱን ወይም ጥላቻውን ገለፀ ማለት ነው፡፡ ይሄን ካደረገ በኔ ብቻ ሳይሆን ፈጣሪዬም ይቀጣኗል፡፡ በልጅቱ ተጉ ጋህጇ የሚቀመጥ፤ እንኳን ወንድ፤ ሴት ጓደኛዋም ብትሆን ልጅቱ የምትረዳው እንደናቋትና ጥላቻቸውን እንደገለፁላት ነው፡፡ ይሄ ደግሞ የቁጣ ምላሽ ከፈጣሪም፣ ከተጉ ጋህጇ ባለቤትም ያስከትላል፡፡ ሌሎች ጓደኞቿም ዝም አይሉም፡፡ ህፃናት እንኳ ሳያውቁ ቢቀመጡ ችግር የለውም፤ አስተምረህ ታስነሳቸዋለህ፡፡ አውቆ በድፍረት ይሄን የሚያደርግ ካለ በተቃራኒው ንቀትና ጥላቻን በራሱ ላይ ያተርፋልና አያደርገውም፡፡ እኔም በእድሜዬ እንዲህ ዓይነት ደፋሮችን አላየሁም፡፡›› (ተ.ቡ.ው.1፤15)



**ፎቶ12፡-** ተጉ ጋህጇ (ወንበሯ)

ልጅቱ የወር አበባ የምትቀበልበት ምጫ የሚባል ከሾላ ዛፍ የሚሰራ ባሕላዊ የንጽህና መጠበቂያ ይሰጣታል፡፡ አጠቃቀሙንም ጓደኛዋ ታሳያታለች፡፡ ምኾማዋ ከሷ በፊት ጋሀጃ ያዩችና የሥርዓቱን አከዋወን በተግባር የምታውቅ ልምድም የምታካፍላት፣ ስትፈራ የምታደፋፍራት ናት፡፡ ምግብ እና ውኃ ታቀርብላታለች፤ የቆሸሸ ልብሷን ታጥብላታለች፡፡ ማታ ማታ ፀሐይ ከገባ በኋላ መጸዳጃ ቤት ትወስዳታለች፤ ጋሀጃ የነካውን ቆሻሻም (የመርገም ጨርቅ) መሬት ቆፍራ ትቀብረዋለች፡፡ ኦካ ጎኩሆ፤ ኦካ ጎፕያ (ፀሐይ ስትገባ፤ ፀሐይ ሳትወጣ)፡- በድግትስ ጋሀጃ ክወና አንዳንዱን ክወና ፀሐይ ስትገባ፤ አንዳንዱን ክወና ፀሐይ ሳትወጣ ይከውኑታል፡፡ ሰባቱንም ቀን የወር አበባ ያየችው ልጅ እና ጓደኛዋ መጸዳጃ ቤት የሚሄዱት፣ ደም የነካውን ቆሻሻ ቆፍረው የሚቀብሩት ማታ ፀሐይ ስትገባ ወይም ሌሊት ፀሐይ ሳትወጣ ነው፡፡ ጓደኞቿን የወር አበባ አይቻለሁ ኑ እንጨፍር የምትላቸው፣ ወንዶችን እንደተኙ አመድ የሚረጯቸው እና በሰባተኛው ቀን ወንዝ ሊታጠቡ የሚሄዱት ሌሊት ወፍ ሳይንጫጫ ፀሐይ ሳትወጣ ነው፡፡ ይሕም ከሰው እይታ ለመራቅ፣ ከፀሐይ ጋር በተያያዘ ከሚመጣ በሽታ ለመራቅ እንደሆነ ይነገራል፡፡ ‹‹በፀሐይ ቆሻሻ ቆፍሮ ለመቅበር ምች ያስመታል፤ ስለዚህ ማታ ቀዝቀዝ ሲል ይሻላል፡፡ ቀን ቀዝቃዛ እንኳ ቢሆን ሴቶች ልጆች ያፍራሉ፡፡ ማክበር እንጅ ማፈር፣ መሳቀቅ የለባቸውም፡፡ የጉሙዝ ሕዝብ ቀን ቀን እርሻ ወይም አደን ስለሚውል ቀን ተሰባስቦ ለመጫወት አይመቸውም፡፡ ስለዚህ ማታ ማታ ተመራጭ ነው፡፡ ወደ ወንዝ ሌሊት የሚሄዱት ግን ለመንጻት፣ በሽታም ካለ ለመዳን ነው፡፡›› (ተ.ቡ.ው. 2፤10)



**ፎቶ13፡-** ምጫ (ባሕላዊ የሴቶች ንፅህና መጠበቂያ)

ልጅቷም ጋህጃ መፍሰስ እንዳቆመ በአምስተኛዋ ቀን ማታ ላይ ከምዥርማ ጋር በመሆን እየዞሩ የአካባቢ ልጃገረዶችን ‹‹ወጄ ብኝን›› ኑ! እንጨፍር በማለት ይጠሯቸዋል፡፡ ልጃገረዶቹም እርሷ ከምትቀመጥበት ጎጆ በመሰባሰብ ‹‹ደግህ ንጓኝይህ አማ›› እንኳን ደስ አለሽ! ‹‹ደግህ ንጓድብፅ አማ›› እንኳን ለዚህ አበቃሽ! በማለት በድግት ስጋጅ ስርዓተ ክወና ወቅት የሚዘፈነውን ዘፈን ይዘፍናሉ፡፡ በተለይ ማታ ማታ ከጎጆዋ በረንዳ ላይ እሳት እያነደዱ በቡድን በቡድን በመሆን ይዘፍናሉ፡፡ በስድስተኛው ቀን ሌሊቱን በሙሉ እያረፉ ይዘፍናሉ፡፡

ሰባተኛው ቀን ሌሊት ሴቶች ዑፋ (አመድ) ይይዙና ወንዶች በተኙበት ‹‹ተሸንፋችኋል፤ ልጃችን አሸንፋለች›› በማለት ይበትኑባቸዋል፡፡ በድግትስ ጋህጃ ክወና አንዱ ትዕምርታዊ ፋይዳ ያለው ዑፋ ነው፡፡ ከልጅቱ (አሂጻ) ዘንድ ሲጨፍሩ ያደሩ ሴቶች ሌሊት ወደ ወንዶች መኝታ ገብተው የተኙትን ወንዶች አመድ ይበትኑባቸዋል፡፡ ይህንንም ሲያደርጉ ‹‹ልጃችን አሸነፈች! ንፁህ ሆናለች! እናንተ ተኝታችሁ ተሸነፋችሁ! እኛ ሌሊቱን በሙሉ ስንዘፍን አድረን አሸነፍን!›› ይላሉ፡፡ ሰባት ቀን ባሕልና ሥርዓት ጠብቃ ንፁህ በመሆኗ አሸነፈች፤ እኛም የሌሊቱን ብርድና ነፋስ፣ እንቅልፋችንንም ታግሰን እናንተን አሸነፍን እንደማለት ነው፡፡ ዑፋ እሳቱን ክስለቱን ሁሉ አልፎ ነጭ በመሆን ያሸነፈ ነውና እንደ አመድ አሸንፋለች፣ ንፁህ ሆናለች ማለት ነው፡፡ በጉሙዝ ባሕል ከአመድ የወጥ እና የሚበሉ ነገሮች ሁሉ ማጣፈጫ ጠሻ የሚባል ጨው ይሰራልና አንቺ ኑሮን፣ ሕይወትን የምታጣፍጭ ጨው ነሽ ሲሉ በዑፋ ይራጫሉ፡፡ ‹‹ዑፋ ነጭ ነው፤ በኛ ንፁሁ የመሆን ምሳሌ ነው፡፡ ሴቶች ወንዶችን ዑፋ የሚረጩቸው ንፁህ ሆናለች፣ አሸንፋለች ለማለት ነው፡፡ የጉሙዝ ሕዝብ ከዑፋ ጠሻ የተባለ ጨው ሰርቶ ለምግብ ማጣፈጫነት ይጠቅማል፡፡ ስለዚህ ልጅቱ ደርሳለች፣ ቤት፣ ኑሮ የምታጣፍጥ ጨው ሁናለች በማለት ሴቶች ወንዶችን በዑፋ ይረጫሉ፡፡ (ተ.ቡ.ው.1፤16) ሴቶች አሸንፈናል፤ ልጃችን ንፁህ ሆነች፤ ለማለት ነዉ ዑፋ የሚረጨን፡፡ እኛም በፍቅራችሁ እና በእናትነታችሁ ተሸንፈናልና ደስ ይለናል፡፡ ስለፍቅር እና እናትነት መሸነፍ በጣም ደስ ይለናል፡፡ (ወጣት አዲሱ ንጉሴ፤ ቃ.መ. 3፤5)

በሰባተኛው ቀን ወፍ ሳይንጫጫ ልጃገረዶች ተሰባሰበው ጋህጃ ያየችውን ልጅ አጅበው እየዘፈኑ ወደ ወንዝ ይሄዳሉ፡፡ ገላቸውን ይተጣጠባሉ፡፡ ጋንዘኛ (**ቁጥር**)[12] እንደጉሙዝ

---

[12] በጉሙዝ ብሔረሰብ ቁጥር አንድ፣ ሁለት... እየተባለ በራሳቸው ቋንቋ ይቆጠራል፡፡ የወር አበባ ከመጣ ጊዜ ጀምሮ ሰባት ቀን ሲሞላ፣ ወይም ወር ሲሞላ፣ ወይም መቶ ሃያ (120) ቀን ማለትም (አራት ወር) ሲሞላ እንዴት ታውቃላችሁ? በማለት ለቀረበላቸው ጥያቄ ወንድ ተተኳሪ የቡድን ተወያዮች ‹‹ቀን የምንቆጥር ገመድ እየቋጠርን ነው፡፡ በአንድ ቀን አንድ ቋጠሮ ነው የምናስረው፡፡ ሰባት ቋጠሮ አንድ ገበያ ይሆናል፡፡ ሰላሳ ቋጠሮ አንድ ቤጃ (ጨረቃ) ይባላል፡፡ መቶ ሃያ ቋጠሮ አራት ቤጃ (ጨረቃ) ይሆናል፡፡ የቀኑን ሰዓት የምናውቀው ግን የፀሐይን ዙረት ከጥላችን ጋር አገኛኛችተን ነው፡፡›› (ተ.ቡ.ው. 2፤8)

ማኅበረሰብ ባሕላዊ እሳቤ የወር አበባ ለመጀመሪያ ጊዜ ያየች ልጅ ሥነ ተፈጥሯዊ ነጻነት እስኪታወጅላት ድረስ ሰባት ቀን ወይም አንድ ገበያ በትንሿ ጎጆ ቤት ትቆያለች፡፡ ሥርዓቱ የሚፈፀምላት ከሆነ በአምስተኛ ቀኗ ማታ ላይ ከምኸማዋ ጋር ወጥታ ጓደኞቿን ትጠራለች፡፡ በቤተሰቧ ውስጥ ሥርዓቱን ለመከወን ችግር ካለ በተለይ እናቷ ወይም አባቷ በክፉ ደዌ ታመው ከሆነ፤ እስከ አራት (ቤጃ) ጨረቃ 120 ቀን ድረስ ትቆያለች፡፡ በጉሙዝ ብሔረሰብ አምስተኛ ቀን የተፈቀደላት ደም መፍሰስ ይቆማል ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ ሰባት ቁጥር ግን የተለዬ ትርጓሜ ይሰጡታል፡፡ ሰባት ሰው ነው ይላሉ፡፡ መነሻም መድረሻም ሰባት ነው ይላሉ፡፡

‹‹አባቶቻችን እንደሚነግሩን ከሆነ፤ ሰባት የነገር መጀመሪያና የነገር መጨረሻ ነው ይሉናል፡፡ መነሻው አንድ ካልተባለ መጨረሻው ሰባት አይባልም፡፡ ድሮ ዓለምን ለስድስት ቀን ጨለማ ውጧት ነበር፤ በሰባተኛው ቀን ብርሃን ሆነ ብለውናል፡፡ እንዲሁም ስድስት ቀን ዝናብ ሆኖ በሰባተኛው በራ ሆነ፡፡ ሰባት መልካም ነገሮች የሚታዩበት የተስፋ ቁጥር ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ሰው በሰባት ነገሮች ቅንጅት የቆመ ነው ይሉናል አባቶቻችን፡፡ ሶስቱ አእምሮ ውስጥ ያሉት ደግ፣ ደግ የሚያስበው፣ ክፉ፣ ክፉ የሚያስበው እና ሁለቱን የሚዳኘው የአእምሮ ክፍል ነው፡፡ ከውጪ ያሉት ደግሞ አራቱ ዐይን፣ ጆሮ፣ ምላስና አፍንጫ ናቸው፡፡ የሰባቱ ቅንጅት ሰውን ሰው በማሰኘት ለውሳኔ ያበቁታል ብለው ይነግሩን ነበር፡፡ በኛም ውስጥ ያለው እምነት ይሄው ነው፡፡ በሰባተኛው ቀን የተበጠበጠው ይጠራል፣ የደፈረሰው ይሰክናል፤ ማዕበልም ቢሆን ይረጋል፣ የቆሸሸው ይነጻል፣ የተቋጠረው ይፈታል ስለዚህ ሥርዓቱ በሰባት ቀን ይጠናቀቃል፡፡›› (ተ.ቡ.ው.2፤9) አራት ቤጃ (ጨረቃ) ወይም መቶ ሃያ /120/ ቀን የሚባለው፤ ቤተሰቦቿ ድኃ ሆነው ዶሮ ማረድ ካልቻሉ ወይም የተለያዩ ችግር ከአጋጠማቸውና የቧን ሥርዓት መፈፀም ካልቻሉ ወይም ከእናትና ከአባቷ አንዳቸው በህመም ላይ ሆነው ዶሮ የማይታረድላትና ሥርዓቱ የማይፈፀምላት ከሆነ፤ ከጎጆዋ ሳትወጣ እስከ አራት ቤጃ (ጨረቃ) ወይም 120 ቀን ማለትም እስከ አራት ወር ድረስ ትቀመጣለች እንጅ አትወጣም፡፡ ቤተሰቡ እስከ አራት ቤጃ (ጨረቃ) ድረስ ይህን ሥርዓት መፈፀም አለበት፤ ሥርዓታዊ ግዴታ ነው፡፡ (ተ.ቡ.ው.1፤2)

መፋጽ ኔል ጋች (ወንዝ መታጠብ)፡- በወራጅ ወንዝ መታጠብ ከቆሻሻ ያነጻል፣ ከደዌ ይፈውሳል ተብሎ ይታመናል፡፡ ወንዙ ወራጅ ስለሆነ ቆሻሻን ጠርጎ እንደሚወስድ፤ የልጅቱን፣ የጓደኞቿን፣ የመንደሩን ሁሉ ክፉ እድል ጠርጎ ይወስዳል፡፡ ወንዙ ከላይ ወደታች እንደሚወርድ ሁሉ የጉሙዝ ብሔረሰብ ባሕልና ሥርዓትም ከአባቶችና ከእናቶች ወደ እኛ ወደ ልጆች ይወርዳል ብለው ያምናሉ፡፡

‹‹ወንዝ ሄደው የሚታጠቡ ንፁህ ለመሆን ነው፡፡ ደሞ ወደ ወንዝ የሚሔዱት ሌሊት የወንዙን ውኃ ወፎች ሳይቀምሱት ነው፡፡ ስንቆሽሽ ያነጻናል፣ ስንታመም ያድነናል ብለን እናምናለን፡፡ ጋሀጃ ያየችውንም ልጅ አጥበው ያሳምሯታል፡፡ መታጠብ የመንጻትና ነፃ የመውጣት ምሳሌ ነው፡፡ (ተ.ቡ.ው.1፤11)

አንተ እንዳልኸው እቤት ቢታጠቡ ምንም ላይሆን ይችላል፤ ግን ወንዝ ወራጅ ነው፤ ሲፈሳት የነበረውን የወር አበባ ጨምሮ ከሰውነታቸው የሚወጣውን ቆሻሻ ይዞት ይሄዳል፡፡ እሷ ብቻ ሳትሆን ሰፈሩም ይነፃል፤ ውኃውም እንደልብ ስለሆነ ያልቅብናል ብለው ሳይሳቀቁ በነፃነት ይታጠባሉ፣ ይዋባሉ፡፡ ከቤት ተነስተው ወንዝ እስኪደርሱ፣ እየተጣጠቡ እና ሲመለሱ የሚጫወቱት ጨዋታ፣ የሚያወሩት ቁም ነገር፣ የእርስ በርስ መስተጋብራቸው፣ ፍቅራቸውን ከፍ ሲያደርገው አይታይህም? የሚያምር ወዝ ያለው እርጥብ ቅጠልም የሚገኘው ወንዝ ዳር እኮ ነው፡፡ (ተ.ቡ.ው.1፤12)

አሂጻና ምኸ'ማ ፀጉራቸውን ከግንባራቸው ጀምረው ዙሪያውን እና ከመሐል እሽክርክሪታቸው ላይ ይስተካከላሉ፡፡ ማንድጉ ሽቤቋ (ፀጉር መስተካከል)፡- የወር አበባ ያችው አሂጻ በሥርዓቱ ማብቂያ ላይ በሰሀዳ ባሕላዊ ምላጭ ዙሪያ ፀጉሯን ትከረከማለች፡፡ መሐል እሽክርክሪቷንም ትላጫለች፡፡ ይህም እንደማንኛውም ፀጉር መስተካከል ለጌጥ ብቻ ሳይሆን ትዕምርታዊ ፋይዳ ኖሮት ይሁነኝ ተብሎ በጥበብ የሚስተካከል የፀጉር አቆራረጥ ነው፡፡ ይሄውም ገበያ ስትወጣ የፀጉሯን አቆራረጥ ዐይተው ‹ይቺ ልጅ አሂጻ ሆናለች፤ የወር አበባ ዐይታለች፣ እናት መሆን፣ ቤት መምራት ትችላለች፤› ብለው እንዲረዱ ያደርጋቸዋል፡፡ በመጨረሻው ቀን አሂጻዋ ፀጉሯን ለምን ትስተካከላለች ቢሉ ‹‹.... ፀጉሬን የምላጨዉ አዲስ ሕይወት መጀመሬን ወይም ከልጅነት ወደ ወጣትነት መሽጋገሬን፣ ለትዳር መድረሴን፣ ለማብሰርና ለማስተዋወቅ ነዉ፡፡ (ወ/ሪት ማሙሽ አቫቢ.ቃ.መ. 1፤ 4)

አዎ ፀጉሯን ትከረከማለች፤ በኛ በጉሙዞች ብዙ ዓይነት የፀጉር አቆራረጥ፣ አለጫጨት አለ፡፡ ዘመድ ሲሞት፤ የቅርብ፣ የሩቅ፣ የልጅ፣ የእህት ሞት ጊዜ ፀጉር አለጫጨታችን የተለያዬ ነው፡፡ የወር አበባ ያየችው ልጃገረድ የምትላጨው የብስራት ማሳያ ምልክት ነው፡፡ ዙሪያውን ክብ ቅርጽ ትስተካከላለች መሐል እሽክርክሪቷ ላይ ትላጫለች፤ ይህም ጋሀጃ ዐይቻለሁ፤ ለአቅመ ሔዋን ደርሻለሁ፤ ማግባትም፣ መውለድም፣ እችላለሁ ማለት ነው፡፡ ... የአዲስነት ምሳሌ ነው፡፡ ጋሀጃ (የወር አበባ) ስታይ ሕይወቷ ይለወጣል፤ እንደ ልጅ ከማሰብ እንደ ወጣት ወደማሰብ፤ ትሸጋገራለች፡፡ አዲስ ሕይወት ጀምሬአለሁ ማለት ነው፡፡ በነገራች ላይ ፀጉሯን

ካልተላጨች የትልቅ ሰው ምግብ፣ እንኩሮ አትበላም፡፡ ያንንም ለመብላት ስትል ትላጫለች፡፡›› (ተ.ቡ.ው.1፤13)



ፎቶ14. የአሂጻ አለጫጨት እና የአንገት ጌጣጌጦች

በቀረው ፀጉራቸውና ገላቸው ላይ ጋፈቃ ወይም ወዝ ያለው ቀይ አፈር ይቀባሉ፡፡ ጋፈቃ (ቀይ የአፈር ቀለም)፡- ወንዝ አካባቢ የሚገኝ ቀይ ቀለምማ ለሰላሳ ድንጋይ ተፈጭቶ በዘይት ተለወሶ ፀጉር የሚቀባ የጉሙዝ ብሔረሰብ መዋቢያ ነው፡፡ በመጨረሻው የክወና ቀን ወንዝ ሔደው ሲታጠቡ የሚቀቡት ከመዋቢያነት ባሻገር አዲስ ሕይወትን የሚያሳይ የራሱ ትዕምርታዊ ፋይዳ ያለው ሀገረሰባዊ መዋቢያ ነው፡፡ ጋፈቃ የምትቀባው ምን ፋይዳ ቢኖረው ነው ቢሊ፡- ጋፈቃ የምትቀባው ደግሞ የአዲስነት ምሳሌ ነው፡፡ ጋሀጃ ስታይ ሕይወቷ ይለወጣል፤ እንደ ልጅ ከማሰብ እንደ ወጣት ወደማሰብ፤ ትሸጋገራለች፡፡ አዲስ ሕይወት ጀምሬአለሁ ማለት ነው፡፡… ውበቷን ከማሳመሩ በላይ የራሱ ትርጉም አለው፡፡ …..፡፡ (ተ.ቡ.ው.1፤13)



**ፎቶ15፡-** *ጋፊታ የሚባለውን ባሕላዊ መዋቢያ ሰውነቷን ስትቀባ፤*

*በምልከታ እንዳረጋገጥሁት ባሕላዊ አልባሳታቸውን ይለብሳሉ፡፡ በእጃቸው ላይ ከዱር እንስሳት ቆዳ የሚሰራ ኬቤያ የሚባል ጌጥ ያደርጋሉ፡፡ በክንዳቸው ላይ ደግሞ ጬቤ፣ በእግራቸው አዬፃ በማድረግ፤ መሬት እየደበደቡ ዘፈኑን የሚያደምቁበት ረዥም ዱላ፣ የምስራች መንገሪያ እርጥብ ቅጠል፤ መልካም ምኞት መግለጫ ትንሽ ቁራጭ እንጨት (ኮታ) እንዲሁም ሌሊት የተሸነፉት ወንዶች መንገድ ላይ እንዳይረብሿቸው ንፁህ አመድ ይዘው ከወንዙ እየጨፈሩ ወደ ቤት ይመለሳሉ፡፡ ጥዋት አመድ (ዑፋ) የተረጩ ወጣት ወንዶችም ሴቶች ከወንዝ ታጥበውና አምረው እየዘፈኑ ሲመለሱ ዘፈኑን በማደናቀፍ ሽንፈታቸውን ለመመለስ ጎጆው አካባቢ መንገድ ዘግተው ይጠብቋቸዋል፡፡ ነገር ግን ሴቶቹ በድብቅ በያዙት አመድ ስለሚረጯቸው ድጋሚ ያሸንፏቸዋል፡፡*

*ዘፈኑ ከመጀመሪያ ቀን እስከ አምስተኛ ቀን ድረስ ማምሻ፣ ማምሻ ትንሽ፣ ትንሽ ከማታ ሁለት ሰዓት እስከ አራት፣ አምስት ሰዓት ድረስ ብቻ እየተደጋገመ ይጨፈራል፡፡ በአምስተኛው ቀን አሂጻዋ ከምኽርማዋ ጋር ማታ ላይ ከጎጆ ወጥተው በየቤቱ ሔደው ስለሚጠሯቸው በቁጥርም በርከት ያሉ ሴቶች ተሰባስበው እስከ ሌሊቱ ሰባት ሰዓት ይዘፍናሉ፡፡ በስድስተኛው ቀን የመጨረሻው ዋዜማ ስለሆነ ሌሊቱን በሙሉ ሲጨፍሩ ያድራሉ፡፡ በሰባተኛውም ቀን የመጨረሻቸው ስለሆነ ከድግሱ በኋላ ሲጨፍሩ ያድራሉ፡፡*

ይሄ ሁሉ ሲሆን የወንዶች ሚና ማጨብጨብ፣ አንዳንዴ ከበሮ መምታት ሲደክማቸው ትተዋቸው ሔደው መተኛት ነው፡፡ በዚህ ሁሉ ቀን በየጊዜው የሚዘፈነው ዘፈን ዜማው፣ ግጥሙ የአጨፋፈር ስልቱ፣ የሙዚቃ መሳሪያው፣ ወዘተ… አንድ ዓይነት ሲሆን አቀንቃኞች ግን ሲደክማቸው ይተጋገዛሉ፡፡ ዜማው በሴቶች ቀጭን የጉሮሮና የቅንጭላት ድምጽ፣ በረጅም ትንፋሽ፣ በተደጋጋሚ ‹ኤ.ኤ.ኤ.ኤ.ኤ.ኤ…› በሚል አዝማች ድምፅ፣ የሚንቆረቆር ነው፡፡ ግጥሙም ተመሳሳይ ይዘት ይዞ በተደጋጋሚ የሚባል፣ በሶስትና በአራት ቃላት ስንኝ የተዋቀረ ነው፡፡ የሙዚቃ መሳሪያቸውም ከበሮ፣ እግር ላይ የሚታሰር አጼጻ እና እርስ በርስ በማጋጨት ድምጽ የሚያወጡ እንጨቶች መሆናቸውን በምልከታ አረጋግጫለሁ፡፡



**ፎቶ16፡-** እግራቸው ላይ የተጠመጠመው አጼጻ የሙዚቃ መሳሪያ፣

አጨፋፈራቸውና ውዝዋዜያቸው በምልከታ እንደታየው ከበሮ መቺዋ ከመሐል ሆና ሰትቀመጥ፤ ሌሎች ክብ ይሰሩና እግራቸውን ከመሬት ጋር በማጋጨት የአጼጻውን ድምፅ ከዜማው ምት ጋር በማዋሐድ ዳሌያቸውን ወደግራ፣ ወደቀኝ፣ ወደፊትና ወደኋላ እያወዛወዙ ወደፊት ወደከበሮ መቺዋ እየደረሱ ወደኋላ ይመለሳሉ፡፡ እንደገና ደግሞ ከቀኝ ወደግራ ክብ እየዞሩ ከዜማው ምት ጋር የእግራቸውን አረጋገጥ እያዋሐዱ የአጼጻውን ድምፅ ተከትለው አንዷ የአንዷን ወገብ ከኋላ በመያዝ ዳሌያቸውን እያወዛወዙ ወደፊት ወደኋላ ይጨፍራሉ፡፡

በተለይ በመጨረሻው ቀን ረዥም ዱላ ስለሚይዙ መሬቱን ሲደበድቡበት ከሚያወጣው ማድመቂያ ድምፅ በተጨማሪ ዳሌያቸውን ለማወዛወዝ የተለዬ ውበት ይሰጠዋል፡፡

በጭፈራው እና በክወናው ልምድ ያላቸው ከዋኞች ደስ በሚል በተለዬ ሳቢ ቁንጥ (Stylistic) ይከውኑታል፡፡ ጨዋታቸውን ለማየት የሚመጡ የሰፈሩ ሰዎችና ሕጻናትም በማጨብጨብና አልፎ አልፎም ጎበዞች በማለት ሞራል ይሰጧቸዋል፡፡ የተለዬ ደስ የሚያሰኝ የአከዋወን ስልት ለሚያሳዩ ሴቶችም ስማቸውን በመጥራት ‹‹ጀግና፣ ጎበዝ›› እያሉ ያበራታታሉ፡፡ አጨፋፈሩንና ዜማውን የሚያበላሽ ከተገኘም ‹‹ተው አታበላሺ፤ እንደዚህ አይደለም፤ እንደዚህ ነው፤›› በማለት የዜማ፣ የግጥምና የውዝዋዜ እርማት ይሰጣሉ፡፡



**ፎቶ17፡- የጉሙዝ ብሔረሰብ ሀገረሰባዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች**

የዘፈኑ ግጥምም፡-

| በጉሙዝኛ ቋንቋ | የአማርኛ ትርጉም |
| --- | --- |
| ያ ዊያ ማሃ፤ | የወር አበባ መጣች፤ |
| ያ ዊያ ጋሀጃ፤ | ልጅቱም መጣች፤ |
| ያ ዊያ ማሃ፤ | የወር አበባ መጣች፤ |
| ያ ዊያ ጋሀጃ፤ | ልጅቱም መጣች፤ |
| ዋ ሌ ኪውጋ ክጋንዛ፤ | ለሽማግሌው ማን ትሄዳለች፤ |
| ባባ ምፅር አንጎ ዋ ሌ፤ | አባቴ ለሽማግሌ አልሄድም፤ |
| ዊ ምቺ ዋ ካ ጋሽላ፤ | ውይ ውይ ለወጣት ነው እንጅ፤ |
| ባባ ምፅራ፤ | አባቴ ለሽማግሌ አልሄድም፤ |
| ጋንዛ ኢ ኢ ያ፤ | ሽማግሌ አይ አይ አልወድም፤ |
| ጋሽላ ይያ ይያ፤ | ወጣት ከሆነ አው፣ አወ እሄዳለሁ፤ |
| ጋንዛ ኢ ኢ ያ፤ | ሽማግሌ አይ አይ አልወድም፤ |
| ጋንዛ ኢ ኢ ያ፤ | ሽማግሌ አይ አይ አልወድም፤ |
| ጋሽላ አንዝሃ ሊቻአዳ፤ | ወጣቱን የኔን እኩያ አለቀውም፤ |
| ጋሽላ አንዝሃ ሊቻአዳ፤ | ወጣቱን የኔን እኩያ አለቀውም፤ |
| ኤኤ ኤ ኤች ዋጋ፤ | ኤ ኤ ኤ የኛ ልጅ ባለ ወዝ ነጭ፤ |
| ኤኤ ኤ ኤች ዋጋ ኢጻ ካይማ፤ | ኤ ኤ ኤ እንደ ፀሐይ አበራች፤ |

የወር አበባ መጣች፤ የምትለው ስንኝ ብሔረሰቡ ለወር አበባ ካለው አመለካከት እና እምነት አንጻር፤ ለአቅመ ሔዋን የመድረስ ምልክት ታዬ፣ እናትነት መጣ ማለት ሲሆን፤ ልጅቱም መጣች፤ በሚለው ቤት መድፊያ ስንኝ ለእናትነት የደረሰችውን ልጅ ይጠቁማሉ፡፡ የልጅነት ጊዜ አለፈ፣ የትልቅነት ጊዜ ደረሰ፣ ሚስት ለሚፈልግ ወጣት ልጃችን ደረሰች፣ ለሽማግሌ ግን አትሆንም ሲሉ ለሽማግሌው ማን ትሔዳለች፤ በማለት የእሷም ፈቃድ እንዳልሆነ ይገልጻሉ፡፡ በዚህ ግጥም ውስጥ በማኅበረሰቡ ዘንድ ያላቻ ጋብቻ በጣም ጽዩፍ፣ የሚነቀፍ እንደሆነ ግጥሙን በዜማ አዋሕደው ይገልፁታል፡፡

አባቴ ለሽማግሌ አልሔድም፤ በማለት በሀሳብም፣ በእድሜም፣ በአካልም ከማይመጥናቸው እና አቻ ከማይሆናቸው ሽማግሌ ጋር በምንም ዓይነት ሁኔታ መጋባት እንደማይፈልጉ አበክረው ይገልጻሉ፡፡ እንደውም ምርጫቸው እንደነሱ ወጣት እንደሆነ ሲጠቁሙ ውይ ውይ ለወጣት ነው እንጅ፤ አባቴ ለሽማግሌ አልሔድም፤ እያሉ ያዜማሉ፡፡ ልጁን ለባል ለመስጠት ሙሉ

ስልጣን ያለው አባቷ ስለሆነ የዘፈኑ መልዕክት በግጥሙ ተላልፎ የሚደርሰው ለአባት ነው፡፡ አባትም ልጁ ካለአቻዋ ተጋብታ ኑሮዋ እንዲንሳቀልባት ስለማይፈል ምኞቷንና ፍላጎቷን ይፈጽምላታል፡፡ (ተ.ቦ.ው.1፤24-25)

ሽማግሌ አይ አይ አልወድም፤ ወጣት ከሆነ አወ፣ አወ እሔዳለሁ፤ በሚለው የግጥም ስንኝ ውስጥ ጎልቶ የሚታየው መልዕክት፤ ካለኔ ፈቃድ ለሽማግሌ ብትድረኝ ትቸው እመጣለሁ፡፡ ወጣት ከሆነ ግን እሺ ብዬ፣ ምርቃትህን ተቀብዬ በደስታ እሔዳለሁ፤ እናትም እሆናለሁ፣ ዘራችንንም እተካለሁ ትለዋለች፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ወጣቱን የኔን እኩያ አለቀውም፤ አልተውም፤ በሚለው የግጥም ስንኝ በቤተሰቤ፣ በአባቴ ወጣት ባል ካልመጣልኝ፤ ወጣቱን የወደደኝን የወደድሁትን እኔ መርጬ እሔዳለሁ በማለት በግጥሙና በዜማው ውሕደት ቁርጡን ለአባቷ ትናገራለች፡፡ በጉሙዝ ብሔረሰብ አምስት ዓይነት የጋብቻ መንገዶች አሉ፡፡ እነሱም፡- የለውጥ ጋብቻ (ማንጅልማ)፣ የጠለፋ ጋብቻ (ማንጉዣ)፣ የጥሎሽ ጋብቻ (ቢዣ)፣ የውርስ ጋብቻ (ቻምብ ድዋ) እና የማደጎ ጋብቻ (ምዳንቋ) ናቸው:: ከእነዚህ ውስጥ ልጅቱ አባቷ ወጣት ባል ካላመጣላት ልትፈፅመው የምትችለው የጠለፋ ጋብቻን (ማንጉዣ) ነው፡፡ ወጣት ካልዳርሽኝ ወድጄ ተጠልፌ ቢጤዬን ወጣት አገባለሁ ማለቷ ነው፡፡ ኤ ኤ ኤ ኤ.. የሚለው በየዜማው እንደ አዝማች የሚደጋገመው ቃል የዜማ አዝማች ሲሆን ለዜማው ደስ የሚል የማይሰለች ውበት ይሰጠዋል፡፡ የኛ ልጅ ባለ ወዝ ነች፤ እንደ ፀሐይ አበራች፤ በሚለው ስንኝ የልጅቱን ውበት፣ ደምግባትና መልከ መልካምነት እየገለፁ፤ በክብሯ፣ በምግባሯ፣ በውበቷ፣ እንደፀሐይ አበራች እያሉ ያሞግሷታል፡፡ (ተ.ቦ.ው.1፤24-25)

ከወንዝ ሲመለሱ የሚይዙትን ዱላ አዳሩን በሙሉ ይጨፍሩበታል፡፡ ጎምቦ (ዱላ)፡-በጉሙዝ ብሔረሰብ ረጅሙ ዱላ ዘፈኑን ከማድመቅ ባሻገር የምርኩዝና የድጋፍ ተምሳሌት ሆኖ ትዕምርታዊ ፋይዳ ይሰጣል፡፡ ረጅም ዱላ የሚይዝ ሽማግሌ ነውና እስከ እርጅና ዘመንሽ ኑሪ በማለት መልካም ምኞታቸው ለመግለፅ ይጠቀሙታል፡፡ ‹‹በዱላው መሬት የሚደበድቡ ዘፈኑን ለማድመቅ ነው፡፡ ሌላው እስከ እርጅና ዘመንሽ ቆይ፤ ሕይወትሽ ሁሉ የደስታ ይሁን፤ ማለት ነው፡፡ ለወላጆሽ፣ ለቤተሰቦችሽ፣ ምርኩዝ ሁኚ ማለት ነው፡፡ ….፡፡›› (ተ.ቡ.ው.1፤11)



**ፎቶ18፡-** የጉሙዝ ብሔረሰብ ሀገረሰባዊ ውዝዋዜ በጎምቦ (ዱላ)፡

መንዛ ፂንጃ (እርጥብ ቅጠል)፡- ከወንዝ የሚያመጡት እርጥብ ቅጠል የመልካም ምኞት፣ የብስራት፣ ተምሳሌት ሆኖ ትዕምርታዊ ፋይዳ ይሰጣል፡፡ ‹‹እርጥቡ ቅጠል የምስራች ነው፡፡ ልጃችን ደርሰሻል፤ እናት መሆን ትችያለሽ፤ እንኳን ደስ አለሽ፤ ቀሪ ዘመንሽ ለምለም ይሁን፤ ማለት ነው፡፡ አሁን ለምልመሻል፤ በቀጣይ ታብቢያለሽ፤ ፍሬም ታፈሪያለሽ ማለት ነው፡፡ .....›› (ተ.ቡ.ው.1፤11)

ከአሄጻ መኖሪያ ቤት በስተ ምዕራብ በኩል እሳት እየነደደ ይጠብቃቸዋል፡፡ የያዙትን ኮታ የሚባል ትንሽ እንጨት በጥርሳቸው ከነከሱ በኋላ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ በመዞር በእሳት ዉሰጥ ይወረውሯታል፡፡ ኮታ (ትንሽ እንጨት) ፡- ላንቺ፣ ለኛ፣ ለመንደራችን ሁሉ ክፉ የሚመኙ ትንሽ ሰዎች በጨለማ ይውደቁ አሳትም ይብላቸው በማለት ለአሄጻ፣ ለራሳቸውና ለመንደራቸው ያላቸውን ፍቅርና ክብር ጠላትን በመርገም የሚገልፁበት ትዕምርታዊ ፋይዳ ነው፡፡ ‹‹ኮታ (ትንሿ እንጨት) ያለፈው ዘመኗ እና ለሷ ክፉ የሚያስቡ፣ የሚመኙ ሰዎች ምሳሌ ናት፡፡ ሁሉም ጓደኞቿ ኮታ ይዘው በምዕራብ አቅጣጫ በሚነድ የምድጃ እሳት አርቀው ይወረውራሉ፤ ያቃጥላሉ፡፡ ትንሽ መሆኗ የትንሽነት /የልጅነት / ዘመንሽ አለፈ፤ ከእንግዲህ እንደ ትልቅ፣ እንደ እናት ነሽ ማለት ነው፡፡ ላንቺ ክፉ የሚያስቡ ትንሾች ጠላቶችሽ እሳት ይብላቸው፤ ይቃጠሉ፣ አንቺ ትልቅ ሆነሻልና ማለት ነው፡፡... በጥርስ መንከሳቸውም ያንቺና የመንደራችን ጠላቶች የኛም ጠላቶች ናቸው በማለት ለጠላት ያላቸውን አቋም ማሳያ ነው፡፡›› (ተ.ቡ.ው.1፤11)

ምውድ አለዳጨ (ምዕራብ አቅጣጫ)፡- በክወናው ወጣት ሴቶች ከወንዝ ሲመለሱ የሚያመጧትን ኮታ (ትንሿ እንጨት) በምዕራብ አቅጣጫ በሚነድ እሳት ይወረውሯታል፡፡ በጉሙዝ ብሔረሰብ ምዕራብ የክፉ ነገር፣ የጨለማ ተምሳሌት ሆኖ ትዕምርታዊ ፋይዳ ይሰጣል፡፡ ‹‹.... ሁሉም ጓደኞቿ ትንሿን እንጨት ይዘው በምዕራብ አቅጣጫ በሚነድ የምድጃ እሳት አርቀው ይወረውሯታል፤ ያቃጥሏታል፡፡ .... በምዕራብ አቅጣጫ በጨለማ ይውደቁ፣ አንቺ ግን በብርሃን ላይ ነሽ ማለት ነው፡፡ ምዕራብ አቅጣጫ ክፉ ነገሮች የሚወድቁበት፣ ፀሐይ እንኳ የምትገባበት፣ ዓለም ጨለማ የሚሆንበት ስለሆነ የምንተረጉመው በመጥፎ ነው፡፡ ሰውን የሚጎዳ በሽታ የሚያመጣ ነፋስ የሚነሳው በምዕራብ በኩል ነውና በክፉ ለሚያስባት፣ ለሚያነሳት ሁሉ መጥፎ ምኞት እያቀረብን ነው፡፡›› (ተ.ቡ.ው.1፤11)

በዚህ ሥርዓት የማይደገመውና አንዴ ብቻ ከሚከወኑ ተግባራት መካከል ከወንዝ ሲመለሱ በልጅቱ እናት፣ ወደትልቁ ቤት ሊገቡ ሲሉ በሴት ደሮ ጀርባዋን እየተመታች በአክስቷ እና ትልቁ ቤት ውስጥ በአባቷና በወንድ ሽማግሌዎች የምትመረቀው ምርቃት ነው፡፡ ሁሉም ምርቃቶች በክወናው የመጨረሻ ቀን የሚከወኑ ናቸው፡፡ ወጣቶቹ በረዥም ዱላ መሬቱን እየመቱና እየዘፈኑ መምጣታቸውን ያሳውቃሉ፡፡ የልጅቱ እናት ከትልቁ ቤት በር ላይ ቆማ እንዲህ እያለች ትመርቃቸዋለች ፡-

| በጉሙዝኛ ቋንቋ | የአማርኛ ትርጉም |
|---|---|
| ዱዋ አለም ዳም ክማነዚማ፤ | ልጄ ለምለም ሁኚ፤ |
| ነፋጋች ሽካ አሉዋ፤ | ዘርሽ ይብዛ፤ |
| ዚዚ ማንግሀቻ አለዋ ነኮድ፤ | ፍቅርሽ ሁሉን ይግዛ፤ |
| ናኢጆቁ አላኩቁ አማ፤ | የሚጠላሽ ይፈር፤ |
| ማፐልጆ ካአማ፤ | እኛ እንኩራብሽ፤ |
| ኤባ አሉዎ ኤባኦ ጲዋ ኢንሀንጎ፤ | መንደሩ ስምሽን ጠርቶ አይጥገብ፤ |
| አቻ ምዥርማ፤ | እናንተም (ጓደኞቿን)፤ |
| ካደምጳ አለቻ ማብኝጳ፣ | ለቤተሰባችሁ ኩራት፣ |
| ካቋይብቻ ጃሃ መድቻ፤ | ለመንደራችሁ መብራት ሁኑ፤ |
| አላውድ አቻ ከምንስልቻ ነኩሆን | |
| አፋህንጃ ኔልችማ፤ | በመጥፎ የሚያያችሁ በዐይኑ በርበሬ ይግባ፤ |
| ማነዚማ ኦትጃ፤ | ለምለም ሁኑ፤ |
| ነፈጋች ሽካ አለቻ፤ | ዘራችሁም ይብዛ፤ (ተ.ቡ.ው. 1፤18) |

እናቲቱ ስትመርቅ ልጆቹ ወደመሬት አንገታቸውን ደፍተው የሁለት እጃቸውን መዳፍ እያዩ በእያንዳንዱ ምርቃት አሜን! ይላሉ፡፡ ምርቃቱ ሲያልቅም በሕብረት እንደ እልልታ ያለ ቀጭን ድምጽ አውጥተው የደሮ እርድ ሰዓት እስኪደርስ ወደጎጆቻቸው ገብተው እረፍት ያደርጋሉ፡፡ ይህ ሥርዓት ደግሞ ምቅኝ ኮታ ሲባል የመጀመሪያ የወር አበባ የሚከበርበት ቀን ማለት ነው፡፡

የምርቃቷ ይዘት ልጄ ለምለም ሁኝ፤ በማለት መልካም ምግባር እንዲኖራት፣ ሰርታ እንድታፈራ፣ ታዛ የልብ እንድታደረስ፣ የበጎ ነገር ሁሉ ምንጭ እንድትሆን ትመኛላታለች፡፡ ዘርሽ ይብዛ፤ በሚለውም አግብታ እንድትወልድ፣ ብዙ ወንዶችና ሴቶች ልጆችን እንድትወልድ ታጠይቃለች፡፡ ከሁሉ ጋር በፍቅርና በሰላም እንድትኖር፣ የተጣሉትን እንድታስታርቅ፣ የራቁትን እንድታቀርብ፣ በማሰብ ፍቅርሽ ሁሉን ይግዛ፤ ትላታለች፡፡ አንቺን በክፉ የሚከስሽ፣ በክፉ ዐይኑም የሚያይሽ፣ ከደግነትና ከመልካምነትሽ ውጭ መጥፎውን ነገር እየሰጠ የሚጠላሽ ጠላትሽ ይፈር፣ አንገቱን ይድፋ፣ ኃፍረትም ይሁንበት ስትል የሚጠላሽ ይፈር፤ በማለት ትመርቃታለች፡፡ ወላጆችሽ በስራሽ ሁሉ ደስ የምንሰኝ እንሁን፣ ከቃላችን ትዕዛዝ አትውጭ፣ ሰርተሽ አርኪን ስትል እኛ እንኩራብሽ፤ ትላታለች፡፡ መንደሩ ስምሽን ጠርቶ አይጥገብ፤ በማለት የመልካም ነገር ሁሉ ምሳሌ ሆነሽ ከአፋቸው አትጥፊ፣ የመንደሩ ሰው ጥሩ ሥራ፣ በጎ ነገር ባዬ ቁጥር ለልጆቹ ስምሽን እየጠራ ምሳሌ ያድርግሽ ትላታለች፡፡(ተ.ቡ.ው. 1፤19)

እናንተም በማለት ጓደኞቿን የቀረቤታ፣ የእናትነት ፍቅር ትሰጣቸዋለች፡፡ ቤተሰብ በልጁ የሚኮራው መልካም ሥራ ሲሠራ፣ የወላጆቹን ትዕዛዝ ሲፈፅም፣ ባሕልና ሥርዓትን ሲጠብቅ፣ በመንደሩ ያሉ ሽማግሌዎችን በጉልበት ሲያግዝ ነው፡፡ ሰው የመንደር መብራት የሚሆነውም በሰው ሁሉ ዘንድ የሚወደድ ሥራ ሲሠራ ነውና ለቤተሰባችሁ ኩራት፤ ለመንደራችሁ መብራት ሁኑ፤ ትላቸዋለች፡፡ በርበሬ በዐይኑ የገባበት ሰው እየለበለበውና እየቆጠቆጠው ምንም ነገር ማዬት አይችልምና፤ እናንተን በክፉት፣ በተንኮል፣ በጥላቻና በምቀኝነት የሚያያችሁ ክፋቱ፣ ተንኮሉ፣ ጥላቻውና ምቀኝነቱ ራሱን ይቆጥቁጠው ስትል በመጥፎ የሚያያችሁ በዐይኑ በርበሬ ይግባ፤ ብላ ትመርቃቸዋለች፡፡ እንደ ልጇ መልካም ምግባራት እንዲኖራቸው፣ ሰርተው እንዲያኮሩ፣ ታዘው የልብ እንዲያደርሱ፣ የበጎ ነገር ሁሉ ምንጭ እንዲሆኑ፤ አግብተው እንዲወልዱ፣ ብዙ ወንዶችና ሴቶች ልጆችን እንዲወልዱ ለምለም ሁኑ፤ ዘራችሁም ይብዛ፤ በማለት ትመርቃቸዋለች፡፡ (ተ.ቡ.ው. 1፤18)

ቤተሰቦቿ ሲዘጋጁበት የሰነበቱትን ድግስ በመደገስ፤ ፍየል ያርዱና የአካባቢውን ሰዎች፣ ሽማግሎዎችን ይጠራሉ፡፡ ልጃቸው ለአቅመ ሔዋን መድረሷን የሚያውጁበት ቀን ስለሆነ ቤተሰቦቿ

በጣም ይደሰታሉ፡፡ ልጅቱም እናት ለመሆን ስለታደለች፤ ለጋብቻ መድረሷን ሰላረጋገጠች ኩራት ይሰማታል፡፡ ከዚህ ቀን ጀምሮ የተሸፈነችበትን ልብስ እንድትጥል ይደረጋል፡፡

በምልከታ እንዳረጋገጥሁት ቀን ፀሐይ ካዘቀዘቀች በኋላ የሰፈሩ ልጆች፣ ወጣት ወንዶች እና ልጃገረዶች እንዲሁም የተጠሩ እናቶችና አባቶች፤ ሽማግሌዎችም ይሰባሰባሉ፡፡ ጭፈራውም በሕብረት ይደምቃል፡፡ የልጅቷ እናትም ሴት ዶሮ ይዛ ከትልቁ ቤት በር ትቆማለች፡፡ እነርሱም መሬት ላይ በመቀመጥ ይጠብቋታል፡፡ እናቲቷም የያዘችውን ዶሮ ስትወረውርላቸው በያዙት እንጨት ወይም ዱላ ዶሮዋን አሯሩጠው በመምታት ይዘው ያመጧታል፡፡ የወረወረቻትን እናት ደሮ ለመያዝ በተደረገው ሩጫ፤ አንዱ ሲወድቅ፣ አንዱ ሲነሳ፣ ደሮዋ ስታመልጥ፣ እርስ በርስ ወጣቶች ሲጋጩ ወዘተ .. በነበረው ትዕይንት ሲሳሳቁ ይቆያሉ፡፡ ደሮዋ ስትያዝ ጭፈራውን ሞቅ ያደርጉታል፡፡ የያዛት እንዲያርዳትና በትልቁ ቤት በራፍ ላይ እንዲያኖራት ይደረጋል፡፡ የልጅቷ አክስት ደግሞ ሌላ ሴት ዶሮ ትይዝና የወር አበባ ያየችውን ልጅ (አሂጻ) እና ጓደኛዋን (ምኸርማ) ጀርባቸውን ተራ በተራ እየመታች ትመርቃቸዋለች፡፡ እንዲህ እያለች፡-

| በጉሙዝኛ ቋንቋ | የአማርኛ ትርጉም |
|---|---|
| ቋኤሉ መኸርግማ ኢለዋ፤ ባቢልማ ዲውታ፤ | ትከሻሽ ጠንካራ፣ ሆድሽ ሰፊ ይሁን፤ |
| ካካላም ዳ ዳሾዋ አማ ካማኸርንሊችማ፤ | ነገር የምትችይ ብርቱ ያድርግሽ፤ |
| ግርባ አሉዋ ኮምድዳ ከመካልሽ | |
| ኢልቆዎ ዲያትጋች አማ፤ | ጉልበትሽ ለስራ፤ ሕሊናሽ ትግስት ለማደረግ ይበርታ፤ |
| ማግበሳ አላምላ ክኸርግ ምዳ ነዲቦጎ | |
| ካማ አጉታ አቢላ፤ | የኛ በደላችን ሳይሆን ምርቃታችን ይድረስሽ፤ |
| አላፎ ንጎላ ነሽጨቋ ከማ፤ | በኛ የጎደለ ላንቺ ይሙላ፤ |
| አሊኢያሽ ኔልቺዎ ከመግህ ቱሱዎ ነኢያች፤ | ለዐይንሽ ማረፊያ፣ ለጥርስሽ ደስታ ይብዛልሽ፤ |

(ተ.ቡ.ው. 1፤20)

አክስቲቱ ስትመርቅ ታዳሚዎቹ ሁሉ ወደመሬት አንገታቸውን ደፍተው የሁለት እጃቸውን መዳፍ እያዩ በእያንዳንዱ ምርቃት አሜን! ይላሉ፡፡ ምርቃቱ ሲያልቅም በሕብረት እንደ እልልታ ያለ ቀጭን ድምጽ አወጡ፡፡ በመቀጠልም ደሮዋን ምኸርማ ይዛት አሂጻ አረደቻት፡፡ ታዳሚዎቹ አሁንም ጎበዝ፣ ጀግና በማለት እልልታና ጭብጨባ አስተጋቡ፡፡ አሂጻና ምኸርማም ደሙን ተረማምደው ወደ ትልቁ ቤት ገቡ፡፡

የአክስቲቷ ምርቃት ትከሻሽ ጠንካራ፣ ሆድሽ ሰፊ ይሁን፤ በማለት ሰው በሕይወት ዘመኑ ክፉም ደግም፣ መከራም ደስታም፣ ሳቅም ለቅሶም ይገጥመዋልና ሁሉንም በልኩ የምትሸከሚ፤ ዐይተሽ

የምታልፊ፣ ሰምተሽ የምትችይ ያድርግሽ ትላታለች፡፡ ጉዳዩን ግልጽ ስታደርግላት ነገር የምትችይ ብርቱ ያድርግሽ፣ በማለት በዓለም ላይ እንደ ክፉ ነገር ትዕግስትን የሚፈታተን፣ አመልን የሚያከፋ፣ ከሰውነት ተራ የሚያወጣ የለምና፤ ነገር የምትችይ ብርቱ ያድርግሽ ብላ ትመርቃታለች፡፡ ሰው የሚከበረው በጉልበቱ ሰርቶ ሲያድር፣ ክፉና ደጉን በትዕግስት ሚዛን ሲዳኝ ነውና ጉልበትሽ ለሥራ፤ ሕሊናሽ ትዕግስት ለማደረግ ይበርታ፤ እያለች የመከበሪያዋና የሰውነት ሚዛን መጠበቂያዋ የሆነውን፤ በጉልበት ሰርቶ ማደርንና ትዕግስት ማድረግን ገንዘቧ እንድታደርግ በመማፀን ትመርቃታለች፡፡ በጣም የሚደንቀው የዚህን ዓለም አላፊና ጠፊ ሀብት እንቺ ብሎ ከመስጠት ወይም አግኚ ብሎ ከመመኘት  ይልቅ፤ አክስቷ ሩቅ አስባና አልማ፤ ልጃቸው የበረከት ተካፋይ እንድትሆን የኛ በደላችን ሳይሆን ምርቃታችን ይድረስሽ፤ በማለት በእናትና በአባት እዳ በደል ልጃቸው እንዳትጎዳ፣ ይልቁንም ከልቧ በተማጽኖ የሚያወጡት በጎ ምርቃት ብቻ እንዲደርሳት በእምነት በመመኘት ትመርቃታለች፡፡ እኛ በዚህ ዓለም ስንኖር ብዙ የጎደለን፣ ብዙ የከፋን፣ ብዙ ተመኝተን ያልተሳክልን ነገር አለና ላንቺ ግን ይሙላልሽ ስትል በኛ የጎደለ ላንቺ ይሙላ፤ በማለት ትመርቃታለች፡፡

በመጨረሻም ሰው በዚህ ዓለም ሲኖር ለዐይኑ ማረፊያ ልጅ፣ ለጥርሱ ደስታ መልካም ቤተሰብ ያስፈልገዋልና ለዐይንሽ ማረፊያ፣ ለጥርስሽ ደስታ ይብዛልሽ፤ እያለች በጎ ምኞቷን ትመርቃታለች፡፡ አንድም ዐይን ማረፊያ ከለለው ይቅበዘበዛልና የምትመኘውን ዓይነት ጀግና ባል ይግጠምሽ፣ አንድም ሰው ልቡን ደስ ካለለው ጥርሱ አይስቅምና የልብሽን ደስታ የሚጠብቅ፣ በፍቅርሽ የሚገዛ ይሁንልሽ በማለት ትመርቃታለች፡፡ (ተ.ቡ.ው. 1፤18)

የተመቱባትን ዶሮ ምኸ`ማዋ በመያዝ አሂጻዋ እንድታርድ ይደረጋል፡፡ ደሙንም ተረማምደው ወደ ትልቁ ቤት እንዲገቡ ይደረጋል፡፡ ጋፋ ግፅኃ (ሴት ደሮ)፡- ሴት ደሮዎቹ እናት እንደመሆናቸው ለልጅቱ እናትነትን ይመኙላታል፡፡ እንደ እናት ጠንካራ፣ ሆደ ሰፊ ታጋሽ፣ ለልጆቿና ለወገኗ ዋጋ የምትከፍል እንድትሆን መልካም ምኞታቸውን የሚገልፁበት ትዕምርታዊ ፋይዳ ነው፡፡ የክብሯን ልዕልና ለማሳየትም በሕይወት ዘመኗ አንድ ጊዜ ያውም በዚህች ዕለት ደሮ ታርዳለች፡፡

‹‹ዶሮዎች ለደስታ መግለጫ የሚታረዱ ናቸው፡፡ እናት ደሮ መሆኗ እናትነት መመኘታችን ነው፡፡ ዶሮዋን እናቲቱ የምትወረውራት እንድትሮጥ ነው፡፡ ልጇን የወደደ ሁሉ ሮጦ አባሮ ዶሮዋን ይዞ ያመጣላታል፡፡ ተመልከት ለሷ ፍቅርና ክብር ያው ሁሉ ከዶሮዋ ጋር በየሰፈሩ ሲሯሯጥ፣ ያዝን ሲሉ ዶሮዋ ስታመልጥ፤ የሰፈሩ ሴትና ወንድ ወጣቶች ለሷ ያላቸውን ፍቅርና ደስታ ለመግለፅ ሲሯሯጡ ስታይ በጣም ደስ ይላታል፡፡ በመጨረሻም እድለኛ ይዞ ያመጣላታል፤ ደሮዋም ታርዳ ልጃችንም ተራምዳ ትገባለች፡፡ ሁሉም ነገር የሚደረገው ለልጅቱ ክብር ነው፤ አክስቷ

የምትመርቃትም ‹ትከሻሽ ሰፊ ይሁን፣ ነገር የምትችይ ብርቱ ያድርግሽ፣ ጉልበትሽ ለስራ፤ ሕሊናሽ ትዕግስት ለማደረግ ይበርታ፤› በማለት ነው፡፡ ሁለቱም ዶሮዎች ለክብሯና ለደስታ ይታረዳሉ፤ በጋራ ይበላሉ፡፡ በሕይወት ዘመኗ ለመጀመሪያም፣ ለመጨረሻም ጊዜ ደሮ የምታርደው በዚህ ለመጀመሪያ ጋሀጃ (የወር አበባ) ባየችበት ጊዜ በሚከወነው ሥርዓት ነው፡፡ የክብሯን ከፍታ ለማሳዬት ተብሎ ነው በዚህ ዕለት የምታርደው፡፡ እሷ ስታርድ ወንዶች በአድናቆት ያጨበጭባሉ፤ ጎበዝ ጀግና ይሏታል፡፡ ከዚህ ቀን በፊት አላረደችም፣ ወደፊትም ባሏ እንጅ እሷ አታርድም፡፡ (ተ.ቦ.ው.1፤17-19) ያረደችውን ደሮ ተራምዳ የምትገባው ወደ ትልቁ ቤት ነው፡፡ ወደ ቤተሰቧና ወደ ፈጣሪ ማደሪያ በሰላም በድል ገባሽ፤ እንኳን ደስ አለሽ ማለት ነው፡፡ ከአሁን ጀምሮ ንፁህ ነሽ ማለት ነው፡፡ ቆሻሻው ደምሽ በንፁህ ደም ተተክቷል ማለት ነው፡፡ ፈጣሪ ሙሳም በፍቅር ያይሻል ማለት ነው፡፡ (ተ.ቦ.ው.1፤23)

የተዘጋጀዉን ምግብ ለመመገብና መጠጡን ለመጠጣት የተጠሩት ትላልቅ ሰዎች እና ሽማግሌዎች ወደ ትልቁ ቤት ይገባሉ፡፡ ሕጻናት እና ወጣቶች ደግሞ ከውጭ ሆነው የመመገቢያ ሰዓታቸው እስኪደርስ በሕብረት ይጨፍራሉ፡፡ ትልቁ ቤት ውስጥ ሽማግሌዎቹ ‹‹ልጃችን እንኳን ከልጅነት ወደ ትልቅ ሰዉነት ተሸጋገርሽ፤ ለመሰብሰብ ምክንያት ሆንሽን፤›› እያሉ መልካም ምኞታቸውን እየገለፁ፤ ሰላምታ እየሰጡ ይቀመጣሉ፡፡ በተዘጋጀላቸው የመቀመጫ ቦታ አረፍ እንዳሉ አክስቲቱና ሌሎች ቅርብ ሰዎች እጅ ያስታጥባሉ፡፡ እናቲቱና ሌሎች የቅርብ ሰዎች ቦርዴና አረቂ (ጸልኛ) ይቀዳሉ፡፡ ከተቀዳላቸው ቦርዴና አረቂ ሁሉም እንደፍላጎታቸው አንዱን ጠጥተው እንደጨረሱ አባትየው ይቆምና አክብረው የመጡትን ሽማግሌዎች፣ ወዳጅ ዘመዶች እና ጎረቤቶች አመስግኖ ለልጁ ምርቃት ይጀምራል፡፡

| በጉሙዝኛ ቋንቋ | የአማርኛ ትርጉም |
|---|---|
| ና ኪ ሙሳ ግሸርማ፤ | ፈጣሪ መልካሙን ይስጥሽ፤ |
| ና ዳዳ ኢትፓቋዋ ኣማ ንባኒያ፤ | ከክፉ ነገር ሁሉ ያውጣሽ፤ |
| ንባ ክቡንጋ ሙሳ ኢታ ዶራጋ ኣማ፤ | እኛ እንደመረቅንሽ ፈጣሪ ይመርቅሽ፤ |
| ባኔ ግሻራም፤ | ሀሳብሽን ፈጣሪ ይሙላው፤ |
| ዴቆ ምጻ ኣሌ፤ | ከጓደኞችሽ እኩል ሁኝ፤ |
| ካ ማዴ ጎንማ፤ | ቤት ያዥ፤ |
| አሌዳቋ አማ ነድ አሉጉትቋ፤ | የሚያገባሽ የተባረከ ይሁን፤ |
| ንግሩ ዱዋ ካሱብ አሉ ክባቻ | |
| ጉንዛ ደዳ ፓቋም፤ | ለዘርሽ ሴት ልጅ፤ ለኩራትሽም ወንድ ልጅ ውለጅ፤ |

| | |
|---|---|
| አላዳቋጸም ኑጉት፤ | የነካሽው ይባረክ፤ |
| ናንዚያች አላውሻም፤ | የዘራሽው ይለምልም፤ |
| ናቢድ አላሲብጽም፤ | የዳሰስሽው ይፈወስ፤ |
| አላንችቋም ኒኢያች፤ | ያቦካሽው ይበርከት፤ |
| መበንጎ አገሽኮ አሉዋ፤ | ትንፋሽሽ አይቀዝቅዝ፤ (ተ.ቡ.ው. 2፤7) |

አባቷ ሲመርቅ ቤት ውስጥ ያሉት ሽማግሌዎችና ጎልማሶች እንዲሁም ውጭ ያሉት ወጣቶችና ሕጻናት በፀጥታ ወደመሬት አንገታቸውን ደፍተው የሁለት እጃቸውን መዳፍ እያዩ በእያንዳንዱ ምርቃት አሜን! ይላሉ፡፡ ምርቃቱ ሲያልቅም በሕብረት እንደ እልልታ ያለ ቀጭን ድምጽ ያሰማሉ፡፡ አባትዬው ምርቃቱን ሲጀምር በክብር የተገኙትን ሁሉ አመስግኖ ፈጣሪ መልካሙን ይስጥሽ፤ ይላታል፡፡ ፈጣሪ ለልጆቹ ክፉ ነገር አያስብም፣ የሙሳ ሀሳብ ሁሌ መልካም ነገር ብቻ ነውና በጎውን እንድታገኝ ይጠይቅላታል፡፡ በዚህም ያስቀጥልና መልካሙን ነገር ከሰጠሽ ሰይጣን በቅናት ክፉ ነገር ያመጣብሻልና ከክፉ ነገር ሁሉ ያውጣሽ፤ ብሎ መጥፎ ነገር እንዳያገኛት ይማፀናል፡፡ የሰው ምርቃት ብቻውን አይፀናምና ከቤተሰቡ፣ ከእናቷ፣ ከአክስቷ፣ ከአባቷና ከሽማግሌዎቹ ምርቃት በላይ ፈጣሪ ሙሳ ቢመርቃት የሁሉም መልካም ምኞት ማረፊያ ያገኛልና እኛ እንደመረቅንሽ ፈጣሪ ይመርቅሽ ይላታል፡፡

ሰው ነሽና በልቡናሽ ብዙ ነገር ታወጫለሽ፣ ታወርጃለሽ፣ በአዕምሮሽም እንዲህ ቢሆንልኝ እያልሽ በጎ በጎውን ታስቢያለሽና ሀሳብሽን ፈጣሪ ይሙላው፤ በማለት ይመርቃታል፡፡ አባት ልጁ ከጓደኞቿ ስታንስ ደስ አይለውምና፤ አንድም ከጓደኞችሽ ብታንሽ ልቤ በሀዘን ይሰበራል ሲል፤ አንድም ከጓደኞችሽ ሁሉ ተለይተሽ ብትበልጭ በቅናት የሚጠላሽ ይበዛል ሲል ከጓደኞችሽ እኩል ሁኚ፤ ብሎ ይመርቃታል፡፡ በጉሙዝ ቤት መያዝ ትዳር መመስረት፣ ሀብት ማፍራት፣ እናት መሆን ነውና ቤት ያዥ፤ ይላታል፡፡ የትዳር አጋሯም በፍቅሯ የሚገዛ፣ አማቾቹን የሚያከብር፣ ቤቱን ቤቱን የሚል፣ ሰርቶ የማይታክት፣ አድኖ የሚመግብ ጀግና እንዲሆን በመመኘት የሚያገባሽ የተባረከ ይሁን፤ ብሎ ይመርቃታል፡፡

ሴት ልጅ የቤተሰቡን ዘር በማስቀጠል፣ እናት በመሆን ታሳድጋለችና፣ ወንድ ልጅም ጠላትን ተዋግቶ በማሸነፍ፣ አድኖ በመግደል ለቤተሰቡ፣ ለመንደሩ ኩራት ይሆናልና ለዘርሽ ሴት ልጅ፣ ለኩራትሽም ወንድ ልጅ ውለጅ፤ በማለት ይመርቃታል፡፡ የቀዳሽው ውኃ፣ የጠመቅሽው ቦርዴ፣ ያወጣሽው አረቂ (ጾልኛ)፣ ያገነፋሽው ገንፎ፣ ያዘጋጀሽው ክማ፣ እንኩሮ፣ ሁሉም በእጅሽ የነካሽው የሚበላው የሚጠጣው የሚያጠግብና የሚያረካ ይሁን ሲል የነካሽው ይባረክ ይላታል፡፡ የጉሙዝ ሴት በእርሻ ሥራ ላይ ትቆፍራለች፣ ዘር ትዘራለች፣ ታርማለች፣ ትኮተኩታለች፣ አዝመራ

ትሰበስባለችና፤ በአንቺ የተሠራ የእርሻ ሥራ ሁሉ ዘሩ ፍሬ ያፍራ፣ የሚደርቅ አይኑር ሲል የዘራሽው ይለምልም ይላታል፡፡ ቤተሰቡ ሁሉ አመመኝ፣ ደከመኝ ሲል በእናትነት ፍቅሯ በመራራት ራሳቸውን፣ ጀርባቸውን፣ እግራቸውን፣ ሆዳቸውን ሙሳ ምሕረት እንዲልክላቸው እኔን፣ እኔን እያለች ትዳስሳለችና በእጅሽ ምሕረት ይምጣ ሲል የዳሰስሽው ይፈወስ ብሎ ይመርቃል፡፡ በቤት ውስጥ እህል እንዳይጠፋ፣ የራበው ሁሉ እንዲበላ ያቦካሽው ይበርክት ይላታል፡፡ ይህ ሁሉ የሚሆነው በአንቺ መኖር ነውና ረጅም ዕድሜ ያድልሽ፣ ሞትም ዐይይሽ ሲል ትንፋሽሽ አይቀዝቅዝ በማለት አባቷ ይመርቃታል፡፡ (ተ.ቡ.ው. 2፤7)

ከአባቷ ምርቃት በኋላ ከሽማግሌዎቹ መካከል በእድሜ በጣም ትልቅና ተደማጭ የሆኑት ሁሉንም ሽማግሌዎች እና መንደሩን ወክለው በመነሳት ይመርቃሉ፡፡

| በጉሙዝኛ ቋንቋ | የአማርኛ ትርጉም |
|---|---|
| ድጃች ኤዲዳ ክማነዚማ፤ | ልጃችን እርጥብ (ለምለም) ሁኝ፤ |
| ዚላ ዳቦላም ኮማንጎ ችማ አምብህች፤ | ዛሬ አብበሻል፤ ነገ ፍሬ አፍሪ፤ |
| ናድ ፋህጻ አሉዋ ዚዚ አለመችግህል፤ | ሕይወትሽ ሁሉ የደስታ ይሁን፤ |
| ነክቻ አሙሳ ካማ አሊሉዋ፤ | ፈጣሪ (ሙሳ) የልብሽን ይስጥሽ፤ |
| ንአክ ምንቋ አሉዋ መተግፅጎ መንስምት፤ | በምጥሽ ጊዜ ክፉ ነገር አያሳይሽ፤ |
| ግርባ ንጎዳም ምዳንጎ መላ አቋማ፤ | ጉልበትሽ ሰርቶ የማይደክም ይሁን፤ |
| አላድፅም ኮማ ትጎትቋ፤ | የነካሽዉ ሁሉ ይበርክት፤ |
| ካፅጨም ነንዶዋ ንሉዋ አፋደቋ | |
| አማ አሙሳ፤ | በመንገድሽ የሚወድቀዉን እንቅፋት ፈጣሪ ያንሳልሽ፤ |
| ከብንጉ ሽጨፅ ክማንግሀይልን | |
| ያሉዋ ዱዋ ነች ካማ፤ | ለጀርባሽ ክብር ለልብሽ ደስታ የሚሆኑ ልጆች ይስጥሽ፡፡ |
| ካውት ጉደንቋ ላውይ ምግህማ፤ | ጥሩ የሆነ ባል ይግጠምሽ፤ |
| ምግህማ ኢትግንዝዋ አግሀ አንጉ፡፡ | ሰነፍ ያልሆነ ስራ የሚችል፤ |
| ምሀ ጋሀጃ ሊግሀ ሙሳ ፤ | የወር አበባው የጤና ይሁንልን፤ |
| ካውት ምድ መንግስታ ምሃላ ፡፡ | መንግስት ሀገር የሚሆነውን፤ የሚያስወልድ ይሁን፡፡ |
| | (አቶ ጊሳ ዝማቻ ቃ.መ.3፤3) |

የሽማግሌው ምርቃት ማጠናቀቂያ ነውና ከእናቷ፣ ከአክስቷና ከአባቷ ተዘንግቶ የቀረውን ወይም የቀረ ከለለ ማኅበረሰቡን ወክለው የሚከውኑት ምርቃት ነው፡፡ የመልካም ምግባር ባለቤት፣ ሰርታ የምታፈራ፣ ታዛ የልብ የምታደረስ፣ የበጎ ነገር ሁሉ ምንጭ፣ እድለኛ እንድትሆን

የመንደሩ ማኅበረሰብ ሁሉ ይመኛልና፤ ዛሬ ደረቅ የሆነ ነገ አብቦ ፍሬ አያፈራምና ሽማግሌው ልጃችን እርጥብ (ለምለም) ሁኝ፤ ብለው ይመርቋታል፡፡ ዛሬ የወር አበባ ዐይተሻል፤ አበባ ሆነሻል ነገ ደግሞ መልካም ፍሬ የምታፈሪ ዛፍ ሁኝ፣ በጥላሽም ሁላችን እንረፍ፣ በጉልበትሽ እንጦር ሲሉ ዛሬ አብበሻል፤ ነገ ፍሬ አፍሪ፤ ይሏታል፡፡ ሰው ፈጣሪን የሚያመሰግን ሕይወቱ በደስታ ሲሞላ ነውና፤ ከአንደበትሽ የምስጋና ቃላት እንዳይጠፉ፤ ፈጣሪም ያንቺ ምስጋና እንዳይጎልበት ሕይወትሽ ሁሉ የደስታ ይሁን፤ በማለት ይመርቋታል፡፡ ልብሽ ብዙ ያስባልና፣ አዕምሮሽም መልካሙን ምኞት ያሰላስላልና መሻትሽን የሚያውቀው ፈጣሪ (ሙሳ) የልብሽን ይስጥሽ፤ ይሏታል፡፡

ሴት ልጅ ጭንቅ የሚይዛት ለመውለድ ስታምጥ ነውና ምጥሽን አያፅናብሽ፣ ያማጥሽውን ፍሬ እቀፊ ሲሉ በምጥሽ ጊዜ ክፉ ነገር ዐያሳይሽ፤ በማለት ይመርቋታል፡፡ አንድም ሴት ልጅ የምትወዳቸው ቤተሰቦቿን ክፉ ነገር ሲገጥማቸው ትጨነቃለችና በጭንቀትሽ ጊዜ መከራሽ ቀላል ይሁን ለማለት ነው፡፡ የሰው እጅ እንዳታይ፣ እጅሽም ለልመና እንዳይዘረጋ፣ ጉልበትን የሚያደክም ህመም ዐይይሽ ሲሉ ጉልበትሽ ሠርቶ የማይደክም ይሁን፤ ትጋትን ገንዘብሽ አድርጊና በሥራሽ ተከበሪ በማለት ይማፀኑላታል፡፡ በቤትሽ የለኝም እንዳትይ የነካሽዉ ሁሉ ይበርክት፤ ጥቂቱ ብዙ ይሁንልሽ ይላሉ፡፡ ሰው ነሽና በሕይወትሽ ምሬትን የሚፈጥሩ በመንገድሽ ወጥመድ የሚዘረጉ ክፉዎች አይጠፉምና በመንገድሽ የሚወድቀዉን እንቅፋት ፈጣሪ ያንሳልሽ፤ በማለት የሕይወት ፈተናዎች ሁሉ ከመንገዱ በፈጣሪ ኃይል እንዲነሱላት ይመርቋታል፡፡ እሷ እኮ ልጆች አሏት፣ ወገን አላት፣ መከታ ጋሻ አላት እንድትባይ፤ ልብሽም በደስታ እንዲኮራ፣ በሰውም ዘንድ ከበሬታ እንድታገኝ ለጀርባሽ ክብር ለልብሽ ደስታ የሚሆኑ ልጆች ይስጥሽ ይሏታል፡፡ ሰነፍ ያልሆነ ስራ የሚችል፤ ጥሩ የሆነ ባል ይግጠምሽ፤ በማለት ለነሱ ጥሩ አማች፣ ለልጃቸው የምትኮራበት ጥሩ ባል ይመኙላታል፡፡ ከሴት ማኅፀን ለበሽታ የሆነ ደም ይፈሳልና ያንቺ ግን የወር አበባው የጤና ይሁንልሽ፤ ይሁንልን ይሏታል፤ የወር አበባው ከወንድ ዘር ጋር ቢዋሐድ ልጅ እንደሚሆን ሲያጠይቁ መንግስት ሀገር የሚሆነውን፤ የሚያስወልድ ይሁን በማለት ሽማግሌው መንደሩን አድባሩን ወክለው ይመርቋታል፡፡ (አቶ ጊሳ ዝማቻ ቃ.መ.3፤3)

ሁሉም ምርቃቱን በአሜንታ ይቀበላሉ፡፡ የመጨረሻ ምርቃት ስለሆነ ሁላቸውም በልባቸው ቀረ ያሉትን ምርቃት በለሆሳስ ይመርቁና የተለመደውን እንደ እልልታ ያለ ቀጭን ድምጽ ያሰማሉ፡፡ እናቷም የልጇን እጅ በመያዝ ወፍጮ መፍጨት፣ ሙቀጫ መውቀጥ፣ ገንፎ ማገንፋት፣ ውኃ መቅዳት፣ ቡና ማፍላት ታስጀምራታለች፡፡ ሽማግሌዎችም አሰራሯን እያዩ ያደንቋታል፡፡ ከኤላ ያያ ማንጎሽ ምዳዳ (በእናቷ እጅ ተይዛ ሥራ መጀመር)፡- በብሔረሰቡ

ዘንድ የራሱ ትርጉም አለው፡፡ ‹‹ልጅቱ ከጋህጃ መንፃት በኋላ ለቤቱ እንግዳ ናት፡፡ ከሙሳ (ፈጣሪ) ጋር የቆየችው እናቷ ናት፡፡ ስለሆነም ከዚህ በኋላ በኃላፊነት ስራዎችን እንድትሰራ የቤቱን እቃዎች ሁሉ ታሳያታለች፡፡ እጇን ይዛ ወፍጮ መፍጨት፣ እህል መውቀጥ ቡና ማፍላት፣ ገንፎ ማገንፋት ታስጀምራታለች፡፡ ከቤተሰቡ፤ ከማኅበረሰቡ ከፈጣሪ፣ ከእቃዎችና ከሥራው ጋር ታስተዋውቃታለች፡፡ ከዚያ በኋላ ያለፍርሃትና ያለኃፍረት መግባት መውጣት እንደልቧ መስራት ትችላለች፡፡ (ተ.ቡ.ው.1፤24) ሁሉም ነገር ስላለቀ ደስ ይለኛል፡፡ እናቴ ከቤታችን አምላክ ሙሳ ጋር እያስተዋወቀችኝ ነዉ፡፡ የቤተሰቡ አባል ነኝ፤ በቀጣይ ደግሞ እኔ እናት እሆናለሁ፤ የቤቱን ኃላፊነት በራሴ እወጣለሁ፤ በዚህም በጣም ደስ ይለኛል፡፡ (ወ/ሪት ማሙሻ አቫቢ ቃ.መ. 1፤ 6)

ምግብና መጠጡ ይበላል፣ ይጠጣል፡፡ ጭፈራውም ደምቆ ይቀጥላል፡፡ በዚህም የዝግጅቱ ፍፃሜ ይሆናል፡፡ ሌሊቱን በሙሉ ሲጨፈር ይታደራል፡፡ እርሷም ወደ ማኅበረሰቡ መቀላቀል እና ወደ ትልቁ ቤት እንደልቧ መግባትና መውጣት ትጀምራለች ፡፡

## 5.4. የድግትስ ጋህጃ ሥነ ልቡናዊ ፋይዳ

እንደ ዩኒሴፍ እውቀት፣ አመለካከትና ተግባር (KAP 2017) ጥናት፤ የወር አበባ ተፈጥሯዊ የሴቶች ጉዳይ ቢሆንም፣ በብዙዎች ላይ የዕውቀት፣ የአመለካከት እና የልምድ ችግር ጎልቶ ይታያል፡፡ ወንዶች ስለሚያሾፉባቸው ሴቶች ብዙውን ጊዜ የወር አበባ ሲያዩ እያለቀሱ ትምሕርታቸውን አቋርጠው መሄዳቸው በምክንያትነት ይነሳል፡፡ አንዳንድ ጊዜ በአጠቃላይ ትምሕርት ቤቱን ለቀው እንዲወጡ ወይም ትምሕርታቸውን እንዲያቋርጡ ምክንያት ይሆናል፡፡

‹‹በኢትዮጵያ ከሚገኙ ልጃገረዶች ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ለመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ ከማየታቸው በፊት ስለወር አበባ ምንም ነገር ስለማያውቁ ይደናገጣሉ፡፡ ብዙ የጉርምስና ዕድሜ ያላቸው ልጃገረዶች ስለወር አበባ ከሌላ ሰው ጋር በጭራሽ አይወያዩም፡፡ በወር አበባ ወቅትም ትምሕርት ቤት የሚቀሩባቸው ዋና ዋና ምክንያቶች የህመም ስሜት፣ ምቾት ማጣት እና መሳለቂያ መሆን የሚሉ ተጠቅሰዋል፡፡ የወር አበባ ለመጀመሪያ ጊዜ ማዬት ሲጀምሩ ‹ልጃገረዶች ከእንግዲህ ድንግል አይደላችሁም› የሚለው የተለመደና የተሳሳተ አመለካከት አለ፡፡ እነዚህ አለመግባባቶች ከማሾፍ በተጨማሪ ልጃገረዶች እፍረት እንዲሰማቸው እና እራሳቸውን እንዲያገሉ ለሥነ ልቡናዊ ጫና ይጋለጣሉ፡፡ እንደ አህጉር በአፍሪካና በኤሺያ

25%፣ በተናጥል ሀገራት ደግሞ በኢትዮጵያ 11% ሴት ተማሪዎች ከወር አበባ ጋር በተያያዘ ምክንያት ትምሕርታቸውን ያቋርጣሉ፡፡›› (©UNICEF Ethiopia /2017/Tadesse KAP፣ 18)

ይህንን ሥነ ልቡናዊ ጫና ከመቋቋምና ለፈተናው እጅ ካለመስጠት አንጻር የጉሙዝ ብሔረሰብ የድግትስ ጋህጃ ከበራ ዓይነተኛ የሥነ ልቡና ማከሚያና ማበልፀጊያ መድኃኒት ሆኖ ይታዬኛል፡፡ ምክንያቱም በብሔረሰቡ ዘንድ የወር አበባ እንደመጥፎ ቆሻሻ ነው የሚታዬው፡፡ ሰው ሰገራውን፣ ንፍጡን፣ አክታውን ሌላ ሰው ዐይቶ እንዳይፀየፍ እንደሚደብቀው ሁሉ እነሱም የወር አበባቸውን ይደብቃሉ፡፡ ‹‹ለመጀመሪያ ጊዜ ጋህጃ (የወር አበባ) ሳይ ትዝ ይለኛል እንጨት ለቅሜ እየተመለስኩ ነበር መንገድ ላይ ነበርኩ፡፡ ትንሽ ሆዴን ቆረጠኝ እና ከዛፍ ስር ጥላ ላይ አረፍኩ ትንሽ ቆይቶ ደም እና የሆነ ነጭ ነገር የቀላቀለ ከማኅፀኔ ፈሰሰ፤ በጣም ደነገጥኩ፣ አለቀስኩ፡፡ የፈሰሰዉን አፈር አልብሼ፤ እንጨቴን ይዤ፣ ቤት ደረስኩና ከጎረቤት ጓደኛዬን ጠርቼ አዋየኋት፡፡ ሰዉነቴም ልብሴም ተበላሽቶ ነበር፡፡ እሷም ጋህጃ (የወር አበባ) እንደሆነ ነገረችኝና አስቀምጣኝ የእጆቼን ጥፍር በቆሻ (ቃጭማ) ፍሬ አጥባኝ ወደ ትንሿ ጎጆ አስገባችኝ፡፡ የቆሸሸ ሰዉነቴንም አጠበችኝ፡፡ ምጫ (ባሕላዊ የሴቶች ንጽህና መጠበቂያ) አምጥታ እንዴት እንደሚታሰር አሳየችኝና ራሴ አስሬ ጋህጃውን (የወር አበባውን) መቀበል ጀመርኩ፡፡ ከዚህ በኋላ ተረጋጋሁ ሶስት ቀን ፈሶኛል፡፡›› (ወ/ሪት ማሙሽ አቫቢ. ቃ.መ. 1፣1)

ከዚህ ምላሿ መረዳት እንደሚቻለው ሴት ልጆች ለመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ ሲያዩ ድንጋጤ፣ ጭንቀት፣ ፍርኃት እንደሚገጥማቸውና ከመረበሻቸው የተነሳ እንደሚሳቀቁና እንደሚያለቅሱ ያሳያል፡፡ ተፈጥሮው በራሱ ስሜት እንደሚረብሽ ይጠቁማል፡፡ ‹‹ዐየሀ የሥርዓቱ መከበር ኃፍረት እና ድንጋጤዋን እስከ መጨረሻው ያባርርላታል፡፡ ለ12 ወይም ለ13ና ለ14 ዓመት በወሬ የሰማችው ነገር በገሃድ ሲመጣባት ከእድሜዋ መድረስ ጋር ተያይዞ ኃፍረት ይይዛታል፤ ድንጋጤም ይወራታል፡፡ በሥርዓቱ ውስጥ ጋህጃ (የወር አበባ) ‹ለኃላፊነት መብቃትሽን፣ ወልደሽ እናት መሆን የምትችይ መሆንሽን፣ ማብሰሪያ ምልክት ነው፡፡ እንኳን ደስ አለሽ!› ስትላት ኃፍረቱ ይገፈፋል፤ ድንጋጤዋም ከላይዋ ላይ ተሽቀንጥሮ ይወድቃል፡፡ አዕምሮዋ (ሥነ ልቦናዋ) ከፍ ይላል፣ ኃላፊነትም ይሰማታል፤ ለእናትነት በአካል ብቻ ሳይሆን በአዕምሮም (በሥነ ልቦናም) መዘጋጀት ትጀምራለች ፡፡›› (ተ.ቡ.ው. 1፣9)

ጓደኛዋ ከአጠገቧ በመሆን በመንደሩ ላሉ ጎረምሶች፣ ለጓደኞቿ፣ ለሽማግሌዎችና ለሕጻናትም ሳይቀር እገሊት የእገሌ ልጅኮ የወር አበባ ዐየች እየተባለ ሲነገር ጥቂት በጥቂቱ ፍርኃቷ እየተወገደ ደስ እያላት ትሄዳለች፡፡ የወር አበባ ማፈሪያ መሸማቀቂያ ሳይሆን ተፈጥሯዊ ፀጋ መሆኑ እየገባት ይመጣል፡፡ ጓደኛዋ ትልቁ ሚናዋ ከአጠገቧ በመሆን ማደፋፈር፣ ማሳየት፣

ማበርታትና ፍርኃቷን ማቅለል ነው፡፡ ‹‹ጓደኛዋ እንደ ሚዜ ነች፤ ከሷ በፊት ሁሉም ሥርዓት የተፈፀመላት፤ ልምድ ያላት ስለሆነች በራሷ እያሳየች ነው እንዲደረግላት የምታደርጋት፡፡ አዲስ ነገርን ለብቻ መቀበል ፍርኃት ስላለው፤ ጓደኛዋ ፍርኃቷንና ኃፍረቷን እያስወገደች እና እያሳየች ለሥርዓቱ ፍፃሜ ታደርሳታለች ፡፡›› (ተ.ቡ.ው. 1፤14)

ይህንንም ከዚህ በፊት የወር አበባ ዐይታ ሥርዓቱ የተፈፀመላት ወጣት ስታረጋግጥ ‹‹በወቅቱ ጓደኛዬ አጠገቤ ስላለች ታደፋፍረኛለች፤ መፍራት እንደሌለብኝ ትነግረኛለች፡፡ የምንሔደዉም አብረን ነዉና አልፈራም አላፍርም፡፡ ጓደኞቼን ስጠራቸዉ ‹‹እንኳን ለዚህ አበቃሽ! ›› ነዉ የሚሉኝ፤ ደስ ይላቸዋል፤ ይህም ፍርኃቴንና ኃፍረቴንም ያባርረዋል፡፡ ጋህጃ (የወር አበባ) እናት የመሆን ምልክት ከዚያም ሲያልፍ ቆሻሻ እንጂ የሚያዋርድ ነገር አይደለም፡፡›› (ወ/ሪት ማሙሻ አቫቢ ቃ.መ. 1፤5)

ለመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ ያየችው ወጣት እንደንግስት ስለምትታይ እሷ የምትቀመጥበት ወንበር ላይ ማንም ድርሽ አይልም፡፡ ይህም ለሷ የሚሰጣት ክብር ምን ያህል የሥነ ልቡና ከፍታ ላይ እንደሚያደርሳት ጠቋሚ ነው፡፡ በክብሯ የመጣም ማኅበረሰባዊ ቁጣና ቅጣት እንደሚጠብቀው ግልፅ ማሳያዎች አሉት፡፡ ‹‹ልጅቷ እኮ ንግስት ናት፤ ወንበሯ የሷ ብቻ ነው፤ በኛ ልቡና የከበረና የተከበረ ስለሆነ ማንም አይቀመጥበትም፡፡ ባሌ በእኔ ተጉ ጋህጃ ላይ ተቀምጦ አያውቅም፤ ለምን ይመስልሃል? ባሌ ስለሚያከብረኝ ነው፤ መገለጫውም ይሄ ነው፡፡ በኔ ተጉ ጋህጃ ላይ ከተቀመጠ ንቀቱን ወይም ጥላቻውን ገለፀ ማለት ነው፡፡ ይሄን ካደረገ በኔ ብቻ ሳይሆን ፈጣሪዬም ይቀጣኗል፡፡ በልጅቱ ወንበር የሚቀመጥ፤ እንኳን ወንድ፤ ሴት ጓደኛዋም ብትሆን ልጅቱ የምትረዳው እንደናቋትና ጥላቻቸውን እንደገለፁላት ነው፡፡ ይሄ ደግሞ የቁጣ ምላሽ ከፈጣሪም፣ ከወንበሩ ባለቤትም ያስከትላል፡፡ ሌሎች ጓደኞቿም ዝም አይሉም፡፡ ሕፃናት እንኳ ሳያውቁ ቢቀመጡ ችግር የለውም፤ አስተምረህ ታስነሳቸዋለህ፡፡ አውቆ በድፍረት ይሄን የሚያደርግ ካለ በተቃራኒው ንቀትና ጥላቻን በራሱ ላይ ያተርፋልና አያደርገውም፡፡ እኔም በእድሜዬ እንዲህ ዓይነት ደፋሮችን አላዬሁም ፡፡›› (ተ.ቡ.ው. 1፤15)

በጉሙዝ ማኅበረስብ ዘንድ የወር አበባ ያየች ሴት ደም እየፈሰሳት ወይም ከታዬ ሰባት ቀን ሳይሞላት ከትልቁ ቤት ገብታ ሥራ አትሠራም፡፡ ይህ ማለት ግን ከውጭ ከትንሿ ቤት ወይም እርሻ ቦታ ካልደከማት፣ ካላመማት ወይም በጣም የሚያስገድድ ችግር ካልገጠማት መሥራት ትችላለች፡፡ ሥራ አትሠራም፣ ከትልቁ ቤት አትገባም የሚባለው ለማግለል ሳይሆን ፈጣሪ ቆሻሻ ነገርን ስለማይወድና እሷም እረፍት እንድታደርግ፣ ሰውነቷንም እንትተጣጠብ በማሰብ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ ‹‹ለምን ታቋርጣለች፤ ንፅህናዋን ጠብቃ ትምሕርት ትቀጥላለች እንጅ

አታቋርጥም፡፡ የወር አበባ መጠኛል ብትልኮ በዐይናቸው እስካላዩት ድረስ ምንም የተለዬ ስሜት አያሳዩዋትም፤ ምንም ማለት አይደለም፡፡ ችግሩ ጨርቋን ነክቶት ዝንብ እኸ'ኸ'ኸ እያለ ከተከተላት እንኳን የወንዱን የሴት ጓደኞቿን መፀየፍና ስድብ አትችለውም፡፡ አንተስ ብትሆን እዚህ ተበላሽቼ ብታዬኝ ፊገግታ ታሳዬኛለህ? ሰው ነህ የሚያፀይፍ ቆሻሻ ስሜትህን ይለውጠዋል፡፡ ካላዬኸው ደሞ በመስማትህ ምንም አትሆንም፡፡›› (ተ.ቡ.ው. 1፤7)

ለሴት ልጃቸው የድግትስ ጋህጃ ክወና የፈፀሙት እናት ‹‹ያዉ እስክነጻ ድረስ ትልቁ ቤት ስለሙሳ ክብር እና ንጽህና አልገባም፡፡ ጎጆ ቤት ሆኜ ትናንሽ የዉጪ ሥራ እሠራለሁ፡፡ እንጀራ አልጋግርም፣ ወደ ትልቁ ቤት የሚገባ ነገር አልሠራም፤ እስክነጻ እና ገላዬን እስክታጠብ ድረስ፡፡ ጋህጃ (የወር አበባ) በራሱ ህመም አለዉ፤ ትልቁ ቤት ሙሳ (ፈጣሪ) ስላለ ቆሻሻ ነገር አይወድም፡፡ ከምንበላዉ ከምንጠጣዉ ነገር ሁሉ ይጋራል፡፡ ስለ ሙሳ ንጽህና ትልቁ ቤት ዉስጥ ንጹህ ነገር ነዉ የሚፈለገዉ፡፡ ተሳስቼ እንኳን ሰርቼ ባስገባ በሽታ ቁስል በሰዉነቴ ይወጣል፡፡›› (ወ/ሮ ምጋካ ንጉሴ ቃ.መ. 2፤5-7)

ይህ ሁሉ ክዋኔ የሚያሳዬው በወር አበባ ምክንያት የሚመጣ የሥነ ልቡናና የማኅበራዊ ግንኙነት ጫና እንዳይኖር ነው፡፡ ሥርዓቱን መፈፀምም ማኅበረሰባዊ ግዴታ፣ የሙሳም (ፈጣሪ) ትዕዛዝ እንደሆነ ይነገራል፡፡ ማንም ከፈጣሪው ትዕዛዝ በመውጣት መቀጣት አይፈልግም፡፡ በሥርዓቱ መፈፀምም ብዙ በረከትና ጥቅም እንጅ ጉዳት የለውም፡፡ ‹‹ይሄ ሥርዓት ባይፈፀም ትታመማለች፣ ከታመመች ደግሞ እሷን ለማንፃትና ለማዳን የፍየል ወይም የደሮ መስዋዕት ለአምላክ ይቀርባል፡፡ እርጥብ ቅጠል ከወንዝ መጦ በውኃ እየተነከረ ትረጫለች፤ በምራቅ እትፍ! እትፍ! እየተባለ ትነፃለች ከበሽታዋም ትድናለች፡፡›› (ተ.ቡ.ው. 1፤10)

የሥርዓቱ መከወን ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ አለው፡፡ ይኸውም በሥነ ልቡና ጫና ምክንያት የሚመጣውን ፍርኃት፣ ኃፍረት፣ መሳቀቅና መሸማቀቅ ያስወግዳል፡፡ በማኅበራዊ ግንኙነቱም ብቸኝነትን፣ ድብቅነትን መተፋፈርን ያስቀራል፡፡ ከባሕላዊ እምነቱ አንጻርም ሲታይ የፈጣሪን ትዕዛዝ መፈፀም የአባቶችና የእናቶች ምርቃት እንዲደርስ ያግዛል፡፡ የልብ ደስታ፣ የህሊና እርካታ ያስገኛልና፡፡ ‹‹በሥርዓቱ መከወን የወር አበባ ማዬቴ በሴቱም በወንዱም ይታወቃል አላፍርም፡፡ ኃላፊነት ይሰማኛል፤ የወር አበባ ሳይ ከጓደኞቼ ጋር እኩል እንደሆንኩ አዉቃለሁ፡፡ በኔም፣ በቤተሰቦቼም ፍቃድ ላገባና እናት ልሆን እንደምችል አዉቃለሁ፡፡ ሥርዓቱ ስለተፈፀመልኝ የአባቶቼ ምርቃት እንደሚደርስልኝ አምናለሁ፡፡ በዚህም ደስተኛ ነኝ፡፡ ጓደኞቼ ክብር ሰጥተዉኝ ሲዘፍኑልኝ፣ አባቶቼ ሲመርቁኝ፤ ከዚህ በኋላ ለእናትነት

ተዘጋጂ ሲሉኝ፣ የማገኘዉ ደስታ ጥቅም አይመስልህም? በዚህ ሥርዓት የፈጣሪን ፈቃድ ማሟላት ያስደስታል፡፡ አሁን እዚህ የወር አበባ ቢመጣኝ አንተ እንዳታየዉና እንዳይሸተን እጠነቀቃለሁ እንጅ አላፍርም አልደነግጥም፡፡ አንተ ሽንትህ እንደመጣህ አድርገህ አስበዉ፣ ሽንትህን ስትሸና ሰዉ ምንም አይልም፣ ምናልባት በልቡ የሚለዉ ነገር ይኖራል፡፡ የኔን የወር አበባ ሌላ ሰዉ ሲያዪዉ ምን ይሰማዋል? በአፉ ባይናገርም ሰዉነቱን ዉርር ያደርዋል፡፡ ለኔ ግን ምንም አይመስለኝም፡፡ አባቶቻችን የወር አበባ እድል ያልቀናዉ፣ ሰዉ መሆን ያልታደለ ነዉ ይላሉ፡፡ እድል ቢገጥመዉ ኖሮ እንደኔና እንዳንተ ሰዉ ይሆን ነበር፡፡ ከወር አበባ እስክነጻ ራሴን ለብቻዬ እንከባከባለሁ፣ የወር አበባ ላይ መሆኔንም የቅርብ ሰዎች ያዉቃሉ፡፡ ከትልቁ ቤት ሥራ ካለ ያግዙኛል፣ ሌላ የውጪ ሥራ ካለኝ እኔ እሠራለሁ፡፡ በወር አበባ ጊዜ የኛ ሴቶች ያርፋሉ፡፡ አትሳቅብኝ እንጂ በኛ ብሔረሰብ ሴቶች የሥራ ጫና አለብን፣ የወር አበባ ግን ያሳርፈናል፡፡ አንዳንዴ ሲደክመኝ ቢመጣልኝ እላለሁ በልቤ (ሳቅ.......) ፡፡ (ወ/ሪት ማሙሻ አቫቢ ቃ.መ. 1፤3-5)

በተመሳሳይ ገበያ መሐል የተገኘችውን ወጣት አሁን እዚህ ያለሽበት የወር አበባ ቢመጣ ታፍሪያለሽ? ስትባል ‹‹ (ሳቀች) ለምን አፍራለሁ? አላፍርም ግን በምን ልሸፍነዉ ብዬ ደንገጥ እላለሁ፡፡ ቆሻሻህን ማንም እንዲያይብህ አትፈልግም፡፡ በተረፈ ለኛ ለሴቶች የማይቀር የወር እንግዳችን ነዉና እንጠብቃለን፡፡›› በማለት ፈገግታ በተሞላበት ስሜት መልሳለች፡፡ (ወ/ሪት ሙሉ ዋድሞ፡ቃ.መ. 1፤9)

## 5.5. የድግትስ ጋህጃ ማኅበራዊ ፋይዳ

በጉሙዝ ማኅበረሰብ ዘንድ የሚከወነው የመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ አቀባበል ሥርዓት ክወና ከሚያበረክታቸው ፋይዳዎች መካከል አይነኬና አይነገሬ የሆነውን ርዕሰ ጉዳይ ሰብሮ ጉዳይ በማድረግ የእርስ በርስ ግንኙነትን ማጠናከር እና ማኅበራዊ ትስስርን ማጥበቅ ነው፡፡ ከማኅበራዊ ትስስሩ ላለመገለል ሲሉ ለሥርዓተ ክዋኔው ይተጋሉ፡፡ በተለይ ወጣቶች እርስ በርስ የሚያደርጉት ጨዋታ ያሰባሰባቸውን የጋህጃ (የወር አበባ) ጉዳይ አስረስቶ በፍቅር እና በአንድነት ያስተሳስባቸዋል፡፡ ሥርዓቱን አለመከወን አይቻልም፡፡ የሚፈፀመው ሥርዓት ብዙ ወጪ አይጠይቅም፡፡ የተለዬ ለቤተሰቡ የሚከብድ ነገርም የለውም፡፡ ድኃ ከሆኑ እንኳ በዶሮ ብቻ መጨረስ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ ለምን ብለው ከባሕላዊ ሥርዓቱና ከማኅበረሰቡ መልካም እሴት ያፈነግጣሉ? ሥርዓቱን ላለመፈፀም ምንም ዓይነት ምክንያት የላቸውም፡፡ ‹‹አንተ እንዳልከው ሥርዓቱ ባይፈፀም ማኅበረሰቡ ከማኅበራዊ አገልግሎት ያገሏቸዋል፡፡ ልጅቱን ከጓደኞቿ በታች በማሳነሳቸው ጉረቤቱና ሽማግሌዎቹ ይወቅሷቸዋል፣ ያገሏቸዋል፣ ሰርግና

ለቅሶ አይጠሯቸውም፣ ቅርጫ ስጋ ላይም አያሳትፏቸውም፣ ደቦ ሥራ ላይም ይነጠላሉ፡፡ ምን ይፈጠራል ላልኸው ትታመማለች፣ ከታመመች ደግሞ እሷን ለማንፃትና ለማዳን የፍየል ወይም የደሮ መስዋዕት ለአምላክ ይቀርባል፡፡ እርጥብ ቅጠል ከወንዝ መጠ በውኃ እየተነከረ ትረጫለች፤ በምራቅ እትፍ! እትፍ! እየተባለ ትነፃለች ከበሽታዋም ትድናለች፡፡›› (ተ.ቡ.ው. 1፤8-10)

ከማኅበረሰቡ ላለመነጠል፣ ከፈጣሪም ላለመጣላት ሲባል ሥርዓተ ክወናው በብሔረሰቡ ዘንድ እንደ ግዴታ ሆኖ በደስታ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ በዚህም ማኅበረሰቡ የክወናው ፋይዳ ተጠቃሚ ይሆናል ማለት ነው፡፡ እርስ በርስ ይቀራረባሉ፣ ይፋቀራሉ፣ ይተዛዘናሉ፤ ከዚህስ የሚበልጥ ማኅበራዊ ፋይዳ ከወዴት ይገኛል? የአሂጸዋ ጓደኞች የወር አበባ ያየችውን ልጅ ይዘው ለመታጠብ ወንዝ ይሄዳሉ፡፡ በጀሪካን ቀድተው ቤት ውስጥ አይታጠቡም፡፡ ‹‹አንተ እንዳልኸው እቤት ቢታጠቡ ምንም ላይሆን ይችላል፤ …… ከቤት ተነስተው ወንዝ እስኪደርሱ፣ እየተጣጠቡ እና ሲመለሱ የሚጫወቱት ጨዋታ፣ የሚያወሩት ቁም ነገር፣ የእርስ በርስ ፍቅራቸውን ከፍ ሲያደርገው አይታይህም? … ፡፡›› (ተ.ቡ.ው. 1፤12)

የአካባቢው ማኅበረሰብ በመንደራቸው ካሉ ወጣቶች ውስጥ የአንዱ ቤተሰብ ልጅ ለመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ እንዳየች ሲሰሙ ደስ ይላቸዋል፡፡ ምክንያቱም በሷ ስም ለመገናኘትና ለመጨዋወት ስለሚያበቃቸው ነው፡፡ ይህ በራሱ ማኅበራዊ ፋይዳ ያለው ምክንያት እየፈለጉ ለመጫወት ለመገናኘት መሻት በማኅበረሰቡ ዘንድ እንዳለ ያመላክታል፡፡ በጉርብትና የሥርዓቱ ተካፋይ የሆኑት ጎልማሳ እና በክወናው ላይ ሚና የነበረው ወጣት ‹‹ያዉ ደስ ይላል፤ መቼ አደገች በማለት እንደነቃለን፡፡ ለእናት አባቷ እንኳን ደስ አላችሁ እንላለን፡፡ ሌላ አገር ያሉ ጓደኞቻችን ገበያ ስንገናኝ የደረሰች ልጅ እኛጋ እንዳለችም እናወራለን፡፡ (አቶ ጊሳ ዝማቻ፡- ቃ.መ. 3፤1) እኛ በጣም ደስ ይለናል፤ ለመዝፈን ድግስ ለመብላት እንቸኩላለን፡፡ ለልጅቱም እንኳን ደስ አለሽ! ደስ ብሎናል እንላታለን፡፡ ከዛ በኋላ እንደ ልጅ ሳይሆን የምናያት እንደ ትልቅ ሴት ነው፡፡ ደግሞ እናከብራታለን፡፡ የኛ ዘር ሁሉ በሷ ይቀጥላልና እንደ መሬት እናከብራታለን፡፡ (ወጣት አዲሱ ንጉሴ፡- ቃ.መ. 3፤4) ብለዋል፡፡

ማኅበረሰቡ ለሥርዓቱ ብቻ ሳይሆን ለባለቤቱም ክብርና ፍቅር እንዲሁም የተለዬ እንክብካቤ ያደርጋል፡፡ ከምትቀመጥበት ወንበር ላይ እንኳ በፍጹም ከሷ በስተቀር ማንም በድፍረትም ይሁን በመናቅ አይቀመጥም፡፡ ለሥርዓቱ የሚታረደውን ፍየል እንኳ ከተሠራ በኋላ ጥርስ አውጥቶ መብላት ከሚችል ሕጻን ጀምሮ እስከ ሽማግሌ ድረስ እኩል ነው የሚያካፍሉት፡፡ ይህም የሚያሳዬው ማኅበራዊ ትስስራቸው የጠበቀ፣ አኗኗራቸው በጋራ የሆነ፣ ለማኅበራዊ

ፍትህና ሥራ በጋራ የሚተጉ መሆናቸውን ነው፡፡ ‹‹ልጅቷ እኮ ንግስት ናት፤ ወንበሯ የሷ ብቻ ነው፤ ….. በልጅቱ ወንበር የሚቀመጥ፤ እንኳን ወንድ፤ ሴት ጓደኛዋም ብትሆን ልጅቱ የምትረዳው እንደናቋትና ጥላቻቸውን እንደገለፁላት ነው፡፡ ይሄ ደግሞ የቁጣ ምላሽ ከፈጣሪም፣ ከወንበሩ ባለቤትም ያስከትላል፡፡ ሌሎች ጓደኞቿም ዝም አይሉም፡፡›› (ተ.ቡ.ው. 1፤15)

ለክብሯ የሚታረደውን ፍየል ከተሰራ በኋላ ስጋ መብላት ከጀመረ ህፃን እስከ ትልቁ ሽማግሌ ድረስ እኩል ነው የሚያካፍሉት፡፡ ‹‹እንኳን ስጋ ዱባም ቢሆን፣ ገንፎም ቢሆን፣ በኛ ባሕል እኩል ነው የምንካፈለው፡፡ ትንሹ ከበቃውና ከተረፈው ለወደደው ይጨመርለታል እንጅ እኛ ያለውን እኩል ማካፈል ባህላችን ነው፡፡ የተመጋቢው ሰው ሆዱ ሰፋ ወይም ጠበበ እኛን አያገባንም፡፡ የኛ ድርሻ እኩል ማካፈል ነው፡፡ ከተከፋፈልን በኋላ እንግዳ ቢመጣ ከሁላችንም ተዋጦ የድርሻው ይሰጠዋል እንጅ መጠባበቂያ ነገር ለነገ ብለንም አናስቀምጥም፡፡›› (ተ.ቡ.ው. 2፤6)

## 5.6. የድግትስ ጋህጃ ሃይማኖታዊ ዕሳቤ

የሃይማኖት ምንጭና መገኛ መለኮታዊነት ነው። ሃይማኖት ከሰው ልጅ ትክክለኛና ጤናማ ተፈጥሮ ጋር የሚጣጣም ነው። ‹‹ሃይማኖት የሚለው ቃል ‹‹አመነ›› ከሚለው የግእዝ ግስ የተገኘ ሲሆን ከእርሱም እምነት /ሃይማኖት/ የሚል ስም ይወጣል፡፡ ትርጓሜውም ማመን፣ መታመን፣ በፅኑ ተስፋ መፅናት ማለት ነው፡፡›› (ትንሳኤ ግዕዝ ገፅ 47) ክወናዎች ማኅበረሰቡ እምነቱን፣ አመለካከቱን፣ ብልሃቱን፣ እውቀቱን…. የሚቀርፅባቸው እና የሚያስተላልፍባቸው መንገዶች ናቸው፡፡ ከተግባራቸው በተጨማሪ ሃይማኖታዊ መልዕክት ማስተላለፊያም ናቸው፡፡ በማለት (Bronner) ያስረዳሉ፡፡

እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ብሏል፡- ‹‹ከግብፅ ምድር ከባርነት ያወጣሁህ እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ፡፡›› (ኦ.ዘዳ 5፤ 1-6)፤ አላህ (ሱ.ወ.) ሙሳን እንዲህ ብሏል፡-‹‹…. ባንተ ላይም ያልተረክናቸውን መልክተኞች እንደላክን ላክንህ። አላህም ስለሃይማኖቱ ሙሳን ማነጋገርን አነጋገረው።›› [አል ኒሳእ፡163-165]፤ ጉሙዞችም በልባቸው በተጻፈው የእምነት መጻሕፍት እንዲህ ይላሉ፡- አምላካችን፣ ፈጣሪያችን ሙሳ ነው፤ ሙሳ ይጠብቀናል፤ በማለት በማመን፣ በመታመን፣ በጽኑ ተስፋ በመፅናት በልባቸው ሰሌዳ በተጻፈው ሕግ ይመራሉ፤ ትእዛዛቱን ይፈጽማሉ፡፡

በጉሙዝ ብሔረሰብ የድግትስ ጋህጃ ሥርዓት ክወና የሚፈፀመው በእምነታቸው ስለሚደገፍ፣ በፅኑ ተስፋም ሃይማኖታዊ ጥቅም ስለሚያገኙበት ነው፡፡ ተዳፍረው ባይፈፅሙት እንኳ ቅጣቱ እንደሚደርስባቸው ስሚያምኑ ነው፡፡ ስለወር አበባ ካላቸው ማኅበረሰባዊ አመለካከት ጀምሮ እስከ መደምደሚያው ክዋኔ የሙሳ ትዕዛዝ የማይጠበቅበት የክዋኔ ቦታ የለም፡፡ የወር አበባ ለጉሙዝ ብሔረሰብ ምን ዓይነት ትርጉም እንዳለው ሲገልፁ፡- ‹‹ጋህጃ በኛ መጥፎ አይደለም፤ እርግማንም እርኩሰትም አለው ብለን አናምንም፡፡ ነገር ግን ከሰገራ በላይ የምንፀየፈው መጥፎ ቆሻሻ ነው፡፡ ቆሻሻ ያየች ሴት የነካቸው እቃ ሁሉ ቆሻሻ ይሆናል፤ በዚህም አምላክ ይቆጣል ብለን እናምናለን፡፡ አምላክ (ሙሳ) ንፁህ ነው፤ ቆሻሻም አይወድም፤ እኛም ቆሻሻ አንወደም፡፡ በተለይ ጋህጃ ሲሆን ደግሞ ሴት ንፁህ እስክትሆን ሥራ እንዳትሠራ ይደረጋል፡፡ … ጋህጃ ከሰውነት ሲወጣ መጥፎ ሽታ አለው፤ ሲታይም ደስ አይልም፡፡ ስለዚህ ለሌሎች አእምሮ ጤንነት፤ ለኛም ደኅንነት በዕረፍት ተቀብለን እናፀዳዋለን፡፡ ጋህጃ ለኛ ኩራት ነው፤ መውለድ እንደምንችል የሚያሳውቀን የደስታ ምልክት ነውና ደስ ይለናል፡፡ አናፍርበትም ደሞ እንኮራበታለን፡፡ ፈጣሪ ለኛ ለሴቶች የሰጠን የእናትነት ፀጋ ምልክት ነው ፡፡›› (ተ.ቡ.ው. 1፤6)

‹‹ጋህጃ (የወር አበባ) እርኩስ ነው ቆሻሻ? ወይስ መርገም ነው ፀጋ?›› በማለት ጥያቄ የቀረበላቸው ‹‹ጋህጃ ቆሻሻ ነዉ እንጂ እርኩስ አይደለም፡፡ ለኛ ለሴቶች ብቻ የተሰጠ ፀጋ እንጅ እርግማን አይደለም፡፡›› (ወ/ሮ ሞጋካ ንጉሴ ቃ.መ.2፤8) በማለት መልሰዋል፡፡ ይህ ሃይማኖታዊ ዕሳቤያቸው ከክርስትና ሃይማኖት አተረጓጎም ከእስላማዊ አስተምህሮ ጋር በአንጻራዊነት ይቀራረባል፡፡

በክርስትና ሃይማኖት የወር አበባ በሴት ተፈጥሮ ወስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የመጣው በገነት ውስጥ በሔዋን የጥፋት እርግማን ምክኒያት እንደሆነ የሃይማኖት መጻሕፍት ይጠቁማሉ፡፡ ‹‹ወበከመ አድመውኪያ ለእንትኩ ዕፅ ከማሁ ድምዊ ለለወርኁ፤ ደመ ዕፀ በለስን አፍስሰሻልና ደምሽ በየወሩ ይፍሰስ!›› ሲል እግዚአብሔር ፈረደባት ይላል፡፡ (ኩፋሌ ትርጓሜ 4÷17 እስከ ፍጻሜ እና ዘፍጥረት 3÷1-19) የወር አበባን በሴት ልጅ ተፈጥሮ ወስጥ ያመጣብን ኃጢአት ወይም/እና ሕግን መተላልፍ ነው፡፡ ይህ ተፈጥሯዊ ክስተት በዘመነ ብሉይ (ኦሪት) የእርኩሰት እና የመርገም ምልክት ነበር፡፡ የወር አበባ ላይ ያለችን ሴት ‹‹በመርገሚ ርኩሰት ሳለች›› እና ‹‹ባለ መርገም ሴት›› በማለት ሲገልፅ፤ ባንጻሩ ደግሞ ከወር አበባዋ ነጻ የሆነችን ሴት ‹‹ከርኩሰቷ ነጽታ›› በማለት የወር አበባ የእርኩሰትና የመርገም ምልክት መሆኑን ይገልጻል፡፡ (ኦ.ዘሌ. 15÷ 19 )

አዳምና ሔዋን በበደሉት በደል ምክንያት የደረሰባቸው እርግማን በልጆቻቸው ላይ ሁሉ መርገም ሆኖ ይኖር ነበር፡፡ የእግዚአብሔር ልጅ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት በዘር ሲተላለፍ የነበረው ኃጢአትና መርገም ሁሉ ተሻረ፡፡ አዳምና ሔዋን ከኃጢአታቸውና ከመርገማቸው ነፃ ወጡ፣ በሰው ልጆች ላይም ተጭኖ የነበረ የሞት ቀንበርና መርገም ተሰበረ፣ ተሻረ፡፡ ‹‹ብሉይ ኪዳን ሲነበብ ያ መጋረጃ ሳይወሰድ እስከዛሬ ድረስ ይኖራልና፤ በክርስቶስ ብቻ የተሻረ ነውና፡፡›› (2ኛ ቆሮ 3፤ 14) እንዲል የነፍስ ሞት ወደ ስጋ ሞት፤ መርገምት ወደ ፀጋ ተቀየረ፡፡ በሐዲስ ኪዳን ቀድሞ መርገምት የነበረው ፀጋ ሆኖ የወር አበባ ተባለ፤ እርኩሰት የነበረው አደፍ (ቆሻሻ) ተባለ፡፡ እርኩሰት ነፍስን የሚነካ ውስጣዊ ሲሆን ካለ ንስሃ አይጠራም፡፡ አደፍ ወይም ቆሻሻ ግን ከማኅፀን ውስጥ ሲወጣ ውጫዊ ገላን (ስጋን) ብቻ የሚያቆሽሽ ሆኗል፡፡ ግዝፈ አካል ላይ ያለ የሚታይና ውኃ የሚያጠራው ነው፡፡ በሴቶች ባህርይ ውስጥ መኖሩ ቆሻሻ አያሰኘውም ነገር ግን እንደ ዛህል (ንፍጥ)፣ ሽንት፣ ምራቅ፣ ዓይነ ምድርና ሌሎችም ከውስጥ ሲወጣ ቆሻሻ ይሆናል፡፡ (ትርጓሜ አዕማደ ምስጢር) የወር አበባ ላይ ሆና ቤተ ክርስቲያን የማትገባው በቤተ መቅደሱ ሁለት ደም ይፈስ ዘንድ ስለማይገባ ነው፡፡ ይኼውም የክርስቶስ ደም ይፈተታልና ነው፡፡ ስለ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እና ስለ ክርስቶስ ንፅህና ቆሻሻ ነገር ወደ ቤተ ክርስቲያን አይገባም፡፡ ወንድም ቢሆን እንቅፋት ቢመታውና ቢደማ፣ ህልመ ሌሊት ቢታዬው እንዲሁ ነው፡፡

በቅዱስ ቁርሃን እንዲህ ይላል፡- ‹‹ ከወር አበባም ይጠይቁሃል፣ እርሱ አስጠያፊ ነው፡፡ ሴቶችንም በወር አበባ ጊዜ ራቋቸው፡፡ ንፁህ እስከሚሆኑም ድረስ አትቅረቧቸው፡፡ ንፁህ በሆኑም ጊዜ አላህ ካዘዛችሁ ስፍራ ተገናኙዋቸው፡፡ አላህ (ከኃጢአት) ተመላሾችን ይወዳል፤ ተጥራሪዎችንም ይወዳል በላቸው፡፡›› (አል በቀራ፤ 222) በሌላ በኩል በእስልምናው አስተምህሮ በአደም ሴት ልጆች ላይ አላህ እንደፈጠረውና በእርግዝና ጊዜ ፅንስን እንዲመግብ፣ በወሊድ ጊዜ ወተት እንዲሆን እና ከእርግዝናም ከወሊድም ነጻ በሆኑ ጊዜ ወቅት ጠብቆ እንዲፈስ የተፈጠረ ነው ይላሉ፡፡

‹‹ሐይድ (የወር አበባ ደም) ማለት ሕመም ወይም ቁስለት ሳይኖር በየተወሰኑ ጊዜያት ከሴት ማኅፀን የሚወጣና የሚፈስ ማለት ነው፡፡ ይህ ደም የአደም ሴት ልጆች ላይ አላህ (ሱ.ወ) የፈጠረው ሲሆን በእርግዝና ወቅት ፅንስን ይመግባል፣ ከውልደት በኋላ ደግሞ ወደ ወተትነት ይቀየራል፡፡ ሴቷ በእርግዝና ወይም በማጥባት ላይ ካልሆነች ይህ ደም የሚሄድበት ስለማይኖረው በየተወሰነ ጊዜው ከማኅፀን ይወጣል፤ ይህም የወር አበባ ተብሎ ይታወቃል፡፡ የወር አበባ የሚከሰተው ከዘጠኝ ዓመት ጀምሮ እስከ ሃምሳ ዓመት ባሉ ሴቶች ነው፡፡›› (ሷላህ

23) የወር አበባ የምታይ ሴት በእስልምና ሃይማኖታዊ ትዕዛዝ መሰረት አትጾምም፣ መስጅድ አትገባም፣ ቅዱስ ቁርሃኑን መንካት አትችልም፣ ሶላት መስገድ አትችልም፣ እንዲሁም ከግብረ ስጋ ግንኙነት ትከለከላለች፡፡ ይህ ሃይማኖታዊ ትዕዛዝ በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ እስከአሁን የሚተገበር ፅኑ ትዕዛዝ ነው፡፡ ይህም የሚሆነው አምላካዊ ትዕዛዝ ስለሆነ እና እስላማዊት ሴትም የተሰጣትን፣ የተፈቀደላትን እንጅ ለሷ ያልሆነውን ሁሉ ስለማትፈልግ ነው፡፡ የወር አበባ ቆሻሻ ስለሆነ ሶላት ያናጥባል፤ ስለዚህም ንፁህ ሲሆኑ በታዘዛችሁት ቦታ ቅረቧቸው ይላል፡፡ አላህ (ከኃጢአት) ተመላሾችን ይወዳል፤ ተጥራሪዎችንም ይወዳል፤ በማለት ንፁህ የሆኑትን እንደሚወድ ያጠይቃል፡፡ ወንድም ቢሆን እንቅፋት ከመታው ሱሪው ላይ ሽንት ከተንጠባጠበ ሶላቱ ይነጅሳል፡፡ ስለዚህ ዋናው ቁምነገሩ የንፅህና ጉዳይ እንጅ ኃጢአተኛ የመሆን እና ያለመሆን ጉዳይ አይደለም፡፡ ስለዚህም በሐይድ ወቅት የማትሰግደውን ስግደት አላህ አይጠይቃትም፡፡

የድግትስ ጋሀጃ ሥርዓት ክወና ባይፈፀም ወይም ቢቀር እንዲሁም ከትንሿ ጎጆ ቤት ወጣ ትልቅ ሰው ብታናግር የሚፈጠረው፣ ከትንሿ ጎጆ ቤት የምትገባበትና ሥርዓተ ክወናውን መተዉ የማይቻልበት እንዲሁም የወር አበባ ላይ ሆና ሥራ የማትሠራበት ምክንያት ከፈጣሪ ሙሳ ጋር የተያያዘ የጉሙዝ ባሕላዊ እምነት ምክንያትና ውጤት ነው፡፡ ‹‹ሥርዓቱ ካልተፈፀመ ልጅቱ የሞራል ድቀት ይደርስባታል፡፡ ከጓደኞቿ ተለይታ ፈዛዛ ትሆናለች፡፡ ሠርታ አይሳካላትም በሕይወቷ ሁሉ ውድቀት ይበዛባታል፡፡ የወር አበባዋ ደስታ ሳይሆን ሰቀቀን ይሆንባታል፤ ሲጠሯት እንኳ ቶሎ አትሰማም፤ ፍዝ ትሆናለች፡፡ በኛ እምነት እና ከዚህ ቀደም ሆኖ ያየነው እንዲሁም የምናውቀው መሐን ትሆናለች፡፡ ካለ እድሜዋም ትሞታለች፡፡ ይህን ስለሚያውቁ በድፍረትም ቢሆን አያደርጉትም፡፡ (ተ.ቡ.ው. 1፤3-4)፤ ትልቁ ቤት ንፁህ ነው፡፡ አምላካችን ሙሳም በትልቁ ቤት ከኛ ጋር ይኖራል ብለን እናምናለን፡፡ እሱ እንደ ሰው አይደለም፤ ለሰው የማይታይ ሁሉ ይታዬዋል፡፡ ስለዚህ ቆሻሻ ጋሀጃ ስታይ እንዳይቆጣት ንፁህ እስክትሆን በጎጆ ቤት ትቆያለች፤ ይህም የኛ እምነት ሥርዓት ነው፡፡ አምላክ ንፁህ ነገር ይወዳል ቆሻሻም ይፀየፋል፡፡›› (ተ.ቡ.ው. 2፤4)

ጋሀጃ በራሱ ህመም አለዉ፤ ትልቁ ቤት ሙሳ ስላለ ቆሻሻ ነገር አይወድም፡፡ ከምንበላዉ ከምንጠጣዉ ነገር ሁሉ ይጋራል፡፡ ስለ ሙሳ ንጽህና ትልቁ ቤት ዉስጥ ንጹህ ነገር ነዉ የሚፈለገዉ፡፡ ተሳስቼ እንኳን ሠርቼ ባስገባ በሽታ ቁስል በሰዉነታችን ይወጣል፡፡ (ወ/ሮ ሞጋካ ንጉሴ፡- ቃ.መ. 2፤7)፤ ሥርዓቱን መተው በፍጹም አይቻልም፤ አይታሰብም፡፡ ከሙሳ ጋር መጣላት የሚያስብም፣ የሚፈግልም የማኅበረሰባችን አባል የለም፡፡ (አቶ ጊሳ ዝማቻ፡-

ቃ.መ. 3፤2) ወንዝ ሄደው ታጥበው እርጥብ ቅጠል፣ እንጨት ይዘው እየዘፈኑ የሚመጡት ወንዙ ያነጻናል፣ ከህመም ያድነናል ብለው በማመን ነው፡፡ በጉሙዝ ብሔረሰብ መታጠብ የመንጻትና ነፃ የመውጣት ምሳሌ ነው፡፡ (ተ.ቡ.ው. 1፤11) የታረደውን ዶሮ ተራምዳ ወደ ትልቁ ቤት የምትገባው ከአሁን ጀምሮ ንፁህ ነሽ ፤ ቆሻሻው ደምሽ በንፁህ ደም ተተክቷል ፤ ፈጣሪ ሙሳም በፍቅር ያይሻል ለማለት ነው፡፡ (ተ.ቡ.ው. 1፤23)

ልጅቱ ከወር አበባ መንፃት በኋላ ለቤቱ እንግዳ ናት፡፡ ከሙሳ ጋር የቆየችው እናቷ ናት፡፡ ስለሆነም ከዚህ በኋላ በኃላፊነት ስራዎችን እንድትሰራ የቤቱን እቃዎች ሁሉ ታሳያታለች፡፡ እጇን ይዛ ወፍጮ መፍጨት፣ እህል መውቀጥ፣ ቡና ማፍላት፣ ገንፎ ማገንፋት ታስጀምራታለች፡፡ ከቤተሰቡ፤ ከማኅብረሰቡ ከፈጣሪ፣ ከእቃዎችና ከሥራው ጋር ታስተዋውቃታለች፡፡ ከዚያ በኋላ ያለፍርሃትና ያለኃፍረት መግባት መውጣት እንደልቧ መሥራት ትጀምራለች፡፡ (ተ.ቡ.ው. 1፤24)

የሥርዓቱ አፈፃፀም በሃይማኖት፣ በጎሳ ወይም በሀብት የተለዬ አፈፃፀም ይኖረው እንደሆነ የተጠየቁት ወንድ ተተኳሪ የቡድን ተወያዮች፡- ‹‹ስርዓቱ የጉሙዝ ባሕል ነው፤ የጉሙዝ አምላካችን ሙሳ ነው ፡፡ ሙሳ ይሄን ይወዳል፣ ይሄን አይወድም፤ ይሄ ኃጢአት ነው፤ ይሄ ፅድቅ ነው፤ የሚለው በልባች ነው፡፡ በሃይማኖት የተለዬ ክዋኔ የለም፡፡ … ስርዓቱን መፈፀም አይተውም ብዬ አምናለሁ፡፡ ምክኒያቱም ጉሙዝ ናቸው፡፡›› (ተ.ቡ.ው. 2፤2)

## 5.7. የድግትስ ጋሀጃ ሥርዓተ ጾታዊ ምልከታ

ሥርዓተ ፆታ የወንዶችና የሴቶች ኅብረተሰባዊ ሚና፣ ግንኙነት፣ ጥቅምና ደረጃ የሚወሰንበት ሥርዓት ነው፡፡ በኅብረተሰብ ባሕል፣ አስተሳሰብ፣ እምነት፣ የአኗኗር ስልትና የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ የሚገለጥና የሚገነባም ሲሆን የርዕዮተ ዓለም አካልም ሆኖ አመለካከታቸውንና ዕሴቶቻቸውን ይወስናል፡፡ ሥርዓተ ፆታ በተረት፣ በሐቲቶች፣ በክወና፣ በቃልና በጽሑፍ መልክ እንደየዘመኑ ደረጃ እየታደሰ እየተጣጣመ ወደ ትውልድ ይሻገራል፡፡ (ተስፋዬ መለሰ Sheehan 2004፤11) ጠቅሶ እንደገለፀው፡፡

ስለሆነም በድግትስ ጋሀጃ ሥርዓተ ክወና ምንም እንኳ የመከወኛ ጉዳዩ የሴቶች የተፈጥሮ ጉዳይ ቢሆንም፤ ወንዶች በክወናው ላይ ተሳታፊና ታዳሚ ሆነው በባለቤትነት ይታያሉ፡፡ ሴቶችም እንደየተልዕኳቸው የራሳቸውን ሚና ይዘው ይከውናሉ፣ ይታደማሉ፡፡ ‹‹ጋሀጃ (የወር አበባ) አቀባበል ሥርዓተ ክዋኔ ወቅት ወንዶች የራሳቸው ሚና አላቸው፡፡ ለምሳሌ፡- አባቷ ለስርዓቱ የሚሆነውን ዶሮ፣ ፍየል፣ አረቄና የቦርዴ እህል ገዝቶ ያቀርባል፡፡ የምትቆይበት ጎጆ

ያረጀ ወይም ያልተሟላ ነገር ካለው እሱን ቶሎ ጠግኖ ያሟላል፡፡ ወጣት ወንዶችም የራሳቸውን ሚና አላቸው፡፡ የልጃገረዷን የወር አበባ ማዬት እንደሰሙ፤ ‹‹እሰይ ደረሰችልን›› ብለው ደስታቸውን በጨዋታ ይገልፃሉ፡፡ በተለይ በሰባተኛው ቀን ሴቶች ወንዝ ታጥበው፣ እርጥብ ቅጠል ይዘው፣ እየዘፈኑ ሲመለሱ፤ ወንዶች ከመንገድ በጨዋታ ይቀበሏቸዋል፡፡ ሴቶችም ወንዶችን አመድ ይረጯቸዋል፤ ሽማግሌ ወንዶችም መመረቅ፤ መልካም መመኘት የስርዓቱ ሚናቸው ነው፡፡›› (ተ.ቡ.ው. 2፤1)

ማኅበረሰቡ ለሴቶችም ከጓዳ ሥራ ባሻገር በክወናው ላይ ለይቶ የሚሰጣቸው ኃላፊነት አለ፡፡ እናቷና አክስቷ ልጃቸውንና ጓደኞቿን ይመርቃሉ፡፡ ወጣት ወንዶችና ሴቶች የየራሳቸውን ሚና በክወናው ላይ ይወጣሉ፡፡ በሥርዓቱ አባቷ የራሱ ድርሻ አለው፡፡ ‹‹ጋሀጃ (የወር አበባ) ካየችበት ቀን ጀምሮ እንደሰማሁ የለበሰችዉ ልብስ የወር አበባ ነክቶ ከሆነ አዲስ ልብስ አመጣለሁ፡፡ ለሥርዓቱ የሚሆነዉን የቦርዲ መሥሪያ እህል፣ ዶሮ፤ ፍየል አቀርባለሁ፡፡ ወንድ ሽማግሌዎችን የመጨረሻዉ እለት ጠርቼ ልጄን አስመርቃለሁ፤ እኔም እመርቃታለሁ፤ ይሄ የኔ ሥራ ነዉ፡፡›› (አቶ አቫቢ ቱሳ፡- ቃ.መ. 2፤3)

በጉሙዝ ብሔረሰብ ማኅበረሰብ ሠራሽ የወንድ እና የሴት ሥራ ቢኖርም፤ ሥርዓተ ክወናው የሴቶች ተፈጥሯዊ ጉዳይ ቢሆንም፤ ወንዶች የራሳቸውን ሚና ጠብቀውና አክብረው ይከውናሉ፡፡ ሴቶችም ወንዶች በነሱ ጉዳይ ተሳታፊ በመሆናቸው ደስተኛ ሲሆኑ በምልከታ ለማዬት ተችሏል፡፡ የራሳቸውን ሚናም በኩራት ጠብቀውና አክብረው ይከውናሉ፡፡ በሥርዓተ ክወናው የትኛውም ጾታ እኔ ሥራ በዛብኝ፣ እኔ አነሰኝ ብለው የመብትና የግዴታ ጉዳይ አያነሱም፡፡ ሁለቱም ጾታዎች ተከባብረው፣ ተዋደው እና ተደማምጠው ሥርዓቱን እስከፈፀሙ ድረስ ሥርዓተ ጾታ ሚዛን ጠብቆ ዕሴቶቻቸውን ያበለፅጋል፡፡

## 5.8. የድግትስ ጋሀጃ እንስታዊነት (ሴትነት) ምልከታ

የእንስታዊነት ጽንሰ ሀሳብ በሥርዓተ ክወናው ውስጥ ሴትነትና የሴት መገለጫ እንዴት እንደተገለፀ የምናይበት መንገድ ነው፡፡ ምንም እንኳ የጥናቱ ጉዳይ የሴቶች ሥነ ተፈጥሯዊ ጉዳይ ቢሆንም በክወናው የሴቶች ተሳትፎና በማኅበረሰቡ ዘንድ የሚሰጠውን እንድምታ ለመተንተን አገልግሏል፡፡ በክወናው የጉዳዩ ባለቤት ሴት ብትሆንም በክወናው የሚሳተፉ ወንዶች ሁሉ ለሴት ልጅ ያላቸውን ክብር፣ ፍቅር፣ አመለካከትና አስተሳሰብ በትጋት ሲገልፁ ይታያል፡፡ የወር አበባ ያየችው ልጃገረድ የምትቀመጥበት ወንበር (ተጉ ጋሀጃ) ላይ ወንዶች አይቀመጡም፡፡ ‹‹ልጅቷ እኮ ንግስት ናት፤ ተጉ ጋሀጃ (ወንበሯ) የሷ ብቻ ነው፡፡ በኛ ልቡና የከበረና የተከበረ ስለሆነ ማንም አይቀመጥበትም፡፡ .... እንኳን ወንድ፤ ሴት ጓደኛዋም ብትሆን ልጅቱ የምትረዳው እንደናቋትና ጥላቻቸውን እንደገለፁላት ነው፡፡ ይሄ ደግሞ የቁጣ ምላሽ ከፈጣሪም፣ ከወንበሩ ባለቤትም ያስከትላል፡፡›› (ተ.ቡ.ው. 1፤15)

በጉሙዝ ማኅበረሰብ ዘንድ ሴት ንግስት ናት፤ ጉልበት ያለውም ይሁን ድፍረት ያለው ማንም እኩል ክብርና ፍቅር ይሰጣታል፡፡ ባሕል ሠራሹን የሥራ ክፍፍል በማፈንገጥ የወር አበባ ለመጀመሪያ ጊዜ ላዬችው ወጣት በማኅበረሰቡ ለወንድ ብቻ የተሰጠውን ደሮ የማረድ ኃላፊነት ይሰጧታል፡፡ ‹‹በሕይወት ዘመኗ ለመጀመሪያም፣ ለመጨረሻም ጊዜ ደሮ የምታርደው በዚህ ለመጀመሪያ የወር አበባ ባዬችበት ጊዜ በሚከወነው ሥርዓት ነው፡፡ የክብሯን ከፍታ ለማሳዬት ተብሎ ነው በዚህ ዕለት የምታርደው፡፡ እሷ ስታርድ ወንዶች በአድናቆት ያጨበጭባሉ፤ ጎበዝ ጀግና ይሏታል፡፡ ከዚህ ቀን በፊት አላረደችም፣ ወደፊትም ባሏ እንጅ እሷ አታርድም፡፡›› (ተ.ቡ.ው. 1፤19)

የወር አበባ ላይ ያለች ሴት በሚገባት ቦታ ሆና እረፍት እንድታደርግ፤ ሥራ እንዳትሠራ ይደረጋል፡፡ በምርቃቱ ላይም ለምለም እንደትሆን፣ ዘሯም እንዲበዛ፤ በፍቅሯ ሁሉን እንድትገዛ፤ የሚጠላት እንዲያፍር፤ ተወዳጅ እንድትሆን እናቷ ትመርቃታለች፡፡ አክስቷም ትከሻሽ ጠንካራ፣ ሆድሽ ሰፊ ይሁን፣ ነገር የምትችይ ብርቱ ያድርግሽ፣ ለዐይንሽ ማረፊያ፣ ለጥርስሽ ደስታ ይብዛልሽ በማለት ትመርቃታለች፡፡ አባቷም ፈጣሪ መልካሙን ይስጥሽ፤ ከክፉ ነገር ሁሉ ያውጣሽ፤ እኛ እንደመረቅንሽ ፈጣሪ ይመርቅሽ፣ ሀሳብሽን ፈጣሪ ይሙላው፤ ከጓደኞችሽ እኩል ሁኝ፣ ቤት ያዥ፤ የሚያገባሽ የተባረከ ይሁን፤ ለዘርሽ ሴት ልጅ፣ ለኩራትሽም ወንድ ልጅ ውለጅ፤ የነካሽው ይባረክ፤ የዘራሽው ይለምልም፤ የዳሰስሽው ይፈወስ፤ ያቦካሽው ይበርክት፤ ትንፋሽሽ አይቀዝቅዝ በማለት ይመርቃታል፡፡ (ተ.ቡ.ው. 2፤7)

ሴት በጉሙዝ ብሔረሰብ እንደ መሬት ትከበራለች፤ መሬት የሰጧትን እንደምታበቅል ሴትም የዘራችን ፍሬ ማያ ናት ይላሉ፡፡ ‹‹ከዛ በኋላ እንደ ልጅ ሳይሆን የምናያት እንደ ትልቅ ሴት ነው፡፡ ደግሞ እናከብራታለን፡፡ የኛ ዘር ሁሉ በሷ ይቀጥላልና እንደ መሬት እናከብራታለን፡፡›› (ወጣት አዲሱ ንጉሴ፡- ቃ.መ. 3፤4) ብለዋል፡፡ሽማግሌውም ማኅበረሰቡን ወክለው የመልካም ምግባር ባለቤት፣ ሰርታ የምታፈራ፣ ታዛ የልብ የምታደረስ፣ የበጎ ነገር ሁሉ ምንጭ፣ እድለኛ እንድትሆን ለጀርባሽ ክብር ለልብሽ ደስታ የሚሆኑ ልጆች ይስጥሽ በማለት ይመርቋታል፡፡ (ቃ.መ.3፤3) በጥቅሉ የድግትስ ጋሀጃ ሥርዓተ ክወና እንስታዊነት የሚፈከርበት፣ ለሴት ልጅ ክብርና ፍቅር የሚታደልበት፣ ሥነ ልቦናዊ ከፍታ የሚሠራበት፣ ማኅበራዊ ትስስር የሚጠናከርበት፣ ሃይማኖታዊ ዕሳቤ የሚፀናበት፣ ሥነ ተፈጥሯዊ ነጻነት የሚታወጅበት ከበራ ነው፡፡

# ምዕራፍ ስድስት

## 6.ማጠቃለያ

የጉሙዝ ብሔረሰብ አባላት ማኅበራዊ ሽግግር ከሚያደርጉባቸው ከበራዎች መካከል ለመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ ላዬች ሴት ልጅ የሚከበረው ሥርዓተ ክወና (ድግትስ ጋህጃ) አንዱ ነው፡፡ ሥርዓቱ ሴት ልጅ ለአቅመ ሔዋን፣ ለጋብቻና ለእናትነት መድረሷን ማብሰሪያ ነው፡፡ በጉሙዝ ቤተሰብ ውስጥ ሴት ልጅ ለመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ ማዬቷ የድግትስ ጋህጃ ሥርዓተ ክወና መከሰቻ አጋጣሚ ሲሆን የሥነ ልቡና፣ የመከወኛ ቦታ፣ የሀገረሰባዊ ምግብና መጠጥ፣ የሀገረሰባዊ ቁሶች፣ የሀገረሰባዊ አልባሳትና ጌጣጌጦች ዝግጅት ይደረግበታል፡፡

ከበራው በጥንድና በቡድን የሚከወን ሲሆን፤ ከጉዳዩ ባለቤት እስከ አካባቢው ማኅበረሰብ በሁሉም የዕድሜ ደረጃ ያሉ በከዋኝነት ይሳተፋሉ፡፡ በሥርዓቱ አከዋወን ላይ ተጨባጭና ማኅበራዊ አውዶች ሲኖሩ፤ ከሕጻናት እስከ ሽማግሌ በታዳሚነት ይሳተፋሉ፡፡ የክዋኔውን አጀማመር፣ የሂደቱን አፈጣጠን እና መጨረሻውን የሚያመላክቱ የክዋኔ ጠቋሚዎችም አሉት፡፡

በጥናቱ የመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ አቀባበል ሥርዓት (ድግትስ ጋህጃ)፣ ትዕምርቶች፣ ክዋኔዎች፣ በእድሜ፣ በጾታና በማኅበራዊ ደረጃ እንዲሁም የሥነ ልቦናዊና የማኅበራዊ ፋይዳዎቹ፣ የሥርዓተ ጾታና የሴትነት ምልከታዎቹ እንዲሁም የሃይማኖታዊ ዕሳቤው ተተንትኗል፡፡ በሥርዓተ ክወናው የሚቀርቡ የዘፈን ግጥሞችና ምርቃቶች ይዘት ተፈክሯል፡፡ የጉሙዝ ብሔረሰብ ስለወር አበባ ያለውን አመለካከትና ማኅበራዊ ግንኙነቱን በማብራራት ዓላማውን ለማሳካት ሞክሯል፡፡

የከበራው መገለጫ አስገዳጅነት ያለው፣ ተለዋዋጭ ያልሆነ (ጥብቅ)፣ ታዳሚዎችም ሆኑ ሌሎች ሰዎች በቀላሉ ሊረዱት የማይቻል፣ ውስጣዊና አላስፈላጊ ድግግሞሾች የሚታዩበት እና በተገደበ ጭብጥ የሚከወን ከበራ ነው፡፡ የከበራውን ዓይነት ከአውድ፣ ከይዘትና ከካትሪን ቤል ምደባ አንጻር ለመለየት ተችሏል፡፡

ከአውድ አንጻር በሥነ ልቡና ዝግጅት ቀድሞ የሚታሰብ ቢሆንም የወር አበባ ድንገት ስለሚመጣና ክዋኔውም ቶሎ ታቅዶ ተፈጻሚ ስለሚሆን በአጭር ጊዜ ዕቅድ በዝቅተኛ አውድ የሚፈፀም ነው፡፡ ከይዘት አንጻር የባሕል ሃይማኖት የሆኑ ጉዳዮችን በትዕምርት ስለሚገልፁባቸው፤ ከዋኞች ስለዓለም፣ ስለሰው፣ ስለሴት፣ ስለሕይወትና ስለወር አበባ ያላቸውን ዕተያይ የሚያሳይ ክወና በመሆኑ መንፈሳዊ ከበራ ነው፡፡ እንደካትሪን ቤል የከበራ ዓይነቶች ምደባ ደግሞ ከአንድ ማኅበራዊ የሕይወት ደረጃ ወደሌላ ሲሸጋገሩ እንደሚከበሩ ከበራዎች

ማለትም የወር አበባ ያየችው ልጅ ከልጅነት ወደ አቅመ ሔዋንነት፣ ወደ እናትነት መሸጋገሯ ስለሚታወጅበት የመሸጋገሪያ ከበራ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ በምልከታ፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት እና በቃለ መጠይቅ የተሰበሰቡትን መረጃዎች አሰናስሎ ለመተንተን እንደተሞከረው ሥርዓቱ የመሸጋገሪያ ከበራ ከመሆኑ ባሻገር፤ ማኅበራዊ ግንኙነት የሚጠናከርበት፣ የባሕል ሃይማኖታዊ ሥርዓት የሚፀናበት፣ ለሥነ ተፈጥሮ እውቅና የሚሰጥበት፣ ከወር አበባ ጋር ተያይዞ የሚመጣ ኃፍረት፣ መሸማቀቅ አጠቃላይ ሥነ ልቡናዊ ጫና የሚሰበርበት፣ እንስታዊ የተፈጥሮ ጉዳይ በሆነው የወር አበባ ላይ ወንዶች ጉዳዬ ብለው የሚሳተፉበት፣ ሴት የመሆን የተፈጥሮ ፀጋ ክብርና ልዕልና የሚያገኙበት ከበራ ነው፡፡

## 6.1 አስተያዬት

በሀገራችን ኢትዮጵያ ከሚገኙ ፀጋዎች ውስጥ ብዝኃ ቋንቋ፣ ብዝኃ ባሕልና ብዝኃ ፎክሎራዊ ጉዳዮች በጥቂቱ የሚጠቀሱት ናቸው፡፡ እነዚህን ሀብቶች ይሁነኝ ብሎ በማጥናት፤ በጥናቱ የተገኙ አስተሳሰቦችን፣ አመለካከቶችን እንደ ሀገር ከተገነባንበት የአብሮነት ሥነ ልቡናዊ ስሪት ጋር በማጣጣም ለሀገር ግንባታ መሳሪያነት መጠቀም ጊዜው ከፎክሎሪቶች የሚጠይቀውና የሚጠብቀው ዓቢይ ተግባር ነው፡፡

የፎክሎር ጥናቶች ታትመው ሽልፍ ከማሞቅ ባሻገር፤ ማኅበራዊ አስተሳሰቦችና አመለካከቶች እንደሀገር ተጣጥመው የሀገራዊ ችግር መፍቻ ቁልፍ እንዲሆኑ ለሕገ መንግስት ማሻሻያነት፣ ለፖሊሲ ግብዓትነት፣ ለአዋጅና ለመመሪያ ማስፈፀሚያነት እንዲውሉ ቢደረግ መልካም ይሆናል፡፡

ሀገራችን የመጤ ባሕል ወረራ እየተፈታተናት፤ የነባር ባሕሎች መዋጥ፣ መለወጥና መክሰም ደግሞ በተቃራኒው ግድ የማይሰጣት በመሆኑ፤ መጤ ጎጂ ባሕሎችን ለመከላከል ነባር ባሕላትን አጉልቶ በማውጣትና በማስተዋወቅ ማኅበራዊ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ ቢቻል ጥሩ ነው፡፡

ዛሬ ዛሬ ከትንንሽ እስከ ትልልቅ ከተሞች ውስጥ ያሉ ወጣቶቻችን ‹‹**የአጥር ወፍ አትስማሽ፤**››[13] እና ‹‹**እንሶስላዬ፤**››[14] የሚባሉ ውብ ባሕሎቻችንን ረስተዋል፡፡ በተቃራኒው ደግሞ **ቤቢ ሻወር** (Baby Shower)[15] እና

---

[13] ‹‹የአጥር ወፍ አትስማሽ›› ማለት ድምጽሽ ሳይሰማ በሰላም ተገላገይ ማለት ነው፡፡ ለወሊድ የደረሰች ሴትን ከመውለዷ ጥቂት ቀናት ቀደም ብለው ጓደኞቿ መልካም ምኞታቸውን ለመግለፅ፤ የወለዱ ባለንጀሮቿ ልምዳቸውን ለማካፈልና ስትወልድ የምትመገበውን የገንፎ እህል አዘጋጅተው ለመቅመስ የሚከወን ውብ ባህላችን ስያሜ ነው፡፡ አሁን አሁን ቤቢ ሻወር (Baby Shower) በሚባል መጤ ባህል ተወሯል፡፡

[14] ‹‹እንሶስላዬ› የመጀመሪያ ጋብቻዋን የምትፈጽም ልጃገረድ ከሰርጓ ሶስት ቀናት ቀደም ብሎ እንሶስላ የምትሞቅበት፣ ያገቡ ባለንጀሮቿ ልምዳቸውን፤ ያላገቡ ጓደኞቿ መልካም ምኞታቸውን፣ ደስታቸውን የሚገልፁበት፣ ሥጦታቸውንም ለማበርከት የሚከበር ድንቅ ባህላችን ነው፡፡ የቅርብ ዘመድና ጓደኛ የመጨረሻ ፍቅርና ክብር የሚገለጥበት እንሶስላዬ እየተባለ እየተዘፈነ ክወና የሚፈፀምበት ነበር፡፡ አሁን አሁን ዊዲንግ ሻወር (Weeding Shower) በሚባል መጤ ባህል ተወሯል፡፡

[15] ቤቢ ሻወር (Baby Shower) የሚባለው የምዕራባውያን መጤ ባህል ሲሆን ትርጉሙም አንድ ሴት መውለጃዋ ሲደርስ በጓደኞቿ ሰርፕራይዝ ተደርጋ ኬክ የምትቆርስበት፣ የህጻን ልብስ ስጦታ የምትቀበልበት ዝግጅት ነው፡፡ ኢትዮጵያዊ ለዛ የለውም፡፡ በእንግሊዝኛው እንዲህ ይፈታዋል፡- A baby shower is a party of gift-giving or a ceremony that has different names in different cultures. It celebrates the delivery or expected birth of a child or the transformation of a woman into a mother. ቤቢ ሻወር በተለያዩ ባህሎች ውስጥ የተለያዩ ስሞች ያሉት የስጦታ ዝግጅት የሚከወንበት ሥነ ሥርዓት ነው። ከበራው የሚፈፀመው የአዲስ ልጅ መውለድን በጉጉት በመጠበቅ እና/ወይም የሴቷን ወደ እናትነት መለወጥ ተስፋ በማድረግ የሚፈፀም ነው።

**ዊዲንግ ሻወር** (Weeding Shower)[16] የሚባሉት መጤ የምዕራባዊያን ክዋኔዎችን አለመፈፀም በሕግ ያስቀጣል የተባለ ይመስል፤ እንደሐኪም ትዕዛዝ ከምዕራቡ ዓለም በተቀዳው አፈጻፀም መሠረት እየተከወነ ነው፡፡ ነገ ደግሞ ለመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ ያዬችን ሴት ልጅ ሥነ ልቡና ከፍ ለማድረግ፣ ለሥነ ተፈጥሮ እውቅና ለመስጠት፣ የሽግግር ወቅትን ለማስተዋወቅ፣ የሚውል አጭር ከበራ በራሳቸው ሥነ ልቡናና ባሕል ሰፍተው እንደማይጭኑብን ምንም ዋስትና የለንም፡፡ ስለሆነም በራሳችን ሜዳ፣ በራሳችን ኳስና በራሳችን ዳኞች ምርጥ ተሸናፊዎች እንዳንሆን ይህን የጉሙዝ ብሔረሰብ የመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ ላዬች ወጣት የሚሰጠውን ሥነ ልቡናዊ ከፍታ፣ ማኅበራዊ ትስስርና ሥነ ተፈጥሯዊ እውቅና እንደሀገር በሚመጥን ሥነ ልቡናዊ ስሪት ክወናውን ቀርጾ ማስተዋወቅና ለአገልግሎት ማዋል ይገባል፡፡

እውቅና አግኝቶ መሠረታዊ ዓላማውን እየሳተ ያለውን ‹‹**አበባ አየሽ ወይ፣ ለምለም**››[17] እና ከጉሙዝ ማኅበረሰብ ውጪ ብዙም የማይታወቀውን ‹‹ድግትስ ጋሀጃ›› በሥነ ልቡናዊና በማኅበራዊ ፋይዳቸው በማስተሳሰር ወይም በማዋሐድ፤ እንደሀገር ለመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ የሚያዩ ወጣት ሴቶችን ከጓደኞቻቸው (ከወንዶችና ከሴቶች) ጋር ሆነው ለሥነ ተፈጥሮ እውቅና እንዲሰጡ በሚያስችል መልኩ ማክበር ቢቻል ፋይዳው የጎላ ይሆናል፡፡

በሀገራችን ላለው ቀላል የማይባል የሴት ልጆች በትምህርት ገበታ **መጠነ ማቋረጥ መጨመር**[18] የጉሙዝ ብሔረሰብ የወር አበባ ያየችን ልጅ የሚያክምበት፣ ሥነ ልቡናዋን ከፍ የሚያደርግበት፣ ማኅበራዊ ትስስሯን የሚያጠናክርበት የድግትስ ጋሀጃ ከበራን መጠቀም

---

[16] ዊዲንግ ሻወር (Weeding Shower) የሚባለው የምዕራባውያን መጤ ባህል ሲሆን ትርጉሙም አንድ ሴት ሰርጓ አንድ ቀን ሲቀረው በዋዜማው ጓደኞቿ ተመሳሳይ ልብስ ለብሰው ኬክ እያስቆረሱ እንኳን ደስ አለሽ የሚሉበት ዝግጅት ነው፡፡ ኢትዮጵያዊ ለዛና ወዝ የለውም፡፡ በእንግሊዝኛው እንዲህ ይፈታዋል፡- A bridal shower is a gift-giving party held for a bride-to-be in anticipation of her wedding. The history of the custom is rooted not necessarily for the provision of goods for the upcoming matrimonial home, but to provide goods and financial assistance to ensure the wedding may take place. የሙሽሪት ሻወር ሠርጓን በመጠባበቅ ላይ ለምትገኝ ሙሽሪት የሚደረግ የስጦታ ዝግጅት ነው። ከልምድ እንደሚታወቀው ለጋብቻ የሚሆን የቤት ዕቃዎች እርዳታ ማድረግ ሳይሆን፣ ሠርጉ የሚከናወን መሆኑን በማረጋገጥ፣ በማብሰር የስጦታ እቃዎችን ለማበርከት እና የገንዘብ ድጋፍ ለማድረግ የሚፈፀም ከበራ ነው፡፡

[17] ቀደም ባሉት ዘመናት ‹‹አበባ አየሽ ወይ፣ ለምለም›› እየተባለ በዘመን መለወጫ ሴቶች የሚጫወቱት ዘፈን፤ በአሮጌው ዓመት የወር አበባ ያዩ ልጃገረዶች ተሰባስበው በየቤቱ እየዞሩ የሚዘፍኑት፣ ‹እንኳን ለዓዲሱ ዓመት አደረሳችሁ!› እያሉ እነሱም ቤት ለመስራት፣ ትዳር ለመመስረት፣ መድረሳቸውን የሚያውጁበት እንደነበር ይነገራል፡፡ አሁን አሁን ግን ታሪካዊ አመጣጡ፣ ማኅበራዊና ስነ ልቡናዊ ፋይዳው ተረስቶ ወንዶችም እየዘፈኑት፤ አግብተው የፈቱ ሴቶችና ለአቅመ ሔዋን ያልደረሱ የወር አበባ ያላዩ ሕጻናትም ይዘቱን እየለዋወጡ በመዝፈን እያበላሹት ይገኛሉ፡፡ (ካኽሳይ ገብረ እግዚአብሔር)

[18] እንደዩኒሴፍ 2017 ጥናት በአፍሪካና በኤዢያ አህጉራት 25%፤ በሀገራችን ኢትዮጵያ 11% ሴቶች ከወር አበባ ጋር በተያያዘ ችግር ማለትም በማኅበራዊ መገለል እና በስነ ልቡናዊ ጫና ምክንያት ከትምህርት ገበታቸው እየተፈናቀሉ የትምህርት መጠነ ማቋረጥ እየጨመረ ይገኛል፡፡ (©UNICEF Ethiopia /2017/Tadesse KAP)

ማለፊያ በመሆኑ ተጠናክሮና የጋራ በሚያደርግ አከዋወን ተሰርቶ ተግባራዊ ቢደረግ ፍቱን መድኃኒት ይሆናል፡፡

ትምሕርት ቤቶች የድግትስ ጋህጃ ክወናን የማስረጽና የማለማመድ ኃላፊነት ቢሰጣቸውና ጉዳዩን በክፍል ውስጥ የመነጋገሪያ አጀንዳ አድረገው ቢወያዩበት፤ በሚኒ ሚዲያቸውም የጋራ በማድረግ ከማኅበረሰቡ ጋር ቢያዋሕዱት መልካም ይሆናል፡፡

የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች ፋይዳው የጎላውን የሀገራችንን ባሕል በሕዝቡ ላይ ለማስረጽ በቴአትር፣ በፊልም፣ በሙዚቃ፣ በግጥም፣ በልቦለድና በስዕል መልክ ኃላፊነታቸውን ቢወጡ ስኬታማ ይሆናል፡፡ ሚዲያዎችም እንደሀገር እየደረሰ ያለውን የሴት ልጅ ችግር ለመፍታት በዜናና በመርኃ ግብር ሰፊና ተከታታይ ሽፋን ቢሰጡት ለውይይት ዝግ የሆነውን ጉዳይ ክፍት ያደርገዋል፡፡

በየዓመቱ **ግንቦት** 28[19] ቀን ዓለማቀፍ የወር አበባ ቀን ቢከበርም፤ በሚፈለገው ደረጃ ማኅበረሰባዊ ግልፅ ውይይት እንዲደረግበት አይነኬና አይነገሬነቱን መስበር አልተቻለም፡፡ ስለሆነም መንግስት በተለይ የሴቶች ሕጻናትና ወጣቶች ሚኒስቴር፣ የባሕልና ቱሪዝም ሚኒስቴር እና የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በተደራጀና በተቀናጀ መንገድ ክወናው እንዲዘምን፣ እንዲሰርጽና ተግባራዊ እንዲሆን ቢሰሩ በወር አበባ ምክንያት በሴት ልጆቻችን ላይ የሚፈጠረው ችግር ዕድሜ ማጠር ይችላል፡፡

ቤተሰብ ሴት ልጅ የቤቱ መሠረት መሆኗን ተገንዝቦ በወር አበባ ምክንያት በቤት ውስጥ ያለውን አመለካከትና አስተሳብ ሰብሮ፤ የጋራ በማድረግ ከበራውን በኃላፊነት፣ እንደልደት፣ እንደሰርግ፣ እንደምርቃት ዝግጅት ወስደው ተፈጻሚ ቢያደርጉት በልጃቸውና በማኅበረሰባቸው ትርፋማ ይሆናሉ፡፡

---

[19] በየዓመቱ ግንቦት 28 ቀን ዓለማቀፍ የወር አበባ ቀን ተብሎ በዓለማቀፍ ደረጃ እንዲከበር በተባበሩት መንግስታት የዓለም ጤና ድርጅት ተወስኖ እየተከበረ ይገኛል፡፡ ( WHO 2019)

# ዋቢ ጽሑፎች


ሕብረት የሺጥላ፡፡ ‹‹ሕይወተ ወራዙት››፡፡ አዲስ አበባ፣ ጃጃው አሳታሚዎች፣ 2011ዓ.ም ፡፡

ሙስጠፋ ያሲን (ዶር)፡፡ ‹‹ከወር አበባ ጋር ተያይዞ የሚመጡ የህመም ስሜቶች እና መፍትሄዎቻቸው፤›› አዲስ አበባ፤ (ያልታተመ ለሲምፖዚየም የቀረበ ሰነድ) 2009 ዓ.ም፡፡

ሙሐመድ ዓሊ ዳውድ፡፡ ‹‹የወር አበባ፤ ሸሪዓዊ ብይን›› አዲስ አበባ፤ ነጃሽ ማተሚያ ድርጅት፡፡ 2010 ዓም፡፡

ሰሎሞን ተሾመ፡፡ ‹‹ፎክሎር ምንነቱና የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ››፡፡ አዲስ አበባ፣ ፋር ኢስት ማተሚያ፡፡ 2007 ዓ.ም፡፡

ሳሙኤል አክሊሉ፡፡ "የጉሙዝ ብሔረሰብ ሀገረሰባዊ ልማድ በተለይ የጋብቻ ሥርዓትና ክዋኔ፣ ጋብቻ"፣፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምሕርት ክፍል ቢኤ ዲግሪ፡፡ 2000 ዓም፡፡

ሷላህ ቢን ፈውዘን (ዶር)፡፡ ‹‹ተንቢሃት (ሙስሊም ሴቶችን የሚመለከቱ ሕግጋት)፡፡ አዲስ አበባ፣ አል-ተውጣ አሳታሚ፡፡ 2008 ዓም፡፡

ሸይኽ ሰይድ መሐመድ እና ሐጅ መሐመድ ሳኒ፡፡ ‹‹የቅዱስ ቁርሃን አማርኛ ትርጉም››፡፡ አዲስ አበባ፣ ነጃሽ ማተሚያ ቤት፡፡ 2003 ዓም፡፡

ሽፈራው ቁሜና ሌሎችም፡፡ ‹‹የጉሙዝ ብሔረሰብ አኗኗር፣ ወግና ባሕሎች››፡፡ ያልታተመ፡፡ ድባጤ፣ 1993 ዓም፡፡

ተመስገን ሽፈራው፡፡ ‹‹የጉሙዝ ብሔረሰብ ባሔላዊ  የሙዚቃ መሳሪያ በት/ቤት ለሙዚቃ ትምሕርት ለሚሰጥ››፡፡ ያልታተመ፣ 1993 ዓም፡፡

ተስፋየ መለሰ፡፡ ‹‹የድላንታ ወረዳ ማኅበረሰብ ተረቶች ሥርዓተ ጾታዊና እንስታዊ ይዘት ትንተና፡፡›› ወሎ ዩንቨርሲቲ ዐውደ ጥናት የቀረበ፡፡ 2010 ዓ.ም፡፡

ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት፡፡ ‹‹መጻሕፈ ኩፋሌ አንድምታ ትርጓሜ››፡፡ አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት፡፡ ፳፻፮ ዓም፡፡

ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት፡፡ ‹‹መጻሕፍተ ብሉያት፤ ፫ቱ እለ እሙንቱ አሪት ዘሌዋውያን፣ ኦሪት ዘኍልቊ፣ ኦሪት ዘዳግም አንድምታ ትርጓሜ››፡፡ አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት፡፡ ፲፱፻፺፱ ዓም፡፡

ኃይሉና ተዋበች፡፡ ‹‹የመጤ ባሕል ተፅዕኖ ባዲስ አበባ››፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባሕልና ቱሪዝም ቢሮ ጥናታዊ ጽሑፍ፡፡ አዲስ አበባ፣ ያልታተመ፡፡2004 ዓ.ም፡፡

አህመድ ሁሴን፡፡ ‹‹ፈታዋ ለሙስሊም ሴቶች››፡፡ አዲስ አበባ፤ አል-ተውጣ አሳታሚ፡፡

አቡነ ጎርጎሪዮስ ካልዕ፤ ‹‹የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ›› አዲስ አበባ፤ ትንሳኤ ማተሚያ ድርጅት፤1980 ዓ.ም፡፡

አንበሳ አባተና ታፈሰች ጥላሁን፡፡ ‹‹የጉሙዝ ብሄረሰቦች ባህላዊ የፍትህ /የግጭት/ አፈታት ስርዓት››፡፡ አሶሳ፡ ያልታተመ፡፡ 2009 ዓ.ም፡፡

የማስታወቂያ ባሕል ሚኒስቴር፡፡ ‹‹የኢትዮጵያ ፌድራላዊ ሪፐብሊክ የባሕል ፖሊሲ››፡፡ አዲሰ አባባ፣ 1990 ዓ.ም፡፡

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ የባሕል ቡድን፡፡ ‹‹የጉሙዝ ብሔረሰብ ባሕላዊ አኗኗርና ዘይቤ››፡፡ ያልታተመ፡፡ ከማሽ፡፡ 1992 ዓም፡፡

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት፡፡ ‹‹ልሳነ ቤጉ፣ 8ኛ ዓመት ልዩ እትም መጽሔት››፡፡ አሶሳ፣ 2008 ዓ.ም፡፡

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግስት ኮሙኒሚሽን ጉዳዮች ቢሮ፡፡ዝክረ ህዳር ልዩ መጽሔት፡፡ አሶሳ፣ 2007 ዓ.ም፡፡

የኢትዮጵያ መጻሕፍ ቅዱስ ማኅበር፡፡ ‹‹የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፡፡›› አዲስ አበባ፣ ባናዊ ማተሚያ ቤት፡፡ 1992 ዓ.ም፡፡

የኢትዮጵያ መጻሕፍ ቅዱስ ማኅበር፡፡ ‹‹መጽሐፍ ቅዱስ፤ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት››፡፡ አዲስ አበባ፣ ፳፻ ዓም፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፡፡ ‹‹አማረኛ መዝገበ ቃላት››፡፡ አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቱ ፕሬስ፡፡ 1993 ዓ.ም ፡፡

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ፡፡ ‹‹ሕገ መንግስት››፡፡ አዲስ አበባ፤ 1987 ዓ.ም፡፡

ዩኔሴፍ ኢትዮጵያ- ታደሰ (2017) ‹‹የኦሮሚያ እና የሶማሌ ክልሎች የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች የወር አበባ ንጽሕና አጠባበቅ፤›› ያልታተመ፤ አዲስ አበባ፤ 2010 ዓ.ም፡፡

ያለው እንዳወቀ፡፡ ‹‹የምርምር መሰረታዊ መርኆዎችና አተገባበር››፡፡ አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች፡፡ 1998 ዓ.ም፡፡

ዳንኤል ወርቁ (አሰናጅ)፡፡ሐተታ ዘርዓ ያዕቆብ እና ሐተታ ወልደ ሕይወት፡፡ አ/አበባ፤ 2007 ዓ.ም፡፡

ዳዊት ግርማ፡፡ ‹‹እንስታዊነት በኢትዮጵያ ፍልስፍና፣ ሐተታ ዘርዓ ያዕቆብ እና ሐተታ ወልደ ሕይወት›› ደብረ ብርሃን፤ ነሐሴ/2011 ዓ.ም፡፡

ድርብ ወርቅ ብፁዕ፡፡ ‹‹የጉሙዝ ብሔረሰብ ዋና ዋና የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ሥርዓት በማንደራ ወረዳ››፡፡ አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ ሥና ጽሑፍና ፎክሎር ትምሕርት ክፍል ኤምኤ ድማፅ፡፡ 2007 ዓ.ም፡፡

ገረመው ፈይሳ፡፡ ‹‹ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና የሴቶች ተፅዕኖ በጉሙዝ ብሔረሰብ››፡፡ ያልታተመ፣ አሶሳ፡፡ 1995 ዓም፡፡

ፀዳለ ታደሰ፡፡ ‹‹በቀይት ንዑስ ወረዳ የሚከወኑ ሀገረሰባዊ እምነቶች››፡፡ አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ ሥና ጽሑፍና ፎክሎር ትምሕርት ክፍል ኤምኤ ድማፅ፡፡ 2007 ዓ.ም፡፡

ፈቃደ አዘዘ፡፡ ‹‹የስነ-ቃል መምሪያ››፡፡ አዲስ አበባ፣ ኢትዩ ጥቁር ዓባይ አታሚዎች፡፡ 1991 ዓ.ም፡፡

Bauman, Richard. ‹‹Verbal Art as Performance. Rowley, Mass:›› Newbury House Publishers. 1977.

Barnard, Alan and Spencer, Jonathan (ed). Encyclopedia of Social and Culural Antheropology, London and New York, 2002.

Behailu Gebrehiwot. "Omens in Ethiopia." Ethinological society bulletin vol.I nos. 1-10 and vol. II no1 Ed. Alula Pankhurst. Addis Abeba University, 1953.

Bell,Cathrine . Ritual Perspectives and Dimension. New York; Oxford University Press, 1997.

___________. Ritual Theory, Ritual Practice. New York; Oxford University Press, 1992.

Boyer, Pascal and Lie´nard, Pierre. Why ritualized behavior? Precaution Systems and action parsing in developmental, pathological and cultural rituals. United state of America, 2006.

Bronner, J. Simon. Folk Objects. In Elliot Oring (Ed), Folk Groups and Folklore Genres; An Introduction Utah; State University Press. 1986.

David E. Gray. Doing Research in Real World. London .SAGE Publications Thousand Oaks ,New Delhi 2004.

Dornyei, Zoltan. Research Methods in Applied Linguistics. Oxford, UK. Oxford University Press. 2007.

Dorson, Richard M. "Introduction: Concepts of Folklore and Folk Life Studies" In Richard Dorson. (ed). Folklore and Folk Life; An Introduction. Chicago and London: the University of Chicago Press. 1972.

Finnegan, Ruth.. ‹‹Oral Traditions and the Verbal Arts: A Guide to Research Practices.›› London And New York: Rutledge. 1992.

Goldstein, Kenneth. ‹‹A Guide for Field Workers in Folklore.›› American Folklore Society by Folklore Associates,INC. 1964.

Kothari, C. R. ‹‹Research Methodology: Methods & Techniques.›› 2nd ed. India, New International (P) Limited, Publishers. 2004.

Maykut, Pamela and Morehouse, Richard. 1994. ‹‹Beginning Qualitative Research APhilosophic and Practical Guide.›› The Falmer Press, London, Washington, D.C.

Sims, Martha C. and Stephens, Martine. 2004. ‹‹Living Folklore: An Introduction to the Study of People and their Tradition.›› Logan: Utah State University Press.

World Book of Encyclopedia. vol7 1978. World Book-child Craft International,Inc. USA.

www.healthcommunities.com/menstruation/treatment.shtml

Yoder, don. Folk Medicine. In Richard m. Dorson, (Ed)፣ Folklore and Folklife Chicago; The Unveresity of Chicago Press. 1972.

Zoltan Dornyei, ‹‹Research methods in Applied linguistis: Quantitative, Qualitative and mixed methodologies.›› oxford university press. 2007.

# አባሪዎች

## አባሪ አንድ፡- የአጥኚውን የመረጃ ስብሰባ እንቅስቃሴ የሚያሳዩ ፎቶዎች፤

❖ ማሳሰቢያ በጥናቱ ውስጥ ያሉ ፎቶዎች በሙሉ በአጥኚው የተነሱ ናቸው፡፡



ፎቶ1፡- ሴት ተተኳሪ የቡድንን ተወያዮችን በከፊል የሚያሳይ፤



ፎቶ2፡- ወንድ ተተኳሪ የቡድንን ተወያዮችን በከፊል የሚያሳይ፤



ፎቶ3፡- በቃለ መጠይቅ ተሳታፊ የሆኑ ወጣቶችን በከፊል የሚያሳይ፤



ፎቶ4፡- በቃለ መጠይቅ ተሳታፊ የሆኑ ሽማግሌ የሚያሳይ፤



ፎቶ5፡- በሥርዓቱ ክወና ላይ የተሳተፉ እና ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው፤



ፎቶ6፡- በገበያ መሐል ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው፤

## አባሪ ሁለት፡- የጉሙዝኛ ቃላት በጉሙዝኛ ፅህፈት፣ በአማርኛ ንበት እና የአማርኛ አቻ ትርጉማቸው፤

| ተ.ቁ | ጉሙዝኛ ስያሜ | በአማርኛ ንበቱ | አማርኛ ፍቺ |
|---|---|---|---|
| 1 | Manzhilam | ማንጅልማ | የለውጥ ጋብቻ |
| 2 | Manozha | ማንጉዛ | የጠለፋ ጋብቻ |
| 3 | Madàgowa | ምዳንጓ | የማደጎ ጋብቻ |
| 4 | Makàŋ kowta | ምቅኝ ኮታ | ለጋብቻ የነጻነት ስርዓት |
| 5 | Mazham | ምዥማ | ጓደኛ |
| 6 | Mmpaaḱowa | ምፕንቋ | የውልደት ሥርዓት |
| 7 | Shaapha | ሽፓ | የወንድ ልጅ ግርዛት |
| 8 | Biija | ቢዣ | የጥሎሽ ጋብቻ |
| 9 | Kea | ኪያ | ቦርዲ መጠጥ |
| 10 | Tiigowa alaoha-ja | ትጉ አልጋህጃ | የወር አበባ ያየችው ሴት መቀመጫ ወንበር |
| 11 | Caabaduwa | ቻብድዋ | የውርስ ጋብቻ |
| 12 | Cacaa | ችቻ | የሾላ ልጥ |
| 13 | Maća | ምጫ | ከሾላ ዛፍ ልጥ የሚሰራ የወር አበባ መቀበያ ‹‹ሞዴስ›› |
| 14 | Gaafaḱa | ጋፊቃ | መዋቢያ ቀይ አፈር |
| 15 | Daagowana | ዳጉና | ልጃገረድ |
| 16 | Deagats gahaja | ድግትስ ጋህጃ | የወር አበባ ሥርዓት |
| 17 | Muwa /Giiśa | ሙዋ/ጊፃ | ከእንስሳት ቆዳ የሚሰራ የእጅ ጌጥ |
| 18 | Kuwata | ኮታ | እርጥብ እንጨት |
| 19 | Fuḱowa | ፍቋ | የሾላ ዛፍ |
| 20 | Poŋga | ፖኝጋ | ገንፎ |
| 21 | Ḱowsha | ቆሻ | ቃጭማ |
| 22 | Caaga | ቻጋ | ጩቤ |
| 23 | Ofa | ዑፋ | አመድ |
| 24 | Kea-masha | ከይምሻ | ተስካር |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 25 | Ahas`a | አሄጻ | የወር አበባ ያየችው ልጅ |
| 26 | Śolaŋa | ጾልኛ | አረቄ |
| 27 | Mashaa | ምሻ | ሞት |
| 28 | Musaa | ሙሳ | አምላክ |
| 29 | Maheesha | ማህሻ | ወፍጮ |
| 30 | Gaeé gaha-ja | ጌይ ጋህጃ | የመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ ጭፈራ |
| 31 | Kea- gaha-ja | ክይግህጃ | የመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ ጠላ |
| 32 | Manza | ሚንዛ | ጨሌ |
| 33 | Mata | ምታ | ደሮ |
| 34 | Zhama | ዥማ | ቅመማ ቅመም |
| 35 | Gaha-ja | ጋህጃ | የወር አበባ |
| 36 | páansá | ፖንጻ | ገንፎ |
| 37 | B`ija | ቤጃ | ጨረቃ |
| 38 | Galaba | ግላባ | ባህላዊ ጉርድ ቀሚስ |
| 39 | MinzaB`iya | ሚንዘጲያ | የአንገት ጨሌ |
| 40 | Minza | ሚንዛ | ጨሌ |
| 41 | B`akaalagas`aba | ባክላጃባ | ባህላዊ ሸበጥ ጫማ |
| 42 | Caagaabjela | ቻጋ | የክንድ ቢላዋ |
| 43 | labinda | ልባንዳ | ጠመንጃ |
| 44 | zaraana | ዘራነ | ዝናር |
| 45 | Dogwa | ደጓ | ቀስት |
| 46 | Táak`iya | ጣቂያ | ባርኔጣ |
| 47 | Tabaana- s`eya | ትባን ጼያ | የጆሮ ጌጥ |
| 48 | Tabaana- ita | ትባን ኢታ | የአፍንጫ ጌጥ |
| 49 | pahak`a | ፕህቅ | በግንባር ላይ የሚደረግ የዛጎል ጌጥ |
| 50 | pahak`aaliluk`wa | ፕህቅ ልቋ | በራስ ላይ የሚደረግ የዛጎል ጌጥ |
| 51 | hosáaŋnna | ሆሴኛ | በወገብ ላይ የሚደረግ የዛጎል ጌጥ |
| 52 | Liba | ልባ | በወገብ ላይ የሚደረግ የጨሌ ጌጥ |
| 53 | Minza- Cogwa | ሚንዝ ቾጓ | በእግር ላይ የሚደረግ የጨሌ ጌጥ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 54 | Saho-ela | ሰሆኤያ | ከመዳብ የተሰራ የእጅ ጌጥ |
| 55 | Maandigush-beek`wa | ማንድጉሽ ቤቋ | ፀጉር መከርከም |
| 56 | Ampala | አምፕላ | የወንዶች ባህላዊ ቁምጣና ቲሸርት |
| 57 | sarama | ሰርማ | ከበሮ |
| 58 | mas`a- maiya | መጻሚያ | ትልቁ መኖሪያ ቤት |
| 59 | mas`a- kogwa | መጻኮዋ | ትንሿ ጎጆ ቤት |
| 60 | Magwaanguk`wabwa | መነንድቋ አወ | ልብስ መሸፋፈን |
| 61 | Maaŋgisha kababats b`agaa pants`aggo | መክሻ ከበበጻ ብጋ አፕንጽጎ | ትልቅ ሰው አለማናገር |
| 62 | Oka gwaakuho oka gwaapi`ya | ኦካ ጎኩሆ ኦካ ጎፒያ | ፀሐይ ስትገባ፤ ፀሐይ ሳትወጣ |
| 63 | Ganzaŋa | ጋንዘኛ | ቁጥር |
| 64 | Mafts nil giÇ`a | መፋጽ ኔል ጋች | ወንዝ መታጠብ |
| 65 | miud`aeladaÇ`a | ምውድ አለዳጨ | ምዕራብ አቅጣጫ |
| 66 | Manzis`ińja | መንዛ ፂንጃ | እርጥብ ቅጠል |
| 67 | Gomba | ጎምቦ | ዱላ (ዘንግ) |
| 68 | muhwa | ምኋ | አንካሴ |
| 69 | Gaafgas`aha | ጋፋ ግፅኃ | ሴት ደሮ |
| 70 | Masaela- mazhama | ምስኤል ምዥማ | በጓደኛ እጅ መብላት |
| 71 | Kaela-yaayamaan yeeshmadada | ከኤላያ ያማን ጎሽምዳዳ | በእናት እጅ ስራ መጀመር |

| በመገኛ ቋንቋ | በአማርኛ ንበት | የአማርኛ ፍቺ |
|---|---|---|
| Duwa alam daamkamanzima | ዱዋ አለም ዳምክመዚማ | ልጄ ለምለም ሁኚ፤ |
| NafagaaÇshoo kaaluwa | ነፋጋችሾ ካአሉዋ | ዘርሽ ይብዛ፤ |
| ZizimaaŋgahaҪa aluwanaakad | ዚዚማንግሀቻ አለዋነኮድ | ፍቅርሽ ሁሉን ይግዛ፤ |
| Naais`aak`wa alaakok`alama | ናኢጽቁ አላኩቁ አማ | የሚጠላሽ ይፈር፤ |
| maab`aŋalits kaama | ማፕልጽ ካአማ | እኛ እንኩራብሽ፤ |
| Ebaalua ebaaos`eya inahaaggo | ኤባአሉዎ ኤባኦጺዋ ኢንሀንጎ | መንደሩ ስምሽን ጠርቶ አይጥገብ፤ |
| AÇama mazhama | አቻ ምዥማ | እናንተም (ጓደኞቿን) |
| Kadaamas`a alaÇa maab`agatsa, kak`webaÇa jikamadaÇa | ካደምጻ አለቻ ማብኟጻ ካቋይብቻ ጃሃመድቻ | ለቤተሰባችሁ ኩራት፤ ለመንደራችሁ መብራት ሁኑ፤ |
| Alauda Çakamanasal Ça Nakuranafrizhnila Çama | አላውድ አቻ ከምንስልቻ ነኩሆን አፋህን ጃኔል ችማ | በመጥፎ የሚያያችሁ በዐይኑ በርበሬ ይግባ፤ |
| Maanzima otaja | ምንዚማ ኦትጃ | ለምለም ሁኑ፤ |
| Nafagaa Çshookaala Ça | ነፈጋች ሽካአለቻ | ዘራችሁም ይብዛ፤ |
| | | (ተ.ቡ.ው. 1፤18) |

| በመገኛ ቋንቋ | በአማርኛ ንበት | የአማርኛ ትርጉም |
|---|---|---|
| Kwelu mazhijama iluwa, babilama dewota | ቋኤሉ መዥግማ ኢለዋ፤ ባቢ.ልማ ዲውታ | ትከሻሽ ጠንካራ፣ ሆድሽ ሰፊ ይሁን፣ |
| Kakaalm da det`awa amakama zhnli Çma | ካካላም ዳ ዳሾዋ አማካማ ዥንሊ ችማ፤ | ነገር የምትችይ ብርቱ ያድርግሽ፣ |
| Garaba aluwakama dada, kamakaala shiluk`uwa detagaa Çama | ግርባ አሉዋኮም ድዳ ከመካልሽ ኢልቆዎ ዲያትጋ ችአማ | ጉልበትሽ ለስራ፤ ህሊናሽ ትግስት ለማደረግ ይበርታ፤ |
| Madagańasa alamalaka zhigama dand`abogw kaama aguuta ab`la | ማግበሳ አላምላክ ዥግም ዳነዲቦጎ ካማ አጉታ አቢላ | የኛ በደላችን ሳይሆን ምርቃታችን ይድረስሽ፤ |
| Alafona gulanoai Çakas kama | አላፎን ጎላነሽ ጨቋ ከማ | በኛ የጎደለ ላንቺ ይሙላ፤ |
| Aleiyaashnila Çuwa kamagahak`o suwanaa iyaaÇ | አሊኢያሽኔል ቺዎ ከመግህቱ ሱዎነ ኢያች | ለዐይንሽ ማረፊያ፣ ለጥርስሽ ደስታ ይብዛልሽ፤<br>(ተ.ቡ.ው. 1፤18) |

| በመገኛ ቋንቋ | በአማርኛ ንበት | የአማርኛ ትርጉም |
|---|---|---|
| Na- ça musa gasharam. | ና ኪ ሙሳ ግሽርማ | ፈጣሪ መልካሙን ይስጥሽ፤ |
| Na- dadaeta pakãwaama nabanaya. | ና ዳዳኢት ፓቋዋኣማ ንባኒያ | ከክፉ ነገር ሁሉ ያውጣሽ፤ |
| Nabakabango; musa eta dora gaama. | ንባክቡንጋ ሙሳ ኢታ ዶራ ጋኣማ | እኛ እንደ መረቅንሽ ፈጣሪ ይመርቅሽ፤ |
| Bana gasharam | ባኔ ግሻራም | ሃሳብሽን ፈጣሪ ይሙላው፤ |
| Dãko mmasaãla | ዴቆምጻኣሌ | ከንደኞችሽ እኩል ሁኚ፤ |
| Ka madagonama. | ካ ማዴጎንማ | ቤት ያዥ፤ |
| aledáak`wa amanaad alugutuk`wa | አሌዳቋ አማነድ አሉጉትቋ | የሚያገባሽ የተባረከ ይሁን፤ |
| Ŋgafa- duwa kashooka alukabaaÇa Gunza-dida pokw`am | ንግፉ ዱዋ ካሱብ አሉክባቻ ጉንዛ ደዳ ፓቋም | ለዘርሽ ሴት ልጅ፤ ለኩራትሽም ወንድ ልጅ ውለጅ፤ |
| Alaad`aak`o tsaamnugut | አላዳቋ ጸምኑጉት | የነካሽው ይባረክ፤ |
| Naanziyaa Çalaawoshaam | ናንዚያ ችአላውሻም | የዘራሽው ይለምልም፤ |
| Naabid alaasi batsoam | ናቢድ አላሲ ብጽም | የዳሰስሽው ይፈወስ፤ |
| alaanÇa k`waamnai yaaÇ | አላንች ቋምኒ አያች | ያቦካሽው ይበርክት፤ |
| mb`ińaaŋgo agashkw` alu | መበንጎ አገሽኮ አሉዋ | ትንፋሽሽ አይቀዝቅዝ፤ (ተ.ቡ.ው. 2፤7) |

| በመገኛ ቋንቋ | በአማርኛ ንበት | የአማርኛ ትርጉም |
|---|---|---|
| dajaaÇedi dakama nzima | ድጃችኤዲ ዳካማ ነዚማ | ልጃችን እርጥብ (ለምለም) ሁኚ፤ |
| Ziyaala daboiamka maggwaÇama ambahaÇ | ዚላ ዳቦላምኮ ማንጎችማ አምብህች | ዛሬ አብበሻል፤ ነገ ፍሬ አፍሪ፤ |
| Naadfahatsa aluwa zizi ala maaŋgahila | ናድፋህጻ አሉዋ ዚዚ አለ መችግሀል | ሕይወትሽ ሁሉ የደስታ ይሁን፤ |
| naakaÇ amisakaama aliliwa | ነክቻ አምስካማ አሊሉዋ | ፈጣሪ (ሙሳ) የልብሽን ይስጥሽ፤ |
| Naokampok`wa aluwa matigaats`goo mansamat | ንአክምንቋ አሉዋ መተግፅጎ መንስምት | በምጥሽ ጊዜ ክፉ ነገር አያሳይሽ፤ |
| Garbanago`oo dam madaggo male`k`oma | ግርባንጎ ዳም ምዳንጎ መላአቋማ | ጉልበትሽ ሰርቶ የማይደክም ይሁን፤ |
| Alaad ntsaamkoo manugtuk`wa | አላድ ፅምኮ ማትጎትቋ | የነካሽዉ ሁሉ ይበርክት፤ |
| Kaas`aÇ`aamnan dowanaalun afad`ak`w ama amisa | ካፅጨምነን ዶዋንሉዋ አፋደቋ አማ አምሳ | በመንገድሽ የሚወድቀዉን እንቅፋት ፈጣሪ ያንሳልሽ፤ |
| Kaboggusha Ç`atskamaggahilan iluwa duwanaa Çkaama | ከብንጉሸ ጨፅክማንግሀይልን ያሉዋዱዋነ ችካማ | ለጅርባሽ ክብር ለልብሽ ደስታ የሚሆኑ ልጆች ይስጥሽ፡፡<br>(ቃ.መ.3፤3) |

❖ **አባሪ ሶስት፤- የተተኳሪ ቡድን ውይይት አንድ፡- የሴት ሽማግሌዎች የመወያያ ጥያቄዎች፤**

1) ሥርዓቱ መቼ ተጀምሮ መቼ ያልቃል? በሰባት ቀን ያልቃል ይባላል፤ እስከ ሶስት ወይም አራት ወር ይቆያል ይባላል፤ ትክክለኛው የቱ ነው? ምክኒያቱስ?
2) አራት ጨረቃ ወይም መቶ ሃያ /120/ ቀን የሚባለውስ?
3) ሥርዓቱ ባይፈፀም ወይም ቢቀር ምን ይፈጠራል ተብሎ ይታመናል?
4) ከቀኗ ቀድማ ወጣ ትልቅ ሰው ብታናግር ምን ትሆናለች?
5) ምጫውን ማን ሰርቶ ያቀርብላታል?
6) የወር አበባ ለጉሙዝ ምንድን ነው? የፈጣሪ ቁጣ ነው? ቆሻሻ ነው? ወይስ ንፁህ ደም ነው?
7) በወር አበባ ጊዜ ሥራ አትሰሩም፤ ተማሪ ሆና የወር አበባ ቢመጣባትስ? ትምህርቷ ይቋረጣል ወይስ ምን ታደርጋለች?
8) የወር አበባ ላየች ሴት ልጅ የመጀመሪያ ጊዜ ስርዓቱ ባይፈፀምላት ምን ትሆናለች?
9) አጥኝው፡- ለመጀመሪያ ጊዜ ልጃገረዷ የወር አበባ ስታይ ትደነግጣለች? ከስርዓቱ በኋላስ ድንጋጤው ይተዋታል?
10) ይሄ ስርዓት ቢቀር ባይፈፅም ምን ይፈጠራል?
11) ወንዝ ሄደው ታጥበው እርጥብ ቅጠል፣ እንጨት ይዘው እየዘፈኑ ይመጣሉ፡፡ ትንሽ ደረቅ እንጨትም ይዘው በምዕራብ አቅጣጫ ወደ እሳት ይወረውሩታል ምን ትርጉም አለው?
12) ጓደኞቿ የወር አበባ ያየችውን ልጃገረድ ይዘው ለመታጠብ ለምን ወንዝ ይሄዳሉ? ለምን በጀሪካን ቀድተው ቤት ውስጥ አይታጠቡም?
13) የወር አበባ ያየችው ልጅ ፀጉሯን ትስተካከለች፤ መሐል ላይም ትላጫለች ለምን? ጋፊቃስ ለምን ትቀባለች? ኬቢያውስ ምን ትርጉም አለው?
14) የወር አበባ ላየችው ልጃገረድ የሚደረገው ሁሉ ለጓደኛዋም ይደረጋል ለምን?
15) የወር አበባ ያየችው ልጃገረድ የምትቀመጥበት ወንበር (ተጉጋጃ ) ላይ ወንዶች አይቀመጡም፡፡ ለምን? ቢቀመጡ ምን ይሆናሉ?
16) ሴቶች ቅጠል ይዘው እጨፈሩ ከወንዝ ሲመለሱ መንገድ ላይ ወደቤት ሳይገቡ ወንዶች ያገኟቸዋል፤ ሴቶችም ወንዶችን አመድ ይረጯቸዋል፤ ወንዶች አይቆጡም ይሳሳቃሉ ይጫወታሉ አመዱ የምን ምሳሌ ነው?

17) እናቷ ሴት እናት ዶሮ ትወረውውላች፣ ሴቱም ወንዱም በሽመል አሯሩጠው ወይም መትተው ይይዟታል፡፡ ለምን?

18) አክስቷ ደሞ ሌላ እናት ሴት ዶሮ ይዛ፣ የወር አበባ ያየችው ልጃገረድ እየመረቀች ጀርባዋን በዶሮዋ ትመታታለች ምን ማለት ነው?

19) ለክብሯ የተሰጣትን ደሮ ልጅቱ ታርደዋለች፡፡ ሴት ልጅ በጉሙዝ ብሔረሰብ ደሮ ታርዳለች?

20) የወር አበባ ንፅህና መጠበቂያ አሁንም ምጫ ነው የምትጠቀመው ወይስ ጨርቅና ዘመናዊው ሞዴስ እየተጠቀማችሁ ነው?

21) ይህ የመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ አቀባበል ስርዓት የሚፈፀመው በምን በምን ሰዓት ነው? ለምን? የተለየ መፈፀሚያ ቦታስ አለው?

22) የወር አበባ ያየችው ልጃገረድ በጓደኛዋ እጅ የምትበላ ለምንድነው?

23) የታረደውን ዶሮ ለምን ትራመደዋለች? ምን ትርጉም ወይም እምነት አለው?

24) ልጅቱን እናቷ ወፍጮ፣ ሙቀጫ፣ ድስትና ሌሎችንም የቤት እቃዎች እጇን ይዛ ሥራ የምታስጀምራት ለምንድነው?

25) በወር አበባ ጊዜ ምን እየተባለ ነው የሚዘፈን?

26) ለምን ትንሿ ጎጆ ቤት ተመረጠች? ምን የተለየ አመለካከት አለ?››

አባሪ አራት፡- የተተኳሪ ቡድን ውይይት ሁለት የወንድ ሽማግሌዎች የመወያያ ጥያቄዎች፤

1. በየወር አበባ አቀባበል ስርዓት የወንዶች ሚና ምንድን ነው?
2. ክወናው (የስርዓቱ አፈፃፀም) በሃይማኖት፣ በጎሳ ወይም በሀብት የተለየ አፈፃፀም አለው?
3. የወር አበባ ለመጀመሪያ ጊዜ ያየችው ልጃገረድ አስሩን ጣቶቿን በቃጭማ ለምን ትታሻለች?
4. ጎጆ ቤት ውስጥ ለምን ትገባለች?
5. የወር አበባ የመጣት ሴት ምን፣ ምን ትሰራለች? ምን ምንስ አትሰራም?
6. ለክብሯ የሚታረደውን ፍየል ስጋ መብላት ከጀመረ ህፃን እስከ ትልቁ ሽማግሌ ድረስ እኩል ነው የምታካፍሉት፡፡ ህፃናት ትንሽ ነው የሚመገቡ፤ ሌሎች ደግሞ ብዙ የሚበሉ አሉ ለምን አንደ አቅማቸው አይካፈሉም?
7. ምርቃቱ በማን ይጀመራል? ምን ተብሎ ይመረቃል?
8. የወር አበባ ከመጣ ጊዜ ጀምሮ ሰባት ቀን ሲሞላ፣ ወይም ወር ሲሞላ፣ ወይም መቶ ሃያ (120) ቀን ማለትም (አራት ወር) ሲሞላ እንዴት ታውቃላችሁ?
9. ከወር አበባ የምትነፃ በሰባተኛው ቀን ነው፡፡ ለምን በአምስትኛው ቀን ወይም በአስረኛው ቀን አልሆነም? ሰባት በጉሙዝ የተለየ ትርጉም አለው እንዴ?
10. አሂጻና ምኸርማ እንዲሁም ዳጉናዎች መፀዳጃ ቤት የሚሄዱ፣ ቆሻሻ የሚቀብሩ፣ ወንዝ የሚሄዱ፣ ሁሌ የሚጨፍሩ ፀሐይ ከገባች በኋላ እና ሌሊት ፀሐይ ሳትወጣ ነው፡፡ ለምን?

**አባሪ አምስት፡- ቃለ መጠይቅ አንድ የወር አበባ ላየችና ስርዓቱ ለተፈፀመላት እና ምዥማ ለሆነች ሴት የቀረበ ጥያቄ፤**

1) ለመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ ስታይ ምን ተሰማሽ?
2) በዛ ዓመት የወር አበባ እንደምታይ ትገምቺ ነበር?
3) በስርዓቱ መከወን ምን ጥቅም አገኘሽ?
4) ስርዓቱ ሲፈጸም የወር አበባ ያየችዉ ልጅ ለምን ትሽፋፈናለች? ጸጉሯንስ ለምን ትላጫለች?
5) ከጓደኛሽ ጋር በመሆን ለሌሎች ጓድኞችሽ የወር አበባ እንደመጣሽ በየቤታቸዉ እየዞርሽ ትነግሪያቸዋለሽ፤ ይሄ አያሳፍርሽም? አሁንስ አዚህ ያለሽበት ቦታ የወር አበባ ቢመጣሽ ታፍሪያለሽ ወይስ ትደነግጫለሽ?
6) እናትሽ ከስርዓቱ ማብቂያ ላይ የወፍጮ፤ የሙቀጫና የገንፎ ስራ ስታስጀምርሽ ምን ይሰማሻል?
7) የወር አበባ ላየችዉ ልጅ የቅርብ ጓደኛ ሆኖ ለመመረጥ መስፈርቱ ምንድን ነዉ?
8) ለቤተሰቦቿ ልጃቸዉ የወር አበባ እንዳየች ስትናገሪ ምን ተሰማቸዉ?
9) የወር አበባ አሁን ቢመጣብሽ ትደነግጫለሽ? ወይስ ታፍሪያለሽ?

**አባሪ ስድስት፡- ቃለ መጠይቅ ሁለት የወር አበባ ላየችው ልጅ እናትና አባት የቀረበ ጥያቄ፤**

1. ልጃችሁ የወር አበባ አይታ ጓደኛዋ ስትነግራችሁ ምን ተሰማችሁ?
2. አስቀድማችሁ ስለድግትስ ጋሀጃ ታስቡ ነበር?
3. በስርዓቱ የአባቷ ሚና ምንድን ነዉ?
4. ልጅሽ የወር አበባ አየች ስትባይ ምን ተሰማሽ?
5. እርስዎ እናት ነዎት አሁን የወር አበባ ሲመጣ ምን ይሰራሉ? ምንስ አይሰሩም?
6. ሁሉን ስርዓት ከየት አመጣችሁት? እንዴት አወቃችሁት?
7. የወር አበባ ያየች ሴት ስራ የማትሰራዉ ለምንድነዉ?
8. የወር አበባ እርኩስ ነው ቆሻሻ? ወይስ መርገም ነው ፀጋ?

**አባሪ ሰባት ቃለ መጠይቅ ሶስት ለጎረቤቶች የቀረበ ጥያቄ፤**

1) የጎረቤት ልጅ የወር አበባ አየች ሲባል ምን ይሰማዎታል?
2) ይህን ስርዓት መተዉ ይቻላል በጉሙዝ?
3) የወር አበባ ያየችውን ልጅ ምን ብላችሁ ነዉ የምትመርቋት?
4) አንተ ወጣት ነህ ጎረቤት (ሰፈር) ላይ አንድ ልጅ የወር አበባ አየች ሲባል ምን ይሰማሃል?
5) ሴቶች ሲዘፍኑ አድረዉ ወንዶች (ወጣቶች) እንደተኛችሁ አመድ ይረጪችኋል፡፡ ለምንድነዉ?

# አባሪ ስምንት፡- የመረጃ ሰጭዎች ዝርዝር መረጃ፤

➢ የተተኳሪ ቡድን ውይይት አንድ፡- የሴት ሸማግሌዎች፤

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ጾታ | ዕድሜ | ክልል | ዞን | ወረዳ | ቀበሌ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ወ/ሮ ኤዱሹ ጉቋ | ሴ | 46 | ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | መተከል | ማንዱራ | ድዋዝ ባጉና |
| 2 | ወ/ሮ አድጓ ሂሶ | ሴ | 52 | ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | መተከል | ማንዱራ | ድዋዝ ባጉና |
| 3 | ወ/ሮ ጉፋ ዋድም | ሴ | 74 | ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | መተከል | ማንዱራ | ድዋዝ ባጉና |
| 4 | ወ/ሮ ዝባለም ቆጋ | ሴ | 53 | ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | መተከል | ማንዱራ | ድዋዝ ባጉና |
| 5 | ወ/ሮ ሲሳይ አንዱር | ሴ | 46 | ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | መተከል | ማንዱራ | ድዋዝ ባጉና |
| 6 | ወ/ሮ ታንኳ ይባስ | ሴ | 62 | ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | መተከል | ማንዱራ | ድዋዝ ባጉና |

➢ የተተኳሪ ቡድን ውይይት ሁለት፡- የወንድ ሸማግሌዎች፤

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ጾታ | ዕድሜ | ክልል | ዞን | ወረዳ | ቀበሌ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ወርቁ ድሞና | ወ | 61 | ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | መተከል | ማንዱራ | ድዋዝ ባጉና |
| 2 | አቶ ተስፋዬ ካወቃ | ወ | 84 | ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | መተከል | ማንዱራ | ድዋዝ ባጉና |
| 3 | አቶ በዛብህ ገበያው | ወ | 47 | ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | መተከል | ማንዱራ | ድዋዝ ባጉና |
| 4 | አቶ ጥላሁን ባቢስ | ወ | 66 | ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | መተከል | ማንዱራ | ድዋዝ ባጉና |
| 5 | አቶ ጃኔ ድባቦ | ወ | 48 | ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | መተከል | ማንዱራ | ድዋዝ ባጉና |
| 6 | አቶ መርጋ ጊሶ | ወ | 39 | ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | መተከል | ማንዱራ | ድዋዝ ባጉና |

➢ ቃለ መጠይቅ አንድ ፡- የወር አበባ ያየችና ስርዓቱ የተፈፀመላት ወጣት ሴት እና ረዳት ጓደኛ የሆነች ወጣት ሴት፤

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ጾታ | ዕድሜ | ክልል | ዞን | ወረዳ | ቀበሌ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ወ/ሪት ማሙሻ አቫቢ | ሴ | 13 | ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | መተከል | ማንዱራ | ድዋዝ ባጉና |
| 2 | ወ/ሪት ሙሉ ዋድም | ሴ | 17 | ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | መተከል | ማንዱራ | ድዋዝ ባጉና |

➢ ቃለ መጠይቅ ሁለት ፡- የወር አበባ ያየችው ልጅ እናትና አባት

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ጾታ | ዕድሜ | ክልል | ዞን | ወረዳ | ቀበሌ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ አቫቢ ቱሳ | ወ | 43 | ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | መተከል | ማንዱራ | ድዋዝ ባጉና |
| 2 | ወ/ሮ ምጋኳ ንጉሴ | ሴ | 31 | ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | መተከል | ማንዱራ | ድዋዝ ባጉና |

➢ ቃለ መጠይቅ ሶስት፡- ጎረቤቶች፤

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ጾታ | ዕድሜ | ክልል | ዞን | ወረዳ | ቀበሌ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ጊሳ ዝማቻ | ወ | 38 | ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | መተከል | ማንዱራ | ድዋዝ ባጉና |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | |
| 2 | ወጣት አዲሴ ጃኔ | ወ | 24 | ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | መተከል | ማንዱራ | ድዋዝ ባጉና |

➢ **ከጉሙዝኛ ወደ አማርኛ ተርጓሚ**

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ጾታ | ዕድሜ | ክልል | ዞን | ወረዳ | ቀበሌ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | **አቶ ዳኜ ንጻጼ** | ወ | 28 | ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | መተከል | ማንዱራ | ግልገል በለስ |